# የሐዋርያት ሥራ

## መግቢያ

### ጸሐፊው

የመጽሐፉ ጸሐፊ የራሱን ስም ባይገልጽም፣ ከቅዱሳት መጽሐፍት ውጭ የሚገኘው መረጃና ከራሱ ከመጽሐፉ የሚገኘው ፍንጭ ጸሐፊው ሉቃስ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ያደርሳል::

በ170 ዓ.ም. አካባቢ የተጻፈው "የሙራቶሪያን ቀኖና" የተባለ የቤተ ክርስቲያን ጽሑፍ፣ ሉቃስ የሦስተኛው ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ መጻሕፍት ጸሐፊ እንደ ሆነ በግልጽ ያመለክታል:: በ325 ዓ.ም. ገደማ የነበረው አውሳቢዮስ የተባለውም የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባት፣ የሁለቱም መጻሕፍት ጸሐፊ ሉቃስ እንደ ሆነ ዝርዝር መረጃ በማጠናቀር አቅርቦአል::

ጸሐፊው ማን እንደ ሆነ በራሱ ጽሑፍ ውስጥ አንዳንድ ፍንጮች ይታያሉ:-

(1) ***የጳውሎስ ጓደኛ ሉቃስ!*** በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ጸሐፊው አንዳንድ ድርጊቶችን ለመግለጽ "እኛ" የሚለውን ተውላጠ ስም ሲጠቀም ይታያል:: ጸሐፊው ይህን በመጠቀሙ ራሱን የጳውሎስ ጓደኛና የጉዞ ባልደረባ አድርጎ ያቀርባል (16፥10-17፤20፥5-15፤21፤1-18፤27፥1-28፥16):: ዝርዝር ሁኔታ ዎችን በጥንቃቄ እንደዚህ የሚያቀርብ ታሪክ ጸሐፊ፣ "እኛ" ወይም "እነርሱ" ብሎ ለመጻፍ በቂ ምክንያት አለው:: ይህም ጸሐፊው "እኛ" ብሎ በጻፈባቸው ክፍሎች ከጳውሎስ ጋር የነበረ ይመስላል:: እነዚህ "እኛ" በሚል ተውላጠ ስም የተጻፉ ክፍሎች ጳውሎስ በሮም ለሁለት ዓመት እስር ቤት የነበረበትንም ጊዜ (ም 28) ይጨምራል:: ጳውሎስ በእነዚህ ጊዜያት ከሌሎቹ መልእክቶቹ በተጨ ማሪ የፊልሞናንና የቈላስይስን መልእክቶች ጽፎአል:: በእነዚህ መልእክቶች የባልንጀሮቹን ሰላምታ ሲያስተላልፍ የሉቃስ ስም ተጠቅሶአል (ፊሞ 23-24፤ ቈላ4፥10-17):: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በአንድ ወይም በሌላ መስፈርት ምክንያት የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ጸሐፊዎች ይሆናሉ ተብለው የተገመቱት አለመሆናቸው ሲረጋገጥ፣ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ እጩ ሉቃስ ብቻ ይመስላል::

(2) **ባለ መድኀኒቱ ሉቃስ፤** በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን የአነጋገር ዘይቤ በመመልከት ብቻ ጸሐፊው ሐኪም ነው ማለት ባይቻልም፣ የሚጠቀምባቸውን ቃላትና በጽሑፉ ውስጥ የሚንጸባረቁትን የምሁር አገላለጽ ስናይ የሕክምና ሙያ ያለው ሰው እንደ ጻፈው መገንዘብ ያስችለናል (ለምሳሌ:- የ28፥6 ማብ ይመ):: በእርግጥ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት ላይ የነበረ አንድ ሐኪም ለሕክምና ሙያ ብቻ የሚጠቀምባቸው የተለዩ ቃላት ይኖሩታል ማለት አይቻልም፤ ይሁን እንጂ፣ የሉቃስና የሐዋርያት ሥራ መጻሕፍት የቃላት አጠቃቀም የመጻሕፍቱ ጸሐፊ የሕ ክምና ባለ ሙያ እንደ ነበረ የሚያመለክቱ ናቸው:: ጳውሎስም ስለ ሉቃስ በሚናገርበት ጊዜ "ባለ መድኀኒቱ" ማለቱን መገንዘብ ያስፈልጋል (ቈላ4፥14)::

### የተጻፈበት ዘመን

መጽሐፉ የተጻፈበትን ዘመን አስመልክቶ የሚሰጡት አማራጮች (1) በ63 ዓ.ም. ልክ በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ የተጠቀሰው ድርጊት ከተፈጸመ በኋላ ወዲያው፤ ወይም (2) በ70 ዓ.ም. ወይም ከዚያም በኋላ የሚል ነው::

#### የመጀመሪያውን አማራጭ የሚደግፉ ማስረጃዎች:-

(1) **ወደ ኋላ ስለ ተፈጸሙ ድርጊቶች ዝም መባሉ፤** ስለ አንድ ነገር አልተጠቀሰም በማለት ብቻ የመከ ራከሪያ ነጥብ ማንሣት ባይቻልም፣ መጽሐፉ ጳውሎስ በሮም ለሁለት ዓመት ከታሰረ በኋላ ስለ ተፈ ጸሙ ሁናቴዎች ለምሳሌ:- ስለ ሮም ከተማ መቃጠልና ስለ ክርስቲያኖች መሰደድ (64 ዓ.ም.)፣ ስለ ጴጥሮስና ስለ ጳውሎስ ሰማዕትነት (ምናልባት 67 ዓ.ም)፣ እንዲሁም ስለ ኢየሩሳሌም መፈራረስ (70 ዓ.ም.) አይናገርም::

(2) **ስለ ጳውሎስ እስራት የመጨረሻ ሁኔታ አልተጠቀሰም፤** ሐዋርያው ጳውሎስ ይጠባበቅ የነበረውን የፍርድ ውሳኔ ውጤት (28፥30) ሉቃስ ቢያውቅ ኖሮ፣ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ለምን አልጠቀሰም? ምናልባት የፍርዱ ሂደት እስከዚሁ ድረስ ብቻ ስለ ነበረ ይሆናል::

መጽሐፉ የተጻፈው በሁለተኛው አማራጭ ዘመን ነው ብለው የሚያምኑ ሉቃስ ታሪኩን የጻፈው በ1፥8 ላይ ተመሥርቶ ነው፤ ስለዚህም በመጽሐፉ የአጻጻፍ ስልት መሠረት የመደምደሚያ ሐሳቡ በቀጥታ ከዐላማው ጋር ይዛመዳል:: ሉቃስ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እያደገችና እየሰፋች የዘመኑን ዓለም (ኢየሩሳሌም፣ ይሁዳ፣ ሰማርያ፣ የዓለም ዳርቻ) በማዳረስ፣ የዓለም የፖለቲካና የባህል ማእከል ወደ ሆነችው ሮም መድረስ እንደቻለች ለማሳየት ፈልጎአል:: በዚህ አመለካከት ከተሄደ፣ ስለ ጳውሎስ ሰማዕ ትነትና (67 ዓ.ም. አካባቢ) ስለ ኢየሩሳሌም መፈራረስ (70 ዓ.ም) ማውሣት ከጽሑፉ ዐላማ ጋር የማይ ሄድ ይሆናል:: በዚህ መሠረት የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በ70 ዓ.ም. ወይም ከዚያ በኋላ ተጻፈ ማለትም ይቻላል::

### ተደራሲ

የዚህ መጽሐፍና የሉቃስ ወንጌል ተደራሲ ቴዎፍሎስ ነው (የሉቃስ ወንጌል መግቢያ ይመ)::

**የመጽሐፉ አስፈላጊነት**

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ለአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መሸጋገሪያ ያበጃል። መጽሐፉ የሉቃስ ሁለተኛ መጽሐፍ ሆኖ፣ በወንጌላት ውስጥ እንደምናየው፣ "ኢየሱስ ሊያደርግና ሊያስተምር የጀመረውን" (1፥1) በሐዋርያት ስብከትና በቤተ ክርስቲያን ምሥረታ አማካይነት መቀጠሉን ያስረዳል። የወንጌላትን ትረካ በአንድ በኩል የሐዋርያትን መልእክቶች በሌላ በኩል ከማገናኘቱ በተጨማሪ፣ ስለ መልእክቶች ልናገኝ የሚገባንን መረጃዎችና ስለ ሐዋርያው ጳውሎስ የሕይወት ታሪክም ከመጽሐፉ ማግኘት ይቻላል። የትረካው መልክዐ ምድር አቀማመጥ፣ ቤተ ክርስቲያን በተጀመረችበት በኢየሩሳሌምና የሮማውያን የፖለቲካ ማእከል በነበረችው በሮም መካከል ያለውን አካባቢ የሚዳስስ ነው። መጽሐፉ የቤተ ክርስቲያንን የመጀመሪያ ሠላሳ ዓመት ሁኔታ ያካትታል። ከዚህም በላይ፣ የቤተ ክርስቲያንን አጀማመር ከዚያ በኋላ ካለው ዘመን ጋር የሚያዛምድ ነው። ቤተ ክርስቲያን በየትኛውም ዘመን ልትመራበት የሚገባትን መርሐ ከዚህ መጽሐፍ ማግኘት ይቻላል።

**የመጽሐፉ መሪ ሐሳብና ዐላማ**

የመጽሐፉ መሪ ሐሳብ በ1፥8 ላይ በሚገባ ተገልጾአል። በዚያ ዘመን ለነበረ አንድ ታሪክ ጸሐፊ፣ የመጀመሪያውን መጽሐፍ ባጭሩ የተሰናዳ መግለጫ በማቅረብ የሁለተኛውን መጽሐፍ ዐላማ በዚሁ መልክ በመጠቀም መጻፍ የተለመደ ነበር። ሉቃስ የመጀመሪያውን መጽሐፍ እጣሬ በ1፥1-3 ላይ አቅርቦ፣ የሁለተኛውም መጽሐፍ መሪ ሐሳብ ጌታ ኢየሱስ፣ "በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ እንዲሁም በዓለም ዙሪያ ሁሉ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" ባለው ቃል ገልጾአል። ይህ ጥቅስ በአንድ መንገድ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ አስተዋጽኦ ነው ሊባል ይቻላል። ('ዕቅድና አስተዋጽኦ' በሚለው ርእስ ሥር የተጻፈውን ይመ)።

**የመጽሐፉ ዋና ዐላማ የሚከተለውን ይመስላል:-**

1. ***ታሪክን ለማቅረብ፤*** የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ታሪክ በማቅረቡ ረገድ የሚጫወተው ሚና የሚናቅ አይደለም። ስለ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት፣ ስለ ወንጌል ሥርጭት፣ ስለ ማኅበረ ምእመናን አጀማመርና በሐዋርያት ስልት ወንጌልን ስለ ማሠራጨት የሚናገር ነው። ክርስትናን ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ፣ ጽኑ ታሪካዊ መሠረት ላይ መመሥረቱ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና ትምህርት በአራቱ ወንጌሎች ውስጥ ተተርኮአል፤ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን አጀማመር ታሪክ በተቀነባበረ መልኩ አቅርቦአል።
2. **ስለ ክርስትና መከላከያ ለማቅረብ፤** ለአይሁድና (ለምሳሌ:-4፥8-12) ለአሕዛብ (ለምሳሌ:- 25፥8-11) የክርስትና እምነት ትክክለኛ ሃይማኖት መሆኑን በማረጋገጥ እነርሱን ወደ እምነት ለማምጣት ነው።
   መጽሐፉ የጥንት ቤተ ክርስቲያን የአረማውያንንና የአይሁድን አስተሳሰብ፣ እንዲሁም የሮማውያንን መንግሥትና የግሪኮችን ኅብረተሰብ እንዴት እንደ ተቋቋመች ያሳያል።
   ምናልባት ሉቃስ ይህን መጽሐፍ የጻፈው፣ ጳውሎስ ሮም እስር ቤት ሆኖ ፍርድ እየተጠባበቀ ሳለ ሊሆን ይችላል። ጳውሎስ ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከቀረበለት፣ የኢየሱስን የሕይወት ታሪክ፣ የቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ታሪክና (የራሱን የጳውሎስን ድርሻ ጨምሮ) የጻፋቸውን የመጀመሪያ መልእክቶቹን አሰባስቦ ከማቅረብ በላይ ምን ዐይነት መከላከያ ነጥቦችን ሊያቀርብ ይችላል?
3. ***መመሪያ ለመስጠት፤*** ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ዘመን በምድር እንደምትቈይ ሉቃስ የሚያውቅበት ምንም መንገድ አልነበረውም፤ ሆኖም ግን ቤተ ክርስቲያን በምድር እስካለችና በዐላማዋ እስከ ተጓዘች ድረስ፣ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ዋና መመሪያ ነው። ቤተ ክርስቲያን በመከራና በስደት ጊዜ የወሰደችው መሠረታዊ ርምጃ በዚሁ መጽሐፍ ተጠቅሶአል። እነዚህ መመሪያዎች እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድረስ ቤተ ክርስቲያን ተመሳሳይ ችግር ሲገጥማት ሥራ ላይ የሚውሉ ናቸው።
4. **ክርስትና አስከፊ ስደትን በመቋቋም በድል አድራጊነት መውጣት መቻሉን ለማሳየት፤** ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ከኢየሩሳሌም እስከ ሮም ማድረሷና በሮማውያን ግዛት ውስጥ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን በየስፍራው መመሥረት መቻሏ፤ ክርስትና የሚንቀሳቀሰው በሰው ኀይል ወይም በሰው ሥራ ብቻ እንዳልነበረ ያመለክታል፤ የእግዚአብሔር እጅ አብሮአት ነበረ (5፥35-39 ይመ)።

**የጽሑፉ ባሕርያት**

(1) ***በትክክል የቀረበ ዝርዝር ታሪክ፤*** በእያንዳንዱ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ላይ የሚገኝ እያንዳንዱ ገጽ ትክክልና ግልጽ በሆነ ዝርዝር የተሞላ ታሪክ ተመራማሪን የሚያረካ አቀራረብ አለው። ትረካው የሠላሳ ዓመት ታሪክን የሚዳስስና በመልክዐ ምድርም ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ ሮም የሚዘልቅ ነው። ሉቃስ እነዚህን ታሪካዊ ጊዜያትና ስፍራዎች በሚገልጽበት ጊዜ፣ ልዩ ልዩ ሕዝቦችን፣ ባህል፣ የመንግሥት አስተዳደር፣ የቈጵሮስ የፍርድ ቤት ትዕይንቶች፣ እንዲሁም በአንጾኪያ፣ በኤፌሶን፣ በአቴንስ፣ በቆሮንቶስና በሮም የተከሠቱ ድርጊቶችን ያካተተ ነበር። የአረማውያን አገር አውራጃዎችና የአይሁድ መናኸሪያ ስፍራዎችም ተጠቅሰዋል። እንደዚያም ሆኖ፣ በሥነ ቅርስ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ ሉቃስ ለሚገልጸው ለእያንዳንዱ ጊዜና ቦታ ተገቢውን ቃላት ተጠቅሞአል። ሉቃስ የጠቀሳቸው የፖለቲካ ባለሥልጣኖችና መልክዐ ምድሮች በታሪክ ውስጥ በተባለው ጊዜና ቦታ መኖራቸውን ለማስተባበል የሚፈልጉ ተቃዋሚዎች ጥረት ቢያደርጉም

አልተሳካላቸውም።

(2) **ሥነ ጽሑፋዊ ውበት፤** ሉቃስ ከሌሎቹ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ጸሓፊዎች ጋር ሲነጻጸር የቃላት አጠቃቀሙ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያለ ነው፤ ከዚህም በላይ ቃላትን የሚጠቀመው ለጽሑፉ ውበት በሚሰጠው መልክና ሊገልጽ የፈለገውን ድርጊቶች ለተፈጸመበት አካባቢና ጊዜ በሚስማማ፣ የነበረውንም ባህል በሚያንጸባርቅ መልኩ ነው። አንዳንድ ጊዜ ምሁራን የሚጠቀሙበትን የግሪክ ቋንቋ ይጠቀማል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት በፓለስቲናና በአካባቢዋ የሚጠቀሙበትን የአራማይስጥ አገላለጽን ይጠቀምበታል። ይህም የሚያመለክተው ሉቃስ አንድን ድርጊትና ጊዜ ለመግለጽ ያለውን የቋንቋ አጠቃቀም ጥንቃቄ ነው። በፓለስቲና ስለ ተፈጸመ ሁኔታ በሚጽፍበት ጊዜ፣ የአራማይስጥ አገላለጽ ይጠቀማል (ም 1-12)። ነገር ግን ጳውሎስ ግሪክ ተናጋሪ ወደ ሆኑ አካባቢዎች ዘልቆ በሚሄድበት ጊዜ በአራማይስጥ ዘይቤ መጠቀሙ ያከትማል።

(3) **ትዕይንታዊ አገላለጽ፤** ሉቃስ፣ ጥበባዊ በሆነ መልክ ንግግሮችን አስፍሮአል፤ ይህም ትዕይንታዊ ለሆነው የትረካ አገላለጹ አስተዋጽኦ አለው። ይህ ትዕይንታዊ ትረካ የቀረበው የጴጥሮስና የጳውሎስን አገልግሎት ሚዛን ውስጥ በማስገባትና እኩል ስፍራም በመስጠት ነው፤ ከዚህም በላይ የሌሎቹ ሰዎች ንግግርም ለትረካው ለየት ያለ ውበትን አጐናጽፎታል። ሉቃስ ዝርዝር ሁኔታ ውስጥ ገብቶ ትረካውን ማቅረብ መቻሉ ለትዕይንቱ ሕይወት ሰጥቶታል። በየትኛውም የጥንት ጽሑፍ የመርከብ አደጋን በተመለከተ የባሕር፣ የመርከብና የመርከበኞችን ዝርዝር ነገር አካትቶ በማቅረብ (ም 27)፣ እንደ ሉቃስ የተዋጣለት ትረካ ያቀረበ አይገኝም።

(4) **በግል ስሜት ያልተዋጠ አተራረክ፤** ሉቃስ ጽሑፉ ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ አቀነባብሮ ቢያቀርብም፣ ሐቆችን እያዛባ አልነበረም። በጥንት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረውን ውድቀትና ድል፣ ክፉውንና በጐውን ጎን ለጐን ማቅረቡ፣ ትረካው ከግል ስሜት ነጻ መሆኑን ያሳያል። በግሪክ በነበሩ አይሁድና በይሁዳ ምድር በነበሩ አይሁድ መካከል የተነሣውን መቃቃር ብቻ ሳይሆን (6፥1)፣ በጳውሎስና በበርናባስ መካከል የነበረውን አለመግባባትም (15፥39) አቅርቦአል። በምእመናን መካከል የነበረውን መከፋፈልና ልዩነት ሳይጠቅስ አላለፈም (15፥2፤ 21፥20-21)።

**ዕቅድና አስተዋጽኦ**

ሉቃስ፣ የቤተ ክርስቲያን አመሠራረትንና እድገትን በተመለከተ የተለያዩ ርእስ ነገሮችን አቀነባብሮ አቅርቦአል። የመጽሐፉ ንድፍ በሚከተሉት ዋና ዋና ነገሮች ዙሪያ ይሽከረከራል (1) ዋና ዋና ሰዎች:- ጴጥሮስና ጳውሎስ፤ (2) **አስፈላጊ ርእስ ጒዳዮችና ድርጊቶች:-** የመንፈስ ቅዱስ ሚና፣ የወንጌል መልእክተኞች ወደ አዳዲስ መስኮች መላክ፣ የነፍሳት መዳን፣ የቤተ ክርስቲያን እድገት፣ በክርስቲያን ማኅበረ ሰብ ውስጥ ያለ ሕይወት፤ (3) **ጒልሕ ችግሮች:-** በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ያለ ግጭት፣ አይሁድ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያደረሱት ስደት፣ በአይሁድና በሮማውያን ፊት ለፍርድ መቅረብ፣ ከአሕዛብ ጋር የነበረ ግብግብ፣ እንዲሁም በአገልግሎት ላይ የሚገጥሙ ሌሎች መከራዎች፤ (4) ***በመልክዐ ምድር ሽፋን ወደ ፊት መገሥገሥ:-*** አምስት ዋና ዋና ደረጃዎች አለው፣ ይኸውም ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ ሮም ድረስ ነው።

1. ጴጥሮስና በፓለስቲና የቤተ ክርስቲያን መጀመር (ም 1-12)

   ሀ "በይሁዳ፣ በገሊላና በሰማርያ" (1፥1-9፥31፤ ይመ)

   (1) መግቢያ (1፥1-2)
   (2) የክርስቶስ ድኅረ ትንሣኤ አገልግሎት (1፥3-11)
   (3) መንፈስ ቅዱስን የመጠባበቅ ወቅት (1፥12-26)
   (4) በመንፈስ ቅዱስ መሞላት (ም 2)
   (5) የሽባው ሰው መፈወስና በዚሁ ምክንያት የጴጥሮስና የዮሐንስ መያዝ (3፥1-4፥31)
   (6) የጋራ ንብረት (4፥32-5፥11)
   (7) የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መያዝ (5፥12-42)
   (8) የሰባት ዲያቆናት መመረጥ (6፥1-7)
   (9) የእስጢፋኖስ መያዝና ሰማዕትነት (6፥8-7፥60)
   (10) በኢየሩሳሌም የነበሩ ምእመናን መበተን (8፥1-4)
   (11) የፊሊጶስ አገልግሎት (8፥5-40)
      (ሀ) በሰማርያ (8፥5-25)
      (ለ) ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ማገልገሉ (8፥26-40)
   (12) የሳኦል መለወጥ (9፥1-31)

   ለ. "እስከ ፊንቄ፣ ቆጵሮስና አንጾኪያ ድረስ" (9፥32-12፥25፤ 11፥19 ይመ)

   (1) በሜድትራኒያን ባሕር ጠረፍ አካባቢ የጴጥሮስ አገልግሎት (9፥32-11፥18)
      ሀ. ኤንያንና ዶርቃን ማገልገሉ (9፥32-43)
      ለ. ቆርኔሌዎስን ማገልገሉ (10፥1-11፥18)
   (2) በአንጾኪያ አዲስ የተቋቋመችው የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን (11፥19-30)
   (3) ሄሮድስ ቤተ ክርስቲያንን ማሳደዱና መሞቱ (ም 12)

2. የጳውሎስ አገልግሎትና ቤተ ክርስቲያን ከአንጾኪያ እስከ ሮም ድረስ መስፋት (ም 13-28)
   ሀ. "በፍርጊያና በገላትያ አገር" (13፥1-15፥35፤ 16፥6 ይመ)
      (1) የጳውሎስ የመጀመሪያው የወንጌል ተልእኮ ጉዞ (ም 13-14)
      (2) የኢየሩሳሌሙ ጉባኤ (15፥1-35)
   ለ. "ወደ መቄዶንያ ማለፉ" (15፥36-21፥16፤ 16፥9 ይመ)
      (1) የጳውሎስ ሁለተኛው የወንጌል ተልእኮ ጉዞ (15፥36-18፥22)
      (2) የጳውሎስ ሦስተኛው የወንጌል ተልእኮ ጉዞ (18፥23-21፥16)
   ሐ. "ወደ ሮም" (21፥17-28፥31፤ 28፥14 ይመ)
      (1) የጳውሎስ በኢየሩሳሌም መታሰር (21፥17-23፥35)
         (ሀ) መያዙ (21፥17-22፥29)
         (ለ) በአይሁድ ሸንጎ ፊት ለፍርድ መቅረቡ (22፥30-23፥11)
         (ሐ) ወደ ቂሣርያ መወሰዱ (ም 23፥12-35)
      (2) ጳውሎስ በቂሣርያ መታሰሩ (ም 24-26)
         (ሀ) ፊልክስ ፊት ለፍርድ መቅረቡ (ም 24)
         (ለ) ፊስጦስ ፊት ለፍርድ መቅረቡ (25፥1-12)
         (ሐ) ፊስጦስና አግሪጳ ፊት የመከላከያ ንግግር ማድረጉ (25፥13-26፥32)
      (3) ወደ ሮም ጉዞ (27፥1-28፥15)
      (4) ሮም ሁለት ዓመት በግዞት መቀመጡ (28፥16-31)

## ኢየሱስ ወደ ሰማይ ዐረገ

**1** ቴዎፍሎስ ሆይ፤ ኢየሱስ ለማድረግና
ለማስተማር የጀመረውን ሁሉ ቀደም
ባለው መጽሐፌ ጽፌልሃለሁ፤ 2ይኸውም
እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ ለመረጣቸው ሐዋ
ርያት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሰጣ
ቸው ትእዛዝ ነው:: 3ከሕማማቱም በኋላ ራሱ
ቀርቦ ሕያው መሆኑን፣ ለእነዚሁ በብዙ ማስ
ረጃ እያረጋገጠላቸው አርባ ቀንም ዐልፎ ዐልፎ
እየታያቸው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነገራ
ቸው:: 4ከእነርሱም ጋር በማእድ ተቀምጦ ሳለ
እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ "ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤
ነገር ግን እኔ ስናገር የሰማችሁትን፣ አብ የሰጠ
ውን ተስፋ ጠብቁ፤ 5ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ
ነበርና፣ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመ
ንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ::"
6እነርሱም ተሰብስበው ሳሉ፣ "ጌታ ሆይ፤ የእ
ስራኤልን መንግሥት መልሰህ የምታቋቁ
ምበት ጊዜው አሁን ነውን? ብለው ጠየቁት::
7እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "አብ በገዛ
ሥልጣኑ የወሰነውን ጊዜ ወይም ወቅት
ማወቁ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤ 8ነገር ግን
መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት
ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም፣
በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ
ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ::"
9ይህን ካለ በኋላ እያዩት ወደ ላይ ዐረገ፤
ደመናም ከዐይናቸው ሰወረችው::
10እርሱም በሚሄድበት ጊዜ ትኵር
ብለው ወደ ሰማይ ሲመለከቱ፣ እነሆ፤ ነጫጭ
ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ድንገት አጠ
ገባቸው ቆሙ፤ 11እንዲህም አሏቸው፤ "እና
ንት የገሊላ ሰዎች ሆይ፤ ወደ ሰማይ እየተ
መለከታችሁ እዚህ የቆማችሁት ለምንድን
ነው? ይህ ከእናንተ ዘንድ ወደ ሰማይ ሲያርግ
ያያችሁት ኢየሱስ፣ ልክ ወደ ሰማይ ሲወጣ
እንዳያችሁት በዚሁ ሁኔታ ይመለሳል::"

## ማትያስ በይሁዳ ምትክ ተመረጠ

12ከዚያም ደብረ ዘይት ከተባለው ተራራ
ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ ይህም ተራራ
ከኢየሩሳሌም የሰንበት መንገድ ያህል[ሀ] ይርቅ
ነበር:: 13ወደ ከተማይቱም በገቡ ጊዜ ወደ
ሚኖሩበት ሰገነት ወጡ፤ እነዚህም ጴጥሮስ፣
ዮሐንስ፣ ያዕቆብ፣ እንድርያስ፣ ፊልጶስ፣ ቶማስ፣
በርተሎሜዎስ፣ ማቴዎስ፣ የእልፍዮስ ልጅ
ያዕቆብ፣ ቀናኢ የተባለው ስምዖንና የያዕቆብ
ልጅ ይሁዳ ነበሩ::
14እነዚህ ሁሉ ከሴቶቹና ከኢየሱስ እናት ከማ
ርያም ጋር እንዲሁም ከወንድሞቹ ጋር በአንድ
ልብ ሆነው ያለማቋረጥ ተግተው ይጸልዩ ነበር::
15በእነዚያም ቀናት፣ ጴጥሮስ መቶ ሃያ

ሀ12 አንድ ሺህ አንድ መቶ ሜትር ገደማ ነው

1፥1 ሉቃ1፥1-4፤ 3፥23
1፥2 ቍ9:11፤ማቴ 28፥19:20፤ማር6፥30፤ 16፥19፤ዮሐ13፥18፤ 15፥16:19
1፥3 ማቴ3፥2፤ 28፥17፤ ሉቃ24፥34:36፤ ዮሐ 20፥19:26፤ 21፥1:14፤1ቆሮ15፥5-7
1፥4 መዝ27፥14፤ ሉቃ24፥49፤ ዮሐ14፥16፤ ሐሥ2፥33
1፥5 ማር1፥4:8
1፥6 ማቴ17፥11፤ ሐሥ3፥21
1፥7 ዘዳ29፥29፤ መዝ 102፥13፤ ማቴ24፥36
1፥8 ማቴ28፥19፤ ሉቃ24፥48፤ሐሥ 2፥1-4፤8፥1-25
1፥9 ቍ2፤ማር 16፥19
1፥10 ዮሐ20፥12
1፥11 ማቴ16፥27፤ ሐሥ2፥7
1፥12 ማቴ21፥1፤ ሉቃ 24፥52
1፥13 ማቴ10፥2-4፤ ማር3፥16-19፤ሉቃ 6፥14-16፤ሐሥ 9፥37፤ 20፥8
1፥14 ማቴ12፥46፤ ሉቃ18፥1፤23፥49:55፤ ሐሥ2፥42፤4፥24፤ 6፥4፤ሮሜ1፥10

1፥1 ቀደም ባለው *መጽሐፌ፤* የሉቃስን ወንጌል ማለት ነው:: የሐዋርያት ሥራ የተጻፈው ለዚያው ወዳጁና አጋሩ ለቴዎፍሎስ ነው:: *ለማድረግና ለማስተማር የጀመረውን፤* ትክክለኛው የሉቃስ ወንጌል አጠቃላይ ሐሳብ ነው፤ ይኸውም ራሱ ኢየሱስ በቀጥታና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ሥራውን በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንደተገለጠው መቀጠሉን ያመለክታል::

1፥2 *እስከ ዐረገበት፤* ዕርገቱ ለሉቃስ ወንጌል መዝጊያ ሲሆን (24፥50-52)፣ ለዚህ መጽሐፍ ደግሞ መክፈቻ ነው (ቍ 6-11) ያረገውም ከትንሣኤ በኋላ በአርባኛው ቀን ነው (ቍ3)። *በመንፈስ ቅዱስ፤* ጌታ ኢየሱስ ለሐዋርያቱ መመሪያ የሰጣቸው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነበር፤ ሐዋርያቱም ወደ ፊት የሚያከናውኑት ተግባር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መሆኑን ከዚህ ቀጥሎ ያለው ክፍል ግልጽ ያደርገዋል (ቍ4-5:8፤ ሉቃ24፥49፤ ዮሐ20፥22):: ሉቃስ በአገላለጹ ስልቱ የመንፈስ ቅዱስን ሥራና ለአገልግሎትም ኀይልን የሚሰጥ እርሱ መሆኑን በአጽንዖት ይገልጻል (ለምሳሌ ቍ8፤2፥4:17፤4፥8:31፤5፥3፤ 6፥3:5፤7፥55፤8፥16፤9፥17:31፤10፥44፤13፥2:4፤15፥28፤16፥6፤ 19፥2:6፤ የሉቃ 4፥1 ማብ ይመ)::

1፥3 *በብዙ ማስረጃ እያረጋገጠላቸው፤* ጌታ ከትንሣኤ በኋላ የተገለጠባቸውን ሁኔታዎች ይመ (ማቴ 28፥1-20፤ ሉቃ 24፥1-53፤ ዮሐ20፥1-29፤ 1ቆሮ15፥3-8):: *ስለ እግዚአብሔር መንግሥት፤* የጌታ የኢየሱስ ትምህርት መሠረተ ሐሳብ ነው (የማቴ 3፥2፤ ሉቃ 4፥43 ማብ ይመ)::

1፥4 *አብ የሰጠውን ተስፋ፤* መንፈስ ቅዱስ ነው (ዮሐ14፥26፤ 15፥26-27፤ 16፥12-13 ይመ)::

1፥5 *ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ፤* ሉቃ 3፥16 ይመ:: *ከጥቂት ቀን በኋላ፤* በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ እውን የሆነው ከዐሥር ቀን በኋላ በበዓለ ኀምሳ (በጴንጤቆስጤ) ቀን ነበር (2፥1-4)::

1፥6 *የእስራኤልን መንግሥት መልሰህ የምታቋቍምበት፤* እነርሱም እንደ ሌሎች ወገኖቻቸው ሁሉ፣ እስራኤል ከባዕድ አገዛዝ ነጻ ወጥታ የራሷን መንግሥት በዚህ ዓለም እንድታቋቁም ይፈልጉ ነበር:: ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲነሣም አዲስ ዘመን የሚመጣላቸው መስሏቸው ነበር::

1፥7 *ጊዜ ወይም ወቅት፤* መቼ ወይም የአመጣጡ ሁኔታ ምን እንደሚመስል (1ተሰ 5፥1)::

*1፥8፤* የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ ዋና ዋና ሐሳብ የያዘ ነው፤ ሐዋርያት በኢየሩሳሌም (ም 1-7)፣ በይሁዳና በሰማርያ (ም 8-9)፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ማለት በቂሳርያ፣ በአንጾኪያ፣ በትንሹ እስያ፣ በግሪክና በሮም ምስክር ይሆናሉ:: (ም 10፥28)፤ ይሁን እንጂ የመንፈስ ቅዱስን ኀይል ሳይቀበሉ (ቍ4-5)፣ ይህን ከባድ ሥራ መጀመር አይችሉም ነበር:: *ምስክሮቼ፤* በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ዐቢይ ሐሳብ ነው (2፥32፤3፥15፤5፥32፤ 10፥39፤ 13፥31፤22፥15):: *በይሁዳና፤* የኢየሩሳሌም ከተማ የምትገኝበት አውራጃ ነው:: *ሰማርያ፤* ከይሁዳ በስተሰሜን የሚገኝ አጎራባች አውራጃ::

1፥10 ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች፤ መላእክት ብዙ ጊዜ በዚህ መልክ ይገለጻሉ::

1፥11 *የገሊላ ሰዎች፤* ከይሁዳ በቀር ዐሥራ አንዱ ሐዋርያት የገሊላ ሰዎች ናቸው፤ ይሁዳ ከዚህ በኋላ ከሐዋርያት ጋር አይገኝም:: *በዚሁ ሁኔታ፤* "በታላቅ ክብር" (ማቴ 24፥30) በዚሁ በተነሣበት አካል በደመና ይመለሳል ማለት ነው::

1፥12 *ደብረ ዘይት ... ተራራ፤* ጌታ ያረገው በኢየሩሳሌምና በቢታንያ መካከል ከሚገኘው ከዚሁ ተራራ ምሥራቃዊ ተዳፋት ላይ ነው (ሉቃ 19፥28-29:37፤ የዘካ 14፥4 ማር 11፥1፤ ሉቃ 19፥29 ማብ ይመ):: *የሰንበት መንገድ፤* 1.1 ኪሎ ሜትር ያህል ነው:: ይህ ርቀት የተወሰነው በአይሁድ መምህራን ሲሆን፣ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን መሠረት ያደረገ ነው (ዘጸ16፥29፤ ዘኍ35፥5፤ ኢያ3፥4):: አንድ በእምነቱ የጸና አይሁዳዊ በሰንበት ቀን ከዚህ በላይ ርቆ አይሄድም::

1፥13 *ወደሚኖሩበት፤* ምናልባት ይህ ክፍል፣ የአንድ ትልቅ ቤት ሰገነት ሆኖ ጌታ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የመጨረሻውን እራት የበላበት (ማር 14፥15) ወይም የማርቆስ እናት የማርያም ቤት ሊሆን ይችላል (የ12፥12 ማብ ይመ):: *በርተሎሜዎስ፤* በሦስቱ ተመሳሳይ ወንጌሎች (ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ) ያለው የሐዋርያት ስም ዝርዝርና (ማቴ10፥2-4፤ማር 3፥16-19፤ ሉቃ6፥14-16) በዮሐንስ ወንጌል ላይ ያለው ስም ዝርዝር (ዮሐ1:45-49፤21፥2) በርተሎሜዎስ የተባለው ናትናኤል መሆኑን ያመለክታል:: *የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፤* ታናሹ ያዕቆብ የተባለው ነው (ማር15፥40):: *ቀናኢ፤* የማቴ10፥4 ማብ ይመ:: *የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ፤* የአስቆሮቱ ይሁዳ ሳይሆን ታዴዎስ ነው (ማቴ 10፥3፤ ማር 3፥18)::

1፥14 *ከሴቶች...ጋር፤* የሐዋርያት ሚስቶችና (ከ1ቆሮ 9፥5 ጋር ያነጻጽሩ) ጌታን ያገለገሉ ሴቶች ስም ዝርዝር (ማቴ 27፥55፤ ሉቃ 8፥2-3፤ 24፥22) ሊሆን ይችላሉ:: *ከኢየሱስ እናት ከማርያም፤* በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለመጨረሻ ጊዜ የተጠቀሰችው እዚህ ላይ ነው:: *ከወንድሞቹ፤* የሉቃ8፥19 ማብ ይመ:: "ከወንድሞቹ"

በሚሆኑ ወንድሞች[ለ] መካከል ቆሞ፣ 16እንዲህ
አለ፤ “ወንድሞች ሆይ፤ ኢየሱስን ለያዙት
ሰዎች መሪ ስለ ሆናቸው ስለ ይሁዳ፣ መንፈስ
ቅዱስ አስቀድሞ በዳዊት አፍ የተናገረው
የመጽሐፉ ቃል መፈጸም ስላለበት፣ 17እርሱ
ከእኛ እንደ አንዱ ተቈጥሮ በዚህ አገልግ
ሎት የመሳተፍ ዕድል አግኝቶ ነበር።”
18 “ይህ ሰው ስለ ክፉ ሥራው በተከፈለው
ዋጋ መሬት ገዛ፤ በዚያም በግንባሩ ተደፍቶ
ሰውነቱ እመካከሉ ላይ ፈነዳ፤ ሆድ ዕቃውም
ተዘረገፈ፤ 19ይህም በኢየሩሳሌም በሚኖሩት
ሁሉ ዘንድ ተሰማ፤ መሬቱም በቋንቋቸው
‘አኬልዳማ’ ተብሎ ተጠራ፤ ትርጓሜውም
‘የደም መሬት’ ማለት ነው።

20ጴጥሮስም በመቀጠል እንዲህ አለ፤
“በመዝሙር መጽሐፍ፣

‘መኖሪያው ባዶ ትሁን፤
የሚኖርባትም ሰው አይገኝ’ ደግሞም፣
‘ሹመቱን ሌላ ሰው ይውሰደው’
ተብሎ ተጽፎአል።

21ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ በመካከላችን በገባበ
ትና በወጣበት ጊዜ ሁሉ፣ ከእኛ ጋር ከነ
በሩት መካከል አንድ ሰው መምረጥ ያስፈ
ልጋል፤ 22ይኸውም፣ ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ
ኢየሱስ ከእኛ ተለይቶ እስካረገበት ቀን
ድረስ የነበረ መሆን አለበት፤ ምክንያቱም

1፥16 ቍ20፤ ማቴ1፥22፤10፥4፤ ሐሥ6፥3፤11፥1፡12፡ 29፤14፥2፤18፥18፡27፤ 21፥7፤22፥5፤ሮሜ7፥1
1፥17 ቍ25፤ ዮሐ 6፥70፡71
1፥18 ማቴ26፥14፡ 15፤27፥3-10
1፥19 ዮሐ5፥2
1፥20 መዝ69፥25፤ 109፥8
1፥22 ቍ8፤ማር 1፥4፤ሉቃ24፥48
1፥24 1ሳሙ14፥41 ፤ሐሥ6፥6፤13፥3፤ 14፥23፤ራእ2፥23
1፥26 ሐሥ2፥14
2፥1 ዘሌ23፥15፡ 16፤ሐሥ1፥14፤20፥ 16፤1ቆሮ16፥8
2፥2 ሐሥ4፥31
2፥4 ማር16፥17፤ ሉቃ1፥15

ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣ
ኤው ምስክር እንዲሆን ያስፈልጋል።”
23ስለዚህ ኢዮስጦስ የሚሉትን፣ በርስያን
የተባለውን ዮሴፍንና ማቲያስን ሁለቱን
አቀረቡ፤ 24እንዲህም ብለው ጸለዩ፤ “ጌታ
ሆይ፤ አንተ የሰውን ሁሉ ልብ ታውቃለህ፤
ከእነዚህ ከሁለቱ መካከል የመረጥኸውን ሰው
አመልክተንና 25ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ ስፍራ
ትቶት በሄደው በዚህ አገልግሎትና በሐዋ
ርያዊነት ቦታ ላይ ሹመው።” 26ከዚያም ዕጣ
ጣሉላቸው፤ ዕጣውም ለማትያስ ወጣ፤ እር
ሱም ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቈጠረ።

## በበዓለ ኀምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ ወረደ

2 የበዓለ ኀምሳ ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም
በአንድነት፣ በአንድ ስፍራ ተሰብስ
በው ነበር፤ 2ድንገትም እንደ ብርቱ ዐውሎ
ነፋስ ያለ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ ተቀምጠው
የነበሩበትን ቤት እንዳለ ሞላው። 3የእሳት
ምላሶች የሚመስሉም ታዩአቸው፤ ተከፋፍለ
ውም በእያንዳንዳቸው ላይ ዐረፉ። 4ሁሉም
በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈስም እንዲ
ናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋ
ዎች[ሐ] ይናገሩ ጀመር።

[ለ]15 *ወይም አማኞች*
[ሐ]4 *ወይም ልሳኖች፤* እንዲሁም በቍ11

የሚለው ኋላ በቤተ ክርስቲያን ዋና መሪ የሆነውን ያዕቆብን ይጨምራል (12፥17፤15፥13፤ገላ2፥9)።

1፥16 *የመጽሐፉ ቃል መፈጸም ስላለበት፤* ጌታ ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊትና ከመጣም በኋላ በርካታ የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎች ስለ መሲሕ የሚናገሩ ናቸው ተብሎ ይታመናል። መዝሙረኛው በሕይወቱ የደረሰበትና መሲሑ ያለፈበት ሁኔታ ይመሳሰላል። ኢየሱስ በሉቃ 24፥27፡45-47 የሰጠው ትምህርት እነዚህንም መጻሕፍት ይመለከታል።

1፥18 *ይህ ሰው… መሬት ገዛ፤* ራሱ ይሁዳ መሬቱን በቀጥታ አልገዛም፤ ይሁን እንጂ ለካህናት በመለሰው ገንዘብ (ማቴ27፥3) የሸክላ ሠሪው መሬት ተገዝቶበታል (ማቴ27፥7)። *በግንባሩ ተደፍቶ፤* ማቴ27፥5 ይሁዳ ራሱን በራሱ ሰቅሎ እንደ ሞተ ያመለክታል። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው አሟሟቱም በማቴዎስ የተጠቀሰውን በመፈጸም ላይ እንዳለ ወድቆ መሞቱን የሚያሳይ ሳይሆን አልቀረም። ያም ሆነ ይህ አሟሟቱ የከፋ መሆኑ በዚህ ክፍል ተገልጾአል።

1፥19 *‘አኬልዳማ፤’* ቃሉ የአራማይክ ሲሆን፣ ለመሬቱ እንዲህ ያለ ስም የተሰጠው ሁኔታውን በሚያውቁ ሰዎች ነው፤ መሬቱ የተገዛው በይሁዳ የደም ገንዘብ ነበርና (ማቴ 27፥3-8)።

1፥20 *ተጽፎአል፤* ይሁዳ ትቶ በሄደው ቦታ ሌላ ሰው መተካት እንደሚያስፈልግ ለመግለፅ ሁለቱ ጥቅሶች (መዝ 69፥25 እና 109፥8) ተጣምረው ቀርበዋል።

1፥21 *በመካከላችን በወጣበትና በገባበት ጊዜ ሁሉ፤* በይፋ ባገለገለበት ጊዜ ማለት ነው።

1፥22 … *ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምስክር፤* ለዚህ የሚበቁ የሚያሟሉ ብዙ ሰዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ አማኞቹ በዚህ ጊዜ የሚፈልጉት ስለ ትንሣኤው ሳይፈራ ሳያፍር በአደባባይ የሚመሰክር ሰው ነበር፤ ከዚህ የተነሣም ዐሥራ ሁለተኛው ሐዋርያ ሆኖ ለመመረጥ በቃ (ቍ 25)።

1፥23 *በርስያን፤* የስሙ ትርጒም “የሰንበት ልጅ” ማለት ነው። በዚህ ስም ሁለት የጥንት አይሁድ ክርስቲያኖች ተጠርተውበታል፤ እነዚህም ወንድማማቾች ሳይሆኑ አይቀሩም። አንደኛው እዚህ ላይ የተጠቀሰው ዮሴፍ ሲሆን፣ ሁለተኛው በሐሥ 15፥22፡32 ላይ የተጠቀሰው ይሁዳ በኢየሩሳሌም ነቢይ የነበረና፤ ከሲላስ ጋር ወደ አንጾኪያ የተላከ ነው። *ኢዮስጦስ፤* የዮሴፍ የግሪክኛ ስሙ ነው። ስለ እርሱ እዚህ ላይ ከተጠቀሰው ውጪ የሚታወቅ ነገር የለም።

1፥26 *ዕጣ ጣሉላቸው፤* ምሳ16፥33 ይመ። ዕጣ በመጣል የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም አደረጉ፤ ዕጣ የሚጥሉትም ጠጠር ወይም ስንጥር እንጨት በማውጣት ነበር (1 ዜና 26፥13-16 ይመ፤ የነህ11፥1፤ዮና1፥7 ማብ ይመ)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ዕጣ መጣል ለመጨረሻ ጊዜ የተጠቀሰው እዚህ ላይ ነው።

2፥1 *የበዓለ አምሳ ቀን፤* የፋሲካ ሰንበት (ቅዳሜ) ካለፈ በኋላ አምሳኛው ቀን (ዘሌ 23፥15-16)፤ ሲሆን፣ ይህም የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን (እሑድ) ማለት ነው። በዓለ አምሣ፡ (ጰንጤቆስጤ) የሰባቱ ሱባዔ በዓል (ዘዳ 16፥10)፣ የመከር በዓል (ዘፀ 23፥16)፤ የበኵራት ቀንም (ዘኍ 28፥26) ይባላል። *ሁሉም በአንድነት … ተሰብስበው ነበር፤* እዚህ ላይ “ሁሉም” ማለቱ ቀደም ሲል ከተጠቀሰው አንጻር ሲታይ ዐሥራ አንዱን ሐዋርያትና ማትያስን መሆኑ ነው፤ ይሁን እንጂ 1፥13-15 ላይ የተጠቀሱትን ሁሉ ሳይጨምር አይቀርም። *በአንድ ስፍራ፤* ከደብረ ዘይት ተራራ እንደተመለሱ ያረፉበት ቦታ (1፥13) ሳይሆን፣ በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ካለው ስፍራ በአንዱ ማለት ነው፤ ደቀ መዛሙርቱ ቤተ መቅደሱ ክፍት በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ከዚያ አይታጡም ነበርና (ሉቃ 24፥ 53 ማብ ይመ)።

2፥2 *ብርቱ ዐውሎ ነፋስ፤* እስትንፋስ ወይም ነፋስ የእግዚአብሔር መንፈስ ምሳሌ ነው (ሕዝ37፥9፡14፤ዮሐ3፥8 ይመ)። የመንፈስ ቅዱስ መምጣት በጆሮ በሚሰማ (ነፋስ) በዐይን በሚታይ (እሳት) ምልክት ይታወቃል። *ቤት እንዳለ፤* ቤተ መቅደሱን ሳይመለከት አይቀርም (ከ7፥47 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥3 *ምላሶችም፤* በብዙ ቋንቋ ስለመናገር የተጠቀሰበት ቃል በመሆኑ፣ ለዐውዱ ተስማሚ የሆነ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። *እሳት፤* የእግዚአብሔርን መገኘት በምልክትነቱ የሚያመለክት ነው (ዘፀ3፥2 እና ማብ ይመ)፤ ከፍርድም ጋር የተያያዘ ነው (ማቴ 3፥12)።

2፥4 *ሁሉም፤* ሐዋርያት ወይም መቶ ሃያዎቹን ደቀ መዛሙርት ሊያመለክት ይችላል። መቶ ሃያዎቹን ያመለክታል የሚሉት ቍጥሩ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በላይ መሆኑ፣ ከኢዩኤል ትንቢት መፈጸም (ቍ17-18) ጋር ይስማማል ይላሉ፤ ይሁን እንጂ በቅርበት ያለው የዐውዱ ክፍል ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት የሚመለከት ነው (ቍ1 ማብ ይመ)፤ ትረካውም ጴጥሮስና አሥራ አንዱ ሕዝቡን ለማስተማር እንደ ቆሙ ያሳያል (ቍ14)። *በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤* በ1፥5፡8 ላይ የተነገረው መፈጸሙን ያሳያል። ጌታ ኢየሱስ በሉቃ 24፥49 የሰጠውንም ተስፋ ይመ። መንፈሳቸው ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ቍጥጥር ሥር ሆነ፤ ቃላቸውም

[5]በዚህ ጊዜ ከሰማይ በታች ካለው ሕዝብ
ሁሉ የመጡና እግዚአብሔርን የሚፈሩ አይ
ሁድ በኢየሩሳሌም ነበሩ። [6]ይህን ድምፅ ሲሰሙ፣
ብዙ ሕዝብ በአንድነት ተሰበሰቡ፤ እያንዳን
ዱም ሰው፣ ሰዎቹ በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ
በመስማቱ ግራ ተጋባ፤ [7]በመገረምና በመ
ደነቅም እንዲህ አሉ፤ "እነዚህ የሚነጋገሩት
ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? [8]ታዲያ፣
እያንዳንዳችን በተወለድንበት፣ በራሳችን
ቋንቋ ሲናገሩ የምንሰማቸው እንዴት ቢሆን
ነው? [9]እኛ የጳርቴና፣ የሜድ፣ የኢላሜጤም
ሰዎች፣ በመስጴጦምያ፣ በይሁዳ፣ በቀጰዶ
ቅያ፣ በጳንጦስ፣ በእስያ፣ [10]በፍርግያ፣ በጵ
ንፍልያ፣ በግብፅ፣ በቀሬና አጠገብ ባሉት
በሊቢያ አውራጃዎች የምንኖር፣ ከሮም የመ
ጣን [11]አይሁድና ወደ ይሁዲነት የገባን፣
የቀርጤስና የዐረብ ሰዎች ስንሆን፣ ሰዎቹ
የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በየቋንቋችን
ሲናገሩ እንሰማቸዋለን" [12]ሁሉም በአድናቆ
ትና ግራ በመጋባት፣ ይህ ነገር ምን ይሆን"
ተባባሉ።
[13]አንዳንዶቹ ደግሞ "ያልፈላ ብዙ የወይን

2፥5 ሉቃ2፥25፤ ሐሥ 8፥2
2፥7 ቊ12፤ሐሥ 1፥11
2፥9 ሐሥ16፥6:17፤ 18፥2፤19፥10፤ሮሜ 16፥5፤1ቆሮ16፥19፤2 ቆሮ1፥8፤1ጴጥ1፥1፤ ራእ1፥4
2፥10 ማቴ27፥32፤ ሐሥ13፥13፤ 14፥24፤ 15፥38፤16፥6፤18፥23፤
2፥13 1ቆሮ14፥23፤ ኤፌ5፥18

ቃሉ ነበር። *በሌሎች ቋንቋዎች፤* መንፈስ ቅዱስ ከዚህ በፊት ሰምተው በማያውቁት ቋንቋ እንዲናገሩ አደረጋቸው። ይህን በመሰለ በሌላ ቋንቋ መናገር በሐዋርያት ሥራ በሌሎች ሁለት ስፍራዎች ላይ ይገኛል (10፥46፤ 19፥6)። እንዲሁም በሌላ የአዲስ ኪዳን ክፍል (1ቆሮ 12–14) ስለዚሁ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተጽፎ ይገኛል፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ጥቅሶች በተለመዱና በታወቁ ቋንቋዎች መናገርን የሚያመለክቱ ስለ መሆናቸው በሁሉም ሊቃውንት ዘንድ የጋራ ስምምነት የለም። እዚህ ላይ የተጠቀሰው ስጦታ የተለያዩ ነገዶችና የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪዎች በተገኙበት ቦታ በመሆኑ የተለየ ጥቅም አለው።


2፥5 *እግዚአብሔርን የሚፈሩ አይሁድ፤* ከዓለም ዙሪያ የመጡ፣ በዚህ ጊዜ ግን ለጕብኝት ወይም ለጊዜው እዚያ ለመቈየት በኢየሩሳሌም የተሰበሰቡ በሃይማኖታቸው የጸኑ አይሁድ ነበሩ (ከሉቃስ 2፥25 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥6 *በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ፤* ከልዩ ልዩ የዓለም ክፍል የመጡት አይሁድ የእናት አገራቸውን የአራማይክ (የሱርስት) ቋንቋ ያውቃሉ፤ የግሪክ ቋንቋም በዓለሙ ሁሉ የመግባቢያ ቋንቋ ነበር። ሐዋርያት ሲነጋገሩበት የተሰማው ቋንቋ ግን ከየወገኑ የመጡት ሰዎች ሁሉ የሚነጋገሩበት ስለ ነበር በዚህ ወቅት የተከሠተውን ሁኔታ ልዩ ያደርገዋል።

2፥9 *ጳርቴ፤* ከጤግሮስ እስከ ሕንድ አገር የተዘረጋው ምድር። *ሜድ፤* ከመስጴጦምያ በስተ ምሥራቅ፣ ከፋርስ በስተ ሰሜን ምዕራብ፣ ከካስፒያን ባሕርም በስተ ደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ የሚገኝ አገር ነው። *የኢላሜጤም፤* ከፋርስ ባሕረ ሠላጤ በስተ ሰሜን የሚገኝ አገር ሲሆን፣ በምዕራብ በኩልም የጤግሮስ ወንዝ ይዋሰነዋል። *በመስጴጦምያ፤* በኤፍራጥስና በጤግሮስ ወንዞች መካከል የሚገኝ ምድር። *በይሁዳ፤* የአይሁድ አገር ነው። በዚህ ዐውድ ያለው ትርጕም እንደ ብሉይ ኪዳን አገላለጽ ከሆነ፣ ከግብፅ ወንዝ አንሥቶ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ (ዘፍ 15፥18) ያለው አገር ሆኖ ገሊላንም ይጨምራል። ቀጰዶቅያ፣ ጳንጦስ፣ እስያ፤ በታናሹ እስያ የሚገኙ አውራጃዎች።

2፥10 *በፍርግያ እና በጵንፍልያ፤* በታናሹ እስያ የሚገኙ አውራጃዎች። *በግብፅ* አያሌ አይሁድ ይኖሩባት ነበር፤ ከአምስቱ የእስክን ድርያ ክፍለ ከተሞች ሁለቱ የአይሁድ መኖሪያ ነበሩ። *በሊቢያ፤* ከግብፅ በስተ ምዕራብ የሚገኝ አገር። *በቀሬና፤* ቀሬናይ ለተባለው የሊቢያ አውራጃ ዋና ከተማ። *ከሮም፤* በሺህ የሚቈጠሩ አይሁድ በሮም ይኖሩ ነበር።

2፥11 *ወደ ይሁዲነት የገባን፤* የሙሴን ሕግ የተቀበሉ አሕዛብ ከአይሁድ ጋር እኩል ለማምለክ ሙሉ መብት ነበራቸው። *የቀርጤስን፤* ከግሪክ በስተ ደቡብ ምሥራቅ የምትገኝ ደሴት ናት። *ዐረብ፤* ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ያለው ምድር። የናባታውያን *ዐረብ* መንግሥት፣ ከቀይ ባሕር እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ይደርሳል፤ ዋና ከተማውም ጴጥራ ትባል ነበር። *ሲናገሩ እንሰማለን፤* ነገሩ የመስማት ሳይሆን የመናገር ታምር ነው። በሌሎች ቋንቋ ሲናገሩ የተሰሙት ምእመናን የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ይና ገሩ የነበሩት፣ ከልዩ ልዩ ስፍራ የመጡ አይሁድ በሚኖሩባቸው የተለያዩ አገሮች ቋንቋ ነበር።



ጠጅ[a] ጠጥተዋል” በማለት አፌዙባቸው::

**ጴጥሮስ ለሕዝቡ ንግግር አደረገ**

[14]በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ከዐሥራ አንዱ ጋር
ተነሥቶ ቆመ፤ ድምፁንም ከፍ አድርጎ እን
ዲህ ሲል ለሕዝቡ ተናገረ፤ “እናንት የይ
ሁዳ ሰዎች፤ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁሉ፤
ይህን አንድ ነገር ዕወቁ፤ በጥሞናም አድ
ምጡኝ:: [15]ጊዜው ገና ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት
ስለ ሆነ፣ እናንተ እንደምታስቡት እነዚህ
ሰዎች አልሰከሩም:: [16]ነገር ግን ይህ በነቢዩ
በኢዩኤል እንዲህ ተብሎ የተነገረ ነው፤

[17]“እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በመጨረሻው
ቀን፣
መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ
አፈሳለሁ፤
ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት
ይናገራሉ፤
ጕልማሶቻችሁ ራእይ ያያሉ፤
ሽማግሌዎቻችሁ ሕልም ያልማሉ::
[18]በዚያ ጊዜ በወንዶችና በሴቶች
አገልጋዮቼ ላይ፣
መንፈሴን አፈሳለሁ፤
እነርሱም ትንቢት ይናገራሉ::
[19]በላይ በሰማያት ድንቅ ነገሮችን፣
አሳያለሁ፤
በታች በምድርም ምልክቶችን እሰጣለሁ፤
ደምና እሳት፣
የጢስም ጭጋግ ይሆናል::
[20]ታላቅና ክቡር የሆነው የጌታ ቀን
ከመምጣቱ በፊት፣
ፀሐይ ወደ ጨለማ፣
ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣሉ::
[21]የጌታን ስም፣
የሚጠራ ሁሉ ይድናል::’

[22]“የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤ ይህን ቃል ስሙ፤
እናንት ራሳችሁ እንደምታውቁት፣ እግዚአብሔር
በመካከላችሁ ታምራትን፣ ድንቅ ነገሮችንና

2፥15 1ተሰ5፥7
2፥17 ዘኍ11፥25፤ ኢሳ44፥3፤ሕዝ39፥ 29፤ ዮሐ7፥37-39፤ ሐሥ 10፥45፤21፥9
2፥18 ሐሥ21፥9-12
2፥19 ሉቃ21፥11
2፥20 ማቴ24፥29
2፥21 ዘፍ4፥26፤ 26፥25፤መዝ105፥1፤ ኢል2፥28-32፤ ሐሥ 9፥14፤ ሮሜ10፥13፤ 1ቆሮ1፥2፤2ጢሞ2፥22
2፥22 ማር1፥24፤ ዮሐ3፥2፤4፥48
2፥23 ኢሳ53፥10፤ ማቴ16፥21፤ ሉቃ24፥20፤ ሐሥ3፥13፡18፤ 4፥28
2፥24 ቍ32፤ዮሐ 20፥9፤ሐሥ13፥30፡ 33፡34፡37፤17፥31፤ ሮሜ6፥4፤8፥11፤ 10፥9፤ 1ቆሮ6፥14፤ 15፥15፤ኤፌ1፥20፤1 ቆሮ6፥14፤15፥15፤ኤ ፌ1፥20፤ቈላ2፥12፤ ዕብ13፥20፤1ጴጥ 1፥21
2፥27 ቍ31፤ሐሥ 13፥35
2፥28 መዝ16፥8-11
2፥29 1ነገ2፥10፤ነህ 3፥16፤ሐሥ7፥8፡9፤ 13፥36፤22፥5
2፥30 ማቴ1፥1
2፥31 መዝ16፥10
2፥32 ቍ24፤ሉቃ 24፥48
2፥33 ማር16፥19፤ ዮሐ7፥39፤14፥26፤ 15፥26፤ሐሥ1፥4፤ 10፥45፤ፊል2፥9

ምልክቶችን በእርሱ በኩል በማድረግ ለናዝ
ሬቱ ኢየሱስ መስክሮለታል:: [23]እግዚአብሔር
በጥንት ውሳኔውና በቀደመው ዕውቀቱ ይህን
ሰው አሳልፎ በእጃችሁ ሰጣችሁ፤ እናንተም
በክፉ ሰዎች[b] እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት::
[24]እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አስወግዶ
አስነሣው፤ ሞት ይዞ ሊያስቀረው አልቻለ
ምና:: [25]ዳዊትም ስለ እርሱ እንዲህ ይላል፤

“ጌታን ሁልጊዜ በፊቴ አየዋለሁ፤
እርሱ በቀኜ ነውና፣
ከቶ አልታወክም::
[26]ስለዚህ ልቤ ደስ አለው፤ አንደበቴም
ሐሤት አደረገ፤
ሥጋዬም በተስፋ ይኖራል::
[27]ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፤
ቅዱስህም መበስበስን እንዲያይ
አታደርግም::
[28]የሕይወትን መንገድ እንዳውቅ
አደረግኸኝ፤
በፊትህም በሐሤት ትሞላኛለህ::’

[29]“ወንድሞች ሆይ፤ ከቀደምት አባቶች
ዳዊት ሞቶ እንደ ተቀበረ፣ መቃብሩም እስከ
ዛሬ ድረስ በመካከላችን እንደሚገኝ በድፍ
ረት መናገር እችላለሁ:: [30]ነቢይ በመሆ
ኑም፣ እግዚአብሔር ከዘሮቹ አንዱን በዙፋኑ ላይ
እንደሚያስቀምጥ በመሐላ ቃል የገባለት
መሆኑን ዐወቀ:: [31]ይህንን አስቀድሞ በማ
የቱ እርሱ በሲኦል እንደማይቀርና ሥጋውም
እንደማይበሰብስ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ[c]
ተናገረ:: [32]ይህን ኢየሱስ፣ እግዚአብሔር ከሞት
አስነሣው፤ እኛም ሁላችን ለዚህ ነገር ምስ
ክሮች ነን:: [33]ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ
ከፍ ከፍ ካለ በኋላ፣ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ
ከአብ ተቀብሎ አሁን የምታዩትንና የምትሰ

[a]13 ወይም *ጣፋጭ ወይን*
[b]23 ወይም *ሕግ በሌላቸው ሰዎች (አሕዛብን ያመለክታል)*
[c]31 ወይም *መሲሕ፤* በግሪክ *ክርስቶስ፣* በዕብራይስጥ *መሲህ* ማለት *የተቀባው* ማለት ነው፤ እንዲሁም በቍ36

2፥14-40፤ ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ፣ የሚቀጥለው የመልእክቱ አቀራረብና ፍሬ ሐሳቡ በጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን የተለመደ ሆኖ ነበር፤ ይኸውም (1) ሁኔታዎችንና ድርጊቶችን ገልጾ ማስረዳት (ቍ14፥21)፤ (2) ስለ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ማለት ሞት፣ ትንሣኤና ከፍ ከፍ ማለቱን ማስተማር (ቍ22፥36)፤ (3) ለሰዎች የንስሓና የጥምቀት ጥሪ ማቅረብ (ቍ37፥40):: የዚህ ስብከት አጠቃላይ ሐሳብ ከም 3፤10፤13 ጋር ተመሳሳይነት አለው::

2፥14 *ከዐሥራ አንዱ ጋር፤* ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀው:: ለተለያዩ ሰዎች በሌሎች ቋንቋዎች ተናግረው ነበር፤ እዚህ ላይ የምናየው እነርሱ አብረውት ቆመው፣ ጴጥሮስ እነርሱን ተክቶ መናገሩን ነው::

2፥15 *ገና ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት፤* እንደ በዓለ ኀምሳ ባለው ቀን አንድ አይሁዳዊ ከአራት ሰዓት በፊት እህል አይቀምስም:: ስለዚህ ይህን ያህል ብዛት ያለው ሰው፣ ገና በጧቱ ይሰክራል ተብሎ ፈጽሞ አይታሰብም::

2፥17-18 *በሥጋ ለባሽ ሁሉ...ወንዶችና ሴቶች...ልጆቻችሁ ጕልማሶቻችሁ ... በወንዶችና በሴቶች፤* የጾታ፣ የዕድሜና የማዕረግ ልዩነት ሳይደረግ፣ መንፈስ ቅዱስ ለሁሉም እኩል ይሰጣል::

2፥17 *በመጨረሻው ቀን፤* ኢሳ 2፥2፤ ሆሴ 3፥5፤ ሚክ 4፥1 ይመ፤ እንዲሁም የ1ጢሞ 4፥1፤ 2ጢሞ 3፥1፤ ዕብ 1፥1፤ 1ጴጥ 1፥20፤1ዮሐ2፥18 ማብ ይመ:: ይህ ከኢዩኤል የተጠቀሰውን ክፍል ዕብራይስጡ፣ “ከዚህ በኋላ” ሲለው፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ግን፣ “ከእነዚህ ነገሮች በኋላ” ይለዋል:: ጴጥሮስ የተጠቀሰውን ክፍል የተነተነው ከአዲሱ ኪዳን መጨረሻ ዘመን ጋር አዛምዶና (ኤር 31፥33-34፤ ሕዝ 36፥26-27፤ 39፥29 ይመ) ከብሉይ ኪዳን መጀመሪያ ዘመን ጋር አነጻጽሮ ነው:: ይህም ስለ መሲሑ የተነገረው ሁሉ በመፈጸም ላይ መሆኑን ያሳያል:: *መንፈሴን፤* የ1፥2 ማብ ይመ::

2፥21 *የሚጠራ ሁሉ፤* ከቍ39 ጋር ያነጻጽሩ፤ ነገሩ መንፈሳዊ ቃላትን መደርደር ብቻ ሳይሆን፣ እምነትንና መታዘዝን ይጠይቃል (ማቴ 7፥21)::

2፥22 *ታምራትን ድንቅ ነገሮችንና ምልክቶችን ... በማድረግ...መስክሮለታል፤* ኢየሱስ ያከናወናቸው ድንቅ ሥራዎች መሲሕ መምጣቱን የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው::

2፥23 *በክፉ ሰዎች፤* የኦሪትን ሕግ ያልተቀበሉ አሕዛብ ማለት ነው፤ እዚህ ላይ ግን አሕዛብ ክፉ ድርጊት እንደ ፈጸሙ ያሳያል::

2፥27 *ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፤* በቍ31 ላይ እንደምናየው ዳዊት ይህን የተናገረው ስለ ራሱ ብቻ ሳይሆን፣ የኋላ ኋላ ስለ መሲሑ ነበር፤ የመሲሑም ሥጋ በመቃብር እንዲበሰብስ እግዚአብሔር አልፈቀደም::

2፥29 *መቃብሩም ... በመካከላችን እንደሚገኝ፤* የዳዊት መቃብር ዐፅሙን በውስጡ እንደያዘ አሁንም በኢየሩሳሌም ይገኛል:: ስለዚህ በመዝ 16፥8-11 ያለው ቃል ሙሉ በሙሉ ዳዊትን አይመለከትም::

ሙትን አፈሰሰው:: 34 ዳዊት ወደ ሰማያት
አልወጣም፤ እርሱ ራሱ ግን እንዲህ ብሎአል፤

“ ‘ጌታ ጌታዬን፣
35 “ጠላቶችህን ለእግርህ መረገጫ እስክ
ማደርግልህ ድረስ፣
በቀኜ ተቀመጥ” አለው::

36 “እንግዲህ፣ እግዚአብሔር ይህን እናንተ
የሰቀላችሁትን ኢየሱስን፣ ጌታም ክርስቶስም
እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ ይረዳ!”
37 ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ ልባቸው
እጅግ ተነካ፤ ጴጥሮስንና ሌሎቹንም ሐዋር
ያት፣ “ወንድሞች ሆይ፤ ታዲያ ምን እናድ
ርግ?” አሏቸው::
38 ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው፤ “ንስሓ
ግቡ፤ ኀጢአታችሁም እንዲሰረይላችሁ፣ እያ
ንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠ
መቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላ
ላችሁ:: 39 የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆ
ቻችሁ እንዲሁም ጌታ አምላካችን ወደ ራሱ
ለሚጠራቸው፣ በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነውና::”
40 በሌላ ብዙ ቃል እየመሰከረላቸው፣ “ከዚህ
ጠማማ ትውልድ ራሳችሁን አድኑ” በማለት
አስጠነቀቃቸው:: 41 ቃሉን የተቀበሉትም ተጠ
መቁ፤ በዚያ ቀን ሦስት ሺህ ያህል ሰዎች
በቍጥራቸው ላይ ተጨመሩ::

## የአማኞች የኅብረት ኑሮ

42 እነርሱም በሐዋርያት ትምህርትና በኅብ
ረት፣ እንጀራውንም በመቍረስና በጸሎት
ይተጉ ነበር:: 43 በሐዋርያት እጅ ብዙ ድን
ቅና ታምራት ይደረግ ስለ ነበር፣ ሰው ሁሉ
ፍርሀት አደረበት:: 44 ያመኑት ሁሉ በአን
ድነት ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ የጋራ አደ
ረጉ:: 45 ሀብታቸውንና ንብረታቸውንም እየ
ሸጡ ለእያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልገውን
ያህል ይሰጡት ነበር:: 46 በየዕለቱ በቤተ መቅ
ደስ በአንድነት እየተገናኙ፣ በቤታቸውም
እንጀራ እየቈረሱ በደስታና በቀና ልብ
ይመገቡ ነበር፤ 47 እግዚአብሔርንም እያመሰ
ገኑ፣ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው፤
ጌታም የሚድኑትን በቍጥራቸው ላይ ዕለት
በዕለት ይጨምር ነበር::

## ጴጥሮስ ሽባውን ለማኝ ፈወሰ

3 አንድ ቀን ጴጥሮስና ዮሐንስ በጸሎት ጊዜ
ይኸውም ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት፣ ወደ ቤተ
መቅደስ ይወጡ ነበር:: 2 ወደ ቤተ መቅደስ
ከሚገቡት ሰዎች ምጽዋት እንዲለምን፣ ሰዎች
በየዕለቱ ተሸክመው ‘ውብ’ በተባለው የቤተ
መቅደስ መግቢያ በር ላይ የሚያስቀምጡት
አንድ ከተወለደ ጀምሮ ሽባ የሆነ ሰው ነበረ፤

2፥35 መዝ110፥1፤ ማቴ22፥44
2፥36 ማቴ28፥18፤ ሉቃ2፥11
2፥37 ሉቃ3፥10፡12:14፤ሐሥ16፥30
2፥38 ቍ41፤ ኤር 36፥3፤ማር1፥4፤ ሉቃ 24፥47፤ ዮሐ20፥22፤ ሐሥ3፥19፤8፥12:16:36:38፤9፥18:10፥48፤ 16፥15:33፤19፥5፤22፥16፤ቈላ2፥12
2፥39 ኢሳ44፥3፤ 57፥19፤65፥23፤ ሐሥ 10፥45፤ ኤፌ2፥13
2፥40 ዘዳ32፥5፤ ፊል 2፥15
2፥41 ቍ47፤ ሐሥ 4፥4፤5፥14፤ 6፥1:7፤ 9፥31:35:42፤ 11፥21:24፤14፥1:21፤16፥5፤17፥12
2፥42 ማቴ14፥ 19፤ 28፥20፤ሐሥ1፥14
2፥43 ሐሥ5፥12
2፥44 ሐሥ4፥32
2፥45 ማቴ19፥21፤ ሉቃ12፥33፤18፥22፤ ሐሥ4፥34:35፤6፥1
2፥46 ቍ42፤ማቴ 14፥19፤ሉቃ24፥53፤ ሐሥ3፥1፤5፥21:42
2፥47 ቍ41፤ሮሜ 14፥18
3፥1 መዝ55፥17፤ ሉቃ22፥8፤ሐሥ 2፥46፤10፥30
3፥2 ሉቃ16፥20፤ ዮሐ9፥8፤ሐሥ14፥8

2፥34 *ጌታ ጌታዬን ... አለው፤* ‘እግዚአብሔር አምላክ መሲሑን የዳዊት ልጅ ጌታዬን እንዲህ አለው’ ማለት ነው:: ጴጥሮስ በገለጸው መሠረት ዳዊት ከእርሱ ዘር ለተገኘው ጌታ ያልተለመደ አክብሮት ሰጥቶአል፤ ይህም፣ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ መሲሑ ምን ያህል ታላቅና መለኮታዊ ጌታ እንደ ሆነ መረዳቱን (ማቴ 22፥41-45)፣ ከሙታን መነሣቱን ብቻ ሳይሆን፣ከፍ ከፍ ብሎ በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጡንም ጭምር ያሳያል (ቍ 33-35):: ጌታ በአባቱ ቀኝ መቀመጡም መንፈስ ቅዱስን በመላኩ ተረጋግጦአል (ቍ33፤ ዮሐ16፥7)፤ እንዲሁም የመዝ 110፥1 ማብ ይመ::

2፥37 *ልባቸው እጅግ ተነካ፤* ቀድሞ ኢየሱስን ባለመቀበላቸው መጸጸታቸውንና አሁን በእርሱ ማመናቸውን ያመለክታል::

2፥38 *ንስሓ ግቡ ... ተጠመቁ፤* ንስሓ መግባት የጌታን መንገድ ጠራጊ በሆነው በመጥምቁ ዮሐንስ ትምህርት (ማር 1፥4፤ ሉቃ3፥3)፣ በጌታ ኢየሱስ ስብከት (ማር1፥15፤ሉቃ13፥3) እንዲሁም ጌታችን ከዕርገቱ በፊት በሰጠው መመሪያ (ሉቃ 24፥47)፣ መሠረት አስፈላጊነቱ ታውቋል:: እንዲሁም ጥምቀት፣ በመጥምቁ ዮሐንስ ዘንድ (ማር1፥4)፣ ጌታ ኢየሱስ በሰጠው ትምህርት (ማቴ28፥18-19)፣ በሐዋርያት ሥራ ላይ እንደተመለከተው ከእምነት ጋር የመያያዙ አስፈላጊነት እንዲሁም (8፥12፤18፥8) ቃሉን አምኖ ከመቀበል (ቍ41)፣ እና ከንስሓ ጋር ተጣምሮ ከቀረበው (እዚህ ላይ) ስብከት እንደሚታየው አስፈላጊና ዋና ጉዳይ ነው:: (1)*ኀጢአታችሁም እንዲሰረይላችሁ፤* የሚገኘው በጥምቀት በተመሰለው በእምነት ከጌታ ጋር በመቀበርና በመነሣት ነው (ሮሜ6፥3-4 እና ማብ ይመ):: (2) *በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፤* በማቴ 28፥19 ከተሰጠው ዋና መመሪያ ጋር ይቃረናል ማለት አይደለም:: በሐዋርያት ሥራ ጠቅለል ባለ መልክ የቀረበው፣ የጥምቀቱ ዐይነት ቀድሞ ከነበረው ከዮሐንስ ጥምቀት (19፥4-5) የተለየ መሆኑን አበክሮ ለማሳየት ሲሆን፣ በፊተኛው ጥምቀት ያልነበረው የኢየሱስ ስም አሁን መጨመሩን ለማጕላት ነው:: *የመንፈስ ቅዱስንም፤* በዚህ ጊዜ ሁለት ስጦታዎች ተሰጥተዋል፤ ይኸውም የኀጢአት ስርየትና (22፥16 ይመ) መንፈስ ቅዱስ ናቸው:: የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የመሆን ተስፋ የተሰጠውም ለክርስቲያን ሁሉ ነው (ከሮሜ 8፥9-11፤ 1ቆሮ 12፥13 ጋር ያነጻጽሩ)::

2፥41 በቍጥራቸው ላይ ተጨመሩ፤ የክርስትናን ሃይማኖት የተቀበሉትን ለማለት ነው::

2፥42 *በሐዋርያት ትምህርትና፤* ራሱ ጌታ ኢየሱስ ያስተማረውን ሁሉ ይጨምራል (ማቴ28፥20)፤ በተለይም ሞቱን፣ መቀበሩንና ትንሣኤውን መሠረት የሚያደርገውን የወንጌል ክፍል ይመለከታል (ቍ 23፥24፤ 3፥15፤ 4፥10፤ 1ቆሮ15፥1-4 ይመ):: ከእግዚአብሔር በተሰጠና ሐዋርያት በተቀበሉት ሥልጣን መሠረት ያስተማሩት ስለ ሆነም፣ ትምህርቱ ልዩ ነበር (2ቆሮ13፥10፤ 1ተሰ4፥2):: ይህም ትምህርት በዘመናችን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተካቶ ይገኛል:: በ*ኅብረት፤* የክርስቲያኖችን በአንድነት ማምለክ ያመለክታል:: *እንጀራውንም በመቍረስና፤* ይህ አባባል በቍ46፡ ላይ ለመደበኛው ምግብ የዋለ ቢሆንም (ሉቃ 24፥30:35 ይመ)፣ እዚህ ላይ ግን የጌታን እራት የሚመለከት ይመስላል (የ20፥7 ማብ ይመ፤ ከ1ቆሮ 10፥16፤ 11፥20 ጋር ያነጻጽሩ):: *በጸሎት፤* የሐዋርያት ሥራ ጸሎት በክርስትና ሕይወት (በግልም ሆነ በኅብረት) አስፈላጊ መሆኑን በአጽንዖት ያስተምራል (1፥14፤3፥1፤6፥4፤10፥4:31፤ 12፥5፤16፥13:16)።

2፥44 *ያመኑት ሁሉ በአንድነት ነበሩ፤* የቀድሞዪቱን ቤተ ክርስቲያን ኅብረት ያመለክታል:: *ያላቸውንም ሁሉ... የጋራ፤* 4፥34-35 ይመ:: ምንም ለሌላቸው በበጎ ፈቃድ ተነሣሥቶ የሚደረገውን ልግስናና አብሮ መመገብን ያመለክታል (ከ4፥36-5፥9 ካለው ጋር ያነጻጽሩ)::

2፥46 *በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፤* እዚህ ላይ የተመለከተው ክርስቲያኖች በቤተ መቅደስ ከሚያደርጉት ሌላ በየቤታቸው የሚፈጽሙትን ነው፤ ይኸውም የጌታ እራት ሳይሆን፣ ዕለት በዕለት በየቤታቸው እየተሰበሰቡ በደስታና በልግስና ምግባቸውን ይመገቡ እንደ ነበር ይገልጻል:: *በደስታና በቀና* ልብ፤ ኅብረት፣ አንድነትና ያለውን አብሮ መካፈል የቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ናቸው፤ ደስታ ደግሞ በአማኝ ላይ የሚታይ ስሜት ነው (የ16፥34 ማብ ይመ)::

3፥1 *ጴጥሮስና ዮሐንስ፤* “አዕማድ” ተብለው የተጠሩ ሐዋርያት (ገላ 2፥9) ናቸው:: እነዚህም ከዮሐንስ ወንድም፣ ከያዕቆብ ጋር ከሌሎቹ ሐዋርያት ይልቅ ለጌታ ቅርበት ነበራቸው:: (ማር 9፥2፤ 13፥3፤14፥33፤ሉቃ22፥8 ይመ):: በአንድ ላይ ታስረዋል (4፥3)፣ እንዲሁም በሰማርያም አብረው ነበሩ (8፥14):: *በጸሎት ጊዜ፤* በኋለኛው ጊዜ ለአይሁድ እምነት ተከታዮች የነበራቸው ሦስት የጸሎት ጊዜያት፦ጧት በሦስት ሰዓት፣ የምሽት መሥዋዕት በሚቀርብበት ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት፣ ጀንበር ስትጠልቅ ናቸው::

3፥2 *‘ውብ’ በተባለው ... መግቢያ፤* ወደ ቤተ መቅደሱ ቅጥር የሚያስገባ በውበት ያጌጠ፣ የኒክቶር በር በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ በናስ የተለበጠ ሳይሆን አይቀርም:: ከአሕዛብ አደባባይ ተነሥቶ ከዋናው ቤተ መቅደስ በስተምሥራቅ ወዳለው ወደ ሴቶች አደባባይ ይወስዳል፤

3እርሱም ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ቤተ
መቅደስ ሲገቡ አይቶ ምጽዋት ለመናቸው::
4ጴጥሮስም ከዮሐንስ ጋር ወደ እርሱ ትኵር
ብሎ እየውና፣ “እስቲ ወደ እኛ ተመልከት”
አለው:: 5ሰውየውም፣ ከእነርሱ አንድ ነገር
ለማግኘት አስቦ በትኵረት ተመለከታቸው::
6ጴጥሮስ ግን፣ “እኔ ብርና ወርቅ የለኝም፤
ነገር ግን ያለኝን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየ
ሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥተህ በእግርህ ተመ
ላለስ” አለው፤ 7ቀኝ እጁንም ይዞ አስነሣው፤
ወዲያውም እግሩና ቍርጭምጭሚቱ በረታ፤
8ዘሎም ቀጥ ብሎ ቆመ፤ መራመድም ጀመረ፤
ወዲህ ወዲያ እየሄደና እየዘለለም እግዚአብሔ
ርንም እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ ቤተ መቅ
ደሱ አደባባይ ገባ:: 9ሕዝቡም ሁሉ እየተራ
መደና እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሲመላለስ
ባዩት ጊዜ፣ 10ይህ ሰው ቀደም ሲል ‘ውብ’
በተባለው የቤተ መቅደስ መግቢያ በር ላይ
ተቀምጦ ምጽዋት ይለምን የነበረው እርሱ
መሆኑን ዐወቁ፤ በእርሱ ላይ ከተፈጸመውም
ነገር የተነሣ በመደነቅና በመገረም ተሞሉ::

## ጴጥሮስ ለማኙ ሲፈወስ ላየው ሕዝብ ንግግር አደረገ

11የተፈወሰውም ለማኝ ከጴጥሮስና ዮሐ
ንስ ጋር ጥብቅ ብሎ አብሮአቸው ሳለ፣ ሕዝቡ
ሁሉ በመገረም እነርሱ ወደ ነበሩበት ‘የሰ
ሎሞን መመላለሻ’ ወደ ተባለው ስፍራ እየ
ሮጡ መጡ:: 12ጴጥሮስም ይህን ባየ ጊዜ
እንዲህ አላቸው፤ “የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፤
በዚህ ለምን ትደነቃላችሁ? ደግሞም በእኛ
ኀይል ወይም በእኛ ጽድቅ ይህ ሰው ድኖ
እንዲመላለስ እንዳደረግነው በመቍጠር፣
ለምን ወደ እኛ አትኵራችሁ ትመለከታላ
ችሁ? 13የአባቶቻችን አምላክ፣ የአብርሃም፣
የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ብላቴናውን ኢየሱ
ስን አከበረው፤ እናንተ ግን እንዲሞት አሳ
ልፋችሁ ሰጣችሁት፤ ጲላጦስ ሊፈታው ቢፈ
ልግም እናንተ በእርሱ ፊት ካዳችሁት፤ 14ቅዱሱ
ንና ጻድቁን ክዳችሁ ነፍስ ገዳዩ እንዲፈታ
ላችሁ ለመናችሁ፤ 15የሕይወት መገኛ የሆነ
ውን ገደላችሁት፤ እግዚአብሔር ግን ከሙታን
አስነሣው፤ እኛም ለዚህ ምስክሮች ነን:: 16ይህ
የምታዩትና የምታውቁት ሰው የበረታው
በኢየሱስ ስም በማመን ነው፤ ሁላችሁም እን
ደምታዩት ፍጹም ፈውስ እንዲያገኝ ያደረ
ገው የኢየሱስ ስምና በእርሱ አማካይነት
የሚገኘው እምነት ነው::
17“አሁንም ወንድሞች ሆይ፤ እናንተ
ይህን ያደረጋችሁት እንደ አለቆቻችሁ ሁሉ
ባለማወቅ እንደ ሆነ ዐውቃለሁ:: 18እግዚ
አብሔር ግን የእርሱ የሆነው ክርስቶስ[a]
መከራን እንዲቀበል አስቀድሞ በነቢያቱ
ሁሉ አፍ የተናገረውን ፈጽሞአል:: 19እንግዲህ
ኀጢአታችሁ እንዲደመሰስ ንስሓ ግቡ፤
ከመንገዳችሁም ተመለሱ፤ ከጌታም ዘንድ
የመታደስ ዘመን ይመጣላችኋል፤ 20ደግሞም
አስቀድሞ ለእናንተ የተመደበውን ክርስቶ
ስን እርሱም ኢየሱስን ይልክላችኋል:: 21እግዚ
አብሔር አስቀድሞ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ
እንደተናገረ፣ ሁሉን ነገር እስከሚያድስበት
ዘመን ድረስ እርሱ በሰማይ ይቈይ ዘንድ
ይገባል:: 22ሙሴም እንዲህ ብሎአል፤ ‘ጌታ
አምላካችሁ ከእናንተው መካከል እንደ እኔ
ያለ ነቢይ ያስነሣላችኋል፤ እርሱ የሚነግራ
ችሁን ሁሉ ስሙት፤ 23ይህን ነቢይ የማትሰማ
ነፍስ ሁሉ ከሕዝቡ መካከል ተለይታ ትጥፋ::’
24“በእርግጥም ከሳሙኤል ጀምሮ የተነሡት
ነቢያት ሁሉ ስለ እነዚህ ጊዜያት ተናግረዋል::
25እናንተም የነቢያት ልጆች ናችሁ፤ ደግሞም
እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ ‘በዘርህ የምድር

[a]18 ወይም መሲሕ፤ እንዲሁም በቍ 20

3፥6 ቍ16፤ማር 1፥24
3፥8 ኢሳ35፥6፤ሐሥ 14፥10
3፥9 ሐሥ4፥16:21
3፥10 ቍ2
3፥11 ሉቃ22፥8፤ ዮሐ10፥23፤ሐሥ5፥ 12
3፥13 ዘፀ3፥6፤ማቴ 27፥2፤ሉቃ23፥4፤ሐሥ 2፥23፤5፥30፤7፥32፤ 22፥14
3፥14 ማር1፥24፤ 15፥11፤ሉቃ23፥18-25፤ሐሥ4፥27፤7፥52
3፥15 ቍ24፥48 ፤ሐሥ 2፥24
3፥16 ቍ6
3፥17 ሉቃ23፥34፤ ሐሥ13፥27፤22፥5
3፥18 ማቴ1፥22፤ ሉቃ24፥27፤ሐሥ2፥ 23፤17፥2:3፤26፥22:23
3፥19 መዝ51፥1፤ኢሳ 43፥25፤44፥22፤ሐሥ 2፥38
3፥20 ሉቃ2፥11
3፥21 ማቴ17፥11፤ ሉቃ1፥70፤ሐሥ1፥6: 11
3፥22 ዘዳ18፥15: 18፤ሐሥ7፥37
3፥23 ዘዳ18፥19
3፥24 ሉቃ24፥27
3፥25 ዘፍ12፥3፤22፥ 18፤26፥4፤28፥14፤ሐሥ 2፥39፤ሮሜ9፥4:5

3፥6 *በኢየሱስ ክርስቶስ ስም*፤ በራሳቸው ኀይል ሳይሆን በመሲሑ ሥልጣን ማድረጋቸውን ያሳያል::

3፥7 *ይዞ አስነሣው*፤ ሰውዬው ፈቅዶ መነሣቱ ራሱ ለመዳን የሚያስችለው እምነት እንደ ነበረው ያሳያል (ቍ 16)::

3፥8 *ወደ ቤተ መቅደሱ አደባባይ*፤ ከውጭው የአሕዛብ አደባባይ) ገምጀ ቤቱ ወዳለበት ወደ ሴቶች አደባባይ (ማር12፥41-44)፣ ከዚያም ወደ እስራኤል አደባባይ ሄደ፤ ከውጭው አደባባይ ውስጥ ወዳሉት አደባባዮች የሚወስዱ ዘጠኝ በሮች አሉ::

3፥11 *የሰሎሞን መመላለሻ*፤ በውጭው አደባባይ ቅጥር ዙሪያ በስተ ውስጥ በኩል የተሠራ ሲሆን፣ ሃያ ሰባት ጫማ ከፍታ ያላቸው በተርታ የቆሙ የድንጋይ ምሰሶዎች ያሉትና ጣራው ከጥድ የተሠራ ነው (የዮሐ 10፥23 ማብ ይመ)::

*3፥12-26፤ የ2፥14-40* ማብ ይመ::

3፥13 *ብላቴናውን ኢየሱስን*፤ መከራ መቀበል ስለሚገባው ብላቴና በኢሳ 52፥13-53፥12 የተነገረውን ትንቢት ያስታውሳል (የማቴ12፥18፤ሐሥ4፥27:30 ማብ ይመ):: *አሳልፋችሁ ሰጣችሁት፤* ፈረዳችሁበት፤ ናቃችሁት፤ እውነተኛ መሲሕ ነው ብላችሁ አልተቀበላችሁትም:: *ጲላጦስ ሊፈታው ቢፈልግም፤* ዮሐ19፥12 ይመ::

3፥14 *ቅዱሱንና ጻድቁን*፤ በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው ዘንድ ነቀፋ የሌለበት ማለት ነው::

3፥15 *ገደላችሁት፤ እግዚአብሔር...አስነሣው፤እኛም... ምስክሮች ነን*፤ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ለአጽንዖት በተደጋጋሚ የቀረበ ዐቢይ ሐሳብ ነው (2፥23-24፤4፥10፤5፥30-32፤ 10፥39-41፤ 13፥28-29 ይመ፤ ከ1ቆሮ 15፥1-4 ጋር ያነጻጽሩ)::

3፥18 *አስቀድሞ በነቢያቱ ሁሉ... የተናገረውን*፤ ኢየሱስ የተናገረውን ያስተጋባል (ሉቃ24፥26-27):: መሠቃየቱ አስቀድሞ ተነግሮአል (ከሐሥ 8፥32-33፤ መዝ 2፥1-2 ጋር እንዲሁም ከሐሥ 4፥25-26፤ መዝ22፥1 እና ማቴ27፥46 ጋር ያነጻጽሩ፤1ጴጥ1፥11 ይመ)::

3፥19 *ንስሓ ግቡ፤* ንስሓ መግባት በተሠራ ኀጢአት በመጸጸት የልብና የሐሳብ ለውጥ ማድረግ ሲሆን፣ ይህም ወደ አዲስ ሕይወት የሚመራ ነው (የ2፥38 ማብ ይመ):: *ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ፤* ንስሓ መግባትን ተከትሎ የሚመጣ ሲሆን፣ ከንስሓ ጋር ግን ፈጽሞ አንድ አይደለም (11፥21፤26፥20፤9፥35፤14፥15፤ 15፥19፤26፥18፤28፥27 ይመ):: ጠለቅ ተደርጎ ሲታይ ንስሓ ማለት ከኀጢአት መመለስ ሲሆን፣ እምነትም ልብን ወደ እግዚአብሔር ማቅናት ነው፤ ይሁን እንጂ፣ “መመለስ” የሚለው ቃል ትርጕም አገባቡ ይሄ ብቻ አይደለም:: *ኀጢአታችሁ እንዲደመሰስላችሁ፤* ንስሓ በመግባታችሁ ኀጢአታችሁ ይደመሰሳል ማለት ነው::

3፥22-26 *ያስነሣላችኋል ... ባስነሣ ጊዜ፤* ሙሴን ዳዊትንና አብርሃምን በተመለከተ የተነገረው ትንቢት በክርስቶስ ተፈጽሞ አል:: ክርስቶስ እንደ ሙሴ ነቢይ ተብሎአል (ቍ 22-23 ይመ)፤ ሳሙኤል ስለ ዳዊት በተናገረ ጊዜ ስለ ክርስቶስም ተንብዮአል (ቍ 24)፤ ለአብርሃም በተሰጠው ተስፋ መሠረት ክርስቶስ ለሰው ዘር ሁሉ በረከትን የሚያመጣ ነው (ቍ 25-26)::

3፥24 *ከሳሙኤል ጀምሮ የተነሡት ነቢያት*፤ ሳሙኤል፣ ዳዊትን ንጉሥ እንዲሆን ቀባው፤ ስለ ዳዊት መንግሥት መመሥረትም ተናገረ (1ሳሙ 16፥13፤ከ13፥14፤15፥28፤28፥17 ጋር ያነጻጽሩ):: የናታን ትንቢት (2ሳሙ 7፥12-16)፣ መሲሑን በትክክል የሚያመለክት ነው (ሐሥ13፥22-23:34፤ዕብ1፥5 ይመ)::

3፥25 *በዘርህ* ቃሉ ነጠላ ቍጥር ሲሆን፣ ይኸኛውም በመጨረሻ የሚያመለክተው ክርስቶስን ነው (ገላ3፥16 ይመ)::

ወገኖች ሁሉ ይባረካሉ’ ብሎ የገባው ኪዳን
ወራሾች ናችሁ:: 26እግዚአብሔር ብላቴና
ውን ባስነሣ ጊዜ፣ እያንዳንዳችሁን ከክፉ
ታችሁ መልሶ ይባርካችሁ ዘንድ አስቀድሞ
ወደ እናንተ ላከው::”

## ጴጥሮስና ዮሐንስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት

4 ጴጥሮስና ዮሐንስ ለሕዝቡ እየተናገሩ
ሳሉ፣ ካህናትና የቤተ መቅደሱ ጥበቃ
ኀላፊ እንዲሁም ሰዱቃውያን ድንገት ወደ
እነርሱ መጡ:: 2እነርሱም ሐዋርያት ሕዝቡን
በማስተማራቸውና በኢየሱስ ስለ ተገኘው ትን
ሣኤ ሙታን በመስበካቸው እጅግ ተቈጡ::
3ጴጥሮስና ዮሐንስን ያዟቸው፤ ጊዜውም ምሽት
ስለ ነበረ እስኪነጋ ድረስ ወህኒ ቤት አሳደ
ሯቸው:: 4ይሁን እንጂ ቃሉን ከሰሙት መካ
ከል ብዙዎቹ አመኑ፤ የወንዶቹም ቍጥር
ወደ አምስት ሺህ ከፍ አለ::

5በማግስቱም አለቆቻቸውና፣ ሽማግሌዎ
ቻቸው እንዲሁም ጸሐፍት በኢየሩሳሌም ተሰ
በሰቡ:: 6ሊቀ ካህናቱ ሐና፣ ቀያፋ፣ ዮሐ
ንስ፣ እስክንድሮስና የሊቀ ካህናቱ ቤተ ዘመ
ዶች ሁሉ በዚያ ተገኝተው ነበር:: 7እነርሱም
ጴጥሮስንና ዮሐንስን በመካከል አቁመው፣
“ይህን ያደረጋችሁት በምን ኀይል ወይም
በማን ስም ነው?” ብለው ጠየቋቸው::

8በዚህ ጊዜ፣ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ
ተሞልቶ እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ የሕዝብ
አለቆችና ሽማግሌዎች ሆይ፤ 9ዛሬ ለዚህ
ሽባ ሰው ስለ ተደረገው በጎ ሥራ፣ እንዴት
እንደ ዳነ የምትጠይቁን ከሆነ፣ 10እናንተ በስ
ቀላችሁት፣ እግዚአብሔር ግን ከሙታን
ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም
መዳኑንና ፊታችሁ መቆሙን እናንተም
ሆናችሁ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ይህን ይወቁ::
11እርሱም፣

“ ‘እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት፣

3፥26 ቍ22፤ሐሥ 2፥24፤13፥46፤ሮሜ 1፥16
4፥1 ማቴ3፥7፤16፥1፡6፤22፥23፡34፤ሉቃ22፥4፤ሐሥ5፥17፤23፥6-8
4፥2 ሐሥ17፥18
4፥3 ሐሥ5፥18
4፥4 ሐሥ2፥41
4፥5 ሉቃ23፥13
4፥6 ማቴ26፥3
4፥8 ቍ5፤ሉቃ1፥15፤23፥13
4፥9 ሐሥ3፥6
4፥10 ማር1፥24፤ሐሥ 2፥24
4፥11 መዝ118፥22፤ኢሳ28፥16፤ዘካ10፥4፤ማቴ21፥42፤ኤፌ 2፥20፤1ጴጥ2፥7
4፥12 ማቴ1፥21፤ዮሐ14፥6፤ሐሥ 10፥43፤ሮሜ11፥14፤1ጢሞ2፥5
4፥13 ማቴ11፥25፤ማር3፥14፤ሉቃ22፥8
4፥15 ማቴ5፥22
4፥16 ዮሐ11፥47፤ሐሥ3፥6-10
4፥18 አሞ7፥13፤ሐሥ5፥40
4፥19 ሐሥ5፥29
4፥20 ኢዩ32፥18፤ኤር20፥9፤አሞ3፥8፤ሉቃ24፥48
4፥21 ሐሥ5፥26፤ማቴ9፥8

የማእዘን ራስ[ሀ] የሆነው ድንጋይ’ ነው::
12ድነት በሌላ በማንም አይገኝም፤ እንድን
በት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስ
ተቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና::”

13ሰዎቹም፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ እንዲህ በድ
ፍረት ሲናገሩ ባዩአቸው ጊዜ፣ ያልተማሩ ተራ
ሰዎች መሆናቸውን ተረድተው ተደነቁ፤
ከኢየሱስ ጋር እንደ ነበሩም ተገነዘቡ:: 14የተ
ፈወሰውን ሰው እዚያው ከእነርሱ ጋር ቆሞ
ስላዩት የሚናገሩበትን ሰበብ አጡ:: 15ስለዚህ
ከሸንጎው እንዲያወጧቸው አዘዙ፤ ከዚያም
በአንድነት ተሰብስበው ተመካከሩ፤ 16እንዲ
ህም ተባባሉ፤ “እንግዲህ እነዚህን ሰዎች ምን
እናድርጋቸው? በኢየሩሳሌም የሚኖር ሁሉ
በእነርሱ እጅ የተደረገውን ድንቅ ታምር ዐው
ቆአል፣ ስለዚህ ይህንን ማስተባበል አንች
ልም፤ 17ይሁን እንጂ፣ ይህ ነገር ከእንግዲህ
በሕዝቡ መካከል ይበልጥ እንዳይስፋፋ፣ እነ
ዚህም ሰዎች ዳግመኛ በዚህ ስም ለማንም
እንዳይናገሩ እናስጠንቅቃቸው::”

18ከጠሯቸውም በኋላ፣ በኢየሱስ ስም ፈጽሞ
እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዟቸው::
19ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን መልሰው እንዲህ አሏ
ቸው፤ “ከእግዚአብሔር ይልቅ ለእናንተ መታዘዝ
በእግዚአብሔር ፊት ይገባ እንደሆን እስቲ እናን
ተው ፍረዱ፤ 20እኛስ ያየነውንና የሰማነውን
ከመናገር ወደ ኋላ አንልም::”

21እንደ ገና ከዛቱባቸው በኋላም ለቀቋቸው፤
ምክንያቱም ሕዝቡ ሁሉ ስለ ሆነው ነገር
እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ስለ ነበር ሊቀጧቸው
አልቻሉም፤ 22በዚህ ታምር የተፈወሰውም
ሰው ዕድሜው ከአርባ ዓመት በላይ ነበርና::

## የአማኞች ጸሎት

23ጴጥሮስና ዮሐንስም ከተፈቱ በኋላ ወደ
ወገኖቻቸው ተመልሰው የካህናት አለቆችና

[ሀ]11 ወይም *የማእዘን ድንጋይ*

4፥1 *ካህናትና*፤ በዚያው ሰሞን በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ያገለግሉ የነበሩትን ነው (የሉቃ 1፥23 ማብ ይመ):: *የቤተ መቅደሱ ጥበቃ ኀላፊ*፤ በአመራር ላይ ካሉት የካህናት ቤተሰቦች የአንዱ አባል ሲሆን፣ ማዕረጉም ከሊቀ ካህናቱ ቀጥሎ የሚመጣ ነው (5፥24፤26፤ ሉቃ 22፥4፡52 ይመ):: *ሰዱቃውያን*፤ ከአይሁድ ሃይማኖት ክፍል አንዱ ሲሆን፣ አባላቱ ከካህናት ወገን ናቸው:: እነርሱም የቤተ መቅደሱን ሥራ በኀላፊነት የሚመሩ ነበሩ፤ በሙታን ትንሣኤም ሆነ በሥጋ እንደሚገለጥ ትንቢት የተነገረለትን መሲሕ መምጣት አይቀበሉም፣ ይሁን እንጂ የመሲሕ ዘመን መምጫው ስለ ደረሰ መጠባበቅ ያስፈልጋል ብለው ያምናሉ፣ የሸንጎው ሰብሳቢ የሆነው ሊቀ ካህናት ከእነርሱ ወገን የተሾመ ነው (5፥17፤ 23፥6-8፤ ማቴ 22፥23-33 ይመ):: እንዲሁም የማቴ 3፥7፤ ማር 12፥18፤ ሉቃ 20፥ 27 ማብ ይመ::

4፥3 *ምሽት*፤ በምሽት የሚቀርበው መሥዋዕት በዐሥር ሰዓት ገደማ ይጠናቀቅ ስለ ነበር፣ የቤተ መቅደሱም በር በዚህ ጊዜ ይዘጋል፣ ሕይወትንም ሆነ ሞትን በተመለከተ የሚተላለፍ ማንኛውም ፍርድ የቀኑ ብርሃን ሳለ ተጀምሮ ከመምሸቱ በፊት መጠናቀቅ አለበት::

4፥4 *የወንዶቹም*፤ በበዓለ ኀምሳ ቀን የተጨመሩት ሦስት ሺህ ነፍሳት እያደጉና እየሰፉ መሄዳቸውን ያሳያል (2፥41)፤ በኋላ የተጨመረውን (5፥14፤6፥7) ይመ::

4፥5 *አለቆቻቸውና ሽማግሌዎቻቸው እንዲሁም ጸሐፍት*፣ ሦስቱም ወገኖች የአይሁድ ሸንጎ አባላት ናቸው (ሉቃ 22፥66 ይመ፤ እንዲሁም የማቴ 2፥4፤15፥2፤ማር14፥55፤ ሉቃ5፥17 ማብ ይመ)::

4፥6 *ሐና*፤ ከ6-15 ዓ.ም. ሊቀ ካህናት ነበር፤ ሮማውያን ግን እርሱን ከሥልጣን አውርደው ልጁን ኤልኢዜርን ተክተው ነበር፤ ከዚያም ዮሴፍ የተባለውን ዐማቹን ቀያፋን (18-36 ዓ.ም.) ሥልጣን እንዲይዝ አደረጉት፤ ይህም ሆኖ ግን ሐና በሕዝቡ ዘንድ እንደ ሊቀ ካህናት ይታይ ነበር (ሉቃ 3፥2 ይመ፤ ከዮሐ 18፥13፡ 24 ጋር ያነጻጽሩ):: *ዮሐንስ*፤ በ36 ዓ.ም. ሊቀ ካህናት የሆነው፣ የሐና ልጅ ዮናታን ሊሆን ይችላል፤ አንዳንዶች ግን ኢየሩሳሌም ከወደቀች በኋላ የታላቁ ምኵራብ መሪ የነበረው ዮሐንቤንዘካይ ነው ይላሉ:: *እስክንድሮስ*፤ ስሙ የተጠቀሰው እዚህ ላይ ብቻ ነው::

4፥8 *በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ*፤ የ2፥4 ማብ ይመ::

4፥11 *የናቃችሁት ... ድንጋይ*፤ የተነገሩ ትንቢቶች መፈጸም በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ስብከትና ትምህርት ረገድ እጅግ አስፈላጊ ነበር፤ ጌታ ኢየሱስም መዝ118፥22ን በተመሳሳይ መንገድ ተጠቅሞበታል (ማቴ21፥42፤1ጴጥ2፥7 ይመ፤ ከሮሜ9፥33፤ ኢሳ 28፥16 ጋር ያነጻጽሩ)::

4፥12 *ከዚህ ስም በስተቀር*፤ 10፥43፤ዮሐ14፥6፤1ጢሞ2፥5 ይመ:: አማራጭ ትርጕሙን (ማቴ 1፥21 ይመ)::

4፥13 *በድፍረት*፤ እንዲህ ዐይነቱ የሐዋርያት ድፍረት፣ እርግጠኝነትን፣ ሥልጣንንና ቀጥተኛነትን የተላበሰ ነበር (2፥29፤ 4፥29፤28፥31)፤ ይህን ድፍረት ሌሎች አማኞች ተጋርተውታል ይህንኑ ይፈጽሙ ነበር (4፥31):: *ያልተማሩ ተራ ሰዎች*፤ ጴጥሮስና ዮሐንስ በዘመኑ ከነበረው መደበኛ ትምህርት ቤት ገብተው አልተማሩም፤ ወይም በታወቀ የሃይማኖት ተቋም ውስጥ ይህ ነው የሚባል ሥልጣን አልነበራቸውም::

4፥20 *ከመናገር ወደ ኋላ አንልም*፤ 5፥29 ይመ::

4፥23 *ተመልሰው*፤ ምናልባት ቀደም ሲል ደቀ መዛሙርት

ሽማግሌዎች ያሏቸውን ሁሉ ነገሯቸው::
24እነርሱም ይህን በሰሙ ጊዜ ድምፃቸውን
በአንድነት ወደ እግዚአብሔር ከፍ አድርገው
እንዲህ አሉ፤ “ልዑል ጌታ ሆይ አንተ ሰማ
ይንና ምድርን፣ ባሕርንም፣ በውስጣቸውም
የሚኖሩትን ሁሉ ፈጥረሃል፤ 25በመንፈስ
ቅዱስም አማካይነት በአገልጋይህ በአባታ
ችን በዳዊት አፍ እንዲህ ብለህ ተናግረሃል፤

“ ‘አሕዛብ ለምን በቍጣ ተነሣሡ?
  ሕዝቡስ ለምን በከንቱ አሤሩ?
26የምድር ነገሥታት ተሰለፉ፤
  ገዦችም በአንድነት ተሰበሰቡ፤
በጌታ ላይ፣
  በተቀባውም+ ላይ ተከማቹ::’

27በእርግጥም ሄሮድስና ጳንጥዮስ ጲላጦስ
ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በዚህች
ከተማ አንተ በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ
በኢየሱስ ላይ ለማሤር ተሰበሰቡ፤ 28ይህም
የሆነው የአንተ ክንድና ፈቃድ ጥንት የወሰ
ኑት እንዲፈጸም ነው:: 29አሁንም ጌታ ሆይ፤
ዛቻቸውን ተመልከት፤ ባሪያዎችህም ቃል
ህን በፍጹም ድፍረት መናገር እንዲችሉ
አድርጋቸው:: 30ለመፈወስ እጅህን ዘርጋ፤
በቅዱሱ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ድንቅና
ታምራት አድርግ::”

31ከጸለዩም በኋላ የነበሩበት ስፍራ ተና
ወጠ፤ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ የእግ
ዚአብሔርንም ቃል በድፍረት ተናገሩ::

## የአማኞች ማኅበራዊ አኗኗር

32ያመኑትም ሁሉ በአንድ ልብና በአንድ
ሐሳብ ተስማምተው ነበር፤ ያላቸውም ሁሉ
የጋራ ነበር እንጂ የራሱ የሆነውን ሀብት እንኳ
እንደ ግሉ የሚቈጥር ማንም አልነበረም::
33ሐዋርያትም ስለ ጌታ ኢየሱስ ትንሣኤ በታ
ላቅ ኀይል መመስከራቸውን ቀጠሉ፤ በሁላ
ቸውም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበር:: 34ከመካከላ
ቸውም አንድ ችግረኛ አልነበረም፤ ምክን
ያቱም መሬትም ሆነ ቤት የነበራቸውን ሁሉ
እየሸጡ ዋጋውን አምጥተው፣ 35በሐዋርያት
እግር ሥር በማስቀመጥ ለእያንዳንዱ በሚያ
ስፈልገው መጠን ያካፍሉት ነበር::

36በቆጵሮስ የሚኖር ዮሴፍ የሚባል አንድ
ሌዋዊ ነበረ፤ ሐዋርያትም ‘በርናባስ’ ብለው
ጠሩት፤ ትርጕሙም ‘የመጽናናት ልጅ’ ማለት
ነው፤ 37እርሱም መሬቱን ሸጠ፣ ገንዘቡን አም
ጥቶ በሐዋርያት እግር ሥር አስቀመጠ::

## ሐናንያና ሰጲራ

5 ሐናንያ የተባለ ሰው፣ ከሚስቱ ከሰጲራ
ጋር መሬት ሸጠ፤ 2ሚስቱም በሚገባ እያ
ወቀች ከሽያጩ የተወሰነ ገንዘብ በማስቀ
ረት የተረፈውን አምጥቶ በሐዋርያት እግር
ሥር አስቀመጠ::

3ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለ፤ “ሐናንያ ሆይ፤
መንፈስ ቅዱስን ትዋሽና ከመሬቱ ሽያጭ
ታስቀር ዘንድ ሰይጣን ልብህን ለምን ሞላው?
4ሳትሸጠው በፊት የአንተው አልነበረምን?
ከሸጥኸውስ በኋላ ቢሆን ገንዘቡ በእጅህ
አልነበረምን? ለመሆኑ ይህን ነገር እንዴት
በልብህ አሰብህ? የዋሸኸው እኮ እግዚአብሔርን
እንጂ ሰውን አይደለም::”

5ሐናንያም ይህን እንደ ሰማ ወድቆ ሞተ፤
ይህን የሰሙትም ሁሉ ታላቅ ፍርሀት ያዛቸው::

+26 *ወይም ክርስቶስ ወይም መሲሕ ማለት ነው::*

4፥24 ነህ9፥6፤ ኢዮ 41፥11፤ ኢሳ 37፥16፤ሐሥ1፥1
4፥25 ሐሥ1፥16
4፥26 መዝ2፥1:2፤ ዳን9፥25፤ሉቃ4፥18፤ ሐሥ10፥38፤ዕብ1፥9
4፥27 ቍ30፤ ማቴ 14፥1፤27፥2፤ ሉቃ23፥12፤ ሐሥ 3፥13:14
4፥28 ሐሥ2፥23
4፥29 ቍ13:31፤ መዝ138፥3፤ ሐሥ 9፥27፤ 13፥46፤ 14፥3፤28፥31፤ ኤፌ6፥19፤ ፊል1፥14
4፥30 ቍ27፤ ዮሐ 4፥48
4፥31 ቍ29፤ ሉቃ 1፥15፤ ሐሥ2፥2፤ዕብ4፥12
4፥32 ሐሥ2፥44
4፥33 ሉቃ24፥48፤ ሐሥ1፥22፤ሮሜ3፥24
4፥34 ማቴ19፥21፤ሐሥ2፥45
4፥35 ቍ37፤ሐሥ 2፥45፤5፥2፤6፥1
4፥36 ሐሥ9፥27፤ 11፥22:30፤13፥2፤ 1ቆሮ9፥6፤ገላ2፥1: 9:13
4፥37 ቍ35፤ ሐሥ 5፥2
5፥2 ኢሱ7፥11፤ ሐሥ 4፥35:37
5፥3 ቍ9፤ዘዳ 23፥21፤ማቴ4፥10፤ ዮሐ 13፥2:27
5፥4 ዘሌ6፥2፤ ዘዳ 23፥22
5፥5 ቍ10:11፤ መዝ5፥6

ይሰበሰቡበት የነበረው (1፥13)፣ በኋላም ምእመናኑ ማምለኪያና መሰብሰቢያ ያደረጉት የላይኛው ክፍል (ሰገነት) ሊሆን ይችላል (12፥12)::

4፥24 ልዑል *ጌታ ሆይ!* ሉቃ 2፥29 ይመ::

4፥27 *ሄሮድስ፤* ሄሮድስ አንቲጳስ፣ በዮርዳኖስ ማዶ ያለው አገርና በገሊላ የአራተኛው ክፍል ገዥ ነበር (ሉቃ 23፥7-15) *ጳንጥዮስ ጲላጦስ፤* በይሁዳ የሮም ቄሳር መንግሥት እንደራሴ ነበር (ሉቃ 23፥ 1-24)::

4፥28 ጥንት የወሰኑት፤ ይህን እንዲያደርጉ እግዚአብሔር አስገደዳቸው ማለት ሳይሆን፣ እነርሱንና በነጻ ፈቃዳቸው የፈጸሙትን ድርጊት የማዳን ዕቅዱ መፈጸሚያ መሣሪያ አደረገው ማለት ነው::

4፥30 *በቅዱሱ ብላቴናህም፤* የ3፥13 ማብ ይመ::

4፥31 *ተናወጠ!* ጸሎታቸው ለመመለሱ ፈጣን ምልክት ነው (16፥26 ይመ):: *በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤* የ2፥4 ማብ ይመ:: *የእግዚአብሔርንም ቃል...ተናገሩ!* የአይሁድ ሸንጎ ቢያስጠነቅቃቸውም ወንጌልን ከመስበክ ወደ ኋላ አላሉም (የቍ13 ማብ ይመ)::

4፥32 *በአንድ ልብና በአንድ ሐሳብ፤* ፍጹም የሆነ የኅብረት መንፈስ ስለነበራቸውም የግል ሀብትን በጋራ እስከ መካፈል አድርሶአቸዋል (የ2፥44 ማብ ይመ)::

4፥33 *ትንሣኤ ... መመስከራቸውን፤* ትልቁ ነገር የክርስቶስ ሞት የመሆኑን ያህል ትንሣኤውም እንዲሁ ዋናና አስገዳጅነት ያለው ክንዋኔ ነበር፤ ደቀ መዛሙርትም ይህን አይተው ዝም ማለት አልቻሉም::

4፥34 *መሬትም ሆነ ቤት የነበራቸው ... እየሸጡ!* የ2፥44 ማብ ይመ::

4፥36 *ሌዋዊ፤* ሌዋውያን በፓለስታይን ወይም “ቅድስት ኦገር” በተባለው በእስራኤል አገር በውርስ የሚያገኙት መሬት ባይኖርም፣ እንደ ቆጵሮስ ባለው አገር የነበሩትን አይሁድ ግን ይህ ሥርዐት አይመለከታቸውም ነበር፤ ስለዚህ በርናባስ በቆጵሮስ የሚገኘውን ርስቱን ሸጦ ያገኘውን ገንዘብ ለሐዋርያት አስረክቦ ይሆናል (ቍ37)፤ ወይም ባለትዳር ይሆናል፤ የተሸጠውም መሬት የሚስቱ ሊሆን ይችላል፤ ይህ ካልሆነም ሌዋውያን መሬት እንዳያገኙ የሚከለክለው ሕግ በዚያ ዘመን ተፈጻሚነቱ ቀርቶ ይሆናል:: *በቆጵሮስ፤* በሜድትራኒያን ባሕር ውስጥ በምሥራቅ በኩል የምትገኝ ደሴት ናት:: አይሁድ ከመቃብያን ዘመን ጀምሮ በዚህች ደሴት መኖር ጀምረዋል:: *በርናባስ፤* እዚህ ላይ የልግስና ምሳሌ ሆኖ ቀርቦአል:: ሉቃስ የጳውሎስ ዋና ተባባሪ የሚሆነውን ደቀ መዝሙር ያስተዋወቀው በዚህ መልክ ነበር (13፥1-4 ይመ):: ለቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት የዚህ ሰው ልዩ አስተዋፅኦ ምን ያህል እንደ ሆነ ለማወቅ 9፥27፤11፥22:25፤ 15፥37-39 ይመ::

5፥1 *ሐናንያ... ከሰጲራ!* በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማኅበራዊ ኑሮ ጠንቅ በመሆናቸው በመጥፎ አርአያነት ቀርበዋል፤ በአንጻሩ ግን በርናባስ ለማኅበራዊ ኑሮ በጥሩ ምሳሌነት ስለመቅረቡ (የ4፥ 36 ማብ ይመ):: ለታይታ በተደረገ ልግስና ምስጋናን መሻትና የገንዘብ ፍቅር በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመዘገቡ ኀጢአቶች ናቸው፤ ይህም እግዚአብሔር እንደማይዘበትበት (ገላ 6፥7) አንባቢዎችን ክፉኛ ያስጠነቅቃል:: በመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን የተፈጸመውን ይህን ፍርድ፣ እግዚአብሔር በናዳብና በአብዩድ (ዘሌ 10፥2)፣ በአካንና (ኢሱ7፥25) በዖዛ (2ሳሙ 6፥7) ላይ ከፈረደው ፍርድ ጋር ያነጻጽሩ::

5፥2 *በማስቀረት፤* የፈለጉትን ያህል ማስቀረት መብታቸው ነበር፤ ሙሉውን ሳያመጡ እንዳመጡ ማስመሰላቸው ግን ኀጢአት ሆነባቸው::

5፥3 *መንፈስ ቅዱስን ትዋሽና!* ይህ ሐሳብ ከቍ4 ጋር ሲነጻጸር፣ መንፈስ ቅዱስ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑንና ከሕዝቡም ጋር እንዳለ ያመለክታል:: *ሰይጣን ልብህን ለምን ሞላው?* ሰይጣን ባለማቋረጥ የሚሠራው ሥራ እዚህ ላይ ተገልጦአል (ሉቃ 22፥3፤ ዮሐ13፥2:27፤ 1ጴጥ5፥8 ይመ)::

6ጐልማሶችም ተነሥተው አስከሬኑን ገነዙት፤
ወስደውም ቀበሩት።
7ሦስት ሰዓት ያህልም ካለፈ በኋላ፣ ሚስቱ የሆ
ነውን ሳታውቅ መጥታ ገባች። 8ጴጥሮስም፣
"እስቲ ንገሪኝ፤ መሬታችሁን የሸጣችሁት በዚህ
ዋጋ ነውን?" አላት።

እርሷም፣ "አዎን፤ በዚሁ ዋጋ ነው" አለች።

9ጴጥሮስም፣ "የጌታን መንፈስ ትፈታተኑ
ዘንድ እንዴት እንዲህ ተስማማችሁ? እነሆ፤
ባልሽን የቀበሩት ሰዎች ተመልሰው እግራ
ቸው ደጃፍ ላይ ነው፤ አንቺንም ይዘው
ይወጣሉ" አላት።
10እርሷም ወዲያውኑ እግሩ ሥር ወድቃ
ሞተች፤ ጐልማሶቹም ሲገቡ ሞታ አገኟት፤
አውጥተውም በባሏ አጠገብ ቀበሯት።
11መላዪቱን ቤተ ክርስቲያንና ይህን የሰሙ
ትን ሁሉ፣ ታላቅ ፍርሀት ያዛቸው።

## በሐዋርያት እጅ ብዙ ሰው ተፈወሰ

12ሐዋርያትም በሕዝቡ መካከል ብዙ ታም
ራዊ ምልክቶችንና ድንቅ ሥራዎችን አደረጉ፤
አማኞቹም ሁሉ 'የሰሎሞን ደጅ' በተባለው
መመላለሻ ይሰበሰቡ ነበር። 13ከእነርሱ ጋር
ሊቀላቀል የደፈረ ማንም አልነበረም፤ ሆኖም
ሕዝቡ እጅግ ያከብሯቸው ነበር፤ 14ብዙ ወን
ዶችና ሴቶችም ከጊዜ ወደ ጊዜ በጌታ እያ
መኑ ወደ እነርሱ ይጨመሩ ነበር። 15ከዚህም
የተነሣ፣ ጴጥሮስ በዚያ ሲያልፍ፣ ቢያንስ ጥላው
እንኳ በጥቂቶች ላይ እንዲያርፍባቸው በማ
ለት ሕመምተኞችን ወደ ውጭ እያወጡ
በዐልጋና በቃሬዛ በመንገድ ላይ ያስተኙ
ነበር። 16በኢየሩሳሌም አካባቢ ከሚገኙ
ከተሞች፣ ሕመምተኞችንና በርኵሳን[ሀ]
መናፍስት የሚሠቃዩትን ይዘው የሚመጡት
ሰዎች አካባቢውን ያጨናንቁት ነበር፤ የመ
ጡትም ሁሉ ይፈወሱ ነበር።

## ሐዋርያት መከራና ስደት ደረሰባቸው

17ከዚህም የተነሣ ሊቀ ካህናቱና አብረ
ውት የነበሩት የሰዱቃውያን ወገን ሁሉ
በቅናት ተሞሉ፤ 18ሐዋርያትንም ይዘው ማረ
ፊያ ቤት ከተቷቸው። 19ይሁን እንጂ የጌታ
መልአክ በሌሊት የእስር ቤቱን ደጆች ከፍቶ
አወጣቸውና፣ 20"ሂዱ፤ በቤተ መቅደሱም አደ
ባባይ ቁሙ፤ የዚህንም ሕይወት ቃል ሁሉ
ለሕዝብ ንገሩ" አላቸው።
21እንደ ነጋም፣ በተነገራቸው መሠረት፣
ወደ ቤተ መቅደሱ አደባባይ ገብተው ሕዝ
ቡን ማስተማር ጀመሩ።
ሊቀ ካህናቱና ከእርሱ ጋር የነበሩት መጥ
ተው የአይሁድን ሸንጎና የእስራኤልን ሽማ
ግሌዎች ጉባኤ በሙሉ በአንድነት ሰበሰቡ፤
ሐዋርያትንም እንዲያመጡ ሰዎችን ወደ
እስር ቤት ላኩ። 22የተላኩትም ወደ እስር ቤቱ
ሄደው በዚያ አላገኟቸውም፤ ተመልሰውም
እንዲህ አሏቸው፤ 23"እስር ቤቱ በሚገባ ተቈ
ልፎ፣ ጠባቂዎቹም በበሩ ላይ ቆመው አገኘን፤
ከፍተን ስንገባ ግን በውስጡ ማንም አልነ
በረም።" 24የቤተ መቅደሱ ጥበቃ ሹምና የካ
ህናት አለቆችም ይህን በሰሙ ጊዜ በነገሩ ተገ
ረሙ፤ ግራም ተጋቡ።
25በዚህ ጊዜ አንድ ሰው መጥቶ፣ "እነሆ፤
እስር ቤት ያስገባችኋቸው ሰዎች በቤተ
መቅደሱ አደባባይ ቆመው ሕዝቡን እያስተ
ማሩ ናቸው" አላቸው። 26የጥበቃ ሹሙም
ከወታደሮቹ ጋር ሄዶ፣ ይዞ አመጣቸው፤
ያመጧቸው ግን ሕዝቡ በድንጋይ እንዳይወግ
ሯቸው ስለ ፈሩ በኀይል ሳያስገድዱ ነበር።
27ሐዋርያትንም አምጥተው በሸንጎው ፊት

[ሀ]16 ወይም በከቶ

5፥6 ዮሐ19፥40
5፥8 ቍ2
5፥9 ቍ3
5፥10 ቍ5፡6
5፥11 ቍ5፤ ሐሥ 19፥17
5፥12 ዮሐ4፥48፤ 10፥23፤ሐሥ2፥43፤ 3፥11፤4፥32
5፥13 ሐሥ2፥47፤ 4፥21
5፥14 ሐሥ2፥41
5፥15 ሐሥ19፥12
5፥16 ማቴ8፥16፤ ማር16፥17
5፥17 ሐሥ4፥1፤ 15፥5
5፥18 ሐሥ4፥3
5፥19 ዘፍ16፥7፤ዘፀ 3፥2፤መዝ34፥7፤ማቴ 1፥20፤2፥13፡19፤28፥2 ፤ሉቃ1፥11፤2፥9 ዮሐ20፥12፤ሐሥ8፥ 26፤ 10፥3፤12፥7፡23፤16፥2 6፤27፥23
5፥20 ዮሐ6፥63፡68
5፥21 ቍ27፡34፡ 41፤ማቴ5፥22፤ሐሥ 4፥5፡6
5፥22 ሐሥ12፥18፡ 19
5፥24 ሐሥ4፥1
5፥26 ሐሥ4፥21
5፥27 ማቴ5፥22

5፥9 *የጌታን መንፈስ ትፈታተኑ ዘንድ*፤ ይህ ኀጢአት ከፍተኛ ቅጣት ባያስከትል ኖሮ፣ የማታለሉ ተግባር በሚታወቅበት ጊዜ፣ ውጤቱ አደገኛ ይሆን ነበር፤ ማታለል ጥቅም የሚገኝበት መስሎ መታየቱ ብቻ ሳይሆን፣ መንፈስ ቅዱስን ማታለል እንደሚቻል መንገድ በጠረገ ነበር። እንዲህ ያለው ማስመሰልና ማታለል መቀጠል ስለሌለበት እግዚአብሔር በአጭሩ ቀጨው፤ በዚህም የክርስትና ሕይወት ትክክለኛውን ፈር ሊይዝ ቻለ።

5፥11 *ቤተ ክርስቲያን*፤ ይህን ስም በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የምናገኘው እዚህ ላይ ነው። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን (8፥1፤11፥22፤13፥1) ወይም የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ (20፥28 ይመ) ሊያመለክት ይችላል። አቅሌስያ የሚለው የግሪክ ቃል ቤተ ክርስቲያንን የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን፣ ፖለቲካዊ ስብሰባዎችና ሌሎች ጉባኤዎችም ይጠሩበት ነበር (19፥32፡40 ይመ)፤ እንዲሁም በሰብዓ ሊቃናት የብሉይ ኪዳን ትርጕም ቃሉ የእስራኤላውያንን የአምልኮ ስብሰባ ያመለክታል።

5፥12 *የሰሎሞን ደጅ*፤ የ3፥11 ማብ ይመ።

5፥13 *ከእነርሱ ጋር ሊቀላቀል የደፈረ ማንም አልነበረም*፤ በሐናንያና በሚስቱ ላይ ከደረሰው ቅጣት የተነሣ አስመሳዮችና ሁለት ልብ ያላቸው ተከታዮች ከአማኞች ጋር አንድ አካል ሆነው ለመታየት ፈሩ። ስለዚህ በቍ14 ላይ ብዙዎች "በጌታ እያመኑ ወደ እነርሱ ይጨመሩ ነበር" ስለሚል፣ ሉቃስ ይህን ያለው ወደ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ማንም አልተጨመረም ለማለት አይደለም።

5፥14 *ብዙ ወንዶችና ሴቶችም...እያመኑ*፤ 4፥4 ይመ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሴቶች ስለማመናቸው በግልጽ የተወሣው እዚህ ላይ ነው (ለ8፥3፡12፤9፥2፤13፥50፤16፥1፡13-14፤17፥4፡12፡34፤ 18፥2፤ 21፥5 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይሁን እንጂ ከ1፥14 ጋር ያነጻጽሩ።

5፥15 *ጴጥሮስ...ጥላው*፤ ከዚህ ጋር በአቻነት የሚታዩት የጳውሎስ መሐረብና (19፥12) የኢየሱስ የልብሱ ዘርፍ (ማቴ 9፥20) ናቸው፤ እነዚህ አነስተኛ ነገሮችና የሰው ጥላ ራሳቸው ታምራት ያደርጋሉ ማለት ሳይሆን፣ ከጌታና ከሐዋርያት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ ነው፤ አስማታዊ ኃይል ነው ማለት አይደለም።

5፥17 *ሊቀ ካህናቱና*፤ በሮም ሹማምንት ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው ሊቀ ካህናቱ ቀያፋ ነው፤ አይሁድ ግን እውነተኛው ሊቀ ካህናት ነው የሚሉት የቀያፋን ዐማት ሐናን ነበር፤ ሊቀ ካህንነት የዕድሜ ልክ ሹመት ነበርና (የ4፥6 ማብ ይመ)። *አብረውት የነበሩት*፤ ከነቤተ ሰቡ ማለት ነው። *የሰዱቃውያን ወገን*፤ የ4፥1 ማብ ይመ።

5፥18 *ማረፊያ ቤት*፤ በማግስቱ ለፍርድ እስኪቀርቡ ድረስ መቈያ ቦታ።

5፥19 *የጌታ መልአክ*፤ ይህ ሐረግ ከዚህ ሌላ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ አራት ቦታ ይገኛል፤ (1) እስጢፋኖስ ስለ እርሱ ይናገራል (7፥30-38)፤ (2) ፊልጶስን መርቶታል (8፥26)፤ (3) ጴጥሮስን ነጻ አውጥቶታል (12፥7-10)፤ (4) ሄሮድስን ቀሥፎታል (12፥23)። እንዲሁም ማቴ 1፥20-24፤2፥13፡19፤28፥2፤ ሉቃ1፥11-38፤2፥9 ይመ።

5፥21 *የአይሁድን ሸንጎና*፤ ከፍተኛ የአይሁድ የፍርድ ጉባኤ ሲሆን፣ ከሰባ እስከ መቶ የሚደርሱ አባላት አሉት (መደበኛው የአባላቱ ቍጥር ሰባ አንድ ነው)። የጉባኤው አባላት የክብ ግማሽ ቅርጽ ሠርተው የሚቀመጡ ሲሆን፣ የሚረዷቸው (ምሁራን) ደቀ መዛሙርት በሦስት ረድፍ ሆነው ከኋላቸው ይቀመጣሉ፤ ከፊት ለፊታቸውም የሸንጎው ጸሐፊዎች ይቆማሉ።

5፥24 *የቤተ መቅደሱ ጥበቃ ሹምና*፤ የ4፥1 ማብ ይመ።

አቆሟቸው፤ሊቀ ካህናቱም እንዲህ ሲል ጠየ
ቃቸው፤ 28“በዚህ ስም እንዳታስተምሩ በጥ
ብቅ አስጠንቅቀናችሁ ነበር፤ እናንተ ግን
ኢየሩሳሌምን በትምህርታችሁ ሞላችኋት፤
ደግሞም እኛን ለዚህ ሰው ደም ተጠያቂ
ዎች ልታደርጉን ቈርጣችሁ ተነሣችሁ!”
29ጴጥሮስና ሌሎች ሐዋርያትም መልሰው
እንዲህ አሉ፤ “ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር
ልንታዘዝ ይገባል! 30እናንተ በዕንጨት ላይ
ሰቅላችሁ የገደላችሁትን ኢየሱስን፣ የአባቶ
ቻችን አምላክ ከሙታን አስነሣው፤ 31እር
ሱም ለእስራኤል ንስሓንና የኀጢአትን ስር
የት ይሰጥ ዘንድ፣ እግዚአብሔር የሁሉ ራስና
አዳኝ አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው::
32እኛም ለእነዚህ ነገሮች ምስክር ነን፤ ደግ
ሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው
መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው::”
33ሰዎቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ክፉኛ ተቈጡ፤
ሊገድሏቸውም ፈለጉ:: 34ነገር ግን በሕዝቡ
ሁሉ ዘንድ የተከበረ አንድ የሕግ መምህር፣
እርሱም ገማልያል የሚሉት ፈሪሳዊ ተነ
ሥቶ በሸንጎው መካከል ቆመና ሐዋርያ
ትን ወደ ውጭ አውጥተው ለጥቂት ጊዜ
እንዲያቈዩአቸው አዘዘ፤ 35ለሸንጎውም እን
ዲህ አለ፤ “የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤ በእነዚህ
ሰዎች ላይ ልታደርጉ ስላሰባችሁት ነገር
በጥንቃቄ ልታጤኑ ይገባችኋል::
36ከዚህ ቀደም፣ ቴዎዳስ ራሱን ትልቅ
አድርጎ በመቍጠር ተነሥቶ፣ አራት መቶ
ያህል ሰዎች ተባበሩት፤ ነገር ግን እርሱም
ተገደለ፤ ተከታዮቹም ሁሉ ተበታተኑ፤ ነገሩም
እንዳልነበር ሆነ:: 37ከእርሱም በኋላ፣ በሕ
ዝብ ቈጠራው ወቅት ገሊላዊው ይሁዳ ተነ
ሥቶ ብዙ ሕዝብ አሸፈተ፤ ተከታዮችም አግ
ኝቶ ነበር፤ እርሱም ጠፋ፤ ተከታዮቹም
ተበተኑ:: 38ስለዚህ አሁንም የምላችሁ፦ እነ
ዚህን ሰዎች ተዉአቸው፤ አትንኳቸው፤ሐሳ
ባቸው ወይም አድራጎታቸው ከሰው ከሆነ ይጠ
ፋልና፤ 39ከእግዚአብሔር ከሆነ ግን ልትገቷ
ቸው አትችሉም፤ እንዲያውም ከእግዚአብሔር
ጋር ስትጣሉ ትገኙ ይሆናል::”
40እነርሱም ምክሩን ተቀብለው፤ ሐዋርያትን
አስጠርተው አስገረፏቸው፤ ዳግመኛም በኢየ
ሱስ ስም እንዳይናገሩ አዘው ለቀቋቸው::
41ሐዋርያትም፣ ስለ ስሙ ውርደትን ለመቀ
በል በመብቃታቸው ደስ እያላቸው ከሸን
ጎው ወጥተው ሄዱ፤ 42በየዕለቱም፣ በቤተ
መቅደስም ሆነ በየቤቱ፣ ኢየሱስ እርሱ ክር
ስቶስ[+] መሆኑን ከማስተማርና ከመስበክ
ከቶ ወደ ኋላ አላሉም ነበር::

### የሰባቱ ዲያቆናት መመረጥ

6 የደቀ መዛሙርት ቍጥር እየጨመረ
በሄደበት በዚህ ወቅት፣ ከግሪክ አገር
የመጡ አይሁድ በይሁዳ ይኖሩ በነበሩት
አይሁድ ላይ አጕረመረሙ፤ ምክንያቱም
በየዕለቱ በሚከናወነው ምግብ የማደል አሠ
ራር ላይ ከእነርሱ ወገን የሆኑት መበለቶች
ችላ ተብለው ነበር:: 2ስለዚህ ዐሥራ ሁለቱ
ሐዋርያት ሌሎችን ደቀ መዛሙርት በአን
ድነት ሰብስበው እንዲህ አሉ፤ “እኛ የማ
እዱን አገልግሎት ለማስተናገድ ስንል የእግ
ዚአብሔርን ቃል አገልግሎት መተው አይ

[+]42 ወይም መሲሕ

5፥28 ማቴ23፥35፤ 27፥25፤ሐሥ2፥23፡ 36፤3፥14፡15፤4፥18፤ 7፥52
5፥29 ዘፀ1፥17፤ ሐሥ 4፥19
5፥30 ሐሥ 2፥24፤ 3፥13
5፥31 ማቴ1፥21፤ ማር1፥4፤16፥19፤ ሉቃ2፥11፡24፥47፤ ሐሥ 2፥38፤3፥19፤ 10፥43
5፥32 ሉቃ24፥48፤ ዮሐ15፥26
5፥33 ሐሥ2፥37፤ 7፥54
5፥34 ሉቃ2፥46፤ 5፥17፤ሐሥ22፥3
5፥37 ሉቃ2፥1፡2
5፥38 ማቴ15፥13
5፥39 2ዜና13፥12፤ ምሳ21፥30፤ኢሳ46፥10፤ ሐሥ7፥51፤11፥17
5፥40 ማቴ10፥17
5፥41 ማቴ5፥12፤ ዮሐ15፥21
5፥42 ሐሥ2፥46፤ 9፥22፤13፥32
6፥1 ሐሥ2፥41፤ 4፥35፤9፥29፡39፡41፤ 1ጢሞ5፥3
6፥2 ሐሥ11፥26፤ ዕብ4፥12

5፥28 *እኛን ለዚህ ሰው ደም ተጠያቂዎች ልታደርጉን፤* አሁን እንዲህ ያሉት፣ ደቀ መዛሙርቱ በተደጋጋሚ ኢየሱስን የገደሉት አንዳንድ አይሁድና አለቆቻቸው ናቸው ይሉ ስለነበር (2፥23፤ 3፥13-15፤ 4፥10-11፤ ከማቴ 27፥25 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ይህንኑ በማስመልከት ሳይሆን አይቀርም::

5፥30 *በዕንጨት፤* መስቀልን ለማመልከት የገባ ቃል ነው (1ጴጥ2፥24፤ ዘዳ21፥22-23 ይመ):: ይህ ቃል በዕብራይስጡም ሆነ በግሪኩ ዛፍ፣ ምሰሶ፣ ጣውላ፣ ወይም ከዕንጨት የሚሠራ ማናቸውን ነገር ሊያመለክት ይችላል::

5፥32 *ደግሞም ... ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ፤* ዮሐ 15፥26-27 ይመ:: የደቀ መዛሙርቱ ምስክርነት በመንፈስ ቅዱስ የሚመራና የሚረጋገጥ ነበር:: መንፈስ ቅዱስ ዓለምን በእግዚአብሔር ቃል የሚወቅስ ሲሆን (ዮሐ 16፥8-11) “ከእምነት የተነሣ ለሚታዘዙት” የሚሰጥ ነው (ሮሜ 1፥5፤ የ6፥7 ማብ ይመ)::

5፥34 *ገማልያል የሚሉት ፈሪሳዊ፤* በዘመኑ እጅግ የታወቀ መምህር ሲሆን፣ ከዐበይት ሊቃውንት እንደ አንዱ የሚቈጠር ነው:: ምናልባት የሂላል የልጅ ልጅ ሳይሆን አይቀርም:: እርሱም በአመለካከቱ እንደ ሂላል (የማቴ 19፥3 ማብ ይመ)፤ ለዘብ ያለ ሰው ነበር፤ ይህ አመለካከቱም በዚህ ወቅት በሰጠው ምክር እውን ሆኖአል:: (ጳውሎስ) ከተማሪዎቹ አንዱ ሳውል ነበር (22፥3)::

5፥36 *ቴዎዳስ፤* ስለዚህ ሰው፣ ከዚህ ቦታ በስተቀር የሚናገር የታሪክ ምንጭ መኖሩን አናውቅም::

5፥37 *ገሊላዊው ይሁዳ፤* አይሁዳዊው ታሪክ ጸሓፊ ዮሴፍ ወልደኮርዮን ይህ ሰው በጎላንጢስ ውስጥ ጋማላ በተባለ ቦታ እንደ ነበረና፣ ለቄሳር ግብር አልከፍልም በማለት ጽፎለታል:: ይህ ሰው ያስነሳው ዐምፅ ተደምስሶአል፤ እንቅስቃሴው ግን “ተቀናቃኞች” በተባለው ተቃዋሚ ቡድን አማካይነት ነፍስ ዘርቶ ሳይቈይ አልቀረም (1፥13 እና የማቴ10፥4 ማብ ይመ):: *በሕዝብ ቈጠራው ወቅት፤* በሉቃስ ወንጌል 2፥2 ላይ በቀሬኔዎስ ዘመን የተካሄደው የመጀመሪያው የሕዝብ ቈጠራ ሳይሆን፣ በ6 ዓ.ም. የተከናወነው ነው::

5፥40 *አስገረፏቸው፤* በአይሁድ የጅራፍ ቅጣት መሠረት ለአርባ አንድ ሲቀረው 39 ጅራፍ ተገርፈዋል ማለት ነው (2ቆሮ 11፥24)::

6፥1 *የደቀ መዛሙርቱ ቍጥር እየጨመረ በሄደበት ጊዜ፤* ከምዕራፍ 5 መጨረሻ አንሥቶ ይኸም ይብዛ አንድ የተወሰነ ጊዜ ሳያልፍ አልቀረም:: ቤተ ክርስቲያን እያደገች መጣች (5፥14 ይመ)፤ እድገቷ ግን የማይቀረውን ችግር ከውስጥና (6፥1-7) ከውጭ (6፥8-7፥60) አስከተለ:: ቤተ ክርስቲያን በዚህ የእድገት ዘመኗ አማኞቿ በሙሉ አይሁድ ነበሩ፤ ይሁን እንጂ በዚህ ኅብረት የነበሩት ክርስቲያን አይሁድ በሁለት የተከፈሉ ነበሩ፤ 1) *ከግሪክ አገር የመጡ አይሁድ፤* ከፍልስጥኤም ምድር ውጪ በሌላ አገር የተወለዱ አይሁድ ናቸው:: የግሪክ ቋንቋ ይናገራሉ፤ ዝንባሌያቸውና አመለካከታቸውም ዕብራዊ ሳይሆን ግሪካዊ ነው:: 2) *በይሁዳ ይኖሩ በነበሩት አይሁድ፤* (በአራማይክና) በዕብራይስጥ ቋንቋ ወይም በሁለቱም የሚናገሩ ሲሆኑ፣ የአይሁድን ባህልና ልምድ ጠብቀው በእስራኤል ምድር ይኖሩ የነበሩት ናቸው:: *በየዕለቱ በሚከናወነው ምግብ የማደል አሠራር ላይ፤* ባሎቻቸው የሞቱባቸውና ተንከባካቢ ላጡ ሴቶች በእርግጥ እርዳታ ያስፈልግ ነበር፤ ስለዚህም እንደነዚህ ያሉትን ችግረኞች መርዳቱ ደግሞ የቤተ ክርስቲያኒቱ ኀላፊነት ሆነ (ከ4፥35፤ 11፥28-29 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም 1ጢሞ 5፥3-16 ይመ)::

6፥2 *ዐሥራ ሁለቱ፤* በዚህ በመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን እድገት ደረጃ፣ ሐዋርያት በማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዘርፍ የነበራቸው ኀላፊነት የእግዚአብሔርን ቃል ማሠራጨት፣ ማስተማር፣ እንዲሁም ችግረኞችን መርዳት ነበር:: *የማእዱን...፤* የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎትና (“የእግዚአብሔር ቃልና ጸሎት” ቍ4 ይመ) የማኅበራዊ አገልግሎት (“የማእድ አገልግሎት”) ኀላፊነት ነበረባት::

ገባንም:: 3ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ ከእናንተ
መካከል በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉ
ለመሆናቸው የተመሰከረላቸውን ሰባት ሰዎች
ምረጡ፤ ይህን ኀላፊነት ለእነርሱ እንሰጣለን፤
4እኛ ግን በጸሎትና በቃሉ አገልግሎት እን
ተጋለን::"

5አባባሉ ሁላቸውን ደስ አሰኘ፤ በእምነትና
በመንፈስ ቅዱስ የተሞላውን እስጢፋኖስን፣
እንዲሁም ፊልጶስን፣ ጵሮኮሮስን፣ ኒቃሮ
ናን፣ ጢሞናን፣ ጳርሜናንና ወደ ይሁዲነት
ገብቶ የነበረውን አንጾኪያዊውን ኒቆላዎስን
መረጡ:: 6እነዚህንም አምጥተው ሐዋርያት
ፊት አቀረቡአቸው፤ እነርሱም ከጸለዩ በኋላ
እጃቸውን ጫኑባቸው::

7የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ፤
የደቀ መዛሙርቱም ቍጥር በኢየሩሳሌም
እጅግ እየበዛ ሄደ፤ ከካህናትም ብዙዎቹ ለእ
ምነት የታዘዙ ሆኑ::

## የእስጢፋኖስ መያዝ

8በዚህ ጊዜ እስጢፋኖስ ጸጋንና ኀይልን
ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅ ነገሮችንና
ታምራዊ ምልክቶችን ያደርግ ነበር:: 9"የነጻ
ወጪዎች ምኵራብ" ተብሎ የሚጠራው
ምኵራብ አባላት የሆኑ ከቀሬናና ከእስክን
ድርያ፣ እንዲሁም ከኪልቅያና ከእስያ አው
ራጃዎች የመጡ ሰዎችም ተቃውሞ አስነሥ
ተው እስጢፋኖስን ይከራከሩት ጀመር፤
10ይሁን እንጂ ይናገርበት የነበረውን ጥበ
ብና መንፈስ መቋቋም አልቻሉም::

11ስለዚህ፣ "እስጢፋኖስ በሙሴና በእግዚ
አብሔር ላይ የስድብ ቃል ሲሰነዝር ሰም
ተናል" የሚሉ ሰዎችን በስውር አዘጋጁ::

12በዚህ ሁኔታ ሕዝቡን፣ የአገር ሽማግሌ
ዎቹንና የሕግ መምህራኑን በማነሣሣት፣
እስጢፋኖስን አስይዘው በአይሁድ ሸንጎ ፊት
አቀረቡት፤ 13እንዲህ ብለው የሚመሰክሩ
የሐሰት ምስክሮችንም አቆሙበት፤ "ይህ
ሰው በዚህ በተቀደሰው ስፍራና በሕጉ ላይ
የስድብ ቃል መናገሩን በፍጹም አልተወም፤
14ምክንያቱም ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን
ስፍራ እንደሚያጠፋና ከሙሴ የተቀበልነ
ውን ወግ እንደሚለውጥ ሲናገር ሰምተነዋል::"

15በሸንጎው ተቀምጠው የነበሩትም ሁሉ
እስጢፋኖስን ትኵር ብለው ሲመለከቱት
ፊቱ የመልአክ ፊት መስሎ ታያቸው::

6፥3 ዘፀ18፥21፤ ነህ 13፥13፤ ሉቃ1፥15፤ ሐሥ1፥16
6፥4 ሐሥ1፥14
6፥5 ቍ8፤ ሉቃ 1፥15፤ ሐሥ7፥55-60፤ 8፥5-40፤ 11፥19፤ 21፥8፤22፥20
6፥6 ዘኍ8፥10፤ 27፥18፤ማር5፥23፤ ሐሥ 1፥24፤ 9፥17፤19፥6፤ 28፥8፤1ጢሞ4፥14
6፥7 ሐሥ2፥41፤ 12፥24፤19፥20
6፥8 ዮሐ4፥48
6፥9 ማቴ27፥32፤ ሐሥ 2፥9፤ 15፥23፡41፤ 22፥3፤23፥34
6፥10 ሉቃ21፥15
6፥11 1ነገ21፥10፤ ማቴ26፥59-61
6፥12 ማቴ5፥22
6፥13 ዘፀ23፥1፤መዝ 27፥12፤ ማቴ24፥15፤ ሐሥ 7፥48፤21፥28
6፥14 ዮሐ2፥19፤ ሐሥ 15፥1፤21፥21፤ 26፥3፤28፥17
6፥15 ማቴ5፥22

6፥3 *በመንፈስ ቅዱስ...የተሞሉ፤* የ2፥4 ማብ ይመ:: *ሰባት ሰዎች ምረጡ፤* ቤተ ክርስቲያን መረጠቻቸው (ቍ5)፤ ሐዋርያት ሾሟቸው (ቍ6):: እንግዲህ ለተመደቡበት ሥራ የተሰየሙት በዚህ መልክ ነበር::

6፥5 *እስጢፋኖስን... ኒቆላዎስን መረጡ፤* ጕርምርም ታው የተሰማው ግሪክኛ ከሚናገሩት የቤተ ክርስቲያን ወገኖች ስለ ነበር፣ የተመረጡት ሰባቱ ሰዎች ስማቸው የግሪክ መሆኑ ዐቢይ ጕዳይ ነው፤ የእነርሱ ፍላጎት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንዲታይ ሊወክሉአቸው ይችላሉና:: ከሰባቱ ውስጥ ስለ ማንነታቸው ተጨማሪ መግለጫ የተሰጠው ስለ እስጢፋኖስና ስለ ፊልጶስ ብቻ ነው (እስጢፋኖስ 6፥8-7፥60፤ ፊልጶስ 8፥5-40፤21፥8-9):: *ወደ ይሁዲነት ገብቶ የነበረውን አንጾኪያዊውን፤* ከአሕዛብ ወገን የነበረውንና ወደ አይሁድ ሃይማኖት የገባውን ይህን ሰው ሉቃስ ከቍጥር ውስጥ ማስገባቱና የመጣበት አገር አንጾኪያ መሆኑን መግለጹ ዐቢይ ነገር ነው:: ወንጌልም በዚህች ከተማ በፍጥነት የሚሰበከባትና አሕዛብን በወንጌል ለመድረስም ላለው ተልእኮ መናኸሪያ ልትሆን ነው::

6፥6 *ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው፤* በብሉይ ኪዳን ዘመን አንድን ሰው ለመባረክ (ዘፍ 48፥13-20)፣ በደልን ከአንድ ኀጢአተኛ ወደ መሥዋዕቱ ለማስተላለፍ (ዘሌ 1፥4)፣ እንዲሁም አንድን ሰው በአዲስ የኀላፊነት ቦታ ላይ ለመሾም (ዘኍ 27፥23) እጅ ይጫን ነበር:: በአዲስ ኪዳንም ለመፈወስ (28፥8፤ማር1፥41)፣ ለመባረክ (ማር10፥16)፣ለመሾም ወይም በኀላፊነት ቦታ ላይ ለማስቀመጥ (6፥6፤ 13፥3፤ 1ጢሞ 5፥22)፣ ለመንፈስ ቅዱስ ስጦታ (8፥17፤19፥6፤1ጢሞ4፥14፤2ጢሞ 1፥6) እጅ ይጫናል:: ሰባቱም ሰዎች ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ትከሻ ላይ የወደቀውን ኀላፊነት ለመሸከም ተሾሙ:: በግሪኩ፣ "ዲያቆን" የሚለው ቃል፣ "አገልጋይ" ወይም "አሽከር" ተብሎም፣ ሊተረጐም ይችላል:: ሐዋርያት፣ "ዐሥራ ሁለቱ" ተብለው ይጠሩ እንደ ነበር ሁሉ፣ እነዚህም፣ "ሰባቱ" ተብለው ይጠራሉ (21፥8):: እነዚህ ሰባቱ (በ21፥8 ላይ የተጠቀሱት) የመጀመሪያዎቹ ዲያቆናት ይሁኑ ወይም ወደ ኋላ ላይ የተሿሟቸው ሌሎች ይኑሩ አይታወቅም (የ1ጢሞ 3፥8 ማብ ይመ)::

*6፥7፤* በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በተከታታይ ስለ ወንጌል መስፋፋት በየጊዜው ከተነገረባቸው ክፍሎች ውስጥ አንዱ ይህ ነው (1፥15፤ 2፥41፤ 4፥4፤ 5፥14፤ 6፥7፤ 9፥31፤ 12፥24፤ 16፥5፤ 19፥20፤ 28፥31):: *ከካህናትም ብዙዎቹ፤* በብሉይ ኪዳን ሥርዐተ ክህነት በዘር የሚተላለፍ የዕድሜ ልክ አገልግሎት ቢሆንም፣ የቀድሞውን መሥዋዕት ሽሮ አዲሱን መሥዋዕት የሚያውጀውን የሐዋርያትን ስብከት የተቀበሉ ማለት ነው (ዕብ 8፥13፤ 10፥1-4፡ 11-14):: *ለእምነት የታዘዙ ሆኑ፤* የወንጌልን ትምህርት አምነው የተቀበሉ ማለት ነው:: ማመን ሲባል ለእግዚአብሔር መታዘዝ ማለት ነው፤ እምነት ራሱ መታዘዝ ማለት ነው፤ ይሁን እንጂ እምነትም መታዘዝን ያስከትላል (ሮሜ1፥5፤ ኤፌ 2፥8-10፤ ያዕ 2፥14-26)::

6፥8 *ድንቅ ነገሮችንና ታምራዊ ምልክቶችን፤* እስከዚህ ድረስ፣ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሐዋርያት ብቻ ታምራትን እንደሚሠሩ ይተርክ ነበር (2፥43፤3፥4-8፤5፥12)፤ አሁን ግን ሐዋርያት እጃቸውን ከጫኑባቸው በኋላ እስጢፋኖስ ታምራዊ ምልክቶችን እንደ ሠራ ተገልጾአል፤ ፊልጶስም ቀጥሎ እንደዚሁ ሲሠራ ይታያል (8፥6)::

6፥9 *የነጻ ወጪዎች ፤* ከባርነት ነጻ ወጥተው፣ የተለያየ የግሪክ ሥልጣኔ ከደረሰባቸው አገሮች የመጡ ናቸው:: *ቀሬና፤* በእስክንድርያና በቅርጣግና (በካርታጐ) መካከል በሊቢያና በሰሜን አፍሪካ የምትገኝ ታላቅ ከተማ ናት (የ2፥10 ማብ ይመ)፤ ከነዋሪዎቿ መካከል አይሁድ ይገኙ ነበር (11፥19-21 ይመ):: *እስክንድርያ፤* የግብፅ ዋና ከተማ ስትሆን፣ በሮማውያን የቄሳር መንግሥት ከሮም ቀጥላ ትልቅዋ ከተማ ናት:: ከአምስቱ የእስክንድርያ ክፍለ ከተማዎች ሁለቱ የአይሁድ መኖሪያ ነበሩ:: *ኪልቅያ፤* ከታናሹ እስያ ደቡብ ምሥራቅ ዳርቻ ላይ የምትገኝና ከሶርያ ጋር የምትዋሰን የሮም አውራጃ ነበረች:: ጳውሎስ የተወለደበት ጠርሴስ፣ ዐበይት ከሆኑት ከተሞች አንዷ ናት:: *እስያ፤* ከትንሹ እስያ በስተ ምዕራብ የምትገኝ የሮም ግዛት ስትሆን፣ ጳውሎስ በኋላ ጊዜ ወንጌልን ያስተማረባት ኤፌሶን፣ የዚህች አገር ዋና ከተማ ነበረች:: *ሰዎችም...ይከራከሩት ጀመር፤* ሳውል የጠርሴስ ሰው ስለ ነበረ፣ በዚሁ ምኵራብ ሳያመልክ አልቀረም፤ እስጢፋኖስን ይከራከሩ ከነበሩትም ሰዎች አንዱ እርሱ ሊሆን ይችላል፤ እስጢፋኖስ በድንጋይ ሲወገርም ጳውሎስ በዚያ ቦታ ነበር (7፥58)::

6፥11 *በሙሴና በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ሲሰነዝር፤* እስጢፋኖስ ከእንግዲህ እግዚአብሔርን ማምለክ በቤተ መቅደስ ብቻ አይወሰንም በማለቱ (7፥48-49)፣ ተቃዋሚዎቹ ሐሳቡን አጣመው እስጢፋኖስ ቤተ መቅደስን፣ የኦሪትን ሕግና ሙሴን፣ እንዲሁም እግዚአብሔርን ተቃውሞአል የሚል ክስ አቀነባብረው አቀረቡበት::

6፥12 *የአገር ሽማግሌዎቹንና የሕግ መምህራኑን፤* የማቴ 2፥4፤15፥2፤ ሉቃ 5፥17 ማብ ይመ:: *ሸንጎ* የማር 14፥55 ማብ ይመ::

6፥13 *በዚህ በተቀደሰው ስፍራና በሕጉ ላይ የስድብ ቃል መናገሩን፤* በክርስቶስ ላይ ቀርቦ ከነበረው ክስ ጋር ይመሳሰላል (ማቴ 26፥61 ይመ):: እስጢፋኖስ በዮሐ 2፥19 ተጽፎ የሚገኘውን የጌታን ቃል ተጠቅሞ ሊሆን ይችላል፤ ሰዎቹ ግን የተናገረውን በተሳሳተ መልክ ተርጕመውት ይሆናል፤ ወይም ጌታ በተከሰሰ ጊዜ እንዳደረጉት ሁሉ፣ የእስጢፋኖስንም ንግግር ሆን ብለው አጣመው ሊሆን ይችላል (ቍ14)::

## እስጢፋኖስ በሸንጎው ፊት ያደረገው ንግግር

7 ሊቀ ካህናቱም፣ “ይህ የቀረበብህ ክስ
እውነት ነውን?” አለው።
2እስጢፋኖስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ወንድ
ሞችና አባቶች ሆይ፤ አድምጡኝ! አባታችን
አብርሃም ወደ ካራን ከመምጣቱ በፊት፣
ገና በመስጴጦምያ ሳለ፣ የክብር ስምባክ ተገ
ልጦለት፤ 3ከአገርህና ከወገንህ ተለይተህ እኔ
ወደማሳይህ ምድር ሂድ አለው።
4“እርሱም ከከለዳውያን ምድር ወጥቶ በካ
ራን ተቀመጠ። ከአባቱም ሞት በኋላ፣ አሁን
እናንተ ወደምትኖሩበት ወደዚህ አገር
አመጣው። 5በዚህም ስፍራ አንዲት ጫማ
ታህል እንኳ ርስት አልሰጠውም፤ ነገር ግን
በዚያን ጊዜ ምንም ልጅ ሳይኖረው፣ እርሱና
ከእርሱም በኋላ ዘሩ ምድሪቱን እንደሚወርሱ
እግዚአብሔር ቃል ገባለት። 6ደግሞም እግዚአብሔር
እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ ዘርህ በባዕድ አገር መጻ
ተኛ ይሆናል፤ አራት መቶ ዓመትም በባር
ነት ቀንበር ሥር ይማቅቃል። 7ሆኖም በባ
ርነት የሚገዛቸውን ሕዝብ እኔ ደግሞ እቀ
ጣዋለሁ። ከዚያም አገር ወጥተው በዚህች
ስፍራ ያመልኩኛል።’ 8ከዚያም የግዝረትን ኪዳን
ሰጠው፤ አብርሃምም ይስሐቅን ወለደ፤ በስም
ንተኛውም ቀን ገረዘው። ይስሐቅም ያዕቆብን
ወለደ፤ ያዕቆብም ዐሥራ ሁለቱን የነገድ
አባቶች ወለደ።
9“የነገድ አባቶችም በዮሴፍ ቀንተው
በባርነት ወደ ግብፅ ሸጡት፤ እግዚአብሔር ግን
ከእርሱ ጋር ስለ ነበር፣ 10ከመከራው ሁሉ አወ
ጣው፤ በግብፅም ንጉሥ በፈርዖን ፊት ሞገስና
ጥበብን አጐናጸፈው፤ ፈርዖንም በግብፅና
በቤተ መንግሥቱ ሁሉ ላይ ኀላፊ አድርጎ

7፥2 ዘፍ11፥31፤ 15፥7፤መዝ29፥3፤ ሐሥ22፥1
7፥3 ዘፍ12፥1
7፥4 ዘፍ12፥5
7፥5 ዘፍ12፥7፤ 17፥8፤ 26፥3፤ዕብ 11፥13
7፥6 ዘፀ1፥8-11፤ 12፥40
7፥7 ዘፍ15፥13: 14፤ዘፀ3፥12
7፥8 ዘፍ17፥9-14፤ 21፥2-4፤25፥26፤ 29፥ 31-35፤30፥5-13፡17-24፤35፥16-18፡ 22-26
7፥9 ዘፍ37፥4፡11፡ 28፤39፥2፡21፡23፤መዝ 105፥17፤ሐጌ 2፥4
7፥10 ዘፍ41፥37-43፤ መዝ105፥20-22
7፥11 ዘፍ41፥54
7፥12 ዘፍ42፥1፡2
7፥13 ዘፍ45፥1-4፡16
7፥14 ዘፍ45፥9፡ 10፤46፥26፡27፤ ዘፀ1፥5፤ዘዳ10፥22
7፥15 ዘፍ46፥5-7፤ 49፥33፤ዘፀ1፥6
7፥16 ዘፍ23፥16-20፤ 33፥18፡19፤50፥13፤ ኢሱ 24፥32
7፥17 ዘፀ1፥7፤ መዝ 105፥24
7፥18 ዘፀ1፥8
7፥19 ዘፀ1፥10-22
7፥20 ዘፀ2፥2፤ ዕብ 11፥23
7፥21 ዘፀ2፥3-10
7፥22 1ነገ4፥30፤ ኢሳ 19፥11

ሾመው።
11“በዚያ ጊዜም በግብፅና በከነዓን አገር
ሁሉ፣ ታላቅ መከራን ያስከተለ ራብ መጣ፤
አባቶቻችንም የሚበሉትን አጡ። 12ያዕቆ
ብም እህል በግብፅ መኖሩን በሰማ ጊዜ፣
አባቶቻችንን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ግብፅ
ላካቸው፤ 13ለሁለተኛ ጊዜ ሲሄዱ ደግሞ
ዮሴፍ ማንነቱን ለወንድሞቹ ገለጠ፤ ፈርዖ
ንም ስለ ዮሴፍ ዘመዶች ተረዳ። 14ከዚህ በኋላ፣
ዮሴፍ ልኮ አባቱን ያዕቆብንና ሰባ አምስት ነፍስ
የሚሆኑ ቤተ ዘመዶቹን በሙሉ አስመጣ።
15ያዕቆብ ወደ ግብፅ ወረደ፤ እርሱም አባቶቻ
ችንም በዚያ ሞቱ። 16አስከሬናቸውም ወደ
ሴኬም ተወስዶ፣ አብርሃም ከዔሞር ልጆች ላይ
በጥሬ ብር በገዛው መቃብር ተቀበረ።
17“እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃል
የሚፈጸምበት ጊዜ ሲቃረብም፣ በግብፅ የነ
በረው የሕዝባችን ቍጥር እየበዛ ሄደ። 18ከዚያ
በኋላ ዮሴፍን የማያውቅ ሌላ ንጉሥ በግብፅ
ነገሠ። 19እርሱም ሕዝባችንን በተንኰሉ አስጨ
ነቀ፤ ገና የተወለዱ ሕፃናታቸውም ይሞቱ ዘንድ
ወደ ውጭ አውጥተው እንዲጥሏቸው አስገ
ደዳቸው።
20“በዚህ ጊዜ ሙሴ ተወለደ፤ እርሱም በእ
ግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኘ ውብ ሕፃን*
ነበር። በአባቱም ቤት ሦስት ወር በእንክብ
ካቤ አደገ። 21ወደ ውጭ በተጣለም ጊዜ
የፈርዖን ልጅ አግኝታ ወሰደችው፤ እንደ ራሷ
ልጅ አድርጋም አሳደገችው። 22ሙሴም የግ
ብፃውያንን ጥበብ ሁሉ ተማረ፤ በንግግሩና በተ
ግባሩም ብርቱ ሆነ።
23“ሙሴ አርባ ዓመት በሆነው ጊዜ፣ ወንድ
ሞቹን የእስራኤልን ልጆች ሊጐበኝ በልቡ

*20 *ወይም ተራ ልጅ አልነበረም*

7፥1 *ሊቀ ካህናቱም፤* ቀያፋ ሊሆን ይችላል (ማቴ 26፥57-66 ይመ)፤ ሆኖም የ4፥6 ማብ ይመ፤ ከዮሐ 18፥19፡24 ጋር ያነጻጽሩ። *ይህ...ክስ እውነት ነውን?* የ6፥11፡13 ማብ ይመ።

7፥2 *አብርሃም ወደ ካራን ከመምጣቱ በፊት... በመስጴጦምያ ሳለ፤* አብርሃም በመጀመሪያ የተጠራው ከከለዳውያን ከተማ ከዑር ነው እንጂ ከካራን አልነበረም፤ (ዘፍ 15፥7፤ ነህ 9፥7 ይመ) እንዲሁም በዘፍ 12፡1-4 አብርሃም በካራን ሳለም መጠራቱ ተጽፎአል፤ ይህ ግን ዳግመኛ የማጠናከሪያ ጥሪ ሊሆን ይችላል።

7፥4 *ከከለዳውያን ምድር፤* በደቡብ ባቢሎን የምትገኝ አውራጃ ነበረች። ከጊዜ በኋላ ግን ይህ ስም መላውን ባቢሎን የሚያጠቃልል መጠሪያ ሆኖአል። *ከአባቱም ሞት በኋላ፤* ዘፍ 11፥26 ታራ የሰባ ዓመት ሰው ሳለ አብርሃምን፣ ናኮርንና ሐራንን በአንድ ዓመት ውስጥ ወለዳቸው ማለቱ አይደለም ዘፍ 11፥26-12፥1ይመ። ሐራን የታራ መጀመሪያ ልጁ ሳይሆን አይቀርም፤ ከዚያም ከ60 ዓመት በኋላ አብርሃም ተወለደ። ታራ በ205 ዓመቱ የሞተው፣ አብርሃም በ75 ዓመቱ ከካራን ከመውጣቱ ትንሽ ቀደም ብሎ ሊሆን ይችላል።

7፥6 *አራት መቶ ዓመት፤* እስራኤላውያን ከሞላ ጐደል በግብፅ የኖሩበት ዘመን ነው (ዘፀ12፥40-41 *አራት መቶ ሠላሳ ዓመት* ይለዋል)።

7፥8 *የግዝረትን ኪዳን፤* የዘፍ 17፥10-11 ማብ ይመ። ገና ቤተ መቅደስ ከመታነጹና አሁን ያለው የሃይማኖት ሥርዐት ከመጀመሩ በፊት፣ ለእስራኤል ሃይማኖት አስፈላጊዎቹ ሁኔታዎች ቀደም ሲል ተሟልተው ነበር። *ዐሥራ ሁለቱን የነገድ አባቶች፤* ዘፍ 35፥23-26 ይመ።

7፥9 *ሸጡት፤* እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሰዎች እስራኤል ባለመቀበል በእምቢተኝነት ጸንታለች። እስጢፋኖስ፣ ወንድሞቹ ዮሴፍን እንደጠሉት በማመልከት (ዘፍ 37፥12-36)፣ እስራኤላውያን ጌታ ኢየሱስን አለመቀበላቸውን ያመለክታል።

7፥13 *ለሁለተኛ ጊዜ ሲሄዱ፤* ዘፍ 43 ይመ።

7፥14 *ያዕቆብንና ሰባ አምስት የሚሆኑ ቤተ ዘመዶቹን በሙሉ፤* ምንም እንኳ የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ቍጥራቸው ሰባ መሆኑን ቢናገርም (ዘፍ 46፥27፤ ዘፀ 1፥5 ዘዳ 10፥22)፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም በዘፍ 46፥20 ላይ የምናሴን ወንድ ልጅ ስም፣ የኤፍሬምን ሁለት ልጆችና፣ ከእያንዳንዳቸውም የተወለዱትን አንዳንድ የልጅ ልጅ አክሎአል፤ ይህም ቍጥሩን ሰባ አምስት ያደርሰዋል፤ እስጢፋኖስ ያወሣውም ቍጥር ይህንኑ ነው።

*7፥16፤* እስጢፋኖስ በብሉይ ኪዳን የሚገኘውን በአብርሃምና በያዕቆብ የተከናወነውን ሁለት የመሬት ግዥና ሁለት የመቃብር ቦታዎች ማለት ኬብሮንና ሴኬምን በአንድ ስም አጠቃሎ ተርኮአል። በብሉይ ኪዳን ተጽፎ እንደምናገኘው አብርሃም በኬብሮን መሬት ገዝቶአል (ዘፍ23፥17-18)፤ በዚህም እርሱ ራሱ (ዘፍ 25፥9-21) ይስሐቅና (ዘፍ 35፥29)፣ ያዕቆብ (ዘፍ 50፥13) ተቀብረዋል። ያዕቆብ በሴኬም መሬት ገዝቶአል (ዘፍ33፥19)፤ ዮሴፍ የተቀበረውም በዚሁ ቦታ ነው (ኢሱ24፥32)። የዮሴፍም ወንድሞች በኬብሮን መቀበራቸውን ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የተባለው ታሪክ ጸሐፊ መዝግቦት ይገኛል።

7፥18 *ዮሴፍን የማያውቅ ሌላ ንጉሥ፤* የዘፀ 1፥8 ማብ ይመ።

7፥22 *ሙሴም የግብፃውያንን ጥበብ ሁሉ ተማረ፤* በብሉይ ኪዳን የተገለጸ ነገር ባይኖርም፣ በልዕልቲቱ በፈርኦን ልጅ ቤት እስካደገ ድረስ እንዲህ ያለውን ዕውቀት መገብየቱ የማይቀር ነው። ሙሴ የጠለቀ ዕውቀት እንደነበረው ፊሎና ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ጽፈዋል።

7፥23 *ሙሴ አርባ ዓመት በሆነው ጊዜ፤* ሙሴ ለፈርዖን እንዲናገር ከእግዚአብሔር በተላከ ጊዜ የሰማንያ ዓመት (ዘፀ 7፥7) ሲሞትም ደግሞ የመቶ ሃያ ዓመት ሰው ነበር (ዘዳ34፥7)። ሙሴ በመጀመሪያ ከግብፅ የወጣው በአርባ ዓመቱ ነበር ከሚለው ጥንታዊ አባባል ጋር የእስጢፋኖስ አነጋገር ይስማማል።

አሰበ:: 24እርሱም፣ አንድ ግብፃዊ ከወገኖቹ
አንዱን በደል ሲያደርስበት አይቶ ግብፃዊ
ውንም ገደለ፤ ለተገፋው ወገኑም ተበቀለ::
25ወገኖቹም እግዚአብሔር በእርሱ እጅ ነጻ እን
ደሚያወጣቸው የሚያስተውሉ መስሎት ነበር፤
እነርሱ ግን አላስተዋሉም:: 26በማግስቱም
ደግሞ ሁለት እስራኤላውያን ሲጣሉ ደረሰ፤
ሊያስታርቃቸውም ፈልጎ፣ ‘ሰዎች፤ እናንተ
እኮ ወንድማማቾች ናችሁ፤ እንዴት እርስ
በርሳችሁ ትጐዳዳላችሁ?’ አላቸው::
27“በባልንጀራው ላይ በደል ሲያደርስ የነ
በረው ሰው ግን፣ ሙሴን ገፈተረውና እንዲህ
አለ፤ ‘አንተን ገዥና ፈራጅ አድርጎ በእኛ
ላይ የሾመህ ማን ነው? 28ወይስ ትናንት
ግብፃዊውን እንደ ገደልኸው እኔንም ልትገ
ድለኝ ትፈልጋለህን?’ 29ሙሴም ይህን እንደ
ሰማ ሸሽቶ በምድያም አገር መጻተኛ ሆኖ ተቀ
መጠ፤ በዚያም ሁለት ወንዶች ልጆች ወለደ::
30“ከአርባ ዓመት በኋላ፣ በሲና ተራራ
አካባቢ ባለው ምድረ በዳ፣ በሚነድ ቍጥ
ቋጦ ነበልባል ውስጥ መልአክ ተገለጠለት::
31ሙሴም ባየው ነገር ተደነቀ፤ ነገሩን ለማ
ጣራት ወደዚያ ሲቀርብ የጌታ ድምፅ፤ 32‘እኔ
የአባቶችህ አምላክ፣ የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣
የያዕቆብ አምላክ ነኝ’ ሲል ሰማ:: ሙሴም
በፍርሀት ተዋጠ፤ ለመመልከትም አልደፈረም::
33“ጌታም እንዲህ አለው፤ ‘የእግርህን ጫ
ማ አውልቅ፤ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች
ምድር ናትና:: 34በግብፅ ያለውን የሕዝቤን
መከራ በእርግጥ አይቻለሁ፤ የጭንቅ ጩኸ
ታቸውን ሰምቻለሁ፤ ላድናቸውም ወርጃለሁ::
አሁንም ና፤ ወደ ግብፅ መልሼ እልክሃለሁ::’
35“እንግዲህ እነዚያ፣ ‘ገዥና ፈራጅ አድ
ርጎ የሾመህ ማን ነው?’ ብለው የናቁትን ይህ
ንን ሙሴ እግዚአብሔር በቍጥቋጠው ውስጥ
በታየው መልአክ አማካይነት ገዥና ታዳጊ
አድርጎ ወደ እነርሱ ላከው:: 36እርሱም

7፥27 ዘፍ19፥9፤ ዘኍ 16፥13
7፥29 ዘፀ2፥11-15
7፥31 ዘፀ3፥1-4
7፥32 ዘፀ3፥6፤ሐሥ 3፥13
7፥33 ዘፀ3፥5፤ኢሱ 5፥15
7፥34 ዘፀ3፥7-10
7፥35 ቍ27
7፥36 ዘፀ11፥10፤12፥41፤14፥21፤15፥25፤17፥5፡6፤33፥1፤ዮሐ4፥48
7፥37 ዘዳ18፥15፡18፤ሐሥ3፥22
7፥38 ቍ53፤ዘፀ 19፥17፤ዘሌ27፥34፤ ዘዳ32፥45-47፤ ሮሜ3፥2፤ዕብ4፥12
7፥39 ዘኍ14፥3፡4
7፥40 ዘፀ32፥1፡23
7፥41 ዘፀ32፥4-6፤ መዝ106፥19፡20፤ ራእ 9፥20
7፥42 ኢሱ24፥20፤ ኢሳ63፥10፤ ኤር 19፥13
7፥43 አሞ5፥25-27
7፥44 ዘፀ25፥8፡9፡ 40፤38፥21፤ ዘኍ1፥50፤17፥7

መርቶ ከግብፅ አወጣቸው፤ በግብፅ፣ በቀይ
ባሕርና በምድረ በዳ አርባ ዓመት ድንቅ ነገ
ሮችንና ታምራዊ ምልክቶችን አደረገ።
37“የእስራኤልንም ሕዝብ፣ ‘እግዚአብሔር እንደ
እኔ ያለ ነቢይ ከመካከላችሁ ያስነሣላች
ኋል’ ያላቸው ይህንኑ ሙሴ ነበር:: 38እርሱም
በሲና ተራራ ከተናገረው መልአክና ከአባቶ
ቻችን ጋር በሕዝቡ ጉባኤ መካከል ነበር፤ የሕ
ይወትንም ቃል ወደ እኛ ለማስተላለፍ
ተቀበለ::
39“አባቶቻችን ግን ተቃወሙት እንጂ ሊታ
ዘዙት ስላልፈለጉ በልባቸው ወደ ግብፅ
ተመለሱ:: 40አሮንንም፣ ‘ፊት ፊታችን የሚ
ሄዱ አማልክት አብጅልን፤ ከግብፅ ምድር
መርቶ ያወጣን ያ ሙሴ ምን እንደ ደረሰ
በት አናውቅምና’ አሉት:: 41በዚያን ጊዜ
የጥጃ ምስል ሠርተው፣ ለጣዖቱ መሥዋዕት
አቀረቡ፤ በእጃቸውም ሥራ ተደሰቱ፤ ፈነጠ
ዙም:: 42እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ ዘወር አለ፤
ያመልኳቸውም ዘንድ ለሰማይ ከዋክብት
አሳልፎ ሰጣቸው፤ ይህም በነቢያት መጽ
ሐፍ እንዲህ ተብሎ በተጻፈው መሠረት
ተፈጸመ፤

“‘እናንተ የእስራኤል ቤት ሆይ፤ አርባ ዓመት
በምድረ በዳ በነበራችሁ ጊዜ፣
መሥዋዕትንና መባን ለእኔ
አቀረባችሁልኝን?
43ይልቁንም ልታመልኳቸው የሠራችኋቸውን፣
የሞሎክን ድንኳንና የጣዖታችሁን፣
የሬምፋምን ኮከብ ከፍ ከፍ አድርጋችሁ
ያዛችሁ::
ስለዚህ እኔም እንድትጋዙ አደርጋለሁ፤
ከባቢሎንም ወዲያ አሰዳችኋለሁ::

44“እግዚአብሔር ለሙሴ ባሳየው ንድፍና ባዘ
ዘው መሠረት የተሠራችው የምስክር ድንኳን፣
ከአባቶቻችን ጋር በምድረ በዳ ነበረች::

7፥29 *ሸሽቶ በምድያም አገር...ተቀመጠ፤* ሙሴ በወገኖቹ ዘንድ ተቀባይነት ስላጣ፣ ለግብፃውያን እንዳይነግሩበት ፈርቶ ወደ ምድያም መሰደድ ግድ ሆነበት (ዘፀ 2፥15)፤ የምድያም አገር የሚገኘው በቀይ ባሕር ጫፍ ላይ፣ በአካባ ባሕረ ሠላጤ ግራና ቀኝ ነበር:: *ሁለት ወንዶች ልጆች ወለደ፤* እነርሱም ጌርሳምና አልዓዛር ይባላሉ (ዘፀ 2፥22፤ 18፥3-4፤ 1ዜና 23፥15)::

7፥30 *ከአርባ ዓመት በኋላ፤* በቍ23 ላይ ከተገለጸው 40 ዓመት ጋር ሲደመር፣ በዘፀ7፥7 የተመለከተውን 80 ዓመት ያመጣል:: *በሲና ተራራ፤* በዘፀ 3፥1 የኮሬብ ተብሎአል (የዘፀ 3፥1 ማብ ይመ)::

7፥35 *የናቁትን ይህንን ሙሴ...ገዥና ታዳጊ አድርጎ ወደ እነርሱ ላከው፤* እስጢፋኖስ በነበረበት ጊዜ፣ እስራኤላውያን ጌታ ኢየሱስን እንዳልተቀበሉት ሁሉ፣ በዘመኑ የነበሩት እስራኤላውያንም ሙሴን አልተቀበሉትም፤ ይሁን እንጂ ሁለቱም የተላኩት ከእግዚአብሔር ነበር:: *በቍጥቋጠው ውስጥ በታየው መልአክ፤* ዘፀ 3፥2 ይመ::

7፥37 *እንደ እኔ ያለ ነቢይ፤* 3፥22-23 ይመ፤ እንዲሁም የዘዳ 18፥15 ማብ ይመ::

7፥38 *ከተናገረው መልአክና፤* በዚያ ጊዜ በነበረው የአይሁድ ትርጓሜ መሠረት ሕጉ ለሙሴ የተሰጠውም መልአኩ በመጀመሪያ ሙሴን እንደ ጠራው ሁሉ፣ ሙሴ የእሪትን ሕግ የተቀበለውም በመልአክ አማካይነት ነው (ዘፀ3፥2 እንዲሁም ቍ53፤ ገላ 3፥19፤ ዕብ 2፥2 ይመ):: *የሕይወትንም ቃል ወደ እኛ ለማስተላለፍ ተቀበለ፤* ሙሴ በመካከል ሆኖ እግዚአብሔርንና ሰውን በሲና ተራራ ላይ ያገናኘ ነው::

7፥39 *ሊታዘዙት ስላልፈለጉ፤* የእግዚአብሔርን መልእክተኛና ትእዛዙን አሁንም አልተቀበሉም (ቍ27 ይመ)::

7፥40 *አማልክት አብጅልን፤* ሙሴ በሲና ተራራ ላይ ሕግን በሚቀበልበት ጊዜ፣ ሕዝቡ እግዚአብሔርንና ሙሴን ትተው ከወርቅ የጥጃ ምስል ሠሩ (ዘፀ 32፡1):: በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ከግብፅ ባዕድ አምልኮ አልተላቀቁም ነበር::

7፥42 *እግዚአብሔር...አሳልፎ ሰጣቸው፤* የሮሜ 1፥24 ማብ ይመ::

*7፥43፤* እስጢፋኖስ ይህን የሚጠቅሰው በሰብዓ ሊቃናት ከተተረጐመው የትንቢተ አሞጽ መጽሐፍ ወስዶ ነው (አሞ5፥25-27)፤ ልዩነቱ ደማስቆ የሚለውን ቃል በባቢሎን መተካቱ ነው፤ ይኸውም እስራኤላውያን ከተሰፋዪቱ አገር ለመጨረሻ ጊዜ የተማረኩት በባቢሎናውያን መሆኑን ለማመልከት ነው አሞፅ (የተናገረው ግን የሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት መጀመሪያ በምርኮ የተጋዘው በአሦራውያን መሆኑን ነው)::

7፥44-50፤ እስጢፋኖስ “*በተቀደሰው ስፍራና በሕጉ ላይ የስድብ ቃል መናገሩ*” (6፥13) ተብሎ ስለ ተከሰሰ፣ ይህንኑ በማውሣት ትረካውን ይደመድማል:: እዚህ ላይ እስጢፋኖስ ሊሰብክ የፈለ ገው እግዚአብሔር ከእንግዲህ በሕዝቡ መካከል (እንዲሁም በአሕዛብ ሁሉ መካከል ማር 11፥17) የሚገኘው በቤተ መቅደስ አማካይነት ሳይሆን፣ ከሙታን በተነሣው በክርስቶስ አማካይነት መሆ ኑን ለማመልከት ሳይሆን አይቀርም::

7፥44 *የተሠራችው የምስክር ድንኳን፤* እስጢፋኖስ ይህን ያለው በምስክሩ ድንኳን ውስጥ ታቦቱና ሁለቱ ጽላቶች ስለ ነበሩ ነው፤ እነዚህም “ምስክር” ተብለው ይጠሩ ነበር (ዘፀ 25፥16-21 ይመ)::

45አባቶቻችንም ድንኳንዋን ከተቀበሉ በኋላ፣
እግዚአብሔር በኢያሱ መሪነት ያሳደዳቸውን
የአሕዛብን አገር በወረሱ ጊዜ ይዘዋት ገቡ፤
እስከ ዳዊትም ዘመን ድረስ በምድሪቱ ተቀ
መጠች፤ 46ዳዊትም በእግዚአብሔር ፊት
ሞገስ በማግኘቱ ለያዕቆብ[1] አምላክ ማደሪያ
ያዘጋጅ ዘንድ ለመነ፤ 47ነገር ግን የማደ
ሪያውን ቤት የሠራለት ሰሎሞን ነበር።
48"ይሁን እንጂ፣ ልዑል የሰው እጅ በሠ
ራው ቤት ውስጥ አይኖርም፤ ይህም ነቢዩ
እንዲህ ባለው መሠረት ነው፤

49"ሰማይ ዙፋኔ ነው፤
ምድርም የእግሬ ማሳረፊያ ናት፤
ታዲያ ምን ዐይነት ቤት ትሠሩልኛላችሁ?
ይላል ጌታ፤
ወይንስ ማረፊያ የሚሆነኝ የትኛው ቦታ
ነው?
50ይህን ሁሉ የሠራው እጄ አይደለምን?'

51"እናንት ልባችሁና ጆሮአችሁ ያልተገረዘ፣
አንገተ ደንዳኖች! ልክ እንደ አባቶቻችሁ
መንፈስ ቅዱስን ሁል ጊዜ ትቃወማላችሁ።
52ከነቢያት መካከል አባቶቻችሁ ያላሳደዱት
ማን አለ? የጻድቁን መምጣት አስቀድመው
የተናገሩትን እንኳ ገድለዋል፤ እናንተም አሁን
አሳልፋችሁ ሰጣችሁት፤ ገደላችሁትም፤
53በመላእክት አማካይነት የተሰጣችሁንም ሕግ
ተቀበላችሁ እንጂ አልጠበቃችሁትም።"

## የእስጢፋኖስ መወገር

54በሸንጎው ስብሰባ ላይ የነበሩትም ይህን
በሰሙ ጊዜ እጅግ ተቈጡ፤ ጥርሳቸውንም
አፋጩበት። 55እስጢፋኖስ ግን በመንፈስ
ቅዱስ ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኵር ብሎ ሲመ
ለከት፣ የእግዚአብሔርን ክብር፣ እንዲሁም ኢየሱስ
በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና፣ 56"እነሆ፤ ሰማ
ያት ተከፍተው፣ የሰው ልጅም በእግዚአ
ብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ" አለ።
57በዚህ ጊዜ በታላቅ ድምፅ እየጮኹ
ጆሮአቸውን ደፍነው እርሱ ወደ አለበት
በአንድነት ሮጡ፤ 58ይዘውም ከከተማው
ውጭ ጣሉት፤ በድንጋይም ይወግሩት
ጀመር። ይህ በሚሆንበት ጊዜ በዚያ የነ
በሩ ምስክሮችም ልብሳቸውን ሳውል በተ
ባለ ጕልማሳ እግር አጠገብ አስቀመጡ።
59እስጢፋኖስም እየወገሩት ሳለ፣ "ጌታ ኢየ
ሱስ ሆይ፤ ነፍሴን ተቀበላት" ብሎ ጸለየ፤ 60ከዚ
ያም ተንበርክኮ፤ በታላቅ ድምፅ፣ "ጌታ ሆይ!
ይህን ኀጢአት አትቍጠርባቸው" ብሎ ጮኸ፤
ይህን ካለ በኋላም አንቀላፋ።

8ሳውልም በእስጢፋኖስ መገደል ተስማ
ምቶ ነበር።

## የአማኞች መሰደድና መበተን

በዚያ ቀን በኢየሩሳሌም በነበረችው ቤተ
ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ተነሣ፤ ከሐዋ
ርያትም በስተቀር አማኞች በሙሉ በይሁ
ዳና በሰማርያ አውራጃዎች ሁሉ ተበተኑ፤
2በመንፈሳዊ ነገር የተጉ ሰዎችም እስጢፋ
ኖስን ቀበሩት፤ ደግሞም እጅግ አለቀሱ
ለት። 3ሳውል ግን ቤተ ክርስቲያንን ለማ
ጥፋት ታጥቆ ተነሣ፤ ከቤት ወደ ቤት በመ
ግባትም ወንዶችንና ሴቶችን ጐትቶ እያ
ወጣ ወህኒ ቤት ያስገባቸው ነበር።

## ፊልጶስ በሰማርያ

4የተበተኑትም በሄዱበት ሁሉ ቃሉን ሰበ
ኩ፤ 5ፊልጶስም ወደ አንዲት የሰማርያ ከተማ
ወርዶ ክርስቶስን[1] ሰበከላቸው። 6ብዙ ሕዝ
ብም ፊልጶስ የተናገረውን ሲሰሙና ያደረገ
ውንም ታምራዊ ምልክቶች ሲያዩ፣ አንድ
ልብ ሆነው ያዳምጡት ነበር። 7ርኩሳን[1]
መናፍስትም እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ወጡ፤
ብዙ ሽባዎችና አንካሶችም ተፈወሱ፤ 8ከዚህ
የተነሣም በከተማዪቱ ታላቅ ደስታ ሆነ።

7፥45 ኢያ3፥14-17፤ 18፥1፤23፥9፤24፥18፤2 ሳሙ7፥2፡6፤መዝ44፥2
7፥46 2ሳሙ7፥8-16፤ 1ነገ8፥17፤መዝ132፥1-5
7፥47 1ነገ6፥1-38
7፥48 1ነገ8፥27፤ 2ዜና2፥6፤ማር5፥7
7፥49 ማቴ5፥34፡35
7፥50 ኢሳ66፥1፡2
7፥51 ዘፀ32፥9፤ 33፥3፡5፤ዘሌ26፥41፤ ዘዳ10፥16፤ኤር4፥4፤ 9፥26
7፥52 ማቴ5፥12፤ ሐሥ3፥14፤1ተሰ2፥15
7፥53 ቍ38፤ገላ 3፥19፤ዕብ2፥2
7፥54 ሐሥ5፥33
7፥55 ማር16፥19፤ ሉቃ1፥15
7፥56 ማቴ3፥16፤ 8፥20
7፥58 ዘሌ24፥14፡ 16፤ዘዳ17፥7፤ሉቃ4፥2 9፤ሐሥ8፥1፤22፥20
7፥59 መዝ31፥5፤ ሉቃ23፥46
7፥60 ማቴ5፥44፤ 9፥24፤ሉቃ22፥41፤ ሐሥ9፥40
8፥1 ቍ4፤ሐሥ7፥58፤ 9፥31፤11፥19
8፥3 ሐሥ7፥58፤ 9፥1፡13፡21፤22፥4፡19፤ 26፥10፡11፤1ቆሮ15፥9፤ ገላ1፥13፡23፤ፊል3፥6፤ 1ጢሞ1፥13
8፥4 ቍ1፤ሐሥ 15፥35
8፥5 ሐሥ6፥5፤21፥8
8፥7 ማቴ4፥24፤ማር 16፥17

[1]46 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *የያዕቆብ ቤት* ይላሉ።
[1]5 ወይም *መሲሕ*
[1]7 ወይም *ክፉ*

*7፥49፤* ኢሳይያስ ፍጥረት ሁሉ እግዚአብሔር የሠራው ቤተ መቅደስ መሆኑን ለእስራኤላውያን አስገንዝቦአል፤ እስጢፋኖስም ይህን ቃል በማውሣት፣ እግዚአብሔር በመጨረሻ የራሱን ቤተ መቅደስ እንደሚሠራ ያሳስባቸዋል።

7፥51 *ልባችሁና ጆሮአችሁ ያልተገረዘ* በሥጋ የተገረዙ ቢሆኑም እንኳ ተግባራቸው በዙሪያቸው እንዳሉት እንዳልተገረዙ አሕዛብ ነበር፤ ልባቸው ለጌታ ክብር አልተገረዘም፤ ተለይተውም አልተቀደሱለትም።

7፥53 *በመላእክት አማካይነት የተሰጣችሁንም ሕግ፤* የቍ38 ማብ ይመ።

7፥55 *በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፤* የ2፥4 ማብ ይመ፤ እንዲሁም 6፥5 ይመ።

7፥56 *የሰው ልጅም፤* የማር 8፥31 ማብ ይመ። ስለ መሲሑ የተተነበየውን (ማቴ25፥31፤ ዳን7፥13-14) አበክሮ ለማሳየት፣ ኢየሱስ ራሱን በዚህ ስም ይጠራል (ማር2፥10 ይመ)። ኢየሱስ ራሱን በዚህ ስም ከመጥራቱ በስተቀር፣ በዚህ ስም የጠራው ሌላ ሰው አልነበረም፤ እስጢፋኖስ በዚህ ስም መጥራቱም ያልተለመደ ነው (ራዕ1፥13 ይመ)።

7፥58 *ልብሳቸውን ሳውል...እግር አጠገብ አስቀምጠው፤* አንዳንዶች ከዚህ በመነሣት ሳውልን የግድያው አቀነባባሪ አድርገው ይቈጥራሉ፤ ያም ሆነ ይህ ሉቃስ በመጽሐፉ ሁለተኛ ክፍል ላይ ዋና ባለ ታሪክ የሆነውን ጳውሎስን የሚያቀርበው በዚህ መልክ ነው።

7፥60 *ይህን ኀጢአት አትቍጠርባቸው፤* ኢየሱስ በሉቃ 23፥34 ከተናገረው ቃል ጋር ያነጻጽሩ።

8፥1 *ተስማምቶ ነበር፤* 22፥20 ይመ። *ከሐዋርያትም በስተቀር... በሙሉ፤* ሐዋርያት በኢየሩሳሌም መቈየታቸው ለታሰሩት መጽናኛ ለተበታተኑትም አለኝታ ነበር። በዚህ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውስጡን መሥራት ጀመረች። በይሁዳና በሰማርያ አውራጃዎች ሁሉ ተበተኑ፤ በ1፥8 ላይ የተሰጠው ተልእኮ መፈጸም ሲጀመር ይታያል፤ ይህም የተከናወነው ቤተ ክርስቲያን ሆን ብላ ባቀደችው መሠረት ሳይሆን፣ ከአማኞች ቍጥጥር ውጭ ባለ ሁኔታ ነበር።

8፥3 *ለማጥፋት...ተነሣ ፤* 22፥4 ይመ። ይህ ሐረግ በግሪክ ቋንቋ እንደ ዱር አራዊት እንክት አድርጎ መብላትን ሊያመለክት ይችላል።

8፥4 *ቃሉን ሰበኩ፤* ብዙ ምስክሮች የምሥራቹን ቃል በየአገሩ እየሰበኩ ሄዱ። የምስክሮቹ ቍጥር ዕጥፍ ድርብ እየሆነ፣ ወንጌል የሚሠራጭበትም ወሰን እየሰፋ ሄደ (ከ11፥19-20 ጋር ያነጻጽሩ)።

8፥5 *ፊልጶስም፤* በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ ነበር (6፥5)፤ በዚህ ጊዜ ግን ስለ ክርስቶስ ስለ መሲሑ የሚመሰክር ወንጌላዊ ሆነ። እንዲሁም 21፥8 ይመ። ፊልጶስ በየአገሩ ከተበተኑት አንዱ ምሳሌ ነው። *ወደ አንዲት የሰማርያ ከተማ፤* አንዳንድ ቅጆች "የሰማርያ ከተማ" ይላሉ፤ ይኸውም የቀድሞዋን ዋና ከተማ ሰማርያን ለማመልከት ነው፤ ይህችውም በኋላ ሰባስቲ ወይም ኒአጶሊስ ተብላለች፤ በአሁኑ ጊዜ ግን ናብሉስ ትባላለች።

## ጠንቋዩ ሲሞን

[9]ነገር ግን ከዚህ ቀደም ሲል በከተማዪቱ
ውስጥ እየጠንቈለ የሰማርያን ሰዎች ሁሉ
ያስገረመ፣ ሲሞን የሚሉት አንድ ሰው
ነበር፤ እርሱም ራሱን እንደ ታላቅ ሰው
ይቈጥር ነበር። [10]ከታናሽ እስከ ታላቅ
ያለው ሰው ሁሉ፣ "ይህ ሰው 'ታላቁ ኀይል'
በመባል የሚታወቀው መለኮታዊ ኀይል ነው"
በማለት ከልብ ያዳምጡት ነበር፤ [11]ከብዙ ጊዜ
ጀምሮ በጥንቈላ ሥራው ስላስገረማቸውም
ትኵረት ሰጥተው ይከተሉት ነበር። [12]ነገር
ግን ፊልጶስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ
ኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሰበከላቸውን አምነው
በመቀበላቸው ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ፤
[13]ራሱ ሲሞን እንኳ ሳይቀር አምኖ ተጠመቀ፤
ፊልጶስንም ተከትሎ ሄደ፤ የሚደረገውን ምል
ክትና ታላቅ ታምራት አይቶም ተገረመ።
[14]በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማ
ርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል መቀበላ
ቸውን በሰሙ ጊዜ፣ ጴጥሮስንና ዮሐንስን
ወደ እነርሱ ላኳቸው። [15]እነርሱም ሰማርያ
በደረሱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ
ለሰማርያ ሰዎች ጸለዩላቸው፤ [16]ምክንያቱም
በዚያን ጊዜ በጌታ ኢየሱስ ስም ተጠምቀው
ነበር እንጂ ገና መንፈስ ቅዱስ በአንዳቸ
ውም ላይ አልወረደም ነበር። [17]ስለዚህ ጴጥሮ
ስና ዮሐንስ እጃቸውን ጫኑባቸው፤ እነርሱም
መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ።
[18]ሲሞንም ሐዋርያት እጃቸውን በሚጭ
ኑበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ አይቶ፣
ገንዘብ አመጣላቸውና እንዲህ አላቸው፤

8፥9 ሐሥ5፥36፤ 13፥6
8፥10 ሐሥ14፥11፤ 28፥6
8፥12 ማቴ3፥2፤ ሐሥ 2፥38
8፥13 ቊ6፤ ሐሥ 19፥11
8፥14 ቊ1፤ ሉቃ 22፥8፤ዕብ4፥12
8፥15 ዮሐ20፥22
8፥16 ማቴ28፥19፤ ሐሥ2፥38፤10፥44፤ 19፥2
8፥17 ዮሐ20፥22፤ ሐሥ6፥6

8፥9 *ሲሞን* በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ጽሑፍ፣ "አስማተኛው" (ሲሞን ማጉስ) ቀንደኛ መናፍቅና ኖስቲክ ለተባለው የኑፋቄ ትምህርት "አባት" መሆኑ ተገልጿል።

8፥10 *ታላቁ ኀይል*፤ ሲሞን እኔ አምላክ ነኝ ብሎአል ወይም ራሱን እንደ ዋና የእግዚአብሔር እንደ ራሲ አድርጎ ቈጥሮአል።


8፥13 *ራሱ ሲሞን እንኳ...አምኖ ተጠመቀ*፤ የሲሞን እምነት ከልብ መሆኑን ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። ሉቃስ፣ ሲሞን አመነ ይበል እንጂ፣ ጴጥሮስ የሲሞን ልብ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል እንዳልሆነና በሐዋርያት አገልግሎት ተካፋይነት እንደማይኖረው በመናገሩ (ቊ21) እውነተኛ አማኝ መሆኑ ያጠራጥራል።

8፥14 *የእግዚአብሔርን ቃል መቀበላቸውን*፤ እነዚህ የሰማርያ ሰዎች ፊልጶስ ለሰበከላቸው ወንጌል ታዛዦች ሆኑ። *ጴጥሮስንና ዮሐንስን...ላኳቸው*፤ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ሥርጭቱን፣ ጥረት እንዲሁም በየቦታው የተመሠረቱትን ማኅበረ ምዕመናን መንከባከብና መጠበቅን ሥራዬ ብላ ያዘችው (11፥22 ይመ)።

8፥16 *ገና...በአንዳቸውም ላይ አልወረደም ነበር*፤ ከጴንጤቆስጤ ቀን ጀምሮ፤ "የኢየሱስ ክርስቶስ የሆኑት ሁሉ" (ሮሜ 8፥9) መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል። የሰማርያ ክርስቲያኖች ገና መንፈስ ቅዱስን ስላልተቀበሉ ከመሞላት ጋር የሚሰጠውን ስጦታውን አላገኙም ነበር፤ ሆኖም የጐደላቸው በዚህ ጊዜ ተሟላላቸው ( ቊ17 ይመ)።

8፥17 *እጃቸውን ጫኑባቸው*፤ ቊ18፤19፥1-7 ይመ፤ ከ2ጢሞ 1፥6 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም የ6፥6 ማብ ይመ።

8፥18 *ገንዘብ አመጣላቸውና*፤ ቀደም ሲል ሲሞን ኀይል አለኝ ብሎ ይኵራራ ነበር (ቊ10 እና ማብ ይመ)፤ አሁን ደግሞ ሐዋርያት የአስማት ኀይል ያላቸው ስለ መሰለው፣ ይህን ኀይል በገንዘብ ለመግዛት ሞከረ።



[19]“እጄን የምጭንበት ሰው ሁሉ መንፈስ
ቅዱስን እንዲቀበል ይህን ሥልጣን ለእኔም
ስጡኝ::”
[20]ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው፤ “የእግዚአ
ብሔርን ስጦታ በገንዘብ ለመግዛት አስበሃልና፣
አንተም ገንዘብህም አብራችሁ ጥፉ! [21]ልብህ
በእግዚአብሔር ፊት ቅን ስላልሆነ፣ አንተ በዚህ
አገልግሎት ድርሻ ወይም ዕድል ፈንታ የለ
ህም:: [22]አሁንም ስለዚህ ክፋትህ ንስሐ ግባ፤
ወደ ጌታም ጸልይ፤ ምናልባት ይህን የልብህን
ሐሳብ ይቅር ይልህ ይሆናል፤ [23]ምክንያቱም
በመራራነት ተሞልተህ፣ በዐመፅ ሰንሰለት
ተይዘህ አይሃለሁና::”
[24]ሲሞንም መልሶ፣ “ከተናገራችሁት ምንም
ነገር እንዳይደርስብኝ ጌታን ለምኑልኝ” አላቸው::
[25]ጴጥሮስና ዮሐንስም የጌታን ቃል ከመሰ
ከሩና ገልጠው ከተናገሩ በኋላ፣ በብዙ የሰ
ማርያ መንደሮች ወንጌልን እየሰበኩ፣ ወደ
ኢየሩሳሌም ተመለሱ::

## ፊልጶስና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ

[26]የጌታም መልአክ ፊልጶስን፣ “ተነሥተህ
በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ በሚ
ያወርደው በምድረ በዳው መንገድ ሂድ”
አለው፤ [27]እርሱም ተነሥቶ ሄደ:: እነሆ የኢ
ትዮጲያ ንግሥት የህንደኬ ባለሟልና የሀ
ብት ንብረቷ ሁሉ አዛዥ የሆነ አንድ ኢት
ዮጵያዊ ጃንደረባ አገኘ:: ይህም ሰው ሊሰ
ግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር:: [28]ሲመለ
ስም በሠረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን
መጽሐፍ ያነብ ነበር:: [29]መንፈስም ፊልጶስን፣
“ሂድ፤ ወደዚህ ሠረገላ ቅረብ” አለው::
[30]ፊልጶስም ፈጥኖ ወደ ሠረገላው ሄደ፤
ጃንደረባውም የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ
ሲያነብ ሰምቶ፣ “ለመሆኑ፣ የምታነበውን
ታስተውለዋለህን?” አለው::
[31]ጃንደረባውም፣ “የሚያስረዳኝ ሰው ሳይ
ኖር እንዴት አድርጌ አስተውላለሁ” አለው፤
እርሱም ወደ ሠረገላው ወጥቶ አብሮት እን
ዲቀመጥ ፊልጶስን ለመነው::
[32]ጃንደረባው ያነብ የነበረው የመጽሐፍ
ክፍል ይህ ነበር፤

“እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፤
የበግ ጠቦት በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል፣
እንዲሁ አፉን አልከፈተም::
[33]ራሱን በማዋረዱም ፍትሕን ተነፈገ፤
ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና፣
ስለ ትውልዱ ማን ሊናገር ይችላል?”

[34]ጃንደረባውም መልሶ ፊልጶስን፣ “ነቢዩ
ይህን የሚናገረው ስለ ማን ነው? ስለ ራሱ
ነው፣ ወይስ ስለ ሌላ ሰው? እባክህ ንገረኝ”
አለው:: [35]ፊልጶስም አፉን ከፈተ፤ ከዚሁም
መጽሐፍ ክፍል ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌል
ሰበከለት::
[36]በመንገዝ ላይ ሳሉም ውሃ ካለበት ስፍራ
ደረሱ፤ ጃንደረባውም፣ “እነሆ፤ ውሃ እዚህ
አለ፤ ታዲያ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ
ምን ነገር አለ?” አለው:: [37]ፊልጶስም፣ “በፍ
ጹም ልብህ ካመንህ መጠመቅ ትችላለህ” አለው::
ጃንደረባውም፣ “ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚ
አብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ” ሲል
መለሰለት፤ [38]ሠረገላውም እንዲቆም አዘዘ::
ከዚያም ሁለቱ አብረው ወደ ውሃው ወረዱ፤
ፊልጶስም ጃንደረባውን አጠመቀው::[a] [39]ከውሃ
ውም በወጡ ጊዜ፣ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን
ነጥቆ ወሰደው፤ ጃንደረባውም ከዚህ በኋላ
አላየውም፤ ሆኖም ደስ እያለውም ጕዞውን
ቀጠለ:: [40]ከዚያ በኋላ ግን ፊልጶስ በአዛጦን
ታየ፤ ቂሳሪያም እስኪደርስ ድረስ፣ በሚያልፍ
ባቸው ከተሞች ሁሉ ወንጌልን ይሰብክ ነበር::

## የሳውል ማመን

9:1-19ተጓ ምብ-ሐሥ22:3-16፤26:9-18

9 ሳውል ግን የጌታን ደቀ መዛሙርት
ለመግደል አሁንም እየዛተ ወደ ሊቀ ካህ

[a]38 አንዳንድ ቅጆች ይህን ቍጥር አይጨምሩም:: ከአንዳንድ የቅርብ ጊዜ ቅጆች የተወሰደ ነው::

8፥20 2ነገ5፥16፤ ዳን5፥17፤ማቴ10፥8፤ ሐሥ2፥38
8፥21 ነሀ2፥20፤ መዝ78፥37
8፥22 ሐሥ2፥38
8፥24 ዘፀ8፥8፤ዘኍ 21፥7፤1ነገ13፥6፤ኤር 42፥2
8፥25 ቍ40፤ሐሥ 13፥48
8፥26 ሐሥ5፥19፤ 6፥5
8፥27 1ነገ8፥41-43፤ መዝ68፥31፤87፥4፤ኢሳ 56፥3-5፤ሶፎ3፥10፤ ዮሐ 12፥20
8፥29 ሐሥ10፥19፤ 11፥12፤13፥2፤20፥23 ፤21፥11
8፥33 ኢሳ53፥7:8
8፥35 ማቴ5፥2፤ ሉቃ 24፥27፤ ሐሥ13፥32፤ 17፥2፤18፥28፤28፥23
8፥36 ሐሥ2፥38፤ 10፥47
8፥39 1ነገ18፥12፤ 2ነገ2፥16፤ሕዝ3፥12: 14፤8፥3፤11፥1:24፤43፥5፤ 2ቆሮ12፥2፤1ተሰ4፥17፤ ራእ12፥5
8፥40 ቍ25፤ሐሥ 10፥1:24፤12፥19፤ 21፥8:16፤23፥23:33፤ 25፥1:4:6:13
9፥1 ሐሥ8፥3

8፥23 *በመራራነት ተሞልተህ፤* ዘዳ 29፥18 ይመ::

8፥26 *የጌታም መልአክ፤* ከቍ29 ጋር ያነጻጽሩ፤ የ5፥19 ማብ ይመ:: ከኢየሩሳሌም እስከ ጋዛ ያለው ርቀት 80 ኪ.ሜ. ያህል ነው::

8፥27 *አንድ ኢትዮጵያዊ፤* በዚያ ዘመን የኢትዮጲያ ግዛት ከላይኛው ዐባይ ጀምሮ እስከ ካርቱም ድረስ ያለውን የኑብያን ምድር የሚያጠቃልል ነበር:: *ህንደኬ፤* በዚያ ዘመን ንጉሡ እንደ አንድ ቅዱስ ይታይ ስለነበር፣ ማናቸውንም የመንግሥቱን አስ ተዳደር የምታከናውነው እናቱ ስለ ነበረች፣ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ወግ መሠረት የምትጠራበት የማዕረግ ስም ነው:: *ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር፤* ሙሉ በሙሉ ወደ አይሁድ ሃይማኖት የገባ የአሕዛብ ወገን ባይሆንም (ዘፀ 23፥1)፣ ኢትዮጵያዊው እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበር፤ እንዲሁም የዘዳ 23፥1 ማብ ይመ::

8፥30 *ሲያነብ ሰምቶ፤* ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብ የተለመደ ነበር::

8፥34 *ነቢዩ ይህን የሚናገረው ስለ ማን ነው?* ፊልጶስ በኢሳ 53 ላይ ሥቃይ ስለሚቀበለው አገልጋይ የተጻፈውን ለኢትዮጵያዊው ያብራራለት፣ በኢሳ 11 ላይ ከሚገኘው ከዳዊት ዘር ከሆነው መሲሕ ጋር ወይም ዳን 7፥13-14 ላይ ካለው “የሰው ልጅ” ከተባለው ጋር አገናዝቦ ሳይሆን አይቀርም::

8፥35 *ወንጌል፤* በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ድነት የሚገኝበት መንገድ ነው::

8፥36 *ውሃ ካለበት ስፍራ ደረሱ፤* ከሚከተሉት ቦታዎች አንዱን ሊያመለክት ይችላል፤ ዳዊት ጎልያድን ሊገጥም ቡተሻገረው (1ሳሙ 17፥40) በዔላ ሸለቆ ያለ አነስተኛ ወንዝ፣ ከጋዛ በስተሰሜን የሚገኘው የኤልሐሲ ደረቅ ወንዝ ወይም በዚያ አካባቢ ከሚገኙ ኵሬዎች አንዱ ሊሆን ይችላል::

8፥39 *ደስ እያለውም፤* በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ደስታ ከድነት ጋር የተያያዘ ነው (የ16፥34 ማብ ይመ)::

8፥40 *በአዛጦን፤* በብሉይ ኪዳን አሽዶድ ትባላለች (1ሳሙ 5፥1)፤ በፍልስጥኤም አገር ከሚገኙት አምስት ከተሞች አንዷ ነበረች:: ከጋዛ 30 ኪ.ሜ.፣ ከቂሳርያም 96 ኪ.ሜ. ያህል ርቃ ትገኛለች:: *ቂሳርያ፤* እንደገና የተሠራችው በንጉሥ ሄሮድስ ሲሆን ውብ የወደብ ከተማ ነበረች:: ይህች ከተማ የሮማ ገዦች መቀመጫ ነበረች:: የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ስለ ፊልጶስ የሚተርከውን ለጊዜው ከዚህ ላይ ያበቃል፤ ከዚያም ሃያ ዓመት ካለፈ በኋላ በዚሁ ቦታ እንደገና እናገኘዋለን (21፥8)::

9፥1 *ሳውል፤* ማንነቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጸው እስጢፋኖስ በድንጋይ በሚወገርበት ጊዜ ነው (7፥58)፤ በጠርሴስ ተወለደ፤ መምህሩም ገማልያል ነበር (22፥3)፤ የፊል 3፥4-14 ማብ ይመ:: *ለመግደል አሁንም እየዛተ… ሄደ፤* ሳውል ከእስጢፋኖስ ደም በስተቀር እጁን በሌላ ደም ስለማስገባቱ በግልጽ የሚታወቅ ነገር የለም (8፥1)፤ ይሁን እንጂ በሌሎችም ደም እጁን ያስገባ የሚያስመስለው ሁኔታ አለ (22፥4፤ 26፥10):: *ሊቀ ካህናቱን፤* ቀያፋ ሊሆን ይችላል

ናቱ ሄደ፤ 2የጌታን መንገድ የሚከተሉትን
ወንዶችንም ሆኑ ሴቶችን በዚያ ካገኘ አስሮ
ወደ ኢየሩሳሌም ለመውሰድ እንዲችል፣ በደ
ማስቆ ለነበሩት ምኵራቦች ደብዳቤ እንዲ
ሰጠው ሊቀ ካህናቱን ለመነው:: 3ደማስቆ
ለመድረስ ጥቂት ሲቀረው ብርሃን ከሰ
ማይ ድንገት በዙሪያው አንጸባረቀበት፣
4እርሱም በምድር ላይ ወደቀ፤ በዚያ ጊዜም
"ሳውል፤ ሳውል፤ ለምን ታሳድደኛለህ?" የሚል
ድምፅ ሰማ።
5ሳውልም፣ "ጌታ ሆይ፤ አንተ ማን ነህ?"
አለው::
እርሱም እንዲህ አለው፤ "እኔማ አንተ
የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ:: 6አሁንም ተነ
ሥተህ ወደ ከተማዪቱ ግባ፤ ማድረግ የሚገ
ባህም ይነገርሃል::"
7ከሳውል ጋር ይጓዙ የነበሩትም ሰዎች
ድምፁን እየሰሙ ማንንም ባላዩ ጊዜ፣ አፋ
ቸውን ይዘው ቆሙ:: 8ሳውልም ከወደቀ
በት ተነሥቶ ዐይኑን ሲገልጥ ምንም ማየት
አልቻለም፤ ስለዚህ ሰዎቹ እጁን ይዘው እየ
መሩ ወደ ደማስቆ አስገቡት:: 9ሦስት ቀንም
ታወረ፤ እህል ውሃም አልቀመሰም::
10በደማስቆ ሐናንያ የሚባል አንድ ደቀ
መዝሙር ነበር፤ ጌታም በራእይ፣ "ሐናንያ!"
ብሎ ጠራው::
እርሱም፣ "ጌታ ሆይ፤ እነሆኝ" አለ::
11ጌታም እንዲህ አለው፤ "ተነሣና 'ቀጥተኛ
ጐዳና' በተባለው መንገድ ይሁዳ ወደ ተባለ
ሰው ቤት ሂድ፤ እዚያም ሳውል የሚባል አንድ
የጠርሴስ ሰው እየጸለየ ነውና ፈልገው፤
12ምክንያቱም ሐናንያ የሚባል ሰው እርሱ
ወዳለበት መጥቶ እጁን እንደሚጭንበትና
ዐይኑ እንደሚበራለት በራእይ አይቶአል::"
13ሐናንያም መልሶ እንዲህ አለው፤ "ጌታ
ሆይ፤ ይህ ሰው እኮ በኢየሩሳሌም ባሉ ቅዱ
ሳንህ ላይ ምን ያህል ጒዳት እንዳደረሰ ከብዙ
ሰው ሰምቻለሁ፤ 14ወደዚህም የመጣው ስም
ህን የሚጠሩትን ሁሉ ለማሰር ከካህናት
አለቆች ሥልጣን ተቀብሎ ነው::"
15ጌታም እንዲህ አለው፤ "ሂድ፤ ይህ ሰው
በአሕዛብና በነገሥታት ፊት እንዲሁም በእስ
ራኤል ሕዝብ ፊት ስሜን እንዲሸከም የተ
መረጠ ዕቃዬ ነው፤ 16እኔም ስለ ስሜ ምን
ያህል መከራ መቀበል እንዳለበት አሳየዋለሁ::"
17ሐናንያ ሄደ፤ ወደተባለውም ቤት ገባ፤
በሳውልም ላይ እጁን ጭኖ፣ "ወንድሜ ሳውል
ሆይ፤ ወደዚህ ስትመጣ በመንገድ ላይ የተ
ገለጠልህ ጌታ ኢየሱስ፣ ዐይንህ እንዲበራና፣
በመንፈስ ቅዱስም እንድትሞላ እኔን ልኮ
ኛል" አለው:: 18ወዲያውም ከሳውል ዐይን
ላይ ቅርፊት የመሰለ ነገር ወደቀ፤ እንደ
ገና ማየት ቻለ፤ ተነሥቶም ተጠመቀ፤ 19ምግ
ብም በልቶ በረታ::

## ሳውል በደማስቆና በኢየሩሳሌም

ሳውል በደማስቆ ከነበሩት ደቀ መዛ
ሙርት ጋር አያሌ ቀን ተቀመጠ:: 20ወዲ
ያውም፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆ
ኑን በየምኵራቦቹ መስበክ ጀመረ:: 21የሰሙ
ትም ሁሉ በመገረም፣ ይህ ሰው "በኢየሩ
ሳሌም ይህን ስም የሚጠሩትን ሲያጠፋ የነ
በረ አይደለምን? ደግሞም ወደዚህ የመ
ጣው እነርሱን አስሮ ወደ ካህናት አለቆች
ሊወስዳቸው አልነበረምን?" አሉ:: 22ሳውል ግን
እየበረታ ሄደ፤ በደማስቆ ለሚኖሩትም አይሁድ
ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ[ከ] መሆኑን ማስረጃ
እያቀረበ አፋቸውን ያስይዛቸው ነበር::

[ከ]22 ወይም መሲሕ

9፥2 ኢሳ17፥11፤ ኤር49፥23፤ሐሥ 19፥9:23፤22፥4፤24፥14:22
9፥3 1ቆሮ15፥8
9፥4 ኢሳ6፥8
9፥6 ቍ16፤ሕዝ 3፥22
9፥7 ዳን10፥7፤ ዮሐ 12፥29
9፥8 ቍ18
9፥10 ሐሥ10፥3:17:19፤12፥9፤16፥9:10፤18፥9
9፥11 ቍ30፤ሐሥ 11፥25፤21፥39፤22፥3
9፥12 ማር5፥23
9፥13 ቍ32፤ሐሥ 8፥3፤26፥10፤ሮሜ1፥7፤15፥25:26:31፤16፥2:15፤ኤፌ1፥1፤ፊል1፥1
9፥14 ቍ2:21፤ሐሥ 2፥21
9፥15 ሐሥ13፥2፤25፥22:23፤26፥1፤ሮሜ 1፥1፤11፥13፤15፥15:16፤ገላ1፥15:16፤2፥7:8፤1ጢሞ1፥12
9፥16 ሐሥ20፥23፤21፥11፤2ቆሮ6፥4-10፤11፥23-27፤2ጢሞ 1፥8፤2፥3:9
9፥17 ሉቃ1፥15፤ሐሥ 6፥6
9፥18 ሐሥ2፥38
9፥19 ሐሥ11፥26፤26፥20
9፥20 ማቴ4፥3፤ሐሥ 13፥5:14፤14፥1፤17፥2:10:17፤18፥4:19፤19፥8
9፥21 ቍ14፤ሐሥ 8፥3
9፥22 ሉቃ2፥11፤ሐሥ 5፥42፤17፥3፤18፥5:28

(የ4፥6 ማብ ይመ) ወይም በይሁዳና በሌሎች አውራጃዎች በሚኖሩት አይሁድ ላይ ሥልጣን የነበራቸው የሸንጎ አባላት ሊሆኑ ይችላሉ::

9፥2 *የጌታን መንገድ*፤ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በተደጋጋሚ የተገለጸው ክርስትና በዚህ ስም ይታወቃል (16፥17፤ 18፥25-26፤ 19፥9:23፤ 22፥4፤ 24፥14:22፤2ጴጥ 2፥2 ይመ):: ጌታ ኢየሱስ እኔ "መንገድ" ነኝ ብሎአል (ዮሐ 14፥6):: *አስሮ ወደ ኢየሩሳሌም*፤ ሸንጎው ከፍተኛ ሥልጣኑን ተግባራዊ የሚያደርግባት ከተማ ስትሆን፣ በነጻ የመልቀቅ ወይም የይሙት በቃ ፍርድ ይፈረድ የነበረው በዚችው ከተማ ነበር:: *በደማስቆ*፤ በሮማ ግዛት በሶርያ አውራጃ የምትገኝ ከተማ ናት፤ ከፓሌስቲና ውጭ ካሉት ዋና ዋና ከተሞች ይልቅ ለአይሁድ ምድር በጣም ቅርብ ነበረች:: ከፍ ያለ ቍጥር ያላቸው አይሁድ በውስጧ ይኖሩ ነበር:: ከኢየሩሳሌም እስከ ደማስቆ ያለው ርቀት 240 ኪ.ሜ ያህል ሲሆን፣ የአራት ወይም የስድስት ቀን መንገድ ነው::

9፥3 *ብርሃን ከሰማይ*፤ ጊዜው እኩለ ቀን ገደማ ነበር (26፥13)::

9፥4 *ለምን ታሳድደኛለህ?* ቤተ ክርስቲያንን ማሳደድ ማለት ክርስቶስን ማሳደድ ነው፤ ቤተክርስቲያን አካሉ ናትና (1ቆሮ 12፥27፤ ኤፌ 1፥22-23 ይመ)::

9፥5 *ጌታ ሆይ፤ አንተ ማን ነህ?* በአይሁድ መምህራን ወግና ልማድ መሠረት እንደዚህ ያለው ድምፅ ከሰማይ በሚሰማበት ጊዜ፣ ያ ድምፅ የእግዚአብሔር ድምፅ ነው ተብሎ ስለሚታመን፣ ሳውል "ጌታ ሆይ!" ያለው ከዚሁ የተነሣ ነበር:: በሌላም አንጻር ሲታይ የሳውል ስም ተደጋግሞ መጠራቱና የሚያንጸባርቅ ብርሃን ከሰማይ መታየቱ፣ እርሱ በአምላክ ፊት መሆኑን እንዲገነዘብ ያደርገዋል::

9፥7 *ድምፁን እየሰሙ*፤ ከሳውል ጋር የነበሩት ሰዎች ድምፅ ሰምተዋል፤ ንግግሩን ግን አላስተዋሉም ነበር (22፥9 ይመ፤ ከዳን 10፥7 ጋር ያነጻጽሩ)::

9፥10 *ሐናንያ*፤ ስሙን በሌላ ቦታ የምናገኘው በ22፥12 ላይ ብቻ ነው፤ የተለመደም ስም ነው(5፥1፤ 23፥2) የግሪኩ ቃል የተወረሰው "ሐናንያህ" ከሚለው ከዕብራይስጡ ሲሆን፣ ትርጒሙም፣ "እግዚአብሔር ባለ ጸጋ ነው ወይም እግዚአብሔር ጸጋውን አሳየ" ማለት ነው (ዳን 1፥6 ይመ)::

9፥11 *ቀጥተኛ ጐዳና*፤ የሚሄድበት መንገድ በከተማዪቱ መካከል ዛሬም ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ሰንጥቆ የሚያልፈው ረጅሙና ቀጥ ያለው መንገድ ሳይሆን አይቀርም፤ በደማስቆ ውስጥ ከነበሩት አያሌ ዐባጣ ጐርባጣ መንገዶች ጋር ለማነጻጸር ሆን ተብሎ የተጠቀሰ ነው:: *የጠርሴስ*፤ የ22፥3 ማብ ይመ:: *እየጸለየ*፤ በሉቃስ ወንጌልና በሐዋርያት ሥራ ብዙውን ጊዜ ጸሎት ከራእይ ጋር ተዛምዶ ይገኛል::

*9፥13:32፤* ቅዱሳን ለሚለው ቃል የሮም 1፥7፤ ፊል 1፥1 ማብ ይመ::

9፥15 *በአሕዛብ...ፊት*፤ ሮሜ1፥13-14 ይመ:: *ንጉሦቻቸው*፤ አግሪጳና (26፥1) በሮም የሚገኘው ቄሳር (25፥11-12፤ 28፥19) ማለት ነው::

9፥17 *የተገለጠልህ ጌታ ኢየሱስ*፤ ሳውል በደማስቆ ያየው ራእይ ብቻ አልነበረም፣ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣውን ጌታ ኢየሱስንም በትክክል አይቶታል፤ ሳውል ለሐዋርያነቱ ብቃት መመዘኛ ያደረገውም ይህንኑ እውነት ነው (1ቆሮ 9፥1፤ 15፥8)::

9፥20 *ወዲያውም፤* ከተጠመቀ በኋላ ማለት ነው:: *በየምኵራቦቹ*፤ ሳውል፣ ዕድል ቢገጥመው ቍጥር በየምኵራቡ መስበክ የዘወትር ተግባሩ ሆነ (13፥5፤ 14፥1፤ 17፥1-2:10፤ 18፥4:19፤ 19፥8):: *ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን፤* ሳውል የሚያስተላልፈው ዋናው መልእክት ራሱ በደማስቆ መንገድ ላይ የተረዳውንና ያመነውን የክርስቶስን አምላክነትና መሲሕነት ነው::

[23]ከብዙ ቀንም በኋላ፣ አይሁድ ሳውልን
ለመግደል አሤሩ፤ [24]እርሱ ግን ዕቅዳቸ
ውን ዐውቆ ነበር፤ እነርሱም ሊገድሉት የከ
ተማዋን በር ቀንና ሌሊት ይጠብቁ ነበር፤
[25]የእርሱ ተከታዮች ግን በሌሊት በከተማዋ
ቅጥር ቀዳዳ አሾልከው በቅርጫት አወረዱት።
[26]ሳውልም ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ፣
ከደቀ መዛሙርት ጋር ለመቀላቀል ሞከረ፤
እነርሱ ግን በእርግጥ ደቀ መዝሙር መሆ
ኑን ስላላመኑ ሁሉም ፈሩት። [27]ይሁን እንጂ
ባርናባስ ወስዶ ወደ ሐዋርያት አመጣው፤
ሳውልም በጕዞው ላይ ሳለ ጌታን እንዴት
እንዳየው፣ ጌታም እንዴት እንደ ተናገረው
እንዲሁም በደማስቆ የጌታን ስም እንዴት
በድፍረት እንደ ሰበከ ነገራቸው። [28]ስለዚህ
ሳውል አብሮአቸው ተቀመጠ፤ በኢየሩሳሌምም
በመዘዋወር በጌታ ስም በድፍረት ይናገር
ነበር። [29]ከግሪክ አገር ከመጡት አይሁድ ጋር
እየተነጋገረ፣ ይከራከር ነበር፤ እነርሱ ግን
ሊገድሉት ጥረት ያደርጉ ነበር። [30]ወንድሞችም
ይህን ባወቁ ጊዜ፣ ወደ ቂሳርያ አውርደው
ወደ ጠርሴስ ሰደዱት።
[31]በዚህ ጊዜ በይሁዳ፣ በገሊላና በሰማርያ
ያለችው ቤተ ክርስቲያን በሰላም መኖር
ጀመረች፤ ተጠናከረችም። ደግሞም እግዚአ
ብሐርን በመፍራት እየተመላለሰችና በመንፈስ
ቅዱስ እየተጽናናች በቍጥር እየበዛች ሄደች።

## ኤንያና ዶርቃ

[32]ጴጥሮስም ከአገር ወደ አገር በሚዘዋ
ወርበት ጊዜ፣ በልዳ የሚኖሩትን ቅዱሳን

9፥23 ሐሥ20፥3
9፥24 ሐሥ20፥3፡ 19፥23፥16:30
9፥25 1ሳሙ19፥12፤ 2ቆሮ11፥32:33
9፥26 ሐሥ22፥17፤ 26፥20፤ገላ1፥17:18
9፥27 ቍ3-6:20፡ 22፤ሐሥ4፥36
9፥29 ሐሥ6፥1፤ 2ቆሮ11፥26
9፥30 ቍ11፤ሐሥ 1፥16፤8፥40
9፥31 ሐሥ2፥41፤ 8፥1
9፥32 ቍ13

9፥23 *ከብዙ ቀንም በኋላ፤* ሦስት ዓመት ነው (ገላ 1፥17-18)። የዐረብ አገር ወሰኑ ለደማስቆ ቅርብ ነው፤ ይሁን እንጂ ሳውል ከደማስቆ ርቆ ወደ ዐረብ አገር ዘልቆ በመሄድ እዚያ እንደተቀመጠ ይገመታል። *አይሁድ ሳውልን ለመግደል አሤሩ፤* ከንጉሡ ከአርጣስዮስ (አሬታስ) በታች የነበረው ገዥ፣ ወደ ደማስቆ እንደ ተመለሰ ሳውል እንዲታሰር ትእዛዝ ሰጠ (2ቆሮ 11፥32)። ከ34 እስከ 62 ዓ.ም. የሮማውያን ሳንቲሞች በደማስቆ ውስጥ በሥራ ላይ አለመዋላቸው፣ አርጣስዮስ በዚህ ጊዜ ከተማዪቱን ይገዛ እንደ ነበር ሳያመለክት አይቀርም።


9፥25 *በቅርጫት አወረዱት፤* 2ቆሮ 11፥33 ይመ፤ (ከኢ ሱ 2፥15፤ 1ሳሙ 19፥12 ጋር ያነጻጽሩ)።

*9፥26 ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ፤* በዚያ ጊዜ ከጴጥሮስና ከጌታ ወንድም ከያዕቆብ በቀር ሌሎቹ ሐዋርያት እንዳልነበሩ ከገላ 1፥19 ላይ እንረዳለን። ያዕቆብ ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት አንዱ አልነበረም፤ ይሁን እንጂ በኢየሩሳሌም የነበረው ሥልጣን ልክ እንደ አንድ ሐዋርያ የሚያስቈጥረው ነበር።

9፥30 *ቂሳርያ፤* የ8፥40 ማብ ይመ። *ጠርሴስ፤* ሳውል የተወለደበት ቦታ (የ22፥3 ማብ ይመ)።

9፥31 *ቤተ ክርስቲያን፤* በይሁዳ በገሊላና በሰማርያ አውራጃዎች የሚገኘውን ክርስቲያን ሁሉ ማለት እንጂ፣ የተለያዩ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን በተናጠል አይመለከትም (የ5፥11 ማብ ይመ)። *በመንፈስ ቅዱስ እየተጽናናች፤* የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተለየ አጽንዖት ተሰጥቶት እናያለን (13፥2፤ የ1፥2 ማብ ይመ)። መጽሐፉ አንዳንድ ጊዜ 'የመንፈስ ቅዱስ ሥራ' ተብሎ እስከ መጠራት የደረሰውም ከዚህ የተነሣ ነው።

9፥32 *በልዳ፤* ኢዮጴንና ኢየሩሳሌምን ከሚያገናኘው መንገድ በስተሰሜን 3 ወይም 4 ኪ.ሜ ገደማ ላይ ርቃ የምትገኝ ከተማ ናት። ልዳ ከኢዮጴ 19 ኪ.ሜ. ያህል ትርቃለች።




ደማስቆ አክራሪ ፈሪሳዊው ሳውል በተሰለፈበት ክርስቲያኖችን የማጥፋት ዘመቻ ዓይነተኛ ከተማ ስትሆን እስከ ሰሜን ሶርያ፣ መስጴጦሚያ፣ ፋርስና ዐረቢያ የሚዘረጋ የንግድ መስመር የሚነሣበት ሰፊ የንግድ ማዕከልም ናት። አዲሱ የክርስትና "መንገድ" በደማስቆ በሰፋት ቢታወቅ እነዚህን ቦታዎች በፍጥነት ለማዳረስ ቀላል ይሆናል። ስለዚህ በሸንጎውና በዋነኛው አሳዳጅ በሳውል እይታ ይህ እንቅስቃሴ መገታት ያለበት በደማስቆ ነው።

ከተማዋ በምድረ በዳ እንዳለ ኵሬ ውሃ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ አባናና ፋርፋ ተብለው በሚጠሩ ወንዞች አጠገብ የተመሠረተች ናት። የሮማ ሥነ ሕንፃ የግሪኩ የከተማ ፕላን ላይ ተጨማሪ ውበት አከሉ ጁፒተር የተባለውን ታላቅ ቤተ ጣዖትና 1.6 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው (በሐሥ 9:11) ላይ "ቀጥተኛ ጎዳና" በመባል የተጠቀሰውን የንጥፍ ድንጋይ መንገድ ሠሩ። የከተማው በሮችና ከተማውን የሚከፍለው ግድግዳ በጥንታዊው ጎዳና ላይ ከተዘረጉት አነስተኛ ሱቆች ጋር ዛሬም ይታያል።

ጳውሎስ ከደማስቆ ባመለጠበት ዘመን (2 ቆሮ 11:32-33)፣ ዋነኛ የፓለቲካ ሥልጣን የነበረው አርስጦስዮስ አራተኛ (9 ዓ.ቅ.ክ-40 .ም) ሲሆን ዐሥሩ ከተሞች ከሶርያ ክፍለ ሀገር ጋር በድንበር የተዋሰኑ ቢሆንም ከሮማ ግዛት ሥር ነበሩ።

ለመጐብኘት ወረደ:: [33]በዚያም ኤንያ የተ
ባለ፣ ስምንት ዓመት የዐልጋ ቍራኛ የነበረ
አንድ ሽባ ሰው አገኘ:: [34]ጴጥሮስም፣ “ኤንያ
ሆይ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሃል፤ ተነሣና
መኝታህን አንጥፍ” አለው:: ኤንያም ወዲ
ያውኑ ብድግ አለ:: [35]በልዳና በሰሮና የሚ
ኖሩትም ሁሉ እርሱን አይተው ወደ ጌታ
ተመለሱ::

[36]በኢዮጴ ጣቢታ የተባለች አንዲት ደቀ
መዝሙር ነበረች፤ የስሟም ትርጓሜ ዶርቃ[ሽ]
ማለት ነው:: እርሷም ዘወትር በትጋት በጎ
ነገር እያደረገችና ድኾችን እየረዳች ትኖር
ነበር:: [37]በዚያ ጊዜም ታማ ሞተች፤ ሰዎ
ችም አስከሬኗን አጥበው በሰገነት ላይ
ባለው ክፍል አስቀመጡት:: [38]ልዳ ለኢዮጴ
ቅርብ ስለ ነበረች፣ ደቀ መዛሙርትም ጴጥ
ሮስ በልዳ መሆኑን በሰሙ ጊዜ፣ ሁለት
ሰዎች ልከው፣ “እባክህ ፈጥነህ ወደ እኛ ና”
ሲሉ ለመኑት::

[39]ጴጥሮስም ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር
ሄደ፤ እዚያ በደረሰ ጊዜም ሰገነት ላይ
ወዳለው ክፍል አወጡት:: መበለቶቹም
ሁሉ ዶርቃ ከእነርሱ ጋር በነበረችበት ጊዜ
ያደረገቻቸውን ቀሚሶችና ልብሶች እያ
ሳዩት ዙሪያውን ከበው ያለቅሱ ነበር::

[40]ጴጥሮስም ሁሉንም ከክፍሉ አስወጥቶ
ተንበርክኮ ጸለየ፤ ወደ ሬሳውም ዘወር ብሎ፣

9፥34 ሐሥ3፥6፡16፥4፥10
9፥35 1ዜና5፥16፤27፥29፤መሓ2፥1፤ኢሳ 33፥9፤35፥2፤65፥10፤ሐሥ2፥41
9፥36 ኢሱ19፥46፤2ዜና2፥16፤ዕዝ3፥7፤ዮና1፥3፤ሐሥ10፥5፤1ጢሞ2፥10፤ቲቶ3፥8
9፥37 ሐሥ1፥13፤20፥8
9፥38 ሐሥ11፥26
9፥39 ሐሥ6፥1፤1ጢሞ5፥3
9፥40 ማቴ9፥25፤ሉቃ7፥14፤22፥41፤ሐሥ7፥60
9፥42 ሐሥ2፥41
9፥43 ሐሥ10፥6
10፥1 ሐሥ8፥40
10፥2 ቍ22፡35፤ሐሥ13፥16፡26
10፥3 መዝ55፥17፤ሐሥ3፥1፤5፥19፤9፥10
10፥4 መዝ20፥3፤ማቴ10፥42፤26፥13፤ራእ8፥4
10፥5 ሐሥ9፥36

“ጣቢታ፤ ተነሺ” አለ:: እርሷም ዐይኗን
ገለጠች፤ ጴጥሮስንም ባየች ጊዜ ቀና ብላ
ተቀመጠች፤ [41]እርሱም እጇን ይዞ አስነሣት፤
አማኞችንና መበለቶቹንም ጠርቶ ከነሕይወቷ
አስረከባቸው:: [42]ይህም ነገር በመላው ኢዮጴ
ታወቀ፤ ብዙ ሰዎችም በጌታ አመኑ:: [43]ጴጥ
ሮስም ስምዖን ከተባለ ከአንድ ቍርበት
ፋቂ ጋር በኢዮጴ ብዙ ቀን ተቀመጠ::

## ቆርኔሌዎስ ጴጥሮስን አስጠራ

10 በቂሳርያ፣ ‘የኢጣሊያ ክፍለ ጦር’
በሚባለው ሰራዊት ውስጥ የመቶ
አለቃ የሆነ ቆርኔሌዎስ የተባለ አንድ ሰው
ነበረ:: [2]እርሱም ከመላው ቤተ ሰቡ ጋር በመ
ንፈሣዊ ነገር የተጋና እግዚአብሔርን የሚፈራ፣
ለሰዎች እጅግ ምጽዋት የሚሰጥ፣ አዘ
ውትሮ ወደ እግዚአብሔር የሚጸልይ ነበር::
[3]አንድ ቀን፣ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ የእግዚ
አብሔር መልአክ በራእይ ወደ እርሱ መጥቶ፣
“ቆርኔሌዎስ ሆይ!” ሲለው በግልጽ አየ::

[4]ቆርኔሌዎስም በድንጋጤ ትኵር ብሎ እያ
የው፣ “ጌታ ሆይ፤ ምንድን ነው?” አለው:: መል
አኩም እንዲህ አለው፤ “ጸሎትህና ምጽዋትህ
ለመታሰቢያነት ወደ እግዚአብሔር ፊት ዐርጎል
ሃል:: [5]አሁንም ሰዎች ወደ ኢዮጴ ልከህ ጴጥ
ሮስ የተባለውን ስምዖንን አስመጣው፤ [6]እርሱም

[ሽ]36 *ጣቢታ* በአረማይክ ሲሆን *ዶርቃ* ደግሞ በግሪክ ነው፤ ትርጕሙም *ፊቆ* ማለት ነው::

9፥33 *ኤንያ*፤ ጴጥሮስ ወደዚያ የሄደው ክርስቲያኖችን ለመጐብኘት ስለ ነበር፣ ራሱ ኤንያ ክርስቲያን ሳይሆን አይቀርም::

9፥35 *በሰሮና*፤ በሜድትራኒያን ጠረፍ ላይ 80 ኪ.ሜ. ርዝ መት ያለው ከኢዮጴ እስከ ቂሳርያ የተዘረጋ ለምና ረባዳ ምድር ነው:: እዚህ ላይ የተጠቀሰችው ግን፣ የልዳ አጎራብች የሆነችው መንደር ሳትሆን አትቀርም፤ አንድ የግብፅ ጥንታዊ የፓፒረስ ጽሑፍ በፓሌ ስቲና ምድር በዚህ ስም የምትጠራ ከተማ እንደ ነበረች ይገልጻልና::

9፥36 *በኢዮጴ*፤ ከኢየሩሳሌም 60 ኪ.ሜ ያህል ርቃ የም ትገኝ ዋናው የይሁዳ ወደብ ነበረች:: በአሁኑ ጊዜ የቴል አቪቭ ክፍለ ከተማ ስትሆን፣ ጃፋ በሚል ስም ትታወቃለች::

9፥37 *አስከሬኗን አጥበው*፤ የአንድ ሰው ሕይወት ካለፈ በኋላ አስከሬኑ በቅድሚያ ይታጠባል፤ ይህም በአይሁድና በግሪኮች ዘንድ የተለመደ ሙታንን የማንጻት ሥርዐት ነበር:: *በሰገነት ላይ ባለው ክፍል*፤ አንድ ሰው ሞቶ፣ ቀብሩ ሳይፈጸም ከቈየ፣ አስከ ሬኑን ሰገነት ላይ የማቈየት ልማድም ነበር:: በኢየሩሳሌም አንድ ሰው በሞተበት ዕለት መቀበር ነበረበት፤ ከኢየሩሳሌም ውጭ ከሆነ ግን አስከሬኑን እስከ ሦስት ቀን ድረስ ማቈየት ይቻላል::

9፥38 *ለኢዮጴ ቅርብ ስለ ነበረች*፤ የቍ32 ማብ ይመ:: *ፈጥነህ ወደ እኛ ና*፤ እንዲህ ያሉት ለማጽናናት ወይም በታ ምር እንዲያድናት አስበው እንደሆነ አይታወቅም፣ ብቻ ጴጥሮስ ሲትየዋ ከመቀበሯ በፊት በፍጥነት እንዲደርስ ልከውበት ነበር::

9፥40 *ሁሉንም...አስወጥቶ*፤ ከ1ነገ 17፥23፤ 2ነገ 4፥33 ጋር ያነጻጽሩ:: በወንጌል ላይ ተጽፎ እንደሚገኘው፣ ጌታ ኢየሱስ ሦስት ሰዎች ከሞት ሲያስነሣ፣ ጴጥሮስ አብሮት ነበር (ማቴ 9፥25፤ ሉቃ 7፥11-17፤ ዮሐ 11፥1-44)፤ ጌታ የኢያኢሮስን ሴት ልጅ ከሞት ሲያ ስነሣ እንዳደረገው ሁሉ በክፍሉ የነበሩት ሰዎች እንዲወጡ አደረገ፤ ይሁን እንጂ ጌታ ሙታንን ያስነሣው በቃሉ በማዘዝ ብቻ ሲሆን፣ ጴጥሮስ ያስነሣት ግን ተንበርክኮ ከጸለየ በኋላ ነው::

9፥42 *ብዙ ሰዎችም ... አመኑ*፤ ከዮሐ 12፥11 ጋር ያነጻጽሩ::

9፥43 *ቍርበት ፋቂ*፤ ግለሰቦችን ይበልጥ ለማስተዋወቅ፣ ሙያቸውና ስማቸው በአንድነት ይጠቀሳል (16፥14፤ 18፥3፤ 19፥24፤ 2ጢሞ 4፥14 ይመ)፤ እዚህ ላይ ግን የስምዖን ሙያ መጠቀሱ ለተለየ ዐላማ ነው:: የአንድ ቍርበት ፋቂ ተግባር የእ ንስሳትን ቈዳ መፋቅና ማልፋት ነው፤ በአይሁድ ሕግ መሠረትም ይህ ሰው ርኩስ የሆነውን ነገር ስለ ነካ የተናቀ ነበር:: ጴጥሮስ ከእርሱ ጋር ለመቀመጥ መወሰኑ፣ የአይሁድን የጥላቻና የንቀት ስሜት መቃወሙንና በአሕዛብ ዘንድ ወደፊት ለሚኖረው የወንጌል ሥርጭት ተልእኮ መንገድ እየጠረገ መሆኑን ያመለክታል::

10፥1 *በቂሳርያ*፤ ከኢዮጴ በስተ ሰሜን 48 ኪ.ሜ ላይ የም ትገኝ ከተማ ስትሆን፣ ለአውግስጦስ ቄሳር ክብር ሲባል በስሙ ተሰይማለች፤ ለሮማውያንም ወራሪ ሰራዊት መናኸሪያ ነበረች (የ8፥40 ማብ ይመ):: *ቆርኔሌዎስ*፤ ከላቲን የመጣ ስም ነው፤ ከ100 ዓመት በፊት ቆርኔሌዎስ ሱላ የተባለ ሰው ዐሥር ሺህ ባሪ ያዎችን ነጻ በማውጣቱ፣ ይህ ስም ዝነኛ ሆነ:: እነዚህ ነጻ የወጡ ትም ሁሉ በዚሁ ስም መጠራት ጀመሩ:: *የመቶ አለቃ*፤ ቢያንስ መቶ ወታደሮች የሚያዝ ነው (የሉቃ 7፥2 ማብ ይመ):: ስድስት መቶ ወታደሮች የሚገኙበት የሮማውያን ክፍለ ጦር በውስጡ ዐሥር ምድብ ሰራዊት ያለው ሲሆን፣ እያንዳንዱ ምድብ መለያ ስም ነበ ረው፤ ይህኛው “የኢጣሊያ ክፍለ ጦር” ሲባል፣ ሌላው “የንጉሡ ነገ ሥቱ” ወይም “የአውግስጦስ ክፍለ ጦር” ይባል ነበር (27፥1):: አንድ የመቶ አለቃ የሚያዘውም የአንዱን ምድብ ሰራዊት አንድ ስድስተኛ ነበር:: የመቶ አለቆች በጥንቃቄ ይመረጡ ነበር፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስማቸውን የምናገኘው የመቶ አለቆች ሁሉ መልካም ሥነ ምግባር የነበራቸው ይመስላል (ለምሳሌ ሉቃ 7፥5 ይመ):: እነ ዚህ መቶ አለቆች፣ በመላው የሮማ ግዛት ሰላምና መረጋጋት እን ዲሰፍን ያደረጉ ናቸው::

10፥2 *በመንፈሳዊ ነገር የተጋ*፤ ቆርኔሌዎስ ሥነ ምግባሩ ያማረ ቢሆንም እንኳ፣ እንደ እርሱ ሰው ከሆነው መል እክተኛ የድነትን መንገድ መስማት ያስፈልገው ነበር፤ የመል አኩም ድርሻ (ቍ3) ቆርኔሌዎስንና ጴጥሮስን ማገናኘት ነበር (ከ8፥26፤ 9፥10 ጋር ያነጻጽሩ):: *እግዚአብሔርን የሚፈራ*፤ ከአሕዛብ ወገን ወደ አይሁድ ሃይማኖት ሙሉ በሙሉ የገባና በሥርዐቱ የሚመላለስ ሳይሆን፣ እንዲሁ በአንድ አምላክ አምኖ የአይሁድን ሃይማኖትና ምግባር የሚከተል ሰው ነው::

10፥3 *ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ*፤ ቆርኔሌዎስ የአይሁድን ሃይማኖት ሥርዐት የሚከተል ስለ መሆኑ ይህ አንዱ ምልክት ነው:: ዘጠኝ ሰዓት አይሁድ የምሽት ዕጣን የሚያሳርጉበት የጸሎት ጊዜ ነው (3፥1 ይመ):: *ራእይ*፤ በሕልም ወይም በሰመመን ሳይ ሆን፣ ቆርኔሌዎስ በጸሎት ላይ ሳለ መልአክ በገሃድ ተገልጦለት ነው (ቍ 30፤ እንዲሁም የ9፥11 ማብ ይመ)::

10፥4 *ለመታሰቢያነት*፤ ከእህል ቍርባን ተወስዶ በመሠዊያ ላይ ተቃጥሎ ለመታሰቢያነት የሚቀርብ ማለት ነው (ዘሌ 2፥2)::

10፥5-6 *ኢዮጴ...በቍርበት ፋቂው በስምዖን*፤ የ9፥36፡43

በባሕሩ አጠገብ ባለው በቍርበት ፋቂው በስምዖን ቤት በእንግድነት ዐርፎአል።”

[7]ቆርኔሌዎስም፣ ያነጋገረው መልአክ ተለይቶት ከሄደ በኋላ፣ ከአገልጋዮቹ ሁለቱን፣ እንዲሁም በመንፈሳዊ ነገር የተጋና ለእርሱ ታማኝ የሆነውን አንዱን ወታደር አስጠራ፤ [8]የሆነውንም ነገር ሁሉ ከነገራቸው በኋላ ወደ ኢዮጴ ላካቸው።

## ጴጥሮስ ያየው ራእይ

10፡9-32 ማመ - ሐሥ11፡5-14

[9]የተላኩትም ሰዎች በማግስቱ ወደ ከተማዪቱ እንደ ተቃረቡ፣ ጴጥሮስ እኩለ ቀን ገደማ ሲሆን፣ ለመጸለይ ወደ ሰገነት ወጣ። [10]በዚያን ጊዜም ስለ ተራበ የሚበላ ነገር ፈለገ፤ ምግብ እየተዘጋጀ ሳለም አሸለበውና በተመስጦ ውስጥ ሆነ፤ [11]ሰማይም ተከፍቶ አንድ ትልቅ ጨርቅ የሚመስል ነገር በአራቱ ማእዘን ተይዞ ወደ ምድር ሲወርድ አየ። [12]በጨርቁም ላይ አራት እግር ያላቸው የተለያዩ እንስሳት፣ በምድር የሚሳቡ ፍጥረታትና በአየር የሚበሩ አዕዋፍ ነበሩበት። [13]በዚህ ጊዜ፣ “ጴጥሮስ ሆይ፤ ተነሥ፤ እነዚህን ዐርደህ ብላ” የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ።

[14]ጴጥሮስ ግን “ጌታ ሆይ፤ ይህማ አይሆንም፤ እኔ ያልተቀደሰ ወይም ርኩስ ነገር ፈጽሞ በልቼ አላውቅምና” አለ።

[15]ያም ድምፅ እንደ ገና ለሁለተኛ ጊዜ ወደ እርሱ መጥቶ፣ “እግዚአብሔር ንጹሕ ያደረገውን አንተ እንደ ርኩስ አትቍጠረው” አለው።

[16]ይህም ሦስት ጊዜ ተደጋገመ፤ ጨርቁም ወዲያውኑ ወደ ሰማይ ተወሰደ።

[17]ጴጥሮስም ስላየው ራእይ ትርጕም እጅግ ተጨንቆ በማሰላሰል ላይ ሳለ፣ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች የስምዖንን ቤት ፈልገው ካገኙ በኋላ መጥተው በሩ ላይ ቆሙ፤ [18]ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን እዚያ ይኖር እንደ ሆነ ጠየቁ።

[19]ጴጥሮስ የራእዩን ነገር በማሰላሰል ላይ ሳለ፣ መንፈስ እንዲህ አለው፤ “እነሆ፤

10፥6 ሐሥ9፥43
10፥8 ሐሥ9፥36
10፥9 ማቴ24፥17
10፥10 ሐሥ22፥17
10፥11 ማቴ3፥16
10፥14 ዘሌ11፥4-8፡ 13-20፤20፥25፤ዘዳ 14፥3-20፤ሕዝ4፥14፤ ሐሥ9፥5
10፥15 ቍ28፤ዘፍ 9፥3፤ማቴ15፥11፤ ሉቃ11፥41፤ሐሥ 11፥9፤ሮሜ14፥14፡ 17፡20፤ 1ቆሮ10፥ 25፤1ጢሞ4፥3፡4፤ ቲቶ1፥15
10፥17 ቍ7፡8፤ሐሥ 9፥10
10፥19 ሐሥ8፥29፤ 9፥10
10፥20 ሐሥ15፥7-9
10፥22 ቍ2፤ ሐሥ 11፥14
10፥23 ቍ45፤ ሐሥ 1፥16፤11፥12
10፥24 ሐሥ8፥40
10፥26 ሐሥ14፥15፤ ራእ19፥10፤22፥8፡9
10፥27 ቍ24
10፥28 ቍ14፡15፤ ዮሐ4፥9፤18፥28፤ ሐሥ11፥3፤15፥8፡9
10፥30 ዮሐ20፥12

ሦስት* ሰዎች ይፈልጉሃል፤ [20]ስለዚህ ተነሥተህ ውረድ፤ የላክኋቸውም እኔ ስለ ሆንሁ ሳትጠራጠር ከእነርሱ ጋር ሂድ።”

[21]ጴጥሮስም ወርዶ፣ “እነሆ፤ የምትፈልጉት ሰው እኔ ነኝ፤ የመጣችሁበት ጒዳይ ምንድን ነው?” አላቸው።

[22]ሰዎቹ፣ “የመጣነው ቆርኔሌዎስ ከተባለው መቶ አለቃ ዘንድ ነው፤ እርሱም ጻድቅና እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ በአይሁድም ሕዝብ ሁሉ ዘንድ የተከበረ ሰው ነው። አንተን ወደ ቤቱ እንዲያስመጣህና የምትለውን እንዲሰማ ቅዱስ መልአክ ነግሮታል” አሉት። [23]ጴጥሮስም ሰዎቹን ሊያስተናግዳቸው ወደ ቤት አስገባቸው።

## ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት

ጴጥሮስም በማግስቱ ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር ሄደ፤ ከኢዮጴ የመጡ አንዳንድ ወንድሞችም አብረውት ሄዱ፤ [24]በሚቀጥለው ቀን ቂሳርያ ገባ። ቆርኔሌዎስም ዘመዶቹንና የቅርብ ወዳጆቹን ሰብስቦ ይጠብቃቸው ነበር። [25]ጴጥሮስም ወደ ቤቱ በገባ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ተቀበለው፤ እግሩም ላይ ወድቆ ሰገደለት። [26]ጴጥሮስ ግን፣ “እኔም እንዳንተው ሰው ነኝና ተነሥ!” ብሎ አስነሣው።

[27]ጴጥሮስም እያነጋገረው አብሮት ሲገባ ብዙ ሰው ተሰብስቦ አገኘ፤ [28]እንዲህም አላቸው፤ “አንድ አይሁዳዊ ከሌላ ወገን ጋር እንዲተባበር ወይም እንዲቀራረብ ሕጋችን እንደማይፈቅድ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፤ ነገር ግን እኔ ማንንም ርኩስ ወይም ያልተቀደሰ ነው እንዳልል እግዚአብሔር አሳይቶኛል፤ [29]ስለዚህም በተጠራሁ ጊዜ፣ እነሆ ሳላመነታ መጣሁ፤ እንግዲህ፣ ለምን እንደጠራችሁኝ ማወቅ እፈልጋለሁ።”

[30]ቆርኔሌዎስም እንዲህ አለው፤ “ከአራት ቀን በፊት በዚህ ጊዜ ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት በቤቴ ሆኜ እጸልይ ነበር፤ ድንገትም ብሩህ ልብስ የለበሰ ሰው መጥቶ በፊቴ ቆመና

*19 አንድ የጥንት ቅጅ *ሁለት* ይላል፤ ሌሎች የጥንት ቅጆች ይህ ቍጥር የላቸውም።

ማብ ይመ።

10፥9 *ለመጸለይ ወደ ሰገነት ወጣ፤* የመካከለኛው ምሥራቅ ቤቶች ጣራቸው ጠፍጣፋ ሆኖ፣ በውጭ በኩል መወጣጫ ደረጃ ነበራቸው፤ ጣራውም ለመዝናናትና የግል ቈይታ ለማድረግ ያመቸ ነበር።

10፥10 *አሸለበውና በተመስጦ፤* እግዚአብሔር ከጴጥሮስ ጋር ይነጋገር ዘንድ ያመቻቸውና ያሰናዳው ሁኔታ ነበር፤ በራስ ሐሳብ የተፈጠረ ዓለም ወይም ሕልም አልነበረም። ጴጥሮስ ራእዩን ከእግዚአብሔር ለመቀበል በከፍተኛ ንቃት ላይ ነበር።

10፥12 *አራት እግር ያላቸው የተለያዩ እንስሳት ሁሉ፤* በዘሌ 11 ላይ ንጹሕ የሆኑና ያልሆኑ ተብለው የተመደቡትን እንስሳት ሁሉ ማለት ነው።

10፥14 *ጌታ ሆይ፤ ይህማ አይሆንም፤* ንጹሕ የሆነውንና ያልሆነውን የሚያመለክተው የኦሪት ሕግ በጴጥሮስ ልብ ሥር ሰዶ ስለ ነበር፣ ወዲያውኑ ሊታዘዝ አልቻለም። *ያልተቀደሰ ወይም ርኩስ፤* የተገኘው ሁሉ (ንጹሕ ያልሆነ) እንዳይበላ በኦሪት ሕግ የተከለከለ ነበር።

10፥15 *እግዚአብሔር ንጹሕ ያደረገውን፤* የሚበላና የማይበላ ተብሎ በኦሪት ሕግ የተደነገገውን ሥርዐት ጌታ ኢየሱስ ገና በፊቱኑ ሽሮታል (ማቴ 15፥11፤ 1ጢሞ 4፥3-5 ይመ)።

10፥16 *ሦስት ጊዜ፤* ወደ ጴጥሮስ ልብ ዘልቆ እንዲገባ ለማድረግ ነው።

10፥23 *ወደ ቤት አስገባቸው፤* ጴጥሮስ ለሰዎቹ ማረፊያ መስጠቱ አሕዛብን መቀበል መጀመሩን ያሳያል፤ ከአሕዛብ ጋር ይህን የመሰለ ቅርበት መፍጠር፣ ከነባሩ የአይሁድ ሥርዐት ጋር የሚጣጣም አልነበረምና። *በማግሥቱ፤* ወዲያው ተነሥቶ ቢሄድ ቂሳርያ ገብቶ ማደር ስለማይችል፣ ዐድሮ መሄድ ነበረበት (የቍ1 ማብ ይመ)። *አንዳንድ ወንድሞችም፤* ስድስት ነበሩ (11፥12)፤ ሥረ መሠረታቸውም አይሁድ ነበር (10፥45)።


10፥26 *እኔም እንዳንተው ሰው ነኝና፤* ጴጥሮስ ከእግዚአብሔር ስለ ተላከ፣ ቆርኔሌዎስ ራሱን ዝቅ አድርጎ ጴጥሮስን ማክበሩ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ጴጥሮስ ራሱን ከፍጡር በላይ ከፍ በማድረግ እንዲህ ያለውን ክብር መቀበል አልፈለገም።

10፥28 *እግዚአብሔር አሳይቶኛል፤* ጴጥሮስ ባየው ራእይ በሚበሉና በማይበሉ እንስሳት መካከል ያለው ልዩነት መወገዱን፣ ከዚህም በላይ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረው ግድግዳ መፍረሱን ተረድቶአል። (ኤፌ 2፡11-22)።

10፥30 *ከአራት ቀን በፊት፤* አይሁድ ከፊሉን ቀን እንደ አንድ ሙሉ ቀን አድርገው ይቈጥሩታል (1) መልአኩ ለቆርኔሌዎስ የተገለጠበት ቀን፣ (2) መልእክተኞቹ ወደ ኢዮጴ የመጡበትና ጴጥሮስ ራእይ ያየበት ቀን (3) ጴጥሮስና መልእክተኞቹ

# የጳውሎስ ሕይወት

መስመሮች፤ ቅንፎችና ነጠብጣብ መስመሮች የሁነቶችን ቅደም ተከተል ለመስየት ይረዳሉ፤ ይሁን እንጂ በዓመቱ ውስጥ የሚገኙትን ቀናትና ወሮች አቅጩን ለመናገር አይደለም፤ ጊዜዎቹን/ዘመናቱን በትክክል መናገር አስቸጋሪ ነውና።



31እንዲህ አለኝ፤ ‘ቆርኔሌዎስ ሆይ፤ ጸሎትህ
ተሰምቶልሃል፤ ምጽዋትህም ለመታሰቢያነት
በእግዚአብሔር ፊት ደርሶአል:: 32ሰዎችን ወደ
ኢዮጴ ልከህ ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖንን
አስመጣ፤ እርሱም በባሕር አጠገብ ባለው
በቍርበት ፋቂው በስምዖን ቤት በእንግድ
ነት ዐርፎአል::’ 33እኔም ወዲያው ላኩብህ፤
አንተም በመምጣትህ መልካም አድርገሃል::
እንግዲህ እኛ ሁላችን ጌታ ያዘዘህን ስትነግ
ረን ለመስማት በእግዚአብሔር ፊት አለን::

34ጴጥሮስም እንዲህ ሲል መናገር ጀመረ፤
“እግዚአብሔር ለማንም እንደማያዳላ በእርግጥ
ተረድቻለሁ፤ 35ነገር ግን እርሱን የሚፈሩት
ንና ጽድቅን የሚያደርጉትን ሁሉ ከየትኛ
ውም ወገን ቢሆኑ ይቀበላቸዋል:: 36እግዚአብሔር፣
የሁሉ ጌታ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል
የላከውም የሰላም የምሥራች መልእክት ይኸው
ነው:: 37ዮሐንስ ከሰበከው ጥምቀት በኋላ
ከገሊላ ጀምሮ በመላው ይሁዳ የሆነውን
ታውቃላችሁ፤ 38እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየ
ሱስ በመንፈስ ቅዱስና በኀይል ቀባው፤ እር
ሱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ነበረ በደረ
ሰበት ሁሉ መልካም እያደረገ በዲያብሎስ
ሥልጣን ሥር የነበሩትን ሁሉ ፈወሰ::

39“እርሱ በአይሁድ አገርና በኢየሩሳሌም
ላደረገው ሁሉ እኛ ምስክሮች ነን፤ ደግ
ሞም ሰዎች እርሱን በዕንጨት ላይ ሰቅለው
ገደሉት:: 40እግዚአብሔር ግን በሦስተኛው ቀን
ከሙታን አስነሣው፤ እንዲታይም አደረገው፤
41የታየውም ለሁሉ ሰው ሳይሆን፣ ከሙታን
ከተነሣ በኋላ አብረነው ለበላንና ለጠጣን፣
እግዚአብሔርም አስቀድሞ ለመረጠን ለእኛ
ለምስክሮቹ ነው:: 42ለሕዝቡ እንድንሰብክና
በሕያዋንና በሙታንም ላይ እንዲፈርድ እግ
ዚአብሔር የሾመው እርሱ መሆኑን እንድን
መስክር እርሱ ራሱ አዘዘን፤ 43በእርሱም
የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአትን ስርየት
እንደሚቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል::”

44ጴጥሮስ ይህን እየተናገረ ሳለ፣ ቃሉን በሰ
ሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባ
ቸው:: 45ከጴጥሮስ ጋር የመጡት፣ ከተገረ
ዙት ወገን የሆኑት አማኞች፣ የመንፈስ
ቅዱስ ስጦታ በአሕዛብም ላይ ደግሞ መፍ
ሰሱን ሲያዩ ተገረሙ፤ 46ይኸውም በልሳን°
ሲናገሩና እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ስለ ሰሚ
ቸው ነው::

በዚያ ጊዜ ጴጥሮስ እንዲህ አለ፤ 47“እነዚህ
ሰዎች እንደ እኛ መንፈስ ቅዱስን ስለ ተቀ
በሉ፣ እንግዲህ በውሃ እንዳይጠመቁ የሚከ
ለክላቸው ማን ነው?” 48ስለዚህ በኢየሱስ
ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ አዘዛቸው:: ከዚህ
በኋላ፣ ጴጥሮስ ጥቂት ቀን ከእነርሱ ጋር
እንዲቀመጥ ለመኑት::

## ጴጥሮስ አሕዛብ ቤት ለምን እንደገባ አስረዳ

11 ሐዋርያትና በይሁዳ የነበሩት ወንድ
ሞች አሕዛብ ደግሞ የእግዚአብሔርን
ቃል እንደ ተቀበሉ ሰሙ:: 2ስለዚህ ጴጥሮስ
ወደ ኢየሩሳሌም በወጣ ጊዜ፣ ከተገረዙት
ወገን የነበሩ አማኞች ነቀፉት፤ 3እንዲህም
አሉት፤ “ወዳልተገረዙ ሰዎች ገብተህ ከእነ
ርሱ ጋር በላህ::”

4ጴጥሮስ ግን እንዲህ ሲል ነገሩን በቅደም
ተከተል ያስረዳቸው ጀመር፤ 5“በኢዮጴ ከተማ
ስጸልይ በተመስጦ ውስጥ እያለሁ ራእይ
አየሁ፤ ትልቅ ጨርቅ የሚመስል ነገር፣ በአራት

°46 ወይም በሌላ ቋንቋዎች

10፥34 ዘዳ10፥17፤ 2ዜና19፥7፤ ኢዮ34፥19፤ ማር12፥14፤ ሮሜ2፥11፤ገላ2፥6፤ ኤፌ 6፥9፤ቈላ3፥25፤ ያዕ2፥1፤1ጴጥ1፥17
10፥35 ሐሥ15፥9
10፥36 ማቴ28፥18፤ ሉቃ2፥ 14፤ ሐሥ13፥32፤ 1ዮሐ1፥5
10፥38 ማቴ4፥23፤ ዮሐ3፥2፤ሐሥ4፥26
10፥39 ቍ41፤ ሉቃ 24፥48፤ ሐሥ5፥30
10፥40 ሐሥ2፥24
10፥41 ሉቃ24፥43፤ ዮሐ14፥17:22፤ 21፥13፤ሐሥ1፥4
10፥42 ማቴ28፥19: 20፤ዮሐ5፥22፤ ሐሥ 17፥31፤ሮሜ 14፥9፤ 2ቆሮ5፥10፤2ጢሞ 4፥1፤1ጴጥ4፥5
10፥43 ኢሳ53፥11፤ ሉቃ24፥27፤ዮሐ3፥15፤ ሐሥ15፥9፤26፥22
10፥44 ሉቃ1፥15፤ ሐሥ8፥15:16፤ 11፥15፤ 15፥8፤19፥6
10፥45 ቍ23፤ሐሥ 2፥33:38፤11፥18፤15፥8
10፥46 ማር16፥17
10፥47 ዮሐ20፥22፤ ሐሥ8፥36፤11፥17
10፥48 ሐሥ2፥38
11፥1 ሐሥ1፥16፤ ዕብ4፥12
11፥2 ሐሥ10፥45
11፥3 ሐሥ10፥25: 28፤ገላ2፥12

ከኢዮጴ የተነሡበት ቀን፤ (4) ጴጥሮስና መልእክተኞች ቆርኔሌዎስ ቤት የደረሱበት ቀን:: *ብሩህ ልብስ የለበሰ ሰው፤* በሰው ተመስሎ የተገለጠውን መልአክ በዚህ መንገድ ለሌላው መንገር የተለመደ ነበር::

10፥34 *እግዚአብሔር ለማንም እንደማያዳላ፤* እግዚአብሔር አንድን ሰው በሥልጣኑና በማዕረጉ፣ በዜግነቱ ወይም በሀብቱ ብዛት አያከብረውም (የያዕ 2፥1 ማብ ይመ)፤ ሆኖም የአንዱን ሰው ባሕርይና ጠባይ ይመለከታል፤ ሥራውንም ይመዝናል:: ይህም፣ እግዚአብሔር፣ “እርሱን የሚፈሩትንና ጽድቅን የሚያደርጉትን ሁሉ ከየትኛውም ወገን ቢሆኑ ይቀበላል (ቍ35) ከሚለው ቃሉ የተረጋገጠ ነው:: ቆርኔሌዎስ እውነተኛውን አምላክ ያመልክ ነበር፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ገና ስላላመነ (ቍ36) ይህ በቂ አልነበረም::

10፥36 *የሰላም፤* በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለ ዕርቅ:: *የሁሉ ጌታ፤* የአይሁድም የአሕዛብም ጌታ ለማለት ነው (ቍ34-35 ይመ)::

10፥37 *ዮሐንስ ከሰበከው ጥምቀት በኋላ፤ ይህ* ከማርቆስ ወንጌል አስተዋጽኦ ጋር ይመሳሰላል፤ ሁለቱም ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምረው እስከ ኢየሱስ ትንሣኤ ድረስ ይተርካሉ፤ ይህም ዐቢይ ነገር ነው፤ የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች የማርቆስን ወንጌል የጴጥሮስ ስብከት “ትርጓሜ” አድርገው ይቈጥሩታልና:: ቀደም ብሎ ያለውን የጴጥሮስን ስብከት ማጠቃለያ (2፥14-41፤ 3፥12-26፤ 4፥8-12፤ 5፥29-32)፤ እንዲሁም የ2፥4-40 ማብ ይመ::

10፥38 *እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስ...ቀባው፤* ኢሳ 61፥1-3፤ ሉቃ 4፥18-21 ይመ::

10፥39 *በዕንጨት ላይ ሰቅለው፤* የ5፥30 ማብ ይመ::

10፥41 *ለበላንና ለጠጣን፤* ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ከእርሱ ጋር የበሉ ሁሉ፣ በአካል እንደ ተነሣ በማያወላዳ ሁኔታ አረጋግጠዋል (ሉቃ 24፥42-43፤ ዮሐ 21፥12-15 ይመ)::

10፥45 *በአሕዛብም ላይ ደግሞ...ተገረሙ፤* ከአይሁድ ወገን የሆኑት የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች ወንጌል ለአሕዛብም ለአይሁድም እንደ መጣና፣ የድነትን በረከት እኩል የመካፈል መብት እንዳላቸው ማስተዋል እንዳልቻሉ እናያለን:: ነገር ግን ወደ አይሁድ እምነት የገቡት አሕዛብ ተቀባይነት ነበራቸው (6፥5 ይመ)::

10፥47 *እነዚህ ሰዎች...በውሃ እንዳይጠመቁ የሚከለክላቸው ማን ነው?* የአሕዛብ ክርስቲያኖችም እንደ አይሁድ ክርስቲያኖች ሁሉ አንድ ዐይነት የጸጋ ስጦታ ተቀብለዋል (11፥17)፤ የአይሁድ ክርስቲያኖች በጰንጠቆስጤ ቀን በልሳን እንደ ተናገሩ ሁሉ፣ የአሕዛብ ክርስቲያኖችም በልሳን ተናግረዋል:: ይህ እንግዲህ አይሁድም ሆኑ አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እኩል መጠራታቸውን ማንም ሊክደው የማይችል ማረጋገጫ ነው::

11፥1 *ሐዋርያትና...ወንድሞች፤* አንዳንድ ጊዜ “ወንድሞች” ሲባል፣ ከአንድ ዘር የተገኙትን የአይሁድ ወገኖች ያመለክታል (2፥29፤7፥2)፤ በክርስቲያኖቹ ዘንድ ግን በክርስቶስ አንድ የሆኑትን ሁሉ ያጠቃልላል (6፥3፤ 10፥23):: ሐዋርያት በዐቢይ ጕዳዮች ላይ ብቻቸውን አይወስኑም ነበር፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምሪት ይሰጣቸዋል፤ ሐዋርያትም ይህንኑ በተግባር ይተረጕማሉ፤ ሌሎችን ይመክራሉ፤ ይህም ሁሉ ሆኖ የመላው ማኅበረ ምእመናን መስማማት ያስፈልግ ነበር ( “ሕዝቡን በሙሉ” 6፥5፤ “ሐዋርያትና...ወንድሞች” 11፥1፤ “ቤተ ክርስቲያን” 11፥22፤ “ቤተ ክርስቲያን፣ ሐዋርያት እንዲሁም ሽማግሌዎች 15፥4፤ ከ15፥22 ጋር ያነጻጽሩ)::

11፥2 *ከተገረዙት... አማኞች፤* የአይሁድ ክርስቲያኖችን ያመለክታል::

11፥3 *ወዳልተገረዙ ሰዎች፤* የሚበሉና የማይበሉ እንስሳት በማለት የሚለየውን የአይሁድን ሕግ የማያከብሩና ሥርዐታቸውን የማይጠብቁ አሕዛብ::

*11፥4-17፤* በ10፥1-23፡28-33 ላይ በየቍጥሩ የተሰጠውን ማብ ይመ::

ማእዘን ተይዞ ከሰማይ እኔ ወደ ነበርሁበት
ቦታ ሲወርድ አየሁ:: 6አተኵሬም ይህን ነገር
ስመለከት አራት እግር ያላቸው እንስሳት፣
የዱር አራዊት፣ በምድር የሚሳቡ ፍጥረታ
ትና በሰማይ የሚበሩ አዕዋፍ አየሁ:: 7በዚህ
ጊዜ፣ 'ጴጥሮስ ሆይ፤ ተነሣና ዐርደህ ብላ'
የሚለኝን ድምፅ ሰማሁ::
8"እኔም፣ 'ጌታ ሆይ፤ ይህማ አይሆንም፤
እኔ ርኩስ ወይም ያልተቀደሰ ነገር ፈጽሞ ወደ
አፌ ገብቶ አያውቅም' አልሁ::
9"ያም ድምፅ ዳግመኛ፣ 'እግዚአብሔር ንጹሕ
ያደረገውን አንተ እንደ ርኩስ አትቍጠ
ረው' ሲል ከሰማይ ተናገረኝ:: 10ይህም ሦስት
ጊዜ ተደጋገመ፤ ከዚያ ሁሉም እንደ ገና ወደ
ሰማይ ተወሰደ::
11"ልክ በዚያው ሰዓት፣ ሦስት ሰዎች ከቂ
ሳርያ ወደ እኔ ተልከው መጥተው እኔ ባለ
ሁበት ቤት ደጅ ላይ ቆሙ፤ 12መንፈስ
ቅዱስም ምንም ሳላወላውል ከእነርሱ ጋር
እንድሄድ ነገረኝ:: እነዚህም ስድስት ወንድ
ሞች ከእኔ ጋር ሄዱ፤ ወደ ሰውየውም ቤት
ገባን:: 13እርሱም መልአክ በቤቱ ውስጥ
ቆሞ እንደታየውና እንዲህ እንዳለው ነገረን፤
'ወደ ኢዮጴ ሰው ልከህ ጴጥሮስ የተባለውን
ስምዖንን አስጠራ፤ 14እርሱም አንተና የቤ
ትህ ሰዎች ሁሉ የምትድኑበትን ቃል ይነ
ግርሃል::'
15"እኔም ገና መናገር ስጀምር፣ መንፈስ
ቅዱስ፣ በመጀመሪያ በእኛ ላይ እንደ ወረደ
ሁሉ በእነርሱም ላይ ወረደ:: 16በዚህ ጊዜ፣
'ዮሐንስ በውሃ አጠመቀ፤ እናንተ ግን በመ
ንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ' ሲል ጌታ የተና
ገረው ቃል ትዝ አለኝ:: 17እንግዲህ እግዚአ
ብሔር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስናምን
ለእኛ የሰጠንን ስጦታ ለእነርሱም ከሰጣቸው፣
ታዲያ፣ እግዚአብሔርን መቃወም እችል ዘንድ
እኔ ማን ነኝ?"
18ይህን በሰሙ ጊዜም የሚሉትን አጥተው
እንዲህ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ "ይህማ
ከሆነ፣ አሕዛብም ወደ ሕይወት ይመጡ ዘንድ፣
እግዚአብሔር ንስሓን ሰጥቶአል ማለት ነዋ::"

## በአንጾኪያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን

19በእስጢፋኖስ ላይ በተነሣው ስደት ምክ
ንያት የተበተኑት አማኞች ቃሉን ለአ
ይሁድ ብቻ እየተናገሩ እስከ ፊንቄ፣ እስከ
ቆጵሮስና እስከ አንጾኪያ ድረስ ዘለቁ::
20ከቆጵሮስና ከቀሬና የመጡት አንዳንዶች
ሰዎች ግን ወደ አንጾኪያ ሄደው ለግሪኮ
ችም ጭምር በመንገር የጌታን የኢየሱስን
ወንጌል ሰበኩላቸው:: 21የጌታም እጅ ከእነ
ርሱ ጋር ነበረ፤ ቍጥራቸውም እጅግ ብዙ
የሆኑ ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ተመለሱ::
22ወሬውም በኢየሩሳሌም ከነበረችው ቤተ
ክርስቲያን ጆሮ ደረሰ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱም
በርናባስን ወደ አንጾኪያ ላከችው:: 23እርሱም
እዚያ ደርሶ እግዚአብሔር በጸጋው የሠራውን
ባየ ጊዜ ደስ አለው፤ ሁሉም በፍጹም ልብ
በጌታ በመታመን እንዲጸኑ መከራቸው::
24እርሱም መንፈስ ቅዱስንና እምነትን የተ
ሞላ ደግ ሰው ነበር፤ ቍጥሩ ብዙ የሆነ ሕዝ
ብም ወደ ጌታ ተጨመረ::
25ከዚህ በኋላ በርናባስ፣ ሳውልን ለመፈ
ለግ ወደ ጠርሴስ ሄደ፤ 26ባገኘውም ጊዜ
ወደ አንጾኪያ አመጣው:: ሁለቱም እዚያ
ካለችው ቤተ ክርስቲያን ጋር በመሆን አንድ
ዓመት ሙሉ እጅግ ብዙ ሕዝብ አስተማሩ፤
ደቀ መዛሙርትም ለመጀመሪያ ጊዜ በአን
ጾኪያ 'ክርስቲያን' ተብለው ተጠሩ::
27በዚህ ጊዜ አንዳንድ ነቢያት ከኢየሩሳ

11፥5 ሐሥ9፥10፤ 10፥9-32
11፥9 ሐሥ10፥15
11፥11 ሐሥ8፥40
11፥12 ቍ1:29፤ ሐሥ1፥16፤ 8፥29፤ 15፥9፤ሮሜ3፥22
11፥13 ሐሥ5፥19
11፥14 ዮሐ4፥53፤ ሐሥ 10፥36፤16፥15: 31-34፤18፥8፤1ቆሮ 1፥11:16
11፥15 ሐሥ2፥4: 10፥44
11፥16 ማር1፥4:8
11፥17 ሐሥ2፥38፤ 10፥45:47
11፥18 ሮሜ10፥12: 13፤2 ቆሮ7፥10
11፥19 ቍ26: 27፤ሐሥ8፥1:4፤ 13፥1፤ 14፥26፤18፥22፤ገላ2፥11
11፥20 ቍ19፤ማቴ 27፥32፤ሐሥ4፥36፤ 13፥32
11፥21 ሉቃ1፥66፤ ሐሥ 2፥41
11፥22 ሐሥ4፥36
11፥23 ሐሥ13፥43፤ 14፥22:26፤15፥40፤ 20፥24
11፥24 ሉቃ1፥15፤ ሐሥ2፥41
11፥25 ሐሥ9፥11
11፥26 ቍ29፤ሐሥ 6፥1:2፤9፥19:26:38፤ 13፥52፤26፥28፤1ጴጥ 4፥16
11፥27 ሐሥ13፥1፤ 15፥32፤1ቆሮ11፥4፤12፥ 28:29፤14፥29:32:37፤ ኤፌ4፥11

11፥14 *አንተና የቤትህ ሰዎች ሁሉ፤* የሥጋ ዝምድና ያላቸውን የቆርኔሌዎስን ቤተሰቦች ብቻ ሳይሆን፣ በቤቱ ውስጥ ያሉትን ባሪያዎቹን፣ እንዲሁም በሥሩ የሚገኙትን ሠራተኞች ሁሉ ያካትታል::

11፥17 *እግዚአብሔርን መቃወም፡* ጴጥሮስ፣ አሕዛብ እንዳ ይጠመቁና (10፥47) በክርስቶስ ጋር የተሟላ ኅብረት ፈጥረው ከምዕመናን ሁሉ ጋር አንድነት እንዳይኖራቸው ሊያግድ አልቻለም:: ከአይሁድ ወገን የሆኑት ክርስቲያኖች እግዚአብሔር አሕዛብንም አይሁድንም እኩል የሚያድን መሆኑን አምነው እንዲቀበሉ ግድ ሆነባቸው:: ለአሕዛብ በሩ የተከፈተላቸው ሰው ስለ ወደደ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ስለ ፈቀደ ነው::

11፥18 *ወደ ሕይወት ይመጡ ዘንድ...ንስሓን፡* አንድ ሰው ንስሓ ገባ የሚባለው ለኀጢአት ያለው አመለካከት ሲለወጥና ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ ነው፤ ይህም ወደ ዘላለም ሕይወት ያመራዋል ( የ2፥38 ማብ ይመ)::

11፥19 *ፊንቄ፡* 24 ኪ.ሜ. ስፋት፣ 192 ኪ.ሜ. ያህል ርዝመት ያላት ከሜድትራኒያን ባሕር በስተ ሰሜን ምሥራቅ ጠረፍ ላይ የምትገኝ አገር ነበረች (በዘመናችን ሊባኖስ ተብላ ትጠራለች)፤ ዋና ከተሞቿም ጢሮስና ሲዶና ነበሩ:: *ቆጵሮስ፡* በሰሜን ምሥራቅ ሜድትራንያን ባሕር የምትገኝ ደሴት ስትሆን፣ የበርናባስ መኖሪያ ስፍራ ነች (4፥36):: *አንጾኪያ፡* በሮማ ግዛተ ዐጼ ከሮምና ከእስክን ድርያ ቀጥሎ ሦስተኛዋ ታላቅ ከተማ ስትሆን ከሜድትራኒያን ባሕር ሰሜን ምሥራቅ ጠረፍ 24 ኪ.ሜ. ወደ የብስ ገባ ብላ ትገ ኛለች:: አብዛኞቹ የአሕዛብ ምእመናን የነበሯት የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመችው በዚች ከተማ ሲሆን፣ ጳውሎስ ሦስ ቱንም ጊዜ ሐዋርያዊ ጕዞውን ለማካሄድ ማእከል ያደረገው ይህቺን ቤተ ክርስቲያን ነበር (13፥1-4፤ 15፥40፤ 18፥23)::

11፥20 *ከቀሬና፡* የ2፥10 ማብ ይመ:: *ለግሪኮችም፡* ግሪክ ተናጋሪ አይሁድን ሳይሆን፣ አሕዛብን ማለት ነው::

11፥21 *የጌታም እጅ፡* ከ4፥30፤ 13፥11 እንዲሁም ከሉቃ 1፥66 ጋር ያነጻጽሩ:: ዐልፎ ዐልፎ በድንቅና በታምር የሚገለጠውን መለኮታዊ ማረጋገጫና በረከትን ያመለክታል (ዘፀ8፥19)::

11፥22 *በርናባስ፡* የ4፥36፤ የ9፥27 ማብ ይመ:: *አንጾኪያ፡* የቍ19 ማብ ይመ:: በርናባስ መላኩ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን አንድ አዲስ ቤተ ክርስቲያን በሌላ ቦታ መቋቋሙን ስትሰማ ከመሪዎች መካከል አንዱን ወደዚያ የመላክ መርሆዋ ክፍል ነው:: (8፥14 ይመ)::

11፥24 *መንፈስ ቅዱስንና እምነትን የተሞላ፤* ስለ እስጢፋኖስ የተሰጠውን ገለጻ (6፥5 ይመ)::

11፥25 *ጠርሴስ፡* 9፥11:30 እንዲሁም የ22፥3 ማብ ይመ::

11፥26 *አንድ ዓመት ሙሉ፤* ሉቃስ ወቅትን አስመልክቶ ሲጽፍ ትክክለኛውን ጊዜ ይዘግባል (18፥11፤19፥8:10፤ 24፥27፤ 28፥30):: *ክርስቲያን፡* አማኞች ራሳቸው ለራሳቸው ያወጡት ወይም ጠላቶቻቸው ለመዘባበቻ የሰጧአቸው ስም ይሁን አይታወቅም:: ያም ሆነ ይህ "ለክርስቶስ ተከታዮች" ተገቢ ስያሜ ነው፤ ትርጕሙም ይኸው ነውና::

11፥27 *ነቢያት፡* በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ስለ ትንቢት ስጦታ ለመጀመሪያ ጊዜ የተወሣው እዚህ ላይ ነው:: ነቢያት ይሰብካሉ፤ ይመክራሉ፤ ይተረጕማሉ፤ ወይም እዚህ ላይ እንደሚታየው ትንቢት ይናገራሉ (13፥1፤ 15፥32፤ 19፥6፤ 21፥9-10፤ ሮሜ 12፥6፤ 1ቆሮ 12፥10፤ 1ቆሮ 13፥2:8፤ 1ቆሮ 14፥3:6:29-37 ይመ፤

ሌም ወደ አንጾኪያ ወረዱ፤ 28ከእነርሱም
አንዱ አጋቦስ የተባለው ተነሥቶ በዓለም
ሁሉ ታላቅ ራብ እንደሚሆን መንፈስ ቅዱስ
አስመልክቶት ተናገረ፤ ይህም በቀላውዴ
ዎስ ቄሳር ዘመን ተፈጸመ:: 29ደቀ መዛሙ
ርትም እያንዳንዳቸው ዐቅማቸው በፈቀደ
መጠን አዋጥተው በይሁዳ የሚኖሩትን ወን
ድሞች ለመርዳት ወሰኑ፤ 30ርዳታውንም
በበርናባስና በሳውል እጅ ለሽማግሌዎቹ
በመላክ፣ ይህንኑ አደረጉ::

## ጴጥሮስ ከእስር ቤት በታምር ወጣ

12 በዚያ ዘመን ንጉሡ ሄሮድስ አንዳ
ንድ የቤተ ክርስቲያን አባላትን
እያሳደደ ያስጨንቅ ነበር፤ 2የዮሐንስንም
ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ አስገደለ:: 3ይህ
አድራጎቱ አይሁድን ደስ እንዳሰኛቸው ባየ
ጊዜ፣ ጴጥሮስን ደግሞ አስያዘው፤ ይህም
የሆነው በቂጣ በዓል ሰሞን ነበር:: 4ጴጥሮ
ስን ወህኒ ቤት ካስገባው በኋላ፣ አራት አራት
ወታደሮች እየሆኑ እንዲጠብቁት በአራት
ፈረቃ ለተመደቡ ወታደሮች አስረከበው፤
ይህን ያደረገውም የፋሲካ በዓል ካለፈ
በኋላ ሕዝብ ፊት አውጥቶ ሊያስፈርድበት
አስቦ ነው::

5ጴጥሮስም በዚህ መሠረት እስር ቤት
ተጣለ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ግን ስለ እርሱ
አጥብቃ ወደ እግዚአብሔር ትጸልይ ነበር::

6ሄሮድስም ጴጥሮስን ሕዝቡ ፊት ሊያቀ
ርበው አስቦ ሳለ፣ ጴጥሮስ በዚያው ሌሊት
በሁለት ሰንሰለት ታስሮ፣ ከሁለት ወታደሮች
መካከል ተኝቶ ነበር፤ የወህኒ ቤት ጠባቂ
ዎችም እስር ቤቱ በር ላይ ቆመው ነበር::
7የጌታ መልአክም ድንገት ታየ፤ በክፍሉም
ውስጥ ብርሃን በራ፤ መልአኩም የጴጥሮስን
ጐን መታ አድርጎ ቀሰቀሰውና፣ "ቶሎ ተነ
ሣ!" አለው፤ በዚህ ጊዜ ሰንሰለቶቹ ከእጆቹ
ወደቁ::

8መልአኩም፣ "ልብስህን ልበስ፤ ጫማህንም
አድርግ' አለው:: ጴጥሮስም እንደታዘዘው
አደረገ:: መልአኩም ቀጥሎ፣ "መደረቢያህን
ከላይ ጣል አድርገህ ተከተለኝ" አለው:: 9ጴ
ጥሮስም ተከትሎት ከእስር ቤት ወጣ፤
ነገር ግን ራእይ የሚያይ መስለው እንጂ
መልአኩ የሚያደርገው ነገር በእውን መሆኑን
አላወቀም ነበር:: 10የመጀመሪያውንና ሁለተ
ኛውን ዘብ ዐልፈው ወደ ከተማዪቱ በሚወ
ስደው መንገድ ላይ ወዳለው የብረት መዝጊያ
ዘንድ ደረሱ:: መዝጊያውም ራሱ ዐውቆ ተከፈ
ተላቸው፤ እነርሱም ወጥተው ሄዱ፤ አንዲት
ስላች መንገድ እንዳለፉም ወዲያው መል
አኩ ተለየው::

11ጴጥሮስም ሲረጋጋ፣ "ጌታ መልአኩን ልኮ
ከሄሮድስ እጅና አይሁድ ካሰቡብኝ ሁሉ
እንዳወጣኝ አሁን ያለ ጥርጥር ዐወቅሁ" አለ::

12ይህን ከተረዳ በኋላም፣ ብዙ ሰዎች ተሰ
ብስበው በአንድነት ወደሚጸልዩበት፣ ማር
ቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ
ማርያም ቤት ሄደ:: 13እዚያ ደርሶ የውጭ
ውን በር ባንኳኳ ጊዜ፣ ሮዳ የተባለች አን
ዲት የቤት ሠራተኛ ማን እንደ ሆነ ለማጣ
ራት ወደ በሩ ሄደች:: 14የጴጥሮስ ድምፅ
መሆኑንም ባወቀች ጊዜ፣ በጣም ከመደሰቷ
የተነሣ በሩን ሳትከፍት ሮጣ በመመለስ፣
ጴጥሮስ በሩ ላይ ቆሞ እንደሚገኝ ተናገረች::

11፥28 ማቴ24፥14፤ ሐሥ18፥2፤21፥10
11፥29 ቀሉ1:12: 26፤ሐሥ1፥16፤ሮሜ 15፥26፤ 2ቆሮ8፥1-4፤ 9፥2
11፥30 ሐሥ4፥36፤ 12፥25፤14፥23፤15፥2: 22፤20፥17: 1ጢሞ5፥17፤ ቲቶ 1፥5፤ ያዕ5፥14፤ 1ጴጥ5፥1፤2ዮሐ1
12፥1 ማቴ14፥1
12፥2 ማቴ4፥21፤ ማር10፥39
12፥3 ዘፀ12፥15፤ 23፥15፤ሐሥ20፥6፤ 24፥27፤25፥9
12፥4 ዮሐ11፥55
12፥5 ሐሥ1፥14፤ ሮሜ15፥30:31፤ ኤፌ6፥18
12፥6 ሐሥ21፥33
12፥7 መዝ107፥14፤ ሐሥ5፥19፤ 16፥26
12፥9 ሐሥ9፥10
12፥10 ሐሥ5፥19፤ 16፥26
12፥11 መዝ34፥7፤ ዳን3፥28፤6፥22፤ሉቃ 15፥17፤2ቆሮ1፥10፤ 2ጴጥ2፥9
12፥12 ቊ5:25፤ሐሥ 13፥5:13፤15፥37:39፤ ቈላ4፥10፤ 2ጢሞ 4፥11፤ፊሞ24፤ 1ጴጥ 5፥13
12፥13 ዮሐ18፥16፡ 17
12፥14 ሉቃ24፥41

እንዲሁም የዮና 3፥2፤ ዘካ 1፥1 ኤፌ 4፥11 ማብ ይመ)::

11፥28 *አጋቦስ* በኋላ ጊዜ፣ ጳውሎስ እንደሚታሰር ትንቢት የተናገረ ሰው ነበር (21፥10):: በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንደም ናየው የነቢያት ተግባር ወደፊት የሚሆነውን አስቀድሞ መናገር ብቻ ሳይሆን (ቊ27፤21፥9-10)፣ መልእክቱንም ለሚመለከተው በቀጥታ ማድረስ ነበር (15፥32)::

11፥30 *ለሽማግሌዎቹ፤* ቃሉ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ላይ መጀመሪያ የተጠቀሰው እዚህ ላይ ነው (የ1ጢሞ 3፥1፤ 5፥17 ማብ ይመ):: ሐዋርያት እዚህ ላይ ያለመጠቀሳቸው ምክ ንያት በዚህ ጊዜ ከኢየሩሳሌም ስለወጡ ሊሆን ይችላል::

12፥1 *በዚያ ዘመን፤* በምዕራፍ 12 ላይ የተመዘገቡት ድር ጊቶች፣ ሄሮድስን የሚመለከቱትን ነገሮች በአንድነት የሰበሰቡአ ቸው ሲሆን፣ የጊዜ ቅደም ተከተልን ግን በሚገባ የጠበቁ አይ ደሉም የሚሉ አንዳንድ ሰዎች አልታጡም:: ለምሳሌ፣ በርናባስና ሳውል ኢየሩሳሌም የደረሱት (11፥30)፣ ሄሮድስ ክርስቲያኖችን ማሳደድ ከጀመረና ጴጥሮስ ከእስር ቤት ከወጣ በኋላ ሊሆን ይችላል:: ሄሮድስ የሞተው በ44 ዓ.ም ስለ ሆነ እነዚህ ድርጊቶች የተፈጸሙት በ43 ዓ.ም ሳይሆን አይቀርም:: በዚህ አመለካከት በ11፥28 ላይ የተጠቀሰው ራብ የተከሠተው፣ ከሄሮድስ ሞት በኋላ (ቊ23)፣ በ46 ዓ.ም ገደማ ሊሆን ይችላል:: ሌሎች ደግሞ ሁኔታዎችን እንደዚህ አቀነባብሮ ማቅረብ አስፈላጊ አይደለም ይላሉ:: ስለዚህ በ11፥30 የተመለከተው ርዳታ የተላከው በ44 ዓ.ም ሄሮድስ ከመሞቱ በፊት ነው፤ በርናባስና ሳውል ርዳታውን አድርሰው የተመለሱትም (ቊ25)፣ ሄሮድስ ከሞተ በኋላ ነበር:: በመጀመሪያው አመለካከት በገላ 2፥1-10 ላይ የተመለከተው የኢ የሩሳሌም ጒብኝት፣ ራቡ ምን ሁኔታ ላይ እንደደረሰ ለማወቅ የተደረገ ጒዞ ነበር (ቊ 25፤ 11፥30):: በኋለኛው አመለካከት ደግሞ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ለተከሠተው ችግር መፍትሔ ለማግኘት ወደ ኢየሩሳሌም የሄዱበት ጒዳይ ሲሆን፣ ይህም በ15፥1-29 የሚገኘው ነው:: *ንጉሡ ሄሮድስ፤* ቀዳማዊ አግሪጳ ሲሆን፣ እርሱም የትልቁ ሄሮድስ የልጅ ልጅ (የማቴ 2፥1፤ 14፥1 ማብ ይመ)፣ የአርስጦቡሎስ ልጅ፣ እንዲሁም የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ ያስቈረጠውና (ማቴ 14፥3-12) ጌታ ኢየሱስን የመረመረው (ሉቃ 23፥8-12) የሄሮድስ አንቲጳስ ወንድም ልጅ ነው:: አጎቱ አንቲጳስ በተሰደደ ጊዜም የእርሱን ክፍለ ግዛት በተ ጨማሪም የፊልጶስንና የሊሳንዮስንም ክፍለ ግዛቶች አጠቃሎ እን ዲይዝ ተደርጎአል (ሉቃ 3፥1 ይመ):: ከዚህም ሌላ በ41 ዓ.ም ይሁ ዳንና ሰማርያን ጨምሮ ገዝቶአል::

12፥2 *ያዕቆብን፤* የሐዋርያው የዮሐንስ ወንድም፣ የዘብዴዎስ ልጅ (ማቴ 4፥21):: የሞተውም ጌታ ሞቶ ከተነሣ ከ10 ዓመት በኋላ ነው፤ ጌታ ኢየሱስም መከራ እንደሚደርስባቸው አስጠንቅቋቸው ነበር (ማቴ 20፥23):: *በሰይፍ አስገደለ፤* እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ራሱን አስቈረጠው ማለት ነው::

12፥3 *በቂጣ በዓል፤* የሉቃ 22፥1 ማብ ይመ::

12፥4 *አራት አራት...እየሆኑ፤* የሌሊቱ ጥበቃ በአራት ክፍለ ጊዜ የተመደበ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ ክፍለ ሌሊት አራት ጠባቂ ዎች ዘብ እንዲቆሙ ይደረግ ነበር:: *የፋሲካ በዓል፤* በሌላ አነጋ ገር፣ ይህ ስም አንዳንድ ጊዜ የፋሲካውን ሰሞን በሙሉ ሊያመ ለክት ይችላል ( የሉቃ 22፥1 ማብ ይመ)::

12፥7 *ብርሃን በራ፤* የጌታ ክብር መገለጥ (ሉቃ 2፥9 ይመ)::

12፥9 *ከእስር ቤት፤* ከቤተ መቅደሱ በስተ ሰሜን ምዕራብ በኩል ሲሆን፣ የአንጦንያ ግምብ ሳይሆን አይቀርም፤ ይህም በኋ ለኛው ጊዜ ጳውሎስ የታሰረበት፣ "የወታደሮች መኖሪያ" ሳይሆን አይቀርም (21፥34 ይመ)::

12፥12 *ማርቆስ...ዮሐንስ!* የቊ25 ማብ ይመ:: *ማርያም፤* የበርናባስ አክስት ናት (ቈላ 4፥10 ይመ):: ቤቷም የክርስቲያኖች መሰብሰቢያ ነበር፤ የጌታ እራት የቀረበበት፣ የላይኛው ደርብም እዚሁ ሳይሆን አይቀርም (ማር 14፥13-15፤ ሐሥ 1፥13 ይመ):: በ4፥31 ላይ የተገለጸው የጸሎት ቦታም ይኸው ይመስላል::

12፥13 *ሮዳ፤* ቅጥር የቤት ሠራተኛ ስትሆን፣ ለቤተሰ

15ሰዎቹም፣ “አብደሻል እንዴ!” አሏት፤
እርሷ ግን ይህንኑ ደጋግማ በነገረቻቸው ጊዜ፣
“እንግዲያውስ የእርሱ መልአክ ነው” አሉ።
16ጴጥሮስ ግን በር ማንኳኳቱን ቀጠለ፤
እነርሱም በሩን ከፍተው ባዩት ጊዜ ተገረሙ።
17እርሱም ዝም እንዲሉ በእጁ ጠቅሶ፣ ጌታ
ከእስር ቤት እንዴት እንዳወጣው አስረዳቸው፣
“ስለ ሁኔታው ለያዕቆብና ለወንድሞች ንገሯ
ቸው” አላቸው፤ ከዚያም ወደ ሌላ ስፍራ ሄደ።
18በማግስቱም ጠዋት ወታደሮቹ፣ “ጴጥሮስ
የት ገባ?” እያሉ በመካከላቸው ትልቅ ትር
ምስ ተፈጠረ። 19ሄሮድስም ጴጥሮስን አስፈ
ልጎ ባጣው ጊዜ፣ ዘብ ጠባቂዎቹን በጥብቅ
ከመረመረ በኋላ እንዲገደሉ አዘዘ።

## የሄሮድስ አሟሟት

ከዚያም ሄሮድስ ከይሁዳ ወደ ቂሳርያ
ወርዶ እዚያ ተቀመጠ። 20እርሱም ከጢ
ሮስና ከሲዶና ሰዎች ጋር ጥለኛ ነበር፤ አገ
ራቸው ምግብ የሚያገኘው ከንጉሡ ግዛት
ስለ ነበር፣ የንጉሡን ባለሟል የብላስጦስን
ድጋፍ ካገኙ በኋላ፣ አንድ ላይ ሆነው ከንጉሡ
ጋር ለመታረቅ ጠየቁ።
21በቀጠሮውም ቀን ሄሮድስ ልብሰ መንግ
ሥቱን ለብሶ በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ፤ ለሕዝ
ቡም ንግግር አደረገ። 22ሕዝቡም፣ “ይህስ
የአምላክ ድምፅ እንጂ የሰው አይደለም!”

12፥15 ማቴ18፥10
12፥17 ሐሥ1፥16፤ 13፥16፤15፥13፤19፥33፤ 21፥40
12፥19 ሐሥ8፥40፤ 16፥27
12፥20 1ነገ5፥9፤ 11፤ሕዝ27፥17፤ ማቴ 11፥21
12፥23 1ሳሙ25፥38፤ 2ሳሙ24፥16፤ 17፤2ነገ19፥35፤ ሐሥ 5፥19
12፥24 ሐሥ6፥7፤ 19፥20፤ዕብ4፥12
12፥25 ቊ12፤ሐሥ 4፥36፤11፥30
13፥1 ማቴ14፥1፤ 27፥32፤ሐሥ4፥36፤ 11፥19፡27፤ኤፌ4፥11
13፥2 ሐሥ8፥29፤ 9፥15፤14፥26፤22፥21
13፥3 ሐሥ6፥6፤ 14፥26
13፥4 ቊ2፡3፤4፥36
13፥5 ሐሥ9፥20፤ 12፥12፤ ዕብ4፥12

ብለው ጮኹ። ሄሮድስም ለእግዚአብሔር ክብር
ስላልሰጠ የጌታ መልአክ ወዲያው መታው፤
በትልም ተበልቶ ሞተ።
24የእግዚአብሔር ቃል ግን እያደገና እየሰፋ
ሄደ።
25በርናባስና ሳውልም ተልእኮአቸውን
ፈጽመው ከኢየሩሳሌምα ተመለሱ፤ ማርቆስ
የተባለውን ዮሐንስንም ከእነርሱ ጋር ይዘ
ውት መጡ።

## በርናባስና ሳውል ተላኩ

13 በአንጾኪያ ባለችው ቤተ ክርስቲያን
ነቢያትና መምህራን ነበሩ፤ እነርሱም፦
በርናባስ፣ ኒጌር የተባለው ስምዖን፣ የቀሬ
ናው ሉክዮስ፣ የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄ
ሮድስ አብሮ አደግ የነበረው ምናሔና ሳውል
ነበሩ። 2እነዚህም ጌታን እያመለኩና እየጾሙ
ሳሉ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ “በርናባስንና ሳውልን
እኔ ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ” አለ። 3እነ
ርሱም ከጾሙና ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን
ጭነው አሰናበቷቸው።

## በርናባስና ሳውል በቆጵሮስ

4በርናባስና ሳውልም በመንፈስ ቅዱስ ተል
ከው ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ፤ ከዚያም በመ
ርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄዱ። 5ስልማና በደረ
ሱም ጊዜ በአይሁድ ምኵራቦች የእግዚአብሔርን

α25 አንዳንድ ቅጆች ወደ ኢየሩሳሌም ይላሉ።

ቡም ሆነ ለቤተ ክርስቲያኗ በጎ አመለካከት ነበራት።

12፥15 *የእርሱ መልአክ* እያንዳንዱ ሰው የሚያገለግለው ጠባቂ መልአክ አለው የሚል እምነት መኖሩን ያንጸባርቃል (ከማቴ 18፥10፤ ዕብ1፥14 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህም መልአክ ዐልፎ ዐልፎ በሚጠብቀው ሰው መልክ የሚገለጥ መሆኑን ያሳያል የሚል ሐሳብ የያዘ ነው።

12፥16 *ተገረሙ*፤ “ስለ እርሱ አጥብቀው ወደ እግዚአብሔር ቢጸልዩም” (ቍ5)፣ መገረማቸው አልቀረም።

12፥17 *ለያዕቆብና*፤ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ የነበረው የጌታ ወንድም ነው (ገላ1፥19)፤ የዮሐንስ ወንድም ያዕቆብ ቀደም ሲል ተገድሎአል (ቍ2 ይመ)።

12፥19 *ቂሳርያ*፤ የሮማ መንግሥት እንደራሴ መቀመጫ ብቻ ሳትሆን፣ እንደራሴዎች ወደ ይሁዳ ምድር ባልተላኩበት ወቅት አግሪጳ የግዛቱ ዋና ከተማ አድርጓት ነበር (የ8፥40፤ 10፥1 ማብ ይመ)።

12፥20 *ከጢሮስና ከሲዶና*፤ የፊንቄ (የአሁኗ ሊባኖስ) ዋና ከተሞች ነበሩ፤ እህል የሚያገኙትም ከገሊላ አውራጃ ነበር። *የብላስጦስ*፤ የግምጃ ቤት ኀላፊ ነው ወይም አይታወቅም።

12፥21 *በቀጠሮውም ቀን*፤ ስለ ቀላውዴዎስ ቄሳር ክብር ሄሮድስ ያዘጋጀው በዓል ነው። *ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ*፤ ታሪክ ጸሓፊው ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ሄሮድስ ያንጊዜ የለበሰው ልብስ ከብር የተሠራ ሆኖ እጅግ የሚያብረቀርቅ እንደ ነበር ገልጾአል። ሕዝቡ “አምላክ ነህ” ባሉት ጊዜ፣ ሄሮድስ አላስተባበለም። ብርቱ ሥቃይ ይዞ ስላስጨነቀው ወዲያውኑ ከዚያ ወጣ፤ በአምስተኛውም ቀን ሞተ።

12፥23 *የጌታ መልአክ*፤ የቍ7 ማብ ይመ። *በትልም ተበልቶ*፤ ሄሮድስ፣ “አምላክ ነህ” ሲሉት ይህንኑ ሳያስተባብል በመቅረቱ በዚህ አስከፊ ሁኔታ ሊሞት በቅቶአል፤ በሌላም አንጻር ሲታይ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን በማሳደዱ አምላክ እንደ ሥራው ሳይከፍለው እንዳልቀረ ይታመናል።

12፥24 *የእግዚአብሔር ቃል…እየሰፋ ሄደ*፤ ይህ ሦስተኛው የስብከተ ወንጌሉ መስፋፋት አጠቃላይ ዘገባ ነው (6፥7፤ 9፥31 ይመ)። ከዚህም በኋላ የሚቀርቡ ሦስት ዘገባዎች አሉ (16፥5፤19፥20፤28፥31)።

12፥25 *ማርቆስ…ዮሐንስንም*፤ ቍ12 ይመ። ኢየሱስ በተያዘባት ሌሊት ሮጦ ያመለጠው ጐበዝ እርሱ ሳይሆን አይቀርም (ማር 14፥51-52)። ሁለተኛውን ወንጌል፣ ማለት የማርቆስን ወንጌል የጻፈውም እርሱ ነው፤ በበርናባስና በሳውል የመጀመሪያ ሐዋርያዊ ጕዞም አብሮአቸው ነበር (የ15፥38-39 ማብ ይመ)።


13፥1 *ነቢያትና*፤ የ11፥27 ማብ ይመ። በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረው በመንፈስ ቅዱስ የመመራት ልዩ ስጦታ (ዘዳ 18፥18-20፤ 2ጴጥ 1፥21) በአዲስ ኪዳንም ዘመን አልተቋረጠም (2፥17-18፤ 1ቆሮ 14፥29-32፤ ኤፌ 3፥5)። ጳውሎስ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ሲዘረዝር ነቢያትን ከሐዋርያት ቀጥሎ ያስቀምጣል (1ቆሮ 12፥28-29፤ ኤፌ2፥20፤ 4፥11 ይመ፤ ከሉቃ 11፥49፤ ከሮሜ 12፥6፤ ከ1ቆሮ 12፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። *መምህራን*፤ 12፥26፤ 15፥35፤ 18፥11፤ 20፥20፤ 28፥31፤ 1ቆሮ12፥28-29፤ ኤፌ 4፥11 ይመ። *በርናባስ… ሳውል*፤ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበሩ፤ ስማቸውም በዚህ ቅደም ተከተል መሠረት መቀመጡ እንደ አገልግሎታቸው ክብደት መጠን ሊሆን ይችላል። *በርናባስ*፤ የ4፥36 ማብ ይመ። ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መጀመሪያ ወደ አንጾኪያ ተልኮ ነበር (11፥22)፤ በቅርቡም የተሰበሰበውን ምጽዋት ወደ ኢየሩሳሌም አድርሶ ተመልሶአል (12፥25)፤ በአንጾኪያም የታወቀ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር። *ኒጌር የተባለው ስምዖን*፤ “ስምዖን” የሚለው ስም አስተዳደጉ በአይሁድ ዘንድ መሆኑን ሲያመለክት፣ “ኒጌር” የሚለው የላቲን ቃል ደግሞ መልኩ ጥቁር መሆኑን የሚገልጽ ነው፤ *የቀሬናው ሉክዮስ*፤ “ሉክዮስ” የላቲን ስም ነው፤ ወደ አንጾኪያ ከመጡት ወንጌላውያን አንዳንዶቹ ከሊቢያ ዋና ከተማ ከቀሬና (11፥20)፣ (6፥9 እና ማብ ይመ) ነበሩ። *ምናሔና*፤ የሄሮድስ አንቲጳስ አብሮ አደግ ስለሆነ፣ የሄሮድስ ሐሳብና ሥራ ምን እንደ ነበር ተናግሮ ሊሆን ይችላል (ሉቃ 9፥7-9 ይመ)።

13፥2 *ጌታን እያመለኩና እየጾሙ ሳሉ*፤ መጀመሪያው የጳውሎስ ሐዋርያዊ ጕዞ በጉባኤ ታቅዶ የጸደቀ ሳይሆን፣ መሪዎቹ በአምልኮ ላይ ሳሉ መንፈስ ቅዱስ እንዳሣሠቶአቸው ነው (ቍ4 ይመ)። መልእክቱ በነቢያት አማካይነት ከመንፈስ ቅዱስ ሊሆን ይችላል።


13፥3 *እጃቸውን ጭነው*፤ ለተባለው ሥራ ሁለቱን ለመለየት ነው (ስለ ተልእኮው መከናወን 14፥26 ይመ)። እንዲህ ዐይነቱም ሹመት በጾምና በጸሎት ይደገፋል (14፥23 ይመ፤ ከሉቃ 2፥37 ጋር ያነጻጽሩ)።

13፥4 *ሴሌውቅያ*፤ ከባሕር ጠረፍ 25 ኪ.ሜ. ያህል ገባ ብላ ለአንጾኪያ ከተማ አገልግሎት የምትሰጥ የወደብ ከተማ። *ቆጵሮስ*፤ አያሌ አይሁድ የሚኖሩባት ደሴት፤ ቀደም ሲል ወንጌልም ተሰብኮላታል (11፥19-20፤ የ11፥19 ማብ ይመ)።


# የወንጌል መስፋፋት




5.
4.
3.
2
1.
1.
በ35 ዓ.ም
ቅፍርናሆም
ቂሣርያ
ሰማርያ
ኢዮጴ
ልድያ
ኢየሩሳሌም
ማይልስ
ኪ.ሜ


ማይልስ 0 50 100 150 200
ኪ.ሜ 0 50 100 150 200 250 300
2.በ40 ዓ.ም
ተርሴስ
አንጾኪያ
ሰልሞን
ቆጵሮስ
ጳፉ
ሲዶና
ጢሮስ
ኢየሩሳሌም

3.
በ48 ዓ.ም
የጳውሎስ የመጀመሪያ
የወንጌል ጉዞ
ጢርስ
የጵስድያ አንጾኪያ
ኤፌሶን
ሉዶቅያ
ቈላስይስ
ሚሊጢን
ልስጥራ
ኢቆንዮን
ደርቤ
ቆጵሮስ

ፊልጵስዮስ
ተሰሎንቄ
ቤርያ
4.
በ52 ዓ.ም የጳውሎስ
ሁለተኛውና ሦስተኛው
የወንጌል ጉዞ
ጢሮአዳ
አቴና
ቆሮንቶስ
ኤፌሶን
ቀርጤስ
ማይልስ 0 50 100
ኪ.ሜ 0 50 100 150 200

5.
በ60 ዓ.ም ጳውሎስ
ወደ ሮም ያደረገው
ጉዞ
ሮም
ፑቲዮሉስ
ሬጊዩም
ሲሲሊያ
ሰራኩስ

ቃል ሰበኩ፤ ዮሐንስም አብሮአቸው ሆኖ ይረ
ዳቸው ነበር።
[6]የቆጵሮስን ደሴት ከዳር እስከ ዳር አቋ
ርጠው ጳፉ በደረሱ ጊዜ፣ በርያሱስ የተባለ
አንድ አይሁዳዊ ጠንቋይና ሐሰተኛ ነቢይ
አገኙ፤ [7]እርሱም ሰርግዮስ ጳውሎስ ከተባ
ለው አስተዋይ አገረ ገዥ ጋር ነበረ። ይህ
አገረ ገዥ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት
ፈልጎ በርናባስንና ሳውልን አስጠራቸው።
[8]ጠንቋዩ ኤልማስ ግን፣ የስሙ ትርጒም
እንዲህ ነበርና፣ አገረ ገዡ እንዳያምን ለማደ
ናቀፍ ስለ ፈለገ ተቃወማቸው። [9]ጳውሎስ
የተባለውም ሳውል በመንፈስ ቅዱስ ተሞ
ልቶ፣ ትኵር ብሎ ተመለከተውና እንዲህ
አለው፤ [10]"አንተ የጽድቅ ሁሉ ጠላት፣ ተንኰ
ልንና ክፋትን ሁሉ የተሞላህ የዲያብሎስ
ልጅ! የጌታን ቀና መንገድ ከማጣመም አታ
ርፍምን? [11]አሁንም የጌታ እጅ በአንተ ላይ
ነው፤ ዕውር ትሆናለህ፤ ከእንግዲህ የፀሐይን
ብርሃን ለአንድ አፍታ እንኳ አታይም።"
ወዲያውም ጭጋግና ጨለማ በላዩ ወረደ፤
እጁን ይዞ የሚመራውንም ሰው ለመፈለግ
ወዲያ ወዲህ ይል ጀመር። [12]አገረ ገዡም የሆ
ነውን ነገር ባየ ጊዜ፣ በጌታ ትምህርት በመ
ደነቅ አመነ።

## በርናባስና ጳውሎስ በጲስድያ

[13]ጳውሎስና ጓደኞቹ ከጳፉ ተነሥተው
በጵንፍልያ ወደምትገኘው ወደ ጴርጌን ሄዱ፤
ዮሐንስም ከእነርሱ ተለይቶ ወደ ኢየሩሳሌም
ተመለሰ። [14]እነርሱ ግን ከጴርጌን ተነሥተው
በጲስድያ ውስጥ ወዳለችው ወደ አንጾኪያ
ሄዱ፤ በሰንበት ቀንም ወደ ምኵራብ ገብተው

13፥6 ማቴ7፥15፤ ሐሥ8፥9
13፥7 ቍ8:12፤ ሐሥ 18፥12፤19፥38
13፥8 ቍ7፤ ኢሳ 30፥11፤ ሐሥ6፥7፤ 8፥9
13፥9 ሉቃ1፥15
13፥10 ሆሴ14፥9፤ ማቴ13፥38፤ዮሐ8፥44
13፥11 ዘፍ19፥10: 11፤ዘፀ9፥3፤1ሳሙ5፥6:7፤2ነገ6፥18፤ መዝ 32፥4
13፥12 ቍ7
13፥13 ቍ6፤ ሐሥ 2፥10፤12፥12
13፥14 ቍ27:42: 44፤ሐሥ9፥20፤14፥19: 21፤16፥13፤18፥4

13፥5 *ሰልማና፤* በቆጵሮስ ደሴት ምሥራቅ ጠረፍ ላይ፣ ከዛሬዋ ፋማጉስታ አጠገብ ምትገኝ ከተማ ናት። *ዮሐንስም፤* ዮሐንስ ማርቆስ የበርናባስ አክስት (የማርያም) ልጅ ነው ቈላ 4፥10፤ እንዲሁም የ12፥25 ማብ ይመ)።

13፥6 *ጳፉ፤* በቆጵሮስ ደሴት ምዕራብ ጠረፍ ላይ፣ ከሰልማና 160 ኪ.ሜ. ርቃ ትገኝ ነበር። ለሮም ግዛትም አስተዳደርዋና ከተማ ነበረች። *ባርያሱስ፤* "ባር" የሚለው ቃል የአራማይክ ሲሆን፣ ትርጒሙም "የ...ልጅ" ማለት ነው፤ "ኢየሱስ" የሚለውም የግሪክ ቃል ሲሆን፣ ትርጒሙ አዳኝ ማለት ነው፤ ስለዚህ "ባር የሱስ" ማለት የ"ኢየሱስ ልጅ" የሚለውን ትርጒም ይይዛል።

13፥7 *አገረ ገዥ፤* ቆጵሮስ በሮም ምክር ቤት የበላይ ጠባቂነት የምትተዳደር አገር በመሆኗ፣ በቅርብ ሆኖ የሚያስተዳድራት ገዥ ተሰይሞላት ነበር።


13፥8 *ኤልማስ፤* ሴማዊ ስም ሲሆን፣ ትርጒሙ ጠንቋይ ወይም ምትሀተኛ ወይም ደግሞ ዐዋቂ ማለት ነው፤ ራሱ ሰውዬው ለራሱ የሰጠው ስም ሳይሆን አይቀርም።

13፥9 *ጳውሎስ የተባለውም ሳውል፤* ጳውሎስ ማለት "ትንሽ" ማለት ሲሆን፣ ሳውል ማለት "ከእግዚአብሔር የተለመነ" ማለት ነው። መቼም መጠሪያ ስም መኖሩ የተለመደ ነው፤ ሳውል (ዕብራዊና የአይሁድን ወግና ሥርዐት መሠረት ያደረገ ዕብራዊ ስም ነው ጳውሎስ በኋላ የተገኘ ስም ሲሆን) የግሪክን ሥልጣኔና ባህል መሠረት ያደረገ፣ ሮማዊ ስም ነው። ከአሁን በኋላ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሳውልን ጳውሎስ እያለ ሲጠራው እናገኛለን። ይህ ስያሜ የመጣው ሳውል ለሰርግዮስ ጳውሎስ ወንጌልን ሰብኮ በማሳመኑ ሊሆን ይችላል (ቍ12) ወይም ሳውል ወንጌልን ለአሕዛብ መስበክ መጀመሩን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ የስም ቅደም ተከተሉ ከ"በርናባስና ከሳውል" ወደ "ጳውሎስና በርናባስ" ሲለወጥ እናያለን፤ ይሁን እንጂ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ ደግሞ ቅደም ተከተሉ፣ "በርናባስና ጳውሎስ" (15፥12) ይሆናል።

13፥12 *አመነ፤* ባየው ታምርና በሰማው የወንጌል ቃል ተረትቶአል ማለት ነው።

13፥13 *በጵንፍልያ...ጴርጌን፤* ጴርጌን በታናሹ እስያ ጠረፍ ላይ ለምትገኘው ለጵንፍልያ አውራጃ ዋና ከተማ ነበረች። *ዮሐንስም...ተለይቶ፤* ዮሐንስ ማርቆስ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሰበት ምክንያት በግልጽ የሚታወቅ ባለመሆኑ፣ የሚከተሉት ሐሳቦች ምክንያት ሆነው ቀርበዋል፤ (ሀ) ዮሐንስ ማርቆስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ ናፍቆት ስላደረበት፣ (ለ) ጳውሎስ በመታመሙ የነበረው ዕቅድ ተለውጦ ወደ ገላትያ መሄድ ስላስፈለገ፣ (ሐ) የበርናባስ መሪነት ወደ ጳውሎስ በመተላለፉ። ጳውሎስ በማርቆስ መለየት ቅሬታ እንዳደረበት በሌላ ስፍራ፣ ተጽፎ ይገኛል (15፥37-39)።

13፥14 *በጲስድያ፤* የ14፥24 ማብ ይመ። *አንጾኪያ፤* ታላቁ እስክንድር ከሞተ በኋላ እርሱን ተክቶ በሶርያ በነገሠው በአንጥያኮስ ስም ተሰይማለች። ከጴርጌን 176 ኪ.ሜ. ርቃ የምትገኝ ስትሆን፣ ከተዋቡ አውራ ጐዳናዎች ጋር የተያያዘች የንግድ ማእከል ነበረች፣ የሮም ቅኝ ግዛት እንደመሆኗ መጠን፣ የተወሰነ ቍጥር ያላቸው በጡረታ የተገለሉ ወታደሮች መኖሪያ አድርገዋታል። እነዚህ ወታደሮቹ መሬት በነጻ፣ እንዲሁም ሙሉ የሮማ ዜግነት




**የጳውሎስ የመጀመሪያ የወንጌል ጒዞ**
46-48 ዓ.ም (ሐሥ 13:4-18:28)

ተቀመጡ:: 15የሕግና የነቢያት መጻሕፍት
ከተነበቡ በኋላ፣ የምኵራብ አለቆች፣ “ወንድ
ሞች ሆይ፤ ሕዝቡን የሚመክር ቃል ካላችሁ
ተናገሩ” ሲሉ ላኩባቸው::
16ጳውሎስም ተነሥቶ በእጁ በመጥቀስ
እንዲህ አለ፤ “የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤ ደግ
ሞም እናንት እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሁሉ፤
አድምጡ:: 17የዚህ የእስራኤል ሕዝብ አምላክ፣
አባቶቻችንን መረጣቸው፤ በግብፅ ምድር
እያሉም ከፍ ከፍ አደረጋቸው፤ በኀያል ክን
ዱም ከዚያ አወጣቸው:: 18አርባ ዓመት ያህልም
በበረሓ ታገሡቸው[*]፤ 19በከነዓን ምድር የነበሩት
ንም ሰባት መንግሥታት አጥፍቶ፣ ምድራቸ
ውን ለገዛ ሕዝቡ ርስት አድርጎ አወረሳ
ቸው:: 20ይህም ሁሉ የተፈጸመው በአራት
መቶ አምሳ ዓመት ያህል ጊዜ ውስጥ ነበር::
“ከዚህ በኋላ፣ እስከ ነቢዩ ሳሙኤል ዘመን
ድረስ መሳፍንትን ሰጣቸው:: 21ከዚያም ሕዝቡ
ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው ለመኑት፤ እግዚአ
ብሔርም ከብንያም ወገን፣ የቂስን ልጅ ሳኦ
ልን ሰጣቸው፤ እርሱም አርባ ዓመት ገዛቸው::
22ሳኦልንም ከሻረው በኋላ፣ ዳዊትን አነገሠ
ላቸው፤ ስለ እርሱም፣ ‘እንደ ልቤ የሆነና
እኔ የምሻውን ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን
ልጅ ዳዊትን አገኘሁ’ ሲል መሰከረለት::
23እግዚአብሔርም በገባው ቃል መሠረት ከዚህ
ሰው ዘር አዳኝ የሆነውን ኢየሱስን ለእስራ
ኤል አመጣ:: 24ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት፣
ዮሐንስ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ንስሓ ገብ
ተው እንዲጠመቁ ሰብኮላቸው ነበር:: 25ዮሐ
ንስ ተልእኮውን በማጠናቀቅ ላይ ሳለ፣ ‘እኔ
ማን መሰልኋችሁ? እኔ እኮ እርሱ አይደለ
ሁም፤ ነገር ግን የእግሩን ጫማ እንኳ መፍ
ታት የማይገባኝ ከእኔ በኋላ ይመጣል’ ይል
ነበር::
26“እናንት ከአብርሃም ዘር የተወለዳችሁ
ወንድሞች፤ ደግሞም በመካከላችሁ እግዚአ
ብሔርን የሚፈሩ ሁሉ፤ ይህ የድነት መልእ
ክት የተላከው ለሁላችንም ነው:: 27የኢየሩ
ሳሌም ሰዎችና አለቆቻቸው ኢየሱስን አላወ
ቁትም፤ ይሁን እንጂ በየሰንበቱ የሚነ
በበው የነቢያት ቃል እንዲፈጸም በእርሱ
ፈረዱበት:: 28ለሞት የሚያበቃው አንድም
ምክንያት ባያገኙበትም እንኳ ጲላጦስ የሞት
ፍርድ እንዲፈርድበት ተማጸኑት:: 29ስለ እርሱ
የተጻፈውን ሁሉ ከፈጸሙ በኋላ ከተሰቀለ
በት ዕንጨት አውርደው በመቃብር ውስጥ
አስገቡት:: 30እግዚአብሔር ግን ከሙታን አስነ
ሣው:: 31ከገሊላ ጀምሮ እስከ ኢየሩሳሌም
ከእነርሱ ጋር ለነበሩትም ብዙ ቀን ታያቸው፤
እነርሱም አሁን ለሕዝቡ ምስክሮቹ ናቸው::
32“እኛም እግዚአብሔር ለአባቶች ቃል የገ
ባውን የምሥራች ቃል ለእናንተ እንሰብካ
ለን፤ 33ኢየሱስንም ከሙታን በማስነሣቱ ለእ
ነርሱ የገባውን ቃል ለእኛ ለልጆቻቸው ፈጽሞ
አል፤ ይኸውም በሁለተኛው መዝሙር እንዲህ
ተብሎ ተጽፎአል፤

“ ‘አንተ ልጄ ነህ፤
እኔ ዛሬ ወለድሁህ::’[†]

34ደግሞም፣ እርሱ እንዳልበሰበሰና እግዚአብሔርም
ከሙታን እንዳስነሣው ለማረጋገጥ እንዲህ
ብሎአል፤

“ ‘የተቀደሰውንና የታመነውን፣
የዳዊትን በረከት እሰጣችኋለሁ::’

35ስለዚህ በሌላም ስፍራ፣

“ ‘ቅዱስህ መበስበስን እንዲያይ
አትፈቅድም’ ይላል::

36“ዳዊት በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ፈቃድ
ካገለገለ በኋላ አንቀላፍቶአል፤ ከአባቶቹም ጋር
ተቀብሮ ሥጋው በስብሶአል:: 37እግዚአብሔር
ከሙታን ያስነሣው እርሱ ግን መበስበስን
አላየም::
38እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ የኀጢአት
ይቅርታ የሚገኘው በኢየሱስ በኩል መሆኑ
እንደ ተሰበከላችሁ ዕወቁ፤ 39በእርሱ የሚ
ያምን ሁሉ በሙሴ ሕግ በኩል ማግኘት
ያልተቻለውን ጽድቅ ያገኛል:: 40ስለዚህ ነቢ
ያት እንዲህ ብለው የተናገሩት እንዳይደር
ስባችሁ ተጠንቀቁ፤

13፥15 ሐሥ15፥21
13፥16 ሐሥ12፥17
13፥17 ዘፀ6፥6:7፤ ዘዳ7፥6-8
13፥18 ዘኍ14፥33፤ ዘዳ1፥31፤መዝ95፥10፤ ሐሥ7፥36
13፥19 ዘዳ7፥1፤ ኢሱ 19፥51፤ መዝ78፥55፤ ሐሥ7፥45
13፥20 መሳ2፥16፤ 1ሳሙ3፥19:20፤ ሐሥ 3፥24
13፥21 1ሳሙ8፥5: 19፤9፥1:2፤10፥1
13፥22 1ሳሙ13፥14፤ 15፥23:26፤16፥13፤ መዝ89፥20፤ኢሳ44፥ 28፤ኤር3፥15
13፥23 ቍ32፤ 2ሳሙ 7፥11፤22፥51፤ኤር30፥9፤ ማቴ1፥1:21፤ሉቃ2፥11
13፥24 ማር1፥4
13፥25 ማቴ3፥11፤ ዮሐ1፥20:27፤ሐሥ 20፥24
13፥26 ሉቃ3፥8፤ ሐሥ4፥12፤22፥5፤28፥28
13፥27 ማቴ1፥22፤ ሉቃ24፥27፤ሐሥ3፥17
13፥28 ማቴ27፥20- 25፤ሐሥ3፥14
13፥29 ማቴ1፥22፤ ሉቃ18፥31፤23፥53፤ ሐሥ5፥30
13፥30 ማቴ16፥21፤ 28፥6፤ሐሥ2፥24
13፥31 ማቴ28፥16፤ ሉቃ24፥48
13፥32 ኢሳ40፥9፤ 52፥7፤ሐሥ5፥42፤ 8፥35፤10፥36፤14፥7:1 5:21፤17፥18፤26፥6፤ ሮሜ1፥2፤4፥13፤9፥4
13፥33 መዝ2፥7፤ ማቴ3፥17፤ሐሥ2፥24
13፥34 ኢሳ55፥3
13፥35 መዝ16፥ 10፤ሐሥ2፥27
13፥36 2ሳሙ7፥ 12፤1ነገ2፥10፤2ዜና 29፥28፤ማቴ9፥24፤ ሐሥ2፥29
13፥37 ሐሥ2፥24
13፥38 ሉቃ24፥ 47፤ ሐሥ2፥38
13፥39 ዮሐ3፥15፤ ሮሜ3፥28

[*]18 አንዳንድ ቅጆች *ተንከባከባቸውም* ይላሉ::
[†]33 ወይም *አባትህ ሆንኹ*

መብት ከሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ጋር ተሰጥቶአቸው ይኖሩ ነበር:: *ምኩራብ፤* አይሁድ እስከ ፈቀዱለትም ድረስ ጳውሎስ በምኵራብ እየተገኘ መስበክን የዘወትር ተግባሩ አድርጎ ይዞት ነበር (ቍ5፤ 14፥1፤ 17፥1:10:17፤18፥4:19፤19፥8 ይመ):: ይህን የሚያደርግበትም ምክንያት የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ ለማስ ተዋል በመብቃቱ ነው (ቍ46፤ ሮሜ 1፥16፤ 2፥9-10፤ እንዲሁም ሮሜ 9-11 ይመ):: ፈርሀ እግዚአብሔር ያደረባቸውና አንዱን አምላክ ብቻ የሚያመልኩ አሕዛብ እዚያው ከሚያስተምርበት ምኵራብ ይገኙ ስለ ነበር፣ ጳውሎስ ለአይሁድ ወገን በማድላት የአሕዛብ ሐዋርያነቱን ችላ ማለቱም አልነበረም፤ ከዚህም በላይ ምኵራብ ለስብከት የሚሆን በቂ ስፍራ ያለውና፣ ዕቅድን ተከትሎ ለማስተማር የተመቸ ቦታ ነበር፤ ብሉይ ኪዳንን የሚያውቁ ምእመናን የሚገኙትም በምኵራብ ነበር:: እንደ ጳውሎስ ያሉ ከሌላ ስፍራ የመጡ መምህራንን እንዲያስተምሩ መጋበዝም የተለመደ ነበር::

13፥15 *የሕግና የነቢያት፤* ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንዱ ክፍል ከተነበበ በኋላ ትንታኔና ምክር ይቀርብ ነበር:: *አለቆች፤* አንባቢዎችንና ሰባኪዎችን የሚጋብዙ፣ የአምልኮውን ሂደት የሚያቀናጁና ሥነ ሥርዐትን የሚያስከብሩ ነበሩ::

13፥16 *እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሁሉ፤* የ10፥2 ማብ ይመ::

13፥20 *በአራት መቶ አምሳ ዓመት ያህል፤* በግብፅ የኖሩበትን 400 ዓመት (ቍ17፤ የ7፥6 ማብ ይመ)፥ 40 ዓመት ሙሉ በምድረ በዳ የተጓዙበትን ጊዜና ዮርዳኖስን ተሻግረው የከነዓንን ምድር በርስትነት ሲከፋፈሉ የነበሩበትን ወቅት ያካትታል (ኢሱ 14-19 ይመ)::

13፥23 *በገባው ቃል መሠረት፤* ለምሳሌም ኢሳ 11፥1-16 ይመ::

13፥29-31 *ዕንጨት... በመቃብር...እግዚአብሔር...አስነሣው... ምስክሮቹ፤* የ3፥14 ማብ ይመ::

13፥31 *ብዙ ቀን፤* አርባ ቀን (1፥3 ይመ)::

13፥33 *እኔ ዛሬ ወለድሁህ፤* የኢየሱስን ትንሣኤ ያመለክታል (የመዝ 2፥7-9 ማብ ይመ፤ ከሮሜ 1፥4 ጋር ያነጻጽሩ)::

13፥35 *ቅዱስህ መበስበስን እንዲያይ አትፈቅድም፤* በበዓለ ኀምሳ ዕለት ጴጥሮስ ይህንኑ ጠቅሶታል (የ2፥27 ማብ ይመ)::

13፥39 *ጽድቅ፤* ጽድቅ ሁለት ነገሮችን ይይዛል፤ ሀ) የኀጢአትን ይቅርታ ማግኘት (በዚህ ክፍል እንደተነገረው)፤ ለ) የጽድቅ ስጦታ

41“ ‘እናንት ፌዘኞች፤ ተመልከቱ፤
ተደነቁ፤ ጥፉም፤
ማንም ቢነግራችሁ፣
የማታምኑትን ሥራ፣
እኔ በዘመናችሁ እሠራለሁና::” ’

42ጳውሎስና በርናባስ ከምኵራብ ሲወጡ፣
ሰዎቹ ስለዚሁ ነገር በሚቀጥለው ሰንበት
እንዲነግሯቸው ለመኗቸው:: 43ጉባኤው ከተበ
ተነ በኋላም፣ ብዙ አይሁድና ወደ ይሁዲ
ሃይማኖት ገብተው በመንፈሳዊ ነገር የበ
ረቱ ሰዎች፣ ጳውሎስንና በርናባስን ተከተሏ
ቸው፤ እነርሱም አነጋገሯቸው፤ በእግዚአብሔ
ርም ጸጋ ጸንተው እንዲኖሩ መከሯቸው::
44በሚቀጥለውም ሰንበት የከተማው ሕዝብ፣
ጥቂቱ ሰው ብቻ ሲቀር፣ በሙሉ የእግዚአብሔርን
ቃል ለመስማት ተሰበሰቡ:: 45አይሁድም
ብዙ ሕዝብ ባዩ ጊዜ፣ በቅናት ተሞሉ፤ የጳውሎ
ስንም ንግግር እየተቃወሙ ይሰድቡት ነበር::

46ጳውሎስና በርናባስም በድፍረት እንዲህ
አሏቸው፤ “የእግዚአብሔር ቃል በመጀመሪያ
ለእናንተ መነገር አለበት፤ እናንተ ግን ናቃ
ችሁት፤ በዚህም የዘላለም ሕይወት እንደማ
ይገባችሁ በራሳችሁ ላይ ስለ ፈረዳችሁ፣
እኛም ወደ አሕዛብ ዞር ለማለት እንገደዳለን::
47ደግሞም ጌታ እንዲህ ብሎ አዞናል፤

“ ‘ድነትን እስከ ምድር ዳርቻ ታደርስ
ዘንድ፣[ሀ]
ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌሃለሁ::’ ”

48አሕዛብ ይህን በሰሙ ጊዜ ደስ አላቸው፤
ለእግዚአብሔርም ቃል ክብርን ሰጡ፤ ለዘላለም
ሕይወት የተዘጋጁትም ሁሉ አመኑ::
49የጌታም ቃል በአካባቢው ባለው አገር
ሁሉ ተስፋፋ:: 50አይሁድ ግን በመንፈሳዊ
ነገር የተጉትንና በኑሮ የከበሩትን ሴቶች እን
ዲሁም የከተማውን ታላላቅ ወንዶች ቀስቅ
ሰው በጳውሎስና በበርናባስ ላይ ስደትን አስ
ነሡ፤ ከአገራቸውም አስወጧቸው:: 51ጳውሎስና
በርናባስም ተቃውሞአቸውን ለመግለጽ የእግ

13፥41 ዕን1፥5
13፥42 ቍ14
13፥43 ሐሥ11፥23፤
14፥22፤ሮሜ3፥24
13፥45 ሐሥ18፥6፤
1ተሰ2፥16፤
1ጴጥ4፥4፤ይሁ10
13፥46 ቍ26፤
ማቴ21፥41፤ሐሥ3፥26፤
18፥6፤22፥21፤26፥20፤
28፥28፤ሮሜ11፥11
13፥47 ኢሳ49፥6፤
ሉቃ2፥32
13፥48 ቍ49፤ሐሥ
8፥25፤15፥35:36፤
19፥10:20
13፥49 ቍ48
13፥50 1ተሰ2፥16
13፥51 ማቴ10፥14፤
ሐሥ14፥1:19:21፤
16፥2፤2ጢሞ3፥11
13፥52 ሉቃ1፥15፤
ሐሥ11፥26
14፥1 ሐሥ2፥41፤
9፥20፤13፥51
14፥2 ሐሥ1፥16
14፥3 ዮሐ4፥48፤
ሐሥ4፥29
14፥4 ሐሥ17፥4:
5፤28፥24
14፥5 ቍ19፤ሐሥ
20፥3
14፥6 ማቴ10፥23
14፥7 ቍ15:21፤
ሐሥ13፥32፤16፥10
14፥8 ሐሥ3፥2
14፥9 ማቴ9፥28:
29፤13፥58
14፥10 ሕዝ2፥1፤
ሐሥ3፥8
14፥11 ሐሥ8፥10፤
28፥6
14፥12 ዘፀ7፥1

ራቸውን ትቢያ አራግፈው ወደ ኢቆንዮን
ሄዱ:: 52ደቀ መዛሙርቱም በደስታና በመን
ፈስ ቅዱስ ተሞሉ::

## ጳውሎስና በርናባስ በኢቆንዮን

14 በኢቆንዮንም ጳውሎስና በርናባስ
አብረው ወደ አይሁድ ምኵራብ
ገቡ፤ በዚያም በሚገባ ስላስተማሩ፣ ከአይሁ
ድም ከግሪክም እጅግ ብዙ ሰዎች አመኑ::
2ያላ መኑት አይሁድ ግን፣ አሕዛብን አነሣሥ
ተው ወንድሞችን እንዲጠሉ አደረጓቸው::
3ጳውሎስና በርናባስም ስለ ጌታ በድፍረት
እየተናገሩ ብዙ ጊዜ እዚያው ቈዩ፤ ጌታም
የሚናገሩትን የጸጋውን ቃል በታምራዊ
ምልክትና በድንቅ ሥራ እየደገፈ ያረጋግ
ጥላቸው ነበር:: 4የከተማውም ሕዝብ ተከፋ
ፈለ፤ ገሚሱ ከአይሁድ ጋር፣ ገሚሱም ከሐ
ዋርያት ጋር ሆነ:: 5በዚህ ጊዜ አሕዛብና
አይሁድ ከመሪ ዎቻቸው ጋር ተባብረው
ሊያንገላቷቸውና በድንጋይ ሊያስወግሯቸው
ሞከሩ:: 6እነርሱ ግን ይህን እንዳወቁ ልስጥ
ራንና ደርቤን ወደተባሉት ወደ ሊቃኦንያ
ከተሞችና በዙሪያቸው ወዳለው አገር ሸሹ፤
7በዚያም ወንጌልን መስበክ ቀጠሉ::

## ጳውሎስና በርናባስ በልስጥራና በደርቤ

8በልስጥራንም፣ እግሩ አንካሳ የሆነና ከተ
ወለደ ጀምሮ ፈጽሞ በእግሩ ሄዶ የማያውቅ
ሽባ ሰው ተቀምጦ ነበር:: 9ይህም ሰው
ጳውሎስ ሲናገር ያደምጥ ነበር:: ጳውሎስም
ወደ እርሱ ትኵር ብሎ ተመለከተና ለመ
ዳን እምነት እንዳለው ባየ ጊዜ በታላቅ ድምፅ፣
“ቀጥ ብለህ በእግርህ ቁም!” አለው፤ በዚህ
ጊዜ ዘሎ ተነሣና መራመድ ጀመረ::
11ሕዝቡም ጳውሎስ ያደረገውን ባዩ ጊዜ፣
በሊቃኦንያ ቋንቋ፣ “አማልክት በሰው ተመ
ስለው ወደ እኛ ወርደዋል!” ብለው ጮኹ፤
12በርናባስን ‘ድያ’ አሉት፤ ጳውሎስም ዋና

[ሀ]47 *ታደርስ ዘንድ* የሚለው በግሪኩ ነጠላ ቍጥር ነው::

(ሮሜ 3፥21-22):: ያመለክታል::

13፥46 *በመጀመሪያ ለእናንተ መነገር አለበት፤* ወንጌል አስቀድሞ የመጣው ከአይሁድና ለአይሁድ በመሆኑ፣ እንዲሁም ጳውሎስ ራሱ ከአይሁድ ወገን ስለ ነበረ፣ ወገኖቹ ድነትን ያገኙ ዘንድ ከፍተኛ ፍላጎት ስላለው ነው (ሮሜ 9፥1-5፤ 10፥1-3):: የቍ 14 ማብ ይመ::

13፥48 *ለዘላለም ሕይወት የተዘጋጁትም ሁሉ አመኑ፤* የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት የመለኮት ጥሪና የሰው እምነት አስፈላጊ ነው::

13፥51 *ትቢያ አራግፈው፤* ሐዋርያቱ ኀላፊነታቸው ምን ያህል ከፍተኛ እንደ ሆነ ለማሳየትና፣ የሰበኩትን ወንጌል ሕዝብ አንቀበልም በማለቱ በእነዚህ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ላይ ከፍተኛ ሥቃይ እንዳስከተሉ ለማሳየት ነው (የሉቃ 9፥5 ማብ ይመ):: *ኢቆንዮን፤* በዘመናችን ቆንያ ትባላለች፤ እርሷ በገላትያ አውራጃ የምትገኝ ሲሆን፣ ዋና ዋና መንገዶች የሚያቋርጧት የግብርና ማእከል ነበረች::

13፥52 *በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤* የ2፥4 ማብ ይመ::

14፥1 *እጅግ ብዙ፤* በመጀመሪያ ሥራው ጥሩ ሆኖ ይካሄድ ነበር፤ ውሎ ዐድሮ ግን ከአይሁድ ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው (ቍ 2)፤ ይሁን እንጂ ሙከራቸው አልተሳካም፤ ጳውሎስና በርናባስም በዚያ ብዙ ቈይተዋል (ቍ 3):: ለሁለተኛ ጊዜም ከፍተኛ የማሳደድና ሁከት የማስነሣት ዕቅድ አዘጋጅተው ነበር (ቍ 5)::

14፥3 *በታምራዊ ምልክትና በድንቅ ሥራ...ያረጋግጥላቸው ነበር፤* ታምር የሚያስፈልግበት ዋናው ምክንያት የቃሉን እውነተኛነት፣ እግዚአብሔር የተቀበለው መሆኑን ለማረጋገጥ ነው::

14፥4 *ከሐዋርያት፤* ጳውሎስም በርናባስም ሐዋርያት ተብለዋል (ቍ 14፤ እንዲሁም የማር6፥30 ማብ ይመ):: እዚህ ላይ የቃሉ አገባብ፣ ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ለማመልከት ሳይሆን፣ ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት ተልከው የሚሄዱትን ሰፋ ባለ መልኩ ለማመልከት ነው (13፥2-3 ይመ)::

14፥5 *በድንጋይ ሊያስወግሯቸው፤* በእግዚአብሔር ላይ ክፉ ቃል የተናገረ ሰው በአይሁድ ሕግ መሠረት በድንጋይ ተወግሮ ይሞት ነበር፤ እዚህ ላይ ሁከት የማስነሣት ዕቅድ ሳይኖራቸው አይቀርም::

14፥6 *ሊቃኦንያ ከተሞችና፤* ሊቃኦንያ ከጲስድያ በስተ ምሥራቅ፣ ከጣውሩስ ተራራዎች በስተ ሰሜን የምትገኝ ወረዳ ስትሆን፣ የሮማውያን ግዛት የሆነው የገላትያ አውራጃ አካል ነበረች:: *ልስጥራንና፤* በሮም ቅኝ ግዛት ውስጥ የምትገኝ ከተማ ነበረች (የ13፥14 ማብ ይመ)፤ ጢሞቴዎስ በኢቆንዮን የታወቀ ሰው ቢሆንም፣ ልስጥራን ደግሞ አገሩ ሳትሆን አልቀረችም:: ልስጥራን ከኢቆንዮን 32 ኪ.ሜ. ያህል ትርቃለች:: *ደርቤ፤* ከልስጥራ 96 ኪ.ሜ. ያህል ትርቃለች፤ የጋይዮስ አገር ናት (20፥4፤ የ14፥20 ማብ ይመ)::

14፥12 *ድያ...ሄርሜን፤* ‘ድያ’ የከተማዋ ጠባቂ አምላክ ተብሎ ይታመን ነበር፤ በከተማይቱ ውስጥ ቤተ መቅደሱ ቆሞ ነበር:: ‘ለድያ’ መሥዋዕት ለማቅረብ የመጡት ሰዎች፣ ድያን

ተናጋሪ ስለ ነበር 'ሄርሜን' አሉት:: 13ከከ
ተማው ወጣ ብሎ የነበረው፣ የድያ ቤተ
መቅደስ ካህንም ኮርማዎችንና የአበባ ጉን
ጉኖችን ወደ ከተማው መግቢያ አምጥቶ፣
ከሕዝቡ ጋር ሆኖ ሊሠዋላቸው ፈለገ::
14ሐዋርያቱ በርናባስና ጳውሎስ ይህን በሰሙ
ጊዜ ልብሳቸውን ቀደው ወደ ሕዝቡ መካ
ከል ሮጡ፤ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው
እንዲህ አሉ፤ 15"እናንት ሰዎች፤ ለምን ይህን
ታደርጋላችሁ? እኛም እኮ እንደ እናንተው
ሰዎች ነን:: እናንተም ደግሞ ከዚህ ከንቱ
ነገር ርቃችሁ ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንም
በውስጣቸውም የሚኖሩትን ሁሉ ወደ ፈጠረ
ወደ ሕያው እግዚአብሔር እንድትመለሱ ወን
ጌልን እንሰብክላችኋለን:: 16እርሱ ባለፉት
ትውልዶች፣ ሕዝቦች ሁሉ በገዛ መንገዳቸው
እንዲሄዱ ተዋቸው፤ 17ይሁን እንጂ ዝናብን
ከሰማይ እንዲሁም ፍሬያማ ወቅቶችን በመ
ስጠቱ፣ ደግሞም ልባችሁን በመብልና በደ
ስታ በማርካቱ መልካምን በማድረግ ራሱን ያለ
ምስክር አልተወም::" 18ይህን ሁሉ ተናግረው
እንኳ፣ ሕዝቡ እንዳይሠዋላቸው ያስተዉት
በብዙ ችግር ነበር::
19አይሁድ ግን ከአንጾኪያና ከኢቆንዮን
መጥተው፣ ሕዝቡን አግባቡ፤ ጳውሎስንም
በድንጋይ ከወገሩት በኋላ፣ የሞተ መስሎ
አቸው ጐትተው ከከተማው ወደ ውጭ አወ
ጡት:: 20ሆኖም ደቀ መዛሙርት ከበውት
እንዳሉ ተነሣ፤ ወደ ከተማም ገባ:: በማግ
ስቱም ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤን ሄዱ::

### ጳውሎስና በርናባስ በሶርያ ወዳለችው አንጾኪያ ተመለሱ

21ጳውሎስና በርናባስ በደርቤን የምሥራቹን
ቃል ሰብከው፣ ብዙ ደቀ መዛሙርትም ካፈሩ
በኋላ፣ ወደ ልስጥራን፣ ወደ ኢቆንዮንና
ወደ አንጾኪያ ተመለሱ:: 22የደቀ መዛሙር
ቱንም ልብ በማበረታታትና በእምነታቸው
ጸንተው እንዲኖሩ በመምከር፣ "ወደ እግዚ
አብሔር መንግሥት ለመግባት በብዙ መከራ
ማለፍ አለብን" አሏቸው:: 23ከዚያም በየአ
ብያተ ክርስቲያናቱ ሽማግሌዎችን ከሾሙ
ላቸው በኋላ፣ በጾምና በጸሎት ላመኑበት
ጌታ ዐደራ ሰጧቸው:: 24በጲስድያም ዐልፈው
ወደ ጵንፍልያ መጡ፤ 25በጴርጌንም ቃሉን
ከሰበኩ በኋላ፣ ወደ አጣልያ ወረዱ::
26ከአጣልያም፣ እስካሁን ላከናወኑት ሥራ፣
በእግዚአብሔር ጸጋ በዐደራ ወደ ተሰጡባት
ከተማ ወደ አንጾኪያ በመርከብ ተመለሱ::
27እዚያም በደረሱ ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያንን
በአንድነት ሰብስበው፣ እግዚአብሔር በእነርሱ
አማካይነት ያደረገውን ሁሉ፣ ደግሞም
ለአሕዛብ እንዴት የእምነትን በር እንደ
ከፈተላቸው ተናገሩ:: 28በዚያም ከደቀ መዛ
ሙርት ጋር ብዙ ጊዜ ተቀመጡ::

### የኢየሩሳሌም ጉባኤ

15 አንዳንድ ሰዎችም ከይሁዳ ወደ አን
ጾኪያ ወርደው፣ "በሙሴ ሥርዐት
መሠረት ካልተገረዛችሁ ልትድኑ አትችሉም"
በማለት ወንድሞችን ማስተማር ጀመሩ::
2ይህም ጳውሎስንና በርናባስን ከእነርሱ ጋር
ወደ ከረረ ጠብና ክርክር ውስጥ ከተታቸው::
ስለዚህ ጳውሎስና በርናባስ ከሌሎች አንዳ
ንድ ምእምናን ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተው

14፥14 ማር14፥63
14፥15 ቍ7:21፤ ዘፍ1፥1፤1ሳሙ12፥21፤ መዝ146፥6፤ማቴ16፥16፤ሐሥ10፥26፤13፥32፤1ተሰ1፥9፤ራእ 14፥7
14፥16 መዝ81፥12፤ ሚክ4፥5፤ሐሥ17፥30
14፥17 ዘዳ11፥14፤ ኢዮ5፥10፤መዝ4፥7፤ 65፥10፤ሮሜ1፥20
14፥19 ሐሥ13፥45: 51፤2ቆሮ11፥25፤ 2ጢሞ 3፥11
14፥20 ቍ22:28፤ ሐሥ11፥26
14፥21 ሐሥ2፥41፤ 13፥32:51
14፥22 ዮሐ16፥33፤ ሐሥ11፥23፤13፥43፤ 1ተሰ3፥3፤ 2ጢሞ 3፥12
14፥23 ሐሥ11፥30፤13፥3፤20፥32
14፥24 ሐሥ2፥10
14፥26 ሐሥ11፥19:23፤13፥1:3
14፥27 ሐሥ15፥4: 12፤21፥19፤1ቆሮ16፥9፤2ቆሮ2፥12፤ ቈላ4፥ 3፤ራእ3፥8
14፥28 ሐሥ11፥26
15፥1 ቍ5:24፤ ሐሥ 1፥16፤6፥14፤ ገላ2፥12፤5፥2:3
15፥2 ሐሥ11፥30፤ ገላ2፥2

ትተው ለጳውሎስና ለበርናባስ መሥዋዕት ለማቅረብ የወሰኑ ይመስላል:: በርናባስ እንደ 'ድያ' የተቈጠረው ግርማ ሞገስ ስላ ለው ሳይሆን አይቀርም፤ ጳውሎስ እንደ ሄርሜን (በሮማውያን አጠራር 'ሜር ኩሪ') የተቈጠረው ደግሞ ዋናው ተናጋሪ እርሱ ስለ ነበረ ነው (28፥6 ይመ):: በዚህ ቦታ እንዲህ ያለ ሁኔታ ሊፈጠር የቻለው፣ 'ድያ' እና 'ሄርሜን' በዚሁ አካባቢ ተከሥተው ነበር የሚል አፈ ታሪክ በመኖሩ ሳይሆን አይቀርም፤ አዩአቸው የተባ ሉትም ያረጁ ባልና ሚስት ብቻ ነበር፤ ስለዚህ የልስጥራን ሰዎች፣ እንደዚህ ያለው ዕድል ዳግመኛ እንዳያመልጣቸው ውሳኔ በማድረግ ሊሠ ውላቸው ተነሡ::

14፥13 *ወደ ከተማው መግቢያ*፤ በግሪክ ቋንቋ አባባሉ የቤተ መቅደስ ደጃፍ፣ የከተማ መግቢያ ወይም የቤት በር ማለት ይሆናል::

14፥14 *ልብሳቸውን ቀደው*፤ በአይሁድ ልማድ ታላቅ የሐ ዘን መግለጫ ምልክት ነው:: (ዘፍ 37፥29:34)::

14፥15 *ከንቱ ነገር*፤ በብሉይ ኪዳን ጣዖታትን ለመግ ለጽ የሚጠቀሙበት አባባል ነው (1ሳሙ 12፥21 ይመ)::

14፥19 *ጳውሎስንም በድንጋይ ከወገሩት*...፤ የወገሩት እን ደተለመደው ከቅጥሩ ውጭ ሳይሆን፣ በከተማው ውስጥ ነበር (ከ2ቆሮ 12፥2 ጋር ያነጻጽሩ)::

14፥20 *ደቀ መዛሙርት ከበውት እንዳሉ*፤ ወጣቱ ጢሞ ቴዎስ በዚያ ተገኝቶ ሊሆን ይችላል (2ጢሞ3፥10-11 ይመ):: *ደርቤን*፤ በገላትያ አውራጃ ከሊቃኦንያ በስተ ደቡብ ምሥራቅ ጠረፍ ላይ የምትገኝ ከተማ ናት (የቍ6 ማብ ይመ):: ከተማዋ ከተቈ ረቈረችበት ስፍራ በስተ ምሥራቅ 48 ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ የዚህችን ከተማ ስም የሚጠቅስ ጽሑፍ ተገኝቷል::

14፥23 *ከሾሙላቸው*፤ ይህን ለመግለጽ የገባው የግሪኩ ቃል (በ2ቆሮ8፥19 ላይ ይገኛል) እንዲህ የሚሉ ትርጕሞች ሊኖሩት ይችላል፤ (1) እጅ መዘርጋት፤ (2) እጅ አውጥቶ መሾም፤ ወይም (3) የትኛውንም መንገድ ሳይከተሉ መሾም ወይም መምረጥ:: በ6፥6 ላይ እንደምናነበው ሰባቱ ዲያቆናት የተሾሙት በቤተ ክር ስቲያኒቱ ከተመረጡና እንዲጸልዩላቸውና እጃቸውን እንዲጭኑባ ቸው ወደ ሐዋርያት ከቀረቡ በኋላ ነው:: እነዚህ ቢያንስ በከፊል ከአረማዊው ኅብረተሰብ የመጡ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት በመሆናቸው መሪዎችን መርጠው የሾሙላቸው ጳውሎስና በርና ባስ ሳይሆኑ አይቀሩም::

14፥24 *በጲስድያም*፤ ከጵንፍልያ በስተ ሰሜን የምትገኝና ቁመቷ 120 ኪሎ ሜትር፣ ወርዷ ደግሞ 80 ኪ.ሜ. የሆነች ወረዳ ናት (13፥13-14):: ሽፍቶች ብዙ ጊዜ ያጠቋት ነበር (ከ2ቆሮ 11፥26 ጋር ያነጻጽሩ):: ጵንፍልያ፤ ከትንሹ እስያ በስተ ደቡብ የምትገኝና ቁመቷ 128 ኪሎ ሜትር፣ ወርዷ ደግሞ 32 ኪሎ ሜትር የሆነች ወረዳ ናት:: ከ74 ዓ.ም. በኋላ ጲስድያ የሮም አውራጃ ከሆነችው ከጵንፍልያ ጋር ተቀላቅላለች (13፥13 ይመ)::

14፥25 *በጴርጌንም*፤ የ13፥13 ማብ ይመ:: አጣልያ፤ በጵን ፍልያ ጠረፍ ዐቢይ የባሕር ወደብ ናት::

14፥26 *አንጾኪያ*፤ 11፥20 ይመ፤ እንዲሁም የ11፥19 ማብ ይመ::

14፥27 *የእምነትን በር...ከፈተላቸው*፤ እግዚአብሔር አሕዛ ብን ወደ እምነት አመጣቸው፤ ያምኑም ዘንድ በር ከፈተላቸው (11፥18 ጋር ያነጻጽሩ)::

14፥28 *ብዙ ጊዜ*፤ ምናልባት ከዓመት በላይ ነው::

15፥1 *አንዳንድ ሰዎችም*፤ ምናልባት "ከፈሪሳውያን ወገን" (ቍ5) የሆኑትን ማለት ሊሆን ይችላል፤ እነዚህ ክርስቲያኖች አንድ ሰው እውነተኛ ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት የሙሴን ሕግ በሚገባ መጠ በቅ አለበት ባይ ናቸው፤ የሕግ አክባሪነቱ መለኪያም ግዝረትን መፈጸም ነው ይሉም ነበር:: *ከይሁዳ*፤ የመደመጥ ዕድል የተሰጣቸው እነዚህ ሕግ አጥባቂ ወገኖች፣ በኢየሩሳሌም የነበሩትን ሐዋርያትና ሽማግሌዎችን የሚወክሉ እንዳልነበሩ ይታወቃል (ከቍ 24 ጋር ያነጻጽሩ)

15፥2 *ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተው*፤ የ12፥1፤ ገላ 2፥1 ማብ ይመ:: ገላ 2፥1-10 የሚያመለክተው በ11፥27-30 እና በ12፥25 ላይ የሰ ፈረውንና የተራቡትን ሰዎች ለመጐብኘት የተደረገውን ጕዞ ነው የሚሉ ሰዎች፣ በገላ 2፥2 ላይ የተጠቀሰውን ጕብኝት በመገለጥ የተደገፈ በመሆኑ፣ በ11፥27-28 ላይ አጋቦስ የተነበየውን የራብ

ስለዚሁ ጉዳይ ሐዋርያትንና ሽማግሌዎ
ችን እንዲጠይቁ ተወሰነ:: 3ቤተ ክርስቲ
ያኒቱም እግረ መንገዳቸውን በፊንቄና በሰ
ማርያ በኩል እንዲያልፉ ላከቻቸው፤ እነ
ርሱም በእነዚህ ቦታዎች ለነበሩት የአሕዛ
ብን መመለስና ማመን ነገሯቸው፤ ወንድ
ሞችም ሁሉ በዚህ እጅግ ደስ አላቸው::
4ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜም፣ ቤተ ክርስቲ
ያንና ሐዋርያት እንዲሁም ሽማግሌዎች
ተቀበሏቸው፤ የተላኩትም እግዚአብሔር ከእነርሱ
ጋር ሆኖ የሠራውን ሁሉ ነገሯቸው::
5ከፈሪሳውያን ወገን ያመኑት አንዳንዶቹ
ተነሥተው በመቆም፣ "አሕዛብ እንዲገረዙና የሙ
ሴን ሕግ እንዲጠብቁ ማድረግ አስፈላጊ ነው" አሉ::
6ሐዋርያትና ሽማግሌዎችም ይህንኑ ጉዳይ
ለማጤን ተሰበሰቡ:: 7ከብዙ ክርክር በኋላ
ጴጥሮስ ተነሥቶ እንዲህ አላቸው፤ "ወንድ
ሞች ሆይ፤ እግዚአብሔር ከጥቂት ጊዜ በፊት
በእናንተ መካከል እኔን መርጦ፣ አሕዛብ
የወንጌልን ቃል ከእኔ አንደበት ሰምተው
እንዲያምኑ ማድረጉን ታውቃላችሁ:: 8ልብን
የሚያውቅ እግዚአብሔር ለእኛ እንደ ሰጠን ሁሉ፣
ለእነርሱም መንፈስ ቅዱስን በመስጠት የተ
ቀበላቸው መሆኑን መሰከረላቸው፤ 9ልባቸ
ውንም በእምነት በማንጻት በእኛና በእነርሱ
መካከል ምንም ልዩነት አላደረገም:: 10እንግ
ዲህ፣ አባቶቻችንም እኛም ልንሸከመው ያል
ቻልነውን ቀንበር በደቀ መዛሙርት ጫንቃ
ላይ በመጫን ለምን አሁን እግዚአብሔርን ትፈታ

15፥3 ሐሥ11፥19፤ 14፥27
15፥4 ቍ12፤ሐሥ 14፥27፤21፥19
15፥5 ቍ1፤ ማቴ3፥ 7፤ሐሥ5፥17
15፥7 ሐሥ10፥1-48
15፥8 ሐሥ10፥44: 47፤ሉእ2፥23
15፥9 ሐሥ10፥28: 34:43፤11፥12
15፥10 ማቴ23፥4፤ ሐሥ5፥9፤ገላ5፥1
15፥11 ሮሜ3፥24፤ ገላ2፥16፤ኤፌ2፥5-8
15፥12 ቍ4፤ዮሐ4፥ 48፤ሐሥ14፥27፤ 21፥19
15፥13 ሐሥ12፥17፤ 21፥18፤1ቆሮ15፥7፤ ገላ1፥19፤2፥9:12
15፥14 2ጴጥ1፥1
15፥17 አሞ9፥11: 12
15፥18 ኢሳ45፥21

ተኑታላችሁ? 11እኛም የዳንነው ልክ እንደ እነርሱ
በጌታ በኢየሱስ ጸጋ መሆኑን እናምናለን::"
12ጉባኤውም በሙሉ ዝም ብሎ፣ በርናባ
ስና ጳውሎስ እግዚአብሔር በእነርሱ አማካይ
ነት በአሕዛብ መካከል ስላደረጋቸው ታም
ራዊ ምልክቶችና ድንቅ ነገሮች ሲናገሩ
ያዳምጣቸው ነበር:: 13እነርሱም ተናግረው
ሲጨርሱ፣ ያዕቆብ ተነሥቶ በመቆም እንዲህ
አለ፤ "ወንድሞች ሆይ፤ ስሙኝ፤ 14እግዚአብሔር
ከአሕዛብ ወገን ለእርሱ የሚሆነውን ሕዝብ
አስቀድሞ እንዴት እንደ ጐበኘ ስምዖን[x]
አስረድቶናል:: 15እንዲህ ተብሎ የተጻፈው
የነቢያቱም ቃል ከዚህ ጋር ይስማማል፤

16" 'ከዚህ በኋላ እመለሳለሁ፤
የፈረሰውን የዳዊትን ቤት እገነባለሁ::
ፍርስራሹን መልሼ አቆማለሁ፤
እንደ ገናም እሠራዋለሁ፤
17ይኸውም የቀሩት ሰዎች ጌታን እንዲ
ፈልጉ፣
ስሜን የተሸከሙ አሕዛብም እንዲሹኝ
ነው፤
እነዚህን ያደረገ ጌታ እንዲህ ይላል፤'
18እነርሱም ከጥንት ጀምሮ የታወቁ
ናቸው::[y]

19"ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር የተመለሱትን አሕ
ዛብ እንዳናስጨንቃቸው ይህ የእኔ ውሳኔ ነው::

[x]14 እርሱም ጴጥሮስ ነው:: [y]17-18 አንዳንድ ቅጆች ...ለጌታ ከጥንት ጀምሮ የታወቀው የራሱ ሥራ ነው ይላሉ::

ዘመን ማመልከት አለበት ይላሉ:: በሌላም በኩል ገላ 2፥1-10 የሚያመለክተው በ15፥1-22 የተመለከተውን በኢየሩሳሌም በተደረገው ጉባኤ ላይ ለመገኘት የሄዱበትን ጉዞ ነው የሚሉ ሰዎች ደግሞ፣ ለተራቡት እርዳታ ለማድረግ ጉዞ የተደረገው ሄሮድስ አግሪጳ በሞተበት በ44 ዓ.ም. ነው ይላሉ (11፥27-30፤ 12፥25):: እንግዲህ ሳውል ወደ ክርስትና እምነት የገባው ከ14 ዓመት በፊት (ገላ 2፥1) በ30 ዓ.ም ከሆነ፣ ጌታ የተሰቀለበት ዓመት ነው ማለት ነው፤ ሳውል በዚህ ጊዜ ወደ ክርስትና እምነት ገባ ከተባለም፣ ጳውሎስ ወደ ክርስትና የመጣበትን ጊዜ ወደዚያ ይስበዋል ማለትም እጅግ ያስቀድመዋል::

*15፥4-22፤* በቍ4፥22 የተገለጹት ተከታታይ ስብሰባዎች 1) የእንኳን ደኅና መጣችሁና የዘገባው ማስሚያ አጠቃላይ ስብሰባ፣ (ቍ4-5) 2)፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ በስብሰባ ላይ እያለች (ቍ6-11)፣ የመሪዎች ስብሰባ በጐን ተደርጎ ሊሆን ይችላል፤ 3) የሐዋርያት የሽማግሌዎችና የጠቅላላው ጉባኤ ስብሰባ (ቍ12፥22) ነው::

*15፥4፤* የመጀመሪያው ስብሰባ በአሕዛብ መካከል ስለ ተከናወነው የወንጌል ሥራ ዘገባ ማቅረብ ሲሆን፣ ይህም በጋለ ስሜት ተቀባይነት አግኝቶአል::

15፥5 *ከፈሪሳውያን ወገን ያመኑት አንዳንዶቹ፤* ከፈሪሳውያን ወገን አንዳንዶቹ ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ አሮጌውን የአይሁድን ሥርዐት እንደያዙ መጡ:: እንደ እነርሱ አመለካከት፣ አሕዛብ በመጀመሪያ ወደ አይሁድ እምነት ገብተው ግዝረትን መቀበል አለባቸው (ቍ1)፤ በእምነት ለመዳንም ይህ በቅድሚያ መሟላት አለበት:: ከእነዚህ አንዳንዶቹ ወደ አንጾኪያ ሄደው የነበሩና በዚህ ጊዜ ጉዳያቸውን ለማቅረብ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱ ሳይሆኑ አልቀሩም::

15፥7 *ጴጥሮስ ተነሥቶ፤* ሐዋርያትና ሽማግሌዎች በነገሩ ላይ በሰፊው ከተወያዩ በኋላ፣ ጴጥሮስ ንግግር አደረገ:: *አሕዛብ... ሰምተው፤* ጴጥሮስ የተናገረው የራሱን ልምድ መሠረት በማድረግ ነው፤ ወደ አሕዛብ ወንጌልን ያደርስ ዘንድ እግዚአብሔር ልኮታልና (10፥28-29)::

15፥8 *ለእነርሱም መንፈስ ቅዱስን በመስጠት፤* እግዚአብሔር አሕዛብን ለመቀበሉ ማንም ሊያስተባብል የማይችለው ማረጋገጫ ነው (10፥44:47፤11፥17-18 ይመ)::

15፥9 *ልባቸውንም በእምነት በማንጻት የጴጥሮስን አባባል ጳውሎስ* በማረጋገጥ ይናገራል (ሮሜ 5፥1፤ ገላ2፥15-16 ጋር ያነጻጽሩ)::

15፥10 *ቀንበር፤* የኦሪትን ሕግ ማለት ነው (ገላ 5፥1 ይመ፤ ከማቴ 11፥28-29 ጋር ያነጻጽሩ)::

15፥11 *በጌታ በኢየሱስ ጸጋ፤* ግዝረት አስፈላጊ አይደለም:: *እኛም የዳነው ልክ እንደ እነርሱ ...፤* ሮሜ 3፥9 ይመ::

15፥12 *ጉባኤውም ... ዝም ብሎ፤* በቍ4-22 ላለው ክፍል የተሰጠውን ማብ ይመ:: ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ተሰብስበው ሳሉ፣ ሕዝቡ ቦታ ቦታውን ይዞ የተቀመጠ ይመስላል:: በዚያ ጊዜ ጉባኤው ጸጥ ብሎ አልተቀመጠም ነበር፤ በዚህ ጊዜ ግን የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ሲናገሩ ለመስማት ሲል ጸጥ አለ:: *በርናባስና ጳውሎስ* እዚህ ላይ፣ ቅደም ተከተሉ በርናባስን የመጀመሪያ ያደርገዋል፤ ይህም በርናባስ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ያለውን ከፍተኛ ግምት ለማሳየት ታስቦ ይሆናል፤ ነገር ግን ሐዋርያዊ ጉዞአቸውን በሚተርክበት ጊዜ በቆጵሮስ ደሴት ከተከሠተው ሁኔታ በኋላ (13፥7:9:13:42)፣ ቅደም ተከተሉ "ጳውሎስና በርናባስ" የሚል ነበር:: *ታምራዊ ምልክቶችና ድንቅ ነገሮች፤* 8፥19-20፤ 14፥3 ይመ::

15፥13 *ያዕቆብ፤* የጌታ ወንድም ነው:: ለማስረዳት ያቀረበው ሐሳብ በቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃነት የተደገፈ ነበር::

15፥14 *ስምዖን፤* ጴጥሮስ ነው (ቍ7 ይመ):: *ለእርሱ የሚሆነውን ሕዝብ፤* በብዛት አሕዛብን ያቀፈ አዲስ ማኅበረሰብ ሲሆን፣ አይሁድንም የሚያካትት ነበር (ዮሐ10፥16፤ ከ1ጴጥ 2፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)::

15፥15 *የነቢያቱም፤* በተለይ በአሞ 9፥11-12 የተገለጸውን ይመለከታል::

15፥16 *ከዚህ በኋላ እመለሳለሁ፤* አንዳንድ ሰዎች ይህን ጥቅስ ከትንቢተ አሞጽ በመውሰድ በመጨረሻው ዘመን ስለሚከናወኑት ተከታታይ ሁኔታዎች እንደሚያመለክት ይናገራሉ፤ ይኸውም (1) የቤተ ክርስቲያንን ዘመን ("ለእርሱ የሚሆነውን ሕዝብ" ቍ14)፤ (2) የእስራኤል መንግሥት እንደ ገና ስለ መቋቋሙ (ቍ16) እና (3) ስለ አሕዛብ በመጨረሻ መዳን (ቍ17-18):: ሌሎቹ ግን እግዚአብሔር አሕዛብን ለማዳን ስላለው ዕቅድ ብቻ እንደሚያስረዳ ይናገራሉ::

15፥19 *እንዳናስጨንቃቸው፤* ግዝረት የግድ አስፈላጊ አይደለም፤ ይሁን እንጂ አራት ደንቦች ተመሥርተዋል (የቍ 20 ማብ ይመ):: እነዚህም የአሕዛብን ደካማነት ለማሳየት የሚቀርቡ ምክንያቶች ሲሆኑ መጣሳቸውም አይሁድን የሚያሸማቅቃቸው

20ይልቁን በጣዖት ከረከሰ ነገር፣ ከዝሙት
ርኵሰት፣ ታንቆ የሞተ እንስሳ ሥጋ ከመ
ብላትና ደም ከመመገብ እንዲርቁ ልን
ጽፍላቸው ይገባል፤ 21የሙሴ ሕግማ ከጥንት
ጀምሮ በየሰንበቱ በምኵራብ ሲነበብና በየ
ከተማው ሲሰበክ ኖሮአልና።”

## ላመኑት አሕዛብ ከጉባኤው የተላከ ደብዳቤ

22በዚህ ጊዜ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ከመላው
ቤተ ክርስቲያን ጋር ሆነው ከመካከላቸው
አንዳንድ ሰዎችን መርጠው፣ ከጳውሎስና
ከበርንባስ ጋር ወደ አንጾኪያ ለመላክ ወሰኑ፤
ከወንድሞችም መካከል ዋነኛ የነበሩትን
በርስያን የተባለውን ይሁዳንና ሲላስን መረጡ፤
23በእነርሱም እጅ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ላኩ፤

ወንድሞቻችሁ ከሆኑት ከሐዋርያትና ከሽ
ማግሌዎች፤

ከአሕዛብ ወገን አምነው በአንጾኪያ፣በሶ
ሪያና በኪልቅያ ለሚገኙ ወንድሞች፤

ሰላምታችን ይድረሳችሁ።

24አንዳንድ ሰዎች ያለ እኛ ፈቃድ ከእኛ
ዘንድ ወጥተው በንግግራቸው ልባችሁን እን
ዳወኩና እንዳናወጧችሁ ሰምተናል። 25ስለዚህ
ጥቂት ሰዎች መርጠን ከተወዳጆቹ ከበርና
ባስና ከጳውሎስ ጋር ወደ እናንተ ለመላክ
ሁላችንም ተስማምተናል፤ 26በርናባስና ጳው
ሎስም ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ
ስም ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ ናቸው።
27ስለዚህ እኛ የጻፍነውን በቃል እንዲያረጋ
ግጡላችሁ፣ እነሆ፤ ይሁዳንና ሲላስን ልከናል።
28ከእነዚህ አስፈላጊ ነገሮች በስተቀር ሌላ
ተጨማሪ ሸክም እንዳንጭንባችሁ፣ ለመንፈስ
ቅዱስም ለእኛም መልካም መስሎ ታይቶ
ናል፤ ይኸውም:- 29ለጣዖት ከተሠዋ ነገር፣
ከደም፣ ታንቆ ከሞተ እንስሳ ሥጋ እንዲሁም

15፥20 ቍ29፤ዘፍ 9፥4፤ዘሌ3፥17፤7፥26፤ 17፥10-13፤19፥26፤ ዘዳ12፥16-23፤1ቆሮ 8፥7-13፤10፥7:8:14-28፤ራእ2፥14:20
15፥21 ሐሥ13፥15፤ 2ቆሮ3፥14:15
15፥22 ቍ27:32:40፤ሐሥ11፥19:30፤ 16፥19:25:29፤2ቆሮ1፥19፤ 1ተሰ1፥1፤2ተሰ1፥1፤ 1ጴጥ5፥12
15፥23 ቍ1:41፤ ሉቃ2፥2፤ሐሥ6፥9፤ 11፥19፤23፥25:26፤ ያዕ1፥1
15፥24 ቍ1፤ገላ 1፥7፤5፥10
15፥26 ሐሥ9፥23-25፤14፥19፤1ቆሮ15፥30
15፥27 ቍ22
15፥28 ሐሥ5፥32
15፥29 ቍ20፤ ሐሥ 21፥25
15፥32 ቍ22፤ ሐሥ 11፥27
15፥33 1ሳሙ1፥17፤ ማር5፥34፤ሉቃ7፥50፤ ሐሥ 16፥36፤ 1ቆሮ16፥11
15፥35 ሐሥ8፥4፤ 13፥48
15፥36 ሐሥ13፥4:13:14:48:51፤14፥1:6:24:25
15፥37 ሐሥ12፥12
15፥38 ሐሥ13፥13
15፥40 ቍ22፤ ሐሥ 11፥23

ከዝሙት ርኵሰት እንድትርቁ ነው። ከእነ
ዚህ ዐይነት ነገሮች ብትርቁ ለእናንተ
መልካም ነው።

ደኅና ሁኑ።

30የተላኩትም ሰዎች ከተሰናበቱ በኋላ
ወደ አንጾኪያም ወረዱ፤ በዚያም የምእመ
ናኑን ጉባኤ በአንድነት ሰብስበው ደብዳቤ
ውን ሰጧቸው። 31ሕዝቡም ካነበቡት በኋላ
አበረታታች በሆነው ቃሉ ደስ ተሰኙ። 32ይሁ
ዳና ሲላስም ራሳቸው ነቢያት ስለ ነበሩ፣
ወንድሞችን ብዙ ንግግር በማድረግ መከሯ
ቸው፤ አበረቷቸውም። 33በዚያም ጥቂት ጊዜ
ከቈዩ በኋላ፣ ከወንድሞች በሰላም ተሰናብ
ተው ወደ ላኳቸው ሰዎች ተመለሱ። 34ሲላስ
ግን እዚያው ለመቅረት ወሰነ። 35ጳውሎ
ስና በርናባስም ከሌሎች ብዙ ሰዎች ጋር
ሆነው የጌታን ቃል እያስተማሩና እየሰበኩ
በአንጾኪያ ተቀመጡ።

## ጳውሎስና በርናባስ በሐሳብ ተለያዩ

36ጳውሎስ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በርናባስን፣
“ተነሣና የጌታን ቃል ወደ ሰበክንባቸው
ከተሞች ሁሉ እንሂድ፤ በዚያ ያሉ ወንድሞ
ችም በምን ሁኔታ እንዳሉ ለማወቅ እንጐ
ብኛቸው” አለው። 37በርናባስም ማርቆስ
የተባለው ዮሐንስ አብሮአቸው እንዲሄድ ፈለገ፤
38ጳውሎስ ግን እርሱን ይዞ ለመሄድ አልፈ
ለገም፤ ምክንያቱም፣ ቀደም ሲል ማርቆስ
ከእነርሱ ተለይቶ በጵንፍልያ ስለ ቀረና ወደ
ሥራ አብሮአቸው ስላልሄደ ነበር። 39እንዲህ
የከረረ አለመግባባት በመካከላቸው ስለ
ተፈጠረ እርስ በርስ ተለያዩ፤ ስለዚህ በር
ናባስ ማርቆስን ይዞ በመርከብ ወደ ቆጵሮስ
ሄደ። 40ጳውሎስ ግን ሲላስን መረጠ፤ ወንድ
ሞችም ለጌታ ጸጋ ዐደራ ከሰጡት በኋላ ተለ

ነበር። እነዚህ ግዴታዎች ተፈጻሚነት ካገኙም፣ የግለሰቡም፣ ደግሞም በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ያለውም ግንኙነት ሰመረ ማለት ነው። ደንቦቹም፣ ሕግ ለሙሴ ከመሰጠቱ በፊት እግዚአብሔር የሰጠን ነው ብለው የሚያምኑትን መመሪያ የሚያመለክቱ ናቸው።

15፥20 *በጣዖት ከረከሰ ነገር*፤ ቍ29፤ 1ቆሮ 8፥7-13፤ ራእ 2፥14:20 ይመ። *ከዝሙት ርኵሰት*፤ በግሪክ ኀብረተ ሰብ እንደ ቀላል ኀጢአት የሚቈጠር፤ ደግሞም ከአንዳንድ የአረማውያን በዓል አከባበር ጋር ተያይዞ የሚፈጸም ነበር። *ታንቆ የሞተ እንስሳ ሥጋ*፤ በዚህ ዐይነት የተገደለ እንስሳ በሕግ የተከለከለውን ደም ወደ መብላት ያደርሳል (ዘፍ 9፥4 ይመ)። *ደም*፤ እንዳይበላ በአይሁድ ሕግ በግልጽ የተከለከለ ነው (ዘሌ 17፥10-12)። እዚህ ላይ የሚያመለክተው ደምን ከሥጋ ጋር መብላትን ሳይሆን፣ ብቻውን መብላትን ሊሆን ይችላል።

15፥22 *ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ከመላው ቤተ ክርስቲያን ጋር*፤ በግልጽ ለመረዳት እንደሚቻለው በመልእክተኞቹ አመራረጥና በደብዳቤው ይዘት አወሳሰን ላይ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ የሚያደርግ ፍጹም ስምምነት (ቍ23-29)። *በርስያን የተባለውን ይሁዳንና*፤ የአባቱ ስም ከዮሴፍ በርስያን አባት ስም ጋር ተመሳሳይ ነው (1፥23 እና ማብ ይመ)፤ ወንድማማቾች ሳይሆኑ አይቀሩም። *ሲላስን*፤ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪም ነቢይም ሲሆን (ቍ32)፣ የሮም ዜጋ ነበር (ቍ16፥37)።

15፥23 *በአንጾኪያ፣ በሶርያና በኪልቅያ*፤ አንጾኪያ፣ ለሁለቱም ማለት ለሶርያና ለኪልቅያ አውራጃዎች ዋና ከተማ ነበረች።

15፥28 *ለመንፈስ ቅዱስም ለእኛም መልካም መስሎ ታይቶናል*፤ ሥልጣኑ በቅድሚያ የመንፈስ ቅዱስ ይሁን እንጂ በሐዋርያት፣ በመሪዎችና በወንድሞችም መካከል በአንድ ልብ የመ ወሰን ሁኔታ ነበር (ቍ22-23)።

15፥29 *ለጣዖት ከተሠዋ ነገር… ከዝሙት ርኵሰት እንድ ትርቁ*፤ የቍ20 ማብ ይመ።

15፥32 *ነቢያት*፤ እዚህ ላይ እንደ ተመለከተው፣ በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ከነቢያት ተግባራት መካከል ዋናው፣ ወንድሞ ችን ማጽናናትና ማበረታታት ነበር።

15፥36 *የጌታን ቃል ወደ ሰበክንባቸው ከተሞች*፤ በመጀ መሪያ ሐዋሪያዊ ጕዞ የተካሄደባቸው ከተሞች ናቸው (13፥4-14፥26 ይመ)።

15፥38 *ከእነርሱ ተለይቶ ስለ ቀረና*፤ ጴርጌን ሲደርሱ ማርቆስ ስለ ተመለሰ፣ ወደ አንጾኪያ፣ ወደ ኢቆንዮን ወደ ልስጥራና ወደ ደርቤ አልሄደም ነበር (የ13፥13 ማብ ይመ)።

15፥39 *ተለያዩ*፤ ከዚህ በኋላ የበርናባስንና የማርቆስን ስም በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሲወሣ አናገኝም። ይሁን እንጂ በ1ቆሮ 9፥6 በርናባስ ከማንም ጥቅም ሳይሻ ራሱን ችሎ አገልግሎት በመ ስጠቱ፣ ጳውሎስ በአርአያነት ጠቅሶታል። እንዲሁም በገላ 2:11-13 በአንጾኪያ ከተማ በርናባስን ያካተተ ሥራ መከናወኑ ተገ ልጿል፤ ማርቆስ ከበርናባስ ጋር የሚሠራውን ትቶ በመመለስ ከጴጥሮስ ጋር እናገኘዋለን (ጴጥ 5፥13 ይመ)። ጳውሎስ መጀ መሪያ በሮም በታሠረ ጊዜ፣ ማርቆስ ከሌሎች ጋር አብሮት ነበረ (ቈላ 4፥10፤ ፊል 24ይመ)። ጳውሎስ፣ ወደ ሕይወቱ ፍጻሜ አካባቢ፣ ማርቆስን እጅግ ከማድነቁ የተነሣ በዚያች በጣት በምት ቈጠር ቀሪ ዘመኑ ከአጠገቡ እንዲሆን ጠይቆታል (2ጢሞ 4፥11)። *ቆጵሮስ*፤ በርናባስ የተወለደባት ደሴት ናት (ከ4፥36 ጋር ያነጻጽሩ)።

15፥40 *ሲላስን*፤ ከኢየሩሳሌም የተላከውን ደብዳቤ ካደረሰ በኋላ፣ ከይሁዳ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶአል (ቍ32-33)።

ይቶአቸው ሄደ፤ [41]አብያተ ክርስቲያናትንም
እያበረታታ በሶርያና በኪልቅያ በኩል ዐለፈ።

**ጢሞቴዎስ ከጳውሎስና ከሲላስ ጋር ተሰማራ**

16 ጳውሎስ ወደ ደርቤንና ወደ ልስጥራን
ደረሰ። በዚያም እናቱ አይሁዳዊት
ሆና በጌታ ያመነች፣ አባቱ ግን የግሪክ ሰው
የሆነ፣ ጢሞቴዎስ የተባለ አንድ ደቀ መዝ
ሙር ነበረ። [2]እርሱም በልስጥራንና በኢቆን
ዮን በነበሩት ወንድሞች ዘንድ መልካም
ምስክርነት ነበረው። [3]ጳውሎስም ይህ ሰው
ከእርሱ ጋር እንዲሄድ ፈለገ፤ ስለዚህ በዚያ
አካባቢ በነበሩ አይሁድ ምክንያት ይዞ ገረ
ዘው፤ እነዚህ አይሁድ በሙሉ የጢሞቴዎስ
አባት የግሪክ ሰው እንደ ሆነ ያውቁ ነበርና።
[4]እነርሱም ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላው በሚ
ያልፉበት ጊዜ፣ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች
በኢየሩሳሌም ያሳለፉትን ውሳኔ ተቀብለው
እንዲጠብቁ ለምእመናኑ ይሰጡ ነበር። [5]አብ
ያተ ክርስቲያናትም በእምነት እየበረቱና ዕለት
ዕለትም በቍጥር እየጨመሩ ይሄዱ ነበር።

**ጳውሎስ ስለ መቄዶንያው ሰው ያየው ራእይ**

[6]ጳውሎስና ባልደረቦቹ ቃሉን በእስያ እን
ዳይሰብኩ መንፈስ ቅዱስ ስለ ከለከላቸው፣
በፍርግያና በገላትያ አገር ዐልፈው ሄዱ።
[7]ወደ ሚስያም በተቃረቡ ጊዜ፣ ወደ ቢታንያ
ሊገቡ ሞከሩ፤ ነገር ግን የኢየሱስ መንፈስ

15፥41 ቍ23፤ ሉቃ 2፥2፤ሐሥ6፥9፤16፥5
16፥1 ሐሥ14፥6፤ 1ቆሮ4፥17፤16፥10፤2 ቆሮ1፥1:19፤ፊል1፥1፤ 2፥19፤1ተሰ3፥2:6፤ 1ጢሞ1፥2:18፤ 2ጢሞ 1፥2:5:6
16፥2 ቍ40፤ ሐሥ 1፥16፤13፥51
16፥3 ገላ2፥3
16፥4 ሐሥ11፥30፤ 15፥2:28:29
16፥5 ሐሥ2፥41፤ 9፥31፤15፥41
16፥6 ሐሥ2፥9:10፤ 18፥23፤ገላ1፥2፤3፥1
16፥7 ሮሜ8፥9፤ገላ 4፥6፤ፊል1፥19፤1ጴጥ1፥11


ወደ ላኩት ወገኖች ከተመለሰ በኋላ፣ እንደገና ወደ አንጾኪያ መም ጣቱ ደግሞ በአንጾኪያ መገኘቱ የአገልግሎት ኀላፊነቱን ለመወጣት በማሰቡ እንደ ሆነ ያመለክታል።

16፥1 *ደርቤና* የ14፥6:20 ማብ ይመ። እዚህ ላይ የከተማ ዎቹ ቅደም ተከተል የተለዋወጠው፣ ጳውሎስ በመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉ ዞው ወደ ደርቤን የመጣው ከዚህኛው በተቃራኒ አቅጣጫ ስለ ነበር ነው። *ልስጥራ*፡ የ14፥6 ማብ ይመ። *ጢሞ ቴዎስ*፡ ጳውሎስ ጢሞቴ ዎስን ከ15 ዓመት በኋላ፣ እንደ ወጣት አድርጎ ስለሚያቀርበው (1ጢ ሞ4፥ 12)፣ ጢሞቴዎስ በዚህ ጊዜ ትንሽ ልጅ ሳይሆን አይቀርም። *አባቱ ግን የግሪክ ሰው*፤ ስለ እናቱ እምነት እዚህና በ2ጢሞ 1፥5 ላይ ሲገለጽ ስለ አባቱ እምነት አለመገለጹ አባቱ የአይሁድ እምነት አለመቀበሉንና በክ ርስቶስም አለማመኑን ያመለክታል።

16፥3 *ይዞ ገረዘው*፤ በአይሁድ ዘንድ የነበረው ሥራ እንዳ ይደናቀፍበት አስቦ ነው። ይኸኛው፣ አንዳንዶች ግዝረትን ለድ ነት አስፈላጊ አድርገው በመቃወም እንደ ተከራከሩበት፣ ከቲቶ ሁኔታ የተለየ አይደለም (ገላ 2፥3)።

16፥6 *ባልደረቦቹ*፤ ሲላስና ጢሞቴዎስ ናቸው። *በእስያ*፤ ይህችኛዪቱም ቀደም ሲል አንዲት አነስተኛ ስፍራ ነበረች፤ በኋላ ግን ሚስያ፣ ሊድያ፣ ካሪያ የተባሉትን የግሪክ ወረዳዎችና ከፍርግያም የተወሰኑ ቦታዎች ጨምራ አውራጃ ሆነች። *በፍር ግያ*፤ ቀደም ሲል ከግሪክ አውራጃዎች እንደ አንዱ ትቈጠር ነበር፤ በኋላ ግን ለሁለቱ የሮማ አውራጃ ለእስያና ለገላትያ ተከ ፍላለች። ኢቆንዮንና አንጾኪያ የተባሉት ከተሞች የሚገኙት በገላ ትያዋ ፍርግያ ውስጥ ነበር። *በገላትያ*፤ ቀድሞ አውራጃዪቱ በግ ሪክ ሥር ነበረች፤ የግሪክን ግዛት በአጠቃላይ የሚያመለክት፤ ነገር ግን ከ25 ዓ.ቅ.ክ በፊት እጅግ ተስፋፍታ በዚሁ ስም የም ትጠራ የሮማ ውያን አውራጃ ሆነች።

16፥7 *ሚስያም*፤ በእስያ አውራጃ ሰሜን ምዕራብ ክፍል ትገኝ ነበር። ሉቃስ እነዚህን አውራጃዪች በቀየው የግሪክ ስማቸው ይጠራቸዋል፤ ጳውሎስ የሚጠራቸው ግን ሮማውያን በሰጧቸው ስም ነው። ቢታኒያ፤ ከ74 ዓ.ቅ.ክ. ጀምሮ የሮማውያን አውራጃ ሆነች፤ የምትገኘውም ከሚስያ በስተ ምሥራቅ ነበር። *የኢየሱስ*




**የጳውሎስ ሁለተኛው የወንጌል ጉዞ**
**49-52 ዓ.ም**
ሐሥ 15:39-18:22

አልፈቀደላቸውም፤ [8]ስለዚህ በሚስያ በኩል
አድርገው ወደ ጢሮአዳ ወረዱ። [9]ጳው
ሎስም ሌሊት በራእይ አንድ የመቄዶንያ
ሰው ቆሞ፣ “ወደ መቄዶንያ ተሻግረህ እር
ዳን” ሲለው አየ። [10]ጳውሎስ ይህን ራእይ ካየ
በኋላ፣ እግዚአብሔር ወንጌልን እንድንሰ
ብክላቸው ጠርቶናል ብለን በመወሰን ወዲ
ያው ወደ መቄዶንያ ለመሄድ ፈለግን።

### ልድያ በፊልጵስዩስ በጌታ አመነች

[11]ከጢሮአዳ በመርከብ ተነሥተን በቀጥታ
ተጕዘን ወደ ሳሞትራቄ መጣን፤ በማግስቱም
ጕዞአችንን ወደ ናጱሌ ቀጠልን፤ [12]ከዚያም
የሮማውያን ቅኝና የአካባቢው የመቄዶንያ
ግዛት ዋና ከተማ ወደ ሆነችው ወደ ፊልጵ
ስዩስ ገባን፤ በዚያም አያሌ ቀን ተቀመጥን።
[13]በሰንበት ቀንም፣ የጸሎት ስፍራ በመ
ፈለግ፣ ከከተማዪቱ በር ወጥተን ወደ አንድ
ወንዝ ወረድን፤ በዚያም ተቀምጠን ተሰብ
ስበው ለነበሩት ሴቶች መናገር ጀመርን።
[14]ከሚያዳምጡትም ሴቶች መካከል ልድያ
የምትባል አንዲት ሴት ነበረች፤ እርሷም
እግዚአብሔርን የምታመልክና ከትያጥሮን ከተማ
የመጣች የቀይ ሐር ነጋዴ ነበረች። ጌታም፣
ጳውሎስ የሚናገረውን በማስተዋል ትሰማ
ዘንድ፣ ልቧን ከፈተላት። [15]እርሷና ቤተ
ሰዎቿ ከተጠመቁ በኋላም፣ “በጌታ ማመ
ኔን በእርግጥ ከተረዳችሁልኝ ወደ ቤቴ
መጥታችሁ ጥቂት ተቀመጡ” በማለት
አጥብቃ ለመነችን።

### ጳውሎስና ሲላስ በወህኒ ቤት

[16]አንድ ቀን ወደ ጸሎት ስፍራ ስንሄድ፣
በጥንቈላ መንፈስ ትንቢት የምትናገር አንዲት
የቤት አገልጋይ አገኘችን፤ እርሷም በዚህ
የጥንቈላ ሥራዋ ለአሳዳሪዎችዋ ብዙ ገን
ዘብ ታስገኝላቸው ነበር። [17]ይህችው አገል
ጋይ ጳውሎስንና እኛን እየተከተለች፣ “እነ
ዚህ ሰዎች የመዳንን መንገድ የሚነግሯችሁ፣
የልዑል እግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው!” በማ
ለት ትጮኽ ነበር፤ [18]ይህንም ብዙ ቀን ደጋ
ገመችው፤ ጳውሎስ ግን በዚህ እጅግ በመ
ታወኩ ዘወር ብሎ ያን መንፈስ፣ ከእርሷ እን
ድትወጣ “በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝ
ሃለሁ!” አለው፤ መንፈሱም በዚያው ቅጽ
በት ወጣላት።
[19]አሳዳሪዎቿም የገንዘብ ማግኛ ተስፋቸው
ወጥቶ መሄዱን በተረዱ ጊዜ፣ ጳውሎስንና
ሲላስን ይዘው እየጐተቱ ባለ ሥልጣኖች ወዳ
ለበት ወደ ገበያ ቦታ አመጧቸው። [20]ገዦቹም
ፊት አቅርበዋቸው እንዲህ አሉ፤ “እነዚህ

16፥8 ቍ11፤ ሐሥ 20፥5፤2ቆሮ2፥12፤ 2ጢሞ 4፥13
16፥9 ሐሥ9፥10፤ 19፥21፡29፤20፥1፡3፤ ሮሜ15፥26፤1ቆሮ 16፥5፤1ተሰ1፥7፡8
16፥10 ቍ10-17፤ 20፥5-15፤21፥1-18፤ 27፥1-28፡16፤ ሐሥ 14፥7
16፥11 ቍ8
16፥12 ቍ9፤ሐሥ 20፥6፤ፊል1፥1፤1ተሰ2፥2
16፥13 ሐሥ13፥14
16፥14 ሉቃ24፥45፤ ራእ1፥11፤2፥18፡24
16፥15 ሐሥ2፥38፤ 11፥14
16፥16 ቍ13፤ዘዳ 18፥11፤1ሳሙ28፥3፡7
16፥17 ማር5፥7
16፥18 ማር16፥17
16፥19 ቍ16፤ሐሥ 8፥3፤15፥22፤17፥6፤ 19፥25፡26፤21፥30፤ ያዕ2፥6
16፥20 ሐሥ17፥6

***መንፈስ፤*** አንዳንድ ጊዜ “እግዚአብሔር” ለማለት “መንፈስ ቅዱስ” የሚለው ስም እግዚአብሔር የሚለውን ስም ተክቶ እንደሚገባ ሁሉ (5፥3-4 ይመ)፣ እዚህም ላይ “መንፈስ ቅዱስ” “የኢየሱስ መንፈስ” ተብሎአል። ***አልፈቀደላቸውም፤*** መንፈስ ቅዱስ በተለያየ መንገድ ምሪት ሰጥቶአቸው ሊሆን ይችላል፤ ይኸውም በራእይ፣ በሁኔታዎች፣ ወይም በነቢያት በኩል ተናግሮ ይሆናል።

16፥8 ***ጢሮአዳ፤*** ከጥንታዊቷ ትሮይ 16 ኪ.ሜ ላይ ርቃ ትገኛለች፤ ሙሉ ስሟ እስክንድርያ ጢሮአዳ ሲሆን፣ የሮም ቅኝ ግዛት ነበረች፤ በአንድ በኩል መቄዶንያንና ግሪክን በሌላም በኩል ትንሿን እስያን የምታገናኝ ዋና የባሕር ወደብ ነበረች። ጳውሎስ በሦስተኛው ሐዋርያዊ ጕዞው (2ቆሮ 2፥12 ይመ) በኤፌሶን ካስተማረ በኋላ ወደ ጢሮአዳ ተመልሶአል። በአንድ ወቅት ጳውሎስ በሁለተኛው ወይም በሦስተኛው ጕዞው ተመልሶ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ በጢሮአዳ የሚገኙ ክርስቲያኖችን አገልግሎ ነበር (20፥5-12)።

16፥9 ***በራእይ፤*** እግዚአብሔር ምሪትን ከሚሰጥባቸው መንገዶች አንዱ ነው (ከ10፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። ***የመቄዶንያ ሰው፤*** በ148 ዓ.ቅ.ክ በፊት መቄዶንያ የሮማውያን አውራጃ ሆነች። አንዳንዶች እንደሚሉት ይህ ሰው ሉቃስ ስለ መሆኑ ምንም ፍንጭ የለም፤ ይሁን እንጂ ሉቃስ ከዚህ ቡድን ጋር የተቀላቀለው በዚህ ጊዜ ነበር ።

16፥10 ***ለመሄድ ፈለግን (እኛ)፤*** በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ “እኛ” በማለት የሚተርከው ክፍል የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው። እንግዲህ እዚህ ላይ ሉቃስ በጢሮአዳ ከቡድኑ ጋር እንደ ተቀላቀለ ለአንባቢ ለመግለጽ ፈልጎአል ማለት ይቻላል።

16፥11 ***ሳሞትራቄ፤*** በኢጂያን ባሕር በሰሜን ምሥራቅ ላይ የምትገኝ ደሴት ናት። በጨለማ በባሕር ላይ ለመጓዝ አስጊ ስትሆን ጀልባዎችን ለማሳረፍ ግን የተመቸች ቦታ ነበረች። ***ናጱሌ፤*** 16 ኪ.ሜ. ላይ ርቃ የምትገኝና ዛሬ ካቫላ ተብላ የምትጠራ ስትሆን፣ ቀድሞ የፊልጵስዩስ ወደብ ነበረች።

16፥12 ***ፊልጳስዩስ፤*** ከመቄዶንያ በስተ ምሥራቅ የምትገኝ ከተማ ስትሆን፣ በትልቅ እስክንድር አባት በዳግማዊ ፊልጶስ ስም የተሰየመች ናት። የሮም ቅኝ ግዛት በመሆኗ፣ ከአውራጃው አስተዳደር ነጻ ሆና፣ ራሱ የቻለ የሮም መንግሥት አስተዳደር ዐይነት መዋቅር ነበራት (የ13፥14 ማብ ይመ)። ብዙዎች በጡረታ የተገለሉ የሮም ወታደሮች ሲኖሩባት፣ በዚያ የሚኖሩት አይሁድ ቍጥር ግን ጥቂት ነበር። ***ዋና ከተማ፤*** ተሰሎንቄ የመቄዶንያ ዋና ከተማ ነበረች፤ መቄዶንያ አራት ወረዳዎች ሲኖሯት ፊልጶስዩስ ግን ከነዚህ ቀዳሚ ነበረች፤ ይሁን እንጂ አምፊጶሊስም የዚህች ወረዳ የመጀመሪያዋ ከተማ ናት።

16፥13 ***የጸሎት ስፍራ፤*** በፊልጵስዩስ የነበሩት አይሁድ በጣም ጥቂት በመሆናቸው፣ ምኵራብ በዚያ አልነበረም፤ ስለዚህ እነዚሁ አይሁድ ለጸሎት ይሰበሰቡ የነበሩት በጋንጊጥ ወንዝ ዳር ነበር። በወንዝ ዳር አጠገብ ጸሎት ማድረግም የተለመደ ነበር።

16፥14 ***ልድያ፤*** በንግድ ሥራ የምትተዳደር ሴት ነበረች፤ ስሟ የተወረሰው ከመጣችበት፣ የግሪክ ወረዳ ከልድያ የተወሰደ ይመስላል። ***ትያጥሮን፤*** በሮም አውራጃ በእስያ የምትገኝ ሲሆን፣ ከጴርጋሞን ደቡብ ምሥራቅ 32 ኪ.ሜ ያህል ትርቃለች። ይህች ከተማ በልብስ ማቅለም ሥራ በተለይም ለቤተ መንግሥት የሚሆን ቀይ ሐር በማቅለም የታወቀች ነበረች፤ ራእ 1፥11 እና የራእ 2፥18 ማብ ይመ። ***እግዚአብሔርን የምታመልክና፤*** ልድያ እንደ ቆርኔሌዎስ ሁሉ ከአሕዛብ ወገን ስትሆን (ሐሥ 10፥2) በአንድ አምላክ አምና በቅዱሳት መጻሕፍት በተደነገገ ሥነ ምግባራዊ ሕይወት የምትመላለስ ነበረች። ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉ ወደ አይሁድ እምነት የገባች አልነበረችም። ***ልቧን ከፈተላት፤*** የደቀ መዛሙርቱ አእምሮ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያስተውል ዘንድ ከትንሣኤ በኋላ ብሩህ ሆኖ ነበር (ሉቃ 24፥45)፤ የልድያም ልብ እንደዚሁ የጳውሎስን ትምህርት ለመቀበል የተመቻቸ ሆነ።

16፥16 ***በጥንቈላ መንፈስ የምትናገር፤*** መንፈሱ የ“ፒቶን” መንፈስ ይባላል። የጋኔን መንፈስ ማለት ነው። “ፒቶን” በግሪኩ የተረታ ተረት እምነት፣ ዘንዶ ሲሆን፣ በዴልፊ ቤተ ጣዖት ይመለካል፤ ከዴልፈም ንግርት ጋር ግንኙነት አለው። ይህ መንፈስ ዐድሮበት በእርሱ አማካይነት ይናገራል ተብሎ የሚታመነውም ሰው፣ በዚሁ ስም መጠራቱ የተለመደ ነበር። እንደዚህ ያለው ሰው የሚናገረውም፣ እርሱ ራሱ የሚያስበውን፣ የሚያወቀውን ሳይሆን፣ ያደረበት መንፈስ ወይም ጋኔን የሚያ ናግረውን በመሆኑ ባገራችን “የዛር ፈረስ” ይባላል። እንግዲህ ይህች ሰው የወደፊቱን ትናገራለች የሚባለው እስከምን ድረስ መሆኑን ማወቅ አይቻልም።

16፥17 ***እኛን፤*** “እኛ” እያለ ሲተርክ የነበረው ክፍል እዚህ ላይ ያበቃለትና (የቍ10 ማብ ይመ)፣ በ20፥5 ላይ እንደገና “እኛ” ብሎ ይጀምራል። ***የልዑል እግዚአብሔር፤*** በርኵስ መንፈስ ተይዞ የነበረው ሰው የተናገረው (ማር5፥7) እዚህም ተደገመ። በአይሁድ ዘንድ አባባሉ የተለመደ (ዘኍ 24፥16፤ ኢሳ 14፥14፤ ዳን 3፥26 ይመ) በግሪኮችም የታወቀ መጠሪያ ነበር (እንደ ድንጋይ፣ እንደ ብረት ባሉ ነገሮች ላይ ተቀርጾ ተገኝቶአል)። ይሁን እንጂ ቃሉ በክርስቲያኖችም ሆነ በአይሁድ ዘንድ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለእግዚአብሔር መጠሪያነት አልዋለም (ከሐሥ 7፥48 ጋር ያነጻጽሩ)።

ሰዎች አይሁድ ሆነው ሳሉ፣ ከተማችንን
አውከዋል፤ [21]ደግሞም እኛ ሮማውያን መቀ
በል ወይም መፈጸም የማይገባንን ልማድ በሕ
ዝቡ መካከል ይነዛሉ።”

[22]ሕዝቡም ተባብረው በጳውሎስና በሲላስ
ላይ ተነሡባቸው፤ ገዦቹም ልብሳቸው ተገፎ
በበትር እንዲደበደቡ አዘዙ። [23]ክፉኛ ከተደ
በደቡ በኋላም ወደ ወህኒ ቤት አስገቧ
ቸው፤ የወህኒ ቤት ጠባቂውም ተጠንቅቆ
እንዲጠብቃቸው አዘዙት። [24]እርሱም ይህን
የመሰለ ትእዛዝ ከተቀበለ በኋላ፣ ወደ ወህኒ
ቤቱ ውስጠኛ ክፍል አስገብቶ እግራቸውን ከግ
ንድ ጋር አጣብቆ አሰራቸው።

[25]እኩለ ሌሊት አካባቢ ጳውሎስና ሲላስ
እየጸለዩና እየዘመሩ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ
ነበር፤ ሌሎቹ እስረኞችም ያዳምጧቸው ነበር።
[26]ድንገትም የወህኒ ቤቱን መሠረት የሚያና
ውጥ ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ሆነ፤ ወዲያ
ውም የወህኒ ቤቱ በሮች ተከፈቱ፤ የሁሉም
እስራት ተፈታ። [27]የወህኒ ቤቱ ጠባቂም ከእ
ንቅልፉ ነቅቶ የወህኒ ቤቱ በሮች ተከፍ
ተው ባየ ጊዜ፣ እስረኞቹ ያመለጡ መስ
ሎት ራሱን ለመግደል ሰይፉን መዘዘ።
[28]ጳውሎስ ግን ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ “እኛ
ሁላችን እዚሁ ስላለን፣ በራስህ ላይ ክፉ
ነገር አታድርስ!” ብሎ ጮኸ።

[29]የወህኒ ቤቱ ጠባቂም መብራት ለምኖ
ወደ ውስጥ ዘሎ ገባ፤ እየተንቀጠቀጠም በጳውሎ
ስና በሲላስ እግር ላይ ወደቀ፤ [30]ይዞአቸው
ከወጣ በኋላ፣ “እናንት ሰዎች፤ እድን ዘንድ
ምን ላድርግ?” አላቸው።

[31]እነርሱም፣ “በጌታ በኢየሱስ እመን፤
አንተም ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ” አሉት።
[32]ከዚያም ለእርሱና በቤቱ ላሉት ሰዎች
ሁሉ የጌታን ቃል ተናገሩ። [33]የወህኒ ቤት ጠባ
ቂውም ሌሊት በዚያኑ ሰዓት ወስዶ ቍስ
ላቸውን አጠበላቸው፤ ወዲያውም እርሱና
ቤተ ሰቡ ሁሉ ተጠመቁ። [34]የወህኒ ቤቱ ጠባ
ቂም ወደ ቤቱ ወስዶ ማእድ አቀረበላቸው፤
ከቤተ ሰቡም ሁሉ ጋር ባለእግዚአብሔር በማመኑ
በደስታ ተሞላ።

[35]ሲነጋም፣ ገዦቹ፣ “እነዚያን ሰዎች
ፈተህ ልቀቃቸው” ብለው መኰንኖቻቸውን
ላኩበት። [36]የወህኒ ቤት ጠባቂውም፣ “ገዦቹ
እንድትፈቱ አዘዋል፤ ስለዚህ ወጥታችሁ በሰ
ላም ሂዱ” ብሎ ለጳውሎስ ነገረው።

[37]ጳውሎስ ግን፣ “እኛ የሮም ዜጎች
ሆነን ሳለን፣ በሕዝብ ፊት ያለ ፍርድ ደብ
ድበው ወደ እስር ቤት ወረወሩን፤ ታዲያ
አሁን በስውር ሊያስወጡን ይፈልጋሉ? ይህማ
አይሆንም፤ እነርሱ ራሳቸው መጥተው ያስ
ወጡን!” አላቸው።

[38]መኰንኖቹም ይህንኑ ቃል ለገዦቹ
ነገሯቸው፤ እነርሱም ጳውሎስና ሲላስ
የሮም ዜጎች መሆናቸውን ሲሰሙ ደነገጡ፤
[39]እነርሱ ራሳቸውም መጥተው ይቅርታ ጠይ
ቀው ከወህኒ ቤቱ አወጧቸው፤ ከተማው
ንም ለቀው እንዲሄዱ ለመኗቸው። [40]ጳው
ሎስና ሲላስ ከእስር ቤቱ ከወጡ በኋላ ወደ
ልድያ ቤት ሄዱ፤ በዚያም ወንድሞችን አግ
ኝተው አበረታቷቸው፤ ከዚያም በኋላ
ሄዱ።

## ጳውሎስና ሲላስ በተሰሎንቄ

**17** ጳውሎስና ሲላስም በአንፊጶልና በአ
ጶሎንያ ዐልፈው ወደ ተሰሎንቄ
ሄዱ፤ በዚያም የአይሁድ ምኵራብ ነበር።
[2]ጳውሎስም እንደ ልማዱ ወደ ምኵራብ
ገባ፤ ሦስት ሰንበትም ከቅዱሳት መጻሕፍት
እየጠቀሰ ከእነርሱ ጋር ተነጋገረ፤ [3]ክርስቶስ[ሙ]
መከራን መቀበል እንዳለበትና ከሙታንም
መነሣት እንደሚገባው እያስረዳ በማረጋ
ገጥ፣ “ይህ እኔ የምሰብክላችሁ ኢየሱስ
እርሱ ክርስቶስ ነው” አላቸው። [4]አይሁድም
አንዳንዶቹ የሰሙትን በመቀበል ከጳውሎ
ስና ከሲላስ ጋር ተባበሩ፤ ደግሞም ቍጥራ

[ሙ]3 ወይም መሲሕ

16፥21 ቍ12፤ አስ 3፥8
16፥22 2ቆሮ11፥25፤1ተሰ2፥2
16፥23 ቍ27፡36
16፥24 ኢዮ13፥27፤33፥11፤ኤር20፥2፡3፤29፥26
16፥25 መዝ119፥55፡62፤ሐሥ15፥22፤ኤፌ5፥19
16፥26 ሐሥ4፥31፤5፥19፤12፥7፡10
16፥27 ሐሥ12፥19
16፥29 ሐሥ15፥22
16፥30 ሐሥ2፥37
16፥31 ዮሐ3፥15፤ሮሜ11፥14፤ሐሥ11፥ 14
16፥33 ቍ25፤ሐሥ2፥38
16፥34 ሐሥ11፥14
16፥36 ቍ23፡27፤ሐሥ15፥33
16፥37 ሐሥ22፥25-29
16፥38 ሐሥ22፥29
16፥39 ማቴ8፥34፤ሉቃ8፥37
16፥40 ቍ2፡14፤ሐሥ1፥16
17፥1 ቍ11፡13፤ፊል4፥16፤1ተሰ1፥1፤2ተሰ1፥1፤2ጢሞ4፥10
17፥2 ሐሥ8፥35፤9፥20፤13፥14፤18፥28
17፥3 ሉቃ24፥26፡46፤ሐሥ2፥24፤3፥18፤9፥22
17፥4 ሐሥ15፥22

16፥21 *የማይገባንን ልማድ፣* አንድ ሃይማኖት የሮምን መንግሥት ፈቃድ ካላገኘ፣ እንደ ሕገ ወጥ ይቈጠር ነበር፤ የአይሁድ ሃይማኖት የመንግሥት ፈቃድ ሲኖረው፣ ክርስትና ግን አልነበረውም።

16፥22 *እንዲደበደቡ፤* በብትር ማለት ነው።

16፥24 *ወህኒ ቤቱ ውስጠኛ ክፍል ...ከግንድ፣* እስረኛው እንዳያመልጥ በጥብቅ ለማሰር ብቻ ሳይሆን፣ ለማሠቃየትም ጭምር ነበር።

16፥27 *ራሱን ለመግደል፤* አንድ እስረኛ ካመለጠ፣ የወሕኒ ጠባቂው በገመዱ ይገባል፤ (12፥19 ይመ)። ዘብ ጠባቂው ራሱን ለማጥፋት የቃጣው ከሥቃዩና ከኀፍረቱ ለመገላገል ሲል ነው።

16፥30 *እድን ዘንድ ምን ላድርግ?* የወህኒ ጠባቂው፣ እነዚህ ሰዎች ስለ ድነት መንገድ የሚሰብኩ መሆናቸውን ሰምቶአል (ቍ17)። ይህ ወቅት መሬት የተንቀጠቀጠበት፣ ሞት በዐናቱ ላይ ያንዣበበበት መሆኑን የተረዳበት ጊዜ በመሆኑ፣ ስለ ትክክለኛው መንገድ ለማወቅ ስለፈለገ ጠየቃቸው።

16፥31 *በጌታ በኢየሱስ እመን፤* ስለ ድነት መንገድ የቀረበ የማያዳግም ቃል ነው (10፥43 ይመ)።

16፥32 *የጌታን ቃል፤* 10፥36 ይመ። ጳውሎስና ሲላስ የወንጌልን ምስጢር ለወህኒ ጠባቂውና ለቤተ ሰቡ ግልጥልጥ አድርገው አብራሩላቸው፤ እናም የሰሙት ሁሉ አምነው ዳኑ (ቍ34)።

16፥34 *በደስታ ተሞላ፤* ማንም ሰው ወንጌልን ከተቀበለ፣ ሁኔታዎች ደስታውን አያስቀሩበትም (የ8፥39 ማብ ይመ)።

16፥37 *ያለ ፍርድ፣* አንድ የሮም ዜጋ የሆነ ሰው፣ እንኳን ያለ ፍርድ ሊገረፍ ይቅርና ቢያጠፋ እንኳን በአደባባይ አይገረፍም፤ በሕግ ያስጠይቃል (ቍ38)። *እነርሱ ራሳቸው መጥተው፣* ጳውሎስና ሲላስ ክብራቸው በመነካቱ፣ ያ እንዲታደስላቸው ሳይሆን፣ በፊልጵስዩስ ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን የሚበጅ ሁኔታ ይመቻችላት ዘንድ ምንም ጥፋት የሌለባቸው መሆኑ እንዲታወቅ ነው።

17፥1 *በአንፊጶልና...ተሰሎንቄ፤* የኢግናትያ መንገድ የተባለው የዛሬዋን ሰሜን ግሪክ ምዕራብ በማቋረጥ ፊልጵስዩስ፣ አንፊጶል፣ አጶሎንያንና ተሰሎንቄ የተባሉትን ከተሞች ያገናኛል። መንገዱ ዛሬም በአንዳንድ ስፍራዎች ማለት በካቫላ (ኒይጶሊስ)፣ በፊልጵስ ዩስና በአጶሎንያ ይገኛል። አንድ ሰው በቀን 48 ኪ.ሜ. መጓዝ ቢችል፣ ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላው ለመድረስ አንድ ቀን ይፈጅ በታል። *ተሰሎንቄ፤* ከፊልጵስዩስ 160 ኪ.ሜ. ያህል ርቃ ትገኛለች። የመቄዶንያ ዋና ከተማ ስትሆን በዚያ የሚኖሩትን አይሁድና ምኵራባቸውን ጨምሮ ከሁለት መቶ ሺህ ሕዝብ በላይ ይኖርባት ነበር። ጳውሎስ በዚህ ቦታ ለመስበክ ያሰበውም ከላይ የተዘረዘረውን ሁሉ በማገናዘብ ነበር።

17፥2 *ምኵራብ፤* የ13፥14 ማብ ይመ። *ሦስት ሰንበትም፣* እነዚህ ሁለቱ ሳምንታት የሚያመለክቱት ጳውሎስ በተሰሎንቄ የቈየባቸውን ጊዜያት በሙሉ ሳይሆን ከአይሁድ ጋር በምኵራብ ሲከራከር የቈየበትን ጊዜ ነው። የተሰሎንቄ መልእክቶች በትኵረት ሲታዩ፣ ጳውሎስ በሁለት ወይም በሦስት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ሊሰጥ የማይችለውን ትምህርት ማስተማሩን እንገነዘባለን።

ቸው ብዙ የሆነ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ግሪ
ኮችና አያሌ ዕውቅ ሴቶች የሰሙትን ተቀ
ብለው ከእነርሱ ጋር ተባበሩ።
5አይሁድ ግን ስለቀኑ ወስላቶችን ከገበያ
ቦታ አሰባሰቡ፤ ሕዝቡንም አነሣሥተው በከ
ተማው ውስጥ ሁከት ፈጠሩ፤ ጳውሎስንና
ሲላስንም አምጥተው ሕዝቡ ፊት[a] ለማቅ
ረብ ወደ ኢያሶን ቤት እየተጣደፉ ሄዱ፤ 6ነገር
ግን ሊያገኟቸው አልቻሉም፤ ስለዚህ ኢያ
ሶንንና ሌሎች ወንድሞችን በከተማው ባለ
ሥልጣናት ፊት እየጐተቷቸው እንዲህ
እያሉ ጮኹ፤ "እነዚህ ሰዎች ዓለሙን ሁሉ
ሲያውኩ ቈይተው፣ አሁን ደግሞ ወደዚህ
መጥተዋል፤ 7ኢያሶንም በቤቱ ተቀብሎአ
ቸዋል፤ እነዚህም ሁሉ፣ 'ኢየሱስ የሚባል
ሌላ ንጉሥ አለ' በማለት የቄሳርን ሕግ
የሚጥሱ ናቸው።" 8ሕዝቡና የከተማውም
ሹማምንት ይህን በሰሙ ጊዜ ተሸበሩ፤ 9ከዚ
ያም ኢያሶንንና ሌሎቹን በዋስ ለቀቋቸው።

## ጳውሎስና ሲላስ በቤርያ

10ወንድሞችም ወዲያው ጳውሎስንና ሲላ
ስን በሌሊት ወደ ቤርያ ሰደዱአቸው፤ እነርሱም
እዚያ በደረሱ ጊዜ፣ ወደ አይሁድ ምኵራብ
ገቡ። 11የቤርያ ሰዎች ከተሰሎንቄ ሰዎች
ይልቅ አስተዋዮች ነበሩ፤ ምክንያቱም ነገሩ
እንደዚህ ይሆንን እያሉ መጻሕፍትን በየዕ
ለቱ በመመርመር ቃሉን በታላቅ ጕጕት
ተቀብለዋል። 12ስለዚህ ከእነርሱ ብዙዎቹ አመኑ፤
ደግሞም ከእነርሱ ጋር ቍጥራቸው ከፍተኛ
የሆነ ዕውቅ የግሪክ ሴቶችና ወንዶችም አመኑ።
13በተሰሎንቄ ያሉት አይሁድም፣ ጳውሎስ
የእግዚአብሔርን ቃል በቤርያ ጭምር መስበኩን
ባወቁ ጊዜ፣ ሕዝቡን ለመቀስቀስና ለማነሣ
ሣት ወደዚያ ደግሞ ሄዱ። 14በዚህ ጊዜ ወን
ድሞች ጳውሎስን ቶሎ ብለው ወደ ባሕሩ
ዳርቻ ሰደዱት፤ ሲላስና ጢሞቴዎስ ግን
እዚያው ቀሩ። 15ጳውሎስን የሸኙት ሰዎ
ችም አቴና አደረሱት፤ ከዚያም ሲላስና ጢሞ
ቴዎስ ወደ እርሱ በፍጥነት እንዲመጡ
የሚል ትእዛዝ ተቀብለው ተመለሱ።

## ጳውሎስ በአቴና

16ጳውሎስ በአቴና ሆኖ ሲጠብቃቸው ሳለ፣
ከተማዪቱ በጣዖት የተሞላች መሆኗን በማ
የት መንፈሱ ተበሳጨበት። 17ስለዚህ በም
ኵራብ ሆኖ ከአይሁድና እግዚአብሔርን ከሚ
ፈሩ ግሪኮች ጋር፣ ደግሞም በገበያ ስፍራ ዕለት
ዕለት ከሚያገኛቸው ሰዎች ጋር ይነጋገር
ነበር። 18ከኤፊቆሮስና ከኢስጦኢክ የፍልስ
ፍና ወገን የሆኑትም ወደ እርሱ መጥተው
ይከራከሩት ነበር። አንዳንዶቹ፣ "ይህ ለፍ
ላፊ ምን ለማለት ይፈልጋል?" ይሉ ነበር፤
ሌሎች ደግሞ ስለ ኢየሱስና ስለ ትንሣኤው
የምሥራች ሲሰብክ ሰምተው፣ "ስለ አዳዲስ
ባዕዳን አማልክት የሚናገር ይመስላል" አሉ።
19ይዘውም አርዮስፋጎስ ወደ ተባለው ስፍራ
በመውሰድ እንዲህ አሉት፤ "አንተ የምታስ
ተምረው ይህ አዲስ ትምህርት ምን እንደ

17፥5 ቍ13፤ ሮሜ16፥21፤ 1ተሰ2፥16
17፥6 ማቴ24፥14፤ ሐሥ1፥16፤16፥19:20
17፥7 ሉቃ23፥2፤ ዮሐ19፥12
17፥9 ቍ5
17፥10 ቍ13፤ሐሥ 9፥20፤15፥22፤20፥4
17፥11 ቍ1፤ዘዳ 29፥29፤ሉቃ16፥29፤ ዮሐ5፥39
17፥12 ሐሥ2፥41
17፥13 ዕብ4፥12
17፥14 ሐሥ 9፥30፤ 15፥22፤16፥1
17፥15 ቍ16:21: 22፤ሐሥ18፥1:5፤ 1ተሰ3፥1
17፥17 ሐሥ9፥20
17፥18 ቍ31: 32፤ሐሥ4፥2፤13፥32
17፥19 ቍ22፤ ማር 1፥27

[a]5 *ወይም በሕዝብ ጉባኤ ፊት*

17፥4 *እግዚአብሔርን የሚፈሩ ግሪኮችና፤* የ10፥2፤16፥14 ማብ ይመ። *ሴቶች፤* ባሎቻቸው በከተማዪቱ ውስጥ የተከበሩ ሰዎች ሳይሆኑ አልቀሩም፤ ይሁን እንጂ መታወቅንና ክብሬታን በራሳቸው ማንነት ያተረፉ ሴቶች ነበሩ (ቍ12 ይመ)።

17፥5 *ስለቀኑ፤* እጅግ ብዙ ሰዎች (ብዛታቸው ጥቂት አይሁድን ጨምሮ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ብዙ አሕዛብ፣ እንዲሁም የታወቁትን ብዙ ሴቶች ያካትታል)። ጳውሎስ ለሰበከው ወንጌል ልባቸውን ክፍት በማድረጋቸው ነው (ከ13፥45 ጋር ያነጻጽሩ)። *የኢያሶን ቤት፤* ጳውሎስ ያረፈው እዚህ ሰው ቤት ሳይሆን አይቀርም።

17፥6 *በከተማው ባለሥልጣናት፤* 'ፖሊታርች' (የከተማው ከንቲባ) የሚለው የግሪክ ቃል እዚህና በቍ8 ላይ ብቻ ቢገኝ እንጂ በሌሎች የግሪክ ሥነ ጽሑፎች የትም ቦታ ላይ አይገኝም ነበር፤ ግን ከተሰሎንቄ በስተ ምዕራብ በአግናትያ መንገድ ላይ ተሠርቶ በነበረው ቅስት ላይ እ.ኤ.አ. በ1835 ዓ.ም. ተቀርጾ ተገኝቶአል። (ቅስቱ እ.ኤ.አ. በ1867 ዓ.ም. እንዳልነበረ ሆኖአል፤ ይሁን እንጂ ጽሑፉ የተቀረጸበት ክፍል ከመውደም ድኖ፣ በአሁኑ ሰዓት በብሪትሽ ሙዚዬም፣ ለንደን ውስጥ ይገኛል)። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በመቄዶንያ ዙሪያ በሚገኙት ከተሞችና በሌሎች ቦታዎች ይህ ቃል በ16 ሌሎች ድንጋይ መሰል ነገሮች ላይ ተቀርጾ ተገኝቶአል።

17፥7 *የቄሳርን ሕግ የሚጥሱ፤* በአይሁድ ዘንድ አንድ ሰው ከፍተኛ ወንጀል ፈጽሞአል የሚባለው፣ በአምላክ ላይ የስድብ ቃል ተናግሮ ሲገኝ ነው፤ በሮማውያን ዘንድ ግን በቄሣር ላይ ያመፀውን ንጉሥ ረድቶ ወይም ደግፎ መገኘት እንደ ትልቅ ክሕደት ሆኖ ይቈጠራል።

17፥9 *በዋስ ለቀቋቸው፤* ኢያሶን የማኅበረ ሰቡ ሰላምና ጸጥታ እንዳይደፈርስ ዋስትና ለመስጠት ተገድዶ ነበር፤ ይህን ባያደርግ ግን ንብረቱን የመወረስ ዐልፎ ተርፎም ሞት ይጠብቀው ነበር።

17፥10 *ጳውሎስና ሲላስ፤* ጢሞቴዎስን በፊልጵስዩስ ትተውት እንደ ገና በቤሪያ እንዳገኙት ይገመታል (ቍ10 እና ቍ14 ያነጻጽሩ)። *ቤሪያ፤* በመቄዶንያ አውራጃ፣ ከተሰሎንቄ ከተማ 80 ኪ.ሜ. ርቃ በሌላ ወረዳ ውስጥ የምትገኝ ከተማ ናት፤ ዛሬም ቤሪያ ትባላለች።

*ምኵራብ፤* የ13፥14 ማብ ይመ።

17፥14 *ወደ ባሕሩ ዳርቻ፤* ጳውሎስ ወደ አቴና የሄደው በጀልባ ነበር ማለት ይቻላል፤ ይሁን እንጂ በባሕሩ ዳርቻም ወደ አቴና የሚወስድ መንገድ ስለ ነበር እስከ ዳርቻው ድረስ 32 ኪ.ሜ. ያህል ከተሸኘ በኋላ ከዚያ በእግሩ ተጕዞ ሊሆን ይችላል፤ ያም ሆነ ይህ፣ አቴና እስኪደርስ ድረስ ወንድሞች አብረውት ነበሩ።

17፥15 *አቴና፤* ጳውሎስ አቴና ከመድረሱ ከአምስት መቶ ዓመት በፊት፣ ይህች ከተማ በኪነ ጥበብ፣ በፍልስፍና፣ እንዲሁም በሥነ ጽሑፍ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሳ ነበር። በፍልስፍና የነበራትን ዕውቅና ለዘመናት እንደያዘች ከመቈየቷም በላይ፣ ጳውሎስ በነበረበት ዘመን ስመጥር ዩኒቨርሲቲ ነበራት።

17፥17 *በምኵራብ፤* የ13፥14 ማብ ይመ። እግዚአብሔርን ከሚፈሩ ግሪኮች፤ የ10፥2 ማብ ይመ።

17፥18 *ከኤፊቆሮስና...የፍልስፍና ወገን፤* መሠረታዊው ትምህርታቸው፣ ዋናው ቁም ነገር ደስታን ማግኘት ነው የሚል ነበር፤ ደስታ ሲባልም ጊዜያዊውንና ዐላፊውን እርካታ ሳይሆን ዘላቂውን ነበር፤ ይሁን እንጂ ይህ ፍልስፍና ጳውሎስ በነበረበት ዘመን ወደ ስሜት እርካታ አስተሳሰብ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። *ከኢስጦኢክ የፍልስፍና ወገን፤* ሰዎች በቃኝ ማለትንና ራስን ችሎ መኖርን ዐውቀው፣ ራሳቸውን ገዝተው ከተፈጥሮ ጋር ተስማምተው መኖር አለባቸው ይሉ ነበር። በደኅና መልኩ ሲታይ የኢስጦኢክ ፍልስፍና የሚደነቅ ነበረ፤ ይሁን እንጂ ጳውሎስ በነበረበት ዘመን ሁሉ ይህኛውም እንደ ኤፊቆሮስ ፍልስፍና ሁሉ ወደ ትዕቢት በማዘንበል ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። *ለፍላፊ፤* ይህ ቃል በግሪክ ቋንቋ፣ ከዚህም ከዚያም ዘር እንደ ምትለቅም ወፍ፣ 'ዘር ለቃሚ' ማለት ነው። ቃሉ በአንጻሩም፣ ከየገበያው አንዳንድ ትምህርት በመቃረም በሚገባ ሳያብላላው እንዲሁ ለሚቀበጣጥር ሥራ ፈት እንዲውል ተደርጎአል።

17፥19 *አርዮስፋጎስ፤* ትርጕሙ "የአሬስ ኰረብታ" ማለት ነው። አሬስ በግሪክ የነጐድጓድና የጦርነት አምላክ ሲሆን፣ በሮማውያን ዘንድ ደግሞ ማርስ ተብሎ ይጠራል። አርዮስፋጎስ ከአክሮጳሊስ (ከፍተኛ ቦታ ላይ ከሚገኝ ከተማ) በስተ ምዕራብ ከአጎራ (ከገበያ ስፍራ) በስተ ደቡብ ላይ ይገኛል፤ ቦታው በአንድ ወቅት የፍርድ ችሎት ማከናወኛ ወይም የመማከርት ሸንጎ ማእከል ሆኖ ነበር።

ሆነ እንድናውቅ ትፈቅዳለህን? 20ደግሞም
በጆሮአችን የምታሰማን እንግዳ ነገር ስለ
ሆነብን፣ ምን ማለት እንደ ሆነ ማወቅ እን
ፈልጋለን።” 21የአቴና ሰዎች በሙሉ እንዲሁም
በዚያ የሚኖሩ የውጭ ሰዎች ጊዜያቸውን
የሚያሳልፉት ስለ አዳዲስ ነገሮች በማውራትና
በመስማት እንጂ በሌላ ጒዳይ አልነበረም።
22ስለዚህ ጳውሎስ በአርዮስፋጎስ በተሰበ
ሰበው ሕዝብ መካከል ቆሞ እንዲህ አለ፤
“የአቴና ሰዎች ሆይ፤ በማናቸውም ረገድ፣
በጣም ሃይማኖተኞች መሆናችሁን አያለሁ፤
23እየተዘዋወርሁ ሳለሁ፣ የምታመልኳቸውን
ነገሮች ስመለከት፣ ‘ለማይታወቅ አምላክ’
የሚል ጽሑፍ ያለበት አንድ መሠዊያ አይ
ቻለሁና፤ እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታ
መልኩትን እገልጽላችኋለሁ።
24“ዓለምንና በውስጡ ያለውን ሁሉ የፈጠረ
እግዚአብሔር እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነው፤
ስለዚህም እርሱ የሰው እጅ በሠራው መቅ
ደስ አይኖርም። 25እርሱ ለሰዎች ሁሉ ሕይ
ወትንና እስትንፋስን እንዲሁም ሌላውንም
ነገር ሁሉ የሚሰጥ ስለ ሆነ፣ የሚጐድለው
ነገር ባለመኖሩ በሰው እጅ አይገለገልም።
26የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ ወገን ፈጥሮ
በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ አደረገ፤ የዘመ
ናቸውን ልክና የመኖሪያ ስፍራቸውንም
ዳርቻ ወሰነላቸው። 27ይኸውም ሰዎች እግዚአ
ብሔርን ፈልገው ተመራምረው ምናልባት ያገኙት
እንደ ሆነ ብሎ ነው፤ ይህም ቢሆን እርሱ
ከእያንዳንዳችን የራቀ ሆኖ አይደለም፤
28የምንኖረውና የምንቀሳቀሰው፣ ያለነውም
በእርሱ ነውና። ከራሳችሁ ባለቅኔዎች ችም
አንዳንዶቹ እንዳሉት፣ ‘እኛም ደግሞ ልጆቹ
ነን።’
29“እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን፣
አምላክ በሰው ሙያና ጥበብ የተቀረጸውን
ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ ይመስ
ላል ብለን ማሰብ አይገባንም። 30ቀደም ሲል
እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን አለማወቅ በትዕ
ግሥት ዐልፎአል፤ አሁን ግን በየቦታው ያሉ
ሰዎች ሁሉ ንስሓ እንዲገቡ ያዛል፤ 31በመረጠው
ሰው አማካይነት በዓለም ላይ በጽድቅ
የሚፈርድበትን ቀን ወስኖአልና፤ እርሱንም
ከሙታን በማስነሣቱ ለሰዎች ሁሉ ይህን
አረጋግጦአል።”
32እነርሱም ስለ ሙታን ትንሣኤ በሰሙ
ጊዜ፣ አንዳንዶቹ አፌዙ፤ ሌሎች ግን፣ “ስለዚህ
ጒዳይ ከአንተ ዳግመኛ ለመስማት እንፈ
ልጋለን” አሉት። 33በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ከመካ
ከላቸው ወጥቶ ሄደ፤ 34አንዳንድ ሰዎች ግን
ጳውሎስ ባለው በመስማማት ተከተሉት፤ አመ
ኑም፤ ከእነዚህም ዲዮናስዮስ የተባለው የአር
ዮስፋጎስ ፍርድ ቤት አባል፣ ደማሪስ የተባ
ለች ሴትና ሌሎችም ሰዎች ነበሩ።

### ጳውሎስ በቆሮንቶስ

18 ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ከአቴና ተነ
ሥቶ ወደ ቆሮንቶስ ሄደ። 2በዚያም
የጳንጦስ ተወላጅ የሆነውን፣ አቂላ የተባለ
ውን አይሁዳዊ አገኘ፤ እርሱም አይሁድ ሁሉ
ከሮም እንዲወጡ ቀላውዴዎስ ባዘዘው መሠ
ረት ከሚስቱ ከጵርስቅላ ጋር በቅርብ ጊዜ

17፥21 ቍ15
17፥22 ቍ16:19
17፥23 ዮሐ4፥22
17፥24 ዘዳ10፥14፤ 1ነገ8፥27፤ኢሳ42፥5፤ 66፥1:2፤ማቴ11፥25፤ ሐሥ7፥48፤14፥15
17፥25 መዝ50፥10-12፤ኢሳ42፥5
17፥26 ዘዳ32፥8፤ ኢዮ12፥23፤
17፥27 ዘዳ4፥7፤ኢሳ 55፥6፤ኤር23፥23:24
17፥28 ዘዳ30፥20፤ ኢዮ12፥10፤ዳን5፥23
17፥29 ኢሳ40፥18-20፤ሮሜ1፥23
17፥30 ቍ23፤ ሉቃ 24፥47፤ ሐሥ14፥16፤ሮሜ 3፥25፤ቲቶ2፥11:12፤1ጴጥ1፥14
17፥31 መዝ9፥8፤ 96፥13፤98፥9፤ ማቴ10፥15፤ሐሥ2፥24፤10፥42
17፥32 ቍ18:31
17፥34 ቍ19:22
18፥1 ሐሥ17፥15፤ 19፥1፤1ቆሮ1፥2:2 ቆሮ1፥1:23፤ 2ጢሞ 4፥20
18፥2 ቍ19:26፤ ሮሜ16፥3፤ሐሥ11፥28፤ 1ቆሮ16፥19፤ 2ጢሞ 4፥19

ሸንጎው በጥንት ጊዜ የግሪክን ከተሞች የሚያስተዳድረው ሸንጐው ነበር፤ በአዲስ ኪዳን ዘመን ግን በአጎራ ሰሜን በቤተ መንግሥቱ መግቢያ ምዕራብ ጥግ ላይ በመሰብሰብ፣ ሃይማኖታዊና ሥነ ምግባራዊ በሆኑ ጒዳዮች ላይ ብቻ ሥልጣን ነበረው። እነዚሁ ሰዎች ራሳቸውን የአዳዲስ ሃይማኖቶችና የባዕዳን አምልኮ ትምህርት ጠባቂዎች አድርገው ይቈጥሩ ነበር።

17፥22 *ሃይማኖተኞች፤* “ብዙዎችን የምታመልኩ” ማለት ሊሆን ይችላል። ይህ ቃል በግሪክ ቋንቋ አንድን ሰው ለማመስገን ወይም ለማንኳሰስ ይውላል፤ ተናጋሪው የትኛውን ማለቱ እንደ ሆነ የሚወሰነውም፣ ከሚገልጸው ወገን ጋር ራሱን በመጨመሩ ወይም ባለመጨመሩ ይሆናል። ጳውሎስ ንግግሩን እስከ ቀጠለ ድረስ የትኛውን ማለቱ እንደ ሆነ የአቴና ሰዎች ሊያውቁ አል ቻሉም፤ ጳውሎስ ግን በዚህ ሁኔታ የቀረበው ተደማጭነትን ለማግኘት ደጋፊ መስሎ ነበር።

17፥23 *‘ለማይታወቅ አምላክ’፤* ግሪኮች ለማንኛውም ባዕድ አምላክ ተገቢውን አክብሮት ነፍገው ላለማስቀየም ሲሉ ይህን ‘ለማይታወቅ አምላክ’ የሚለውን ምልክት አቁመዋል። ሌሎች የግሪክ ጸሓፊዎችም እንደዚህ ያለ ምልክት በአቴና ውስጥ እንደ ነበር አረጋግጠዋል፤ ይህም፣ ጳውሎስ መልእክቱን ያለ ችግር ያቀርብ ዘንድ፣ መልካም አጋጣሚ ሆኖለታል።

17፥24 *ዓለምንና... የፈጠረ አምላክ፤* ግዑዙ ቅጠሉን ሁሉ አምላክ ነው ከሚለው ከኢስጦኢክ ፍልስፍና በመለየት፣ ራሱ ሕያው የሆነ አምላክ መኖሩን በዚህ አቀራረብ አስተማረ።

17፥26 *የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ ወገን ከአዳም ፈጥሮ፤* አቴናዊም ይሁን ሮማዊ፣ የሠለጠነ ግሪካዊም ይሁን ያልሠለጠነ አረማዊ፣ አይሁዳዊም ይሁን አሕዛብ የሰው ወገን ሁሉ የተገኘው ከአንድ ግንድ ነው። *የዘመናቸውን ልክና፤* አንድ ሕዝብ የሚነሣበትና የሚወድቅበት ትክክለኛ ጊዜ ተወስኖለታል። *የመኖሪያ ስፍራቸውንም፤* እያንዳንዱም ሕዝብ የሚኖርበትን ስፍራ ወስኖለታል፤ የኤፊቆሮስ ፍልስፍና ተከታዮች እንደሚሉት ነገር ሁሉ በአጋጣሚ የሚከናወን ሳይሆን፣ ሁሉንም በዕቅድ የሚመራው አንዱ እግዚአብሔር ነው።

17፥28 *ከራሳችሁ ባለ ቅኔዎችም አንዳንዶቹ፤* እዚህ ላይ ሁለት ጥቅሶች ከግሪክ ባለ ቅኔዎች ተወስደዋል (1) “የምንኖረውና የምንቀሳቀሰው፣ ያለነውም በእርሱ ነው” ይህን ያለው ኤፒሜኒዴስ (600 ዓ.ቅ.ክ.) የተባለው የቀርጤስ ባለ ቅኔ ነበር። (2) “እኛም ደግሞ ልጆቹ ነን፤” ይህን ደግሞ ያሉት የኪልቅያው ባለ ቅኔ አራጦስና (315-240 ዓ.ቅ.ክ) ቅሊንጦስ (331-233 ዓ.ቅ.ክ) ነበሩ። ሐዋርያው ጳውሎስ በሌላም ስፍራ የግሪክን ባለ ቅኔዎች ትምህርት ሲጠቅስ እናያለን (1ቆሮ 15፥33፤ ቲቶ 1፥12 እና ማብ ይመ)።

17፥30 *በትዕግሥት ዐልፎአል፤* ባዕዳን አማልክትን ባለ ማወቅ በማምለካቸው እግዚአብሔር አልፈረደባቸውም (ቍ31 ይመ)።

17፥31 *በመረጠውም ሰው፤* የእግዚአብሔር ልጅ ብቻ ሳይሆን፣ የሰው ልጅ የሆነውን ኢየሱስን ነው (ዳን 7፥13 ይመ፤ ከማቴ 25፥31-46፤ ከሐሥ 10፥42 ጋር ያነጻጽሩ)።

17፥33 *ከመካከላቸው፤* ከአርዮስፋጎስ ሸንጎ ማለት ነው።

17፥34 *ዲዮናስዮስ፤* ለማረጋገጥ አዳጋች ቢሆንም እንኳ፣ ከዚያ በኋላ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ትውፊት ይህ ሰው የአቴና ጳጳስ እንደ ነበር ያስረዳል። *ደማሪስ፤* እንደ አርዮስ ፋጎስ ባለ ስብሰባ ላይ የተገኘች፣ የተማረች የውጭ አገር ሴት ናት የሚል ሐሳብ የሰነዘሩ አንዳንድ ሰዎች አሉ፤ ወይም ደግሞ ጳውሎስ በምኵራብ ሲያስተምር የሰማች ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባት የአሕዛብ ወገን ልትሆን ትችላለች (ቍ17)።

18፥1 *ወደ ቆሮንቶስ ሄደ፤* የሄደው በየብስ ወይም በባሕር ሊሆን ይችላል።

18፥2 *የጳንጦስ፤* በትንሿ እስያ በሰሜን ምሥራቅ ክፍል በቢታኒያና በአርሜንያ መካከል፣ በጥቁር ባሕር አጠገብ የምትገኝ አውራጃ ናት (2፥9 ይመ)። *አቂላ ... ከጵርስቅላ፤* ወደ ክርስትና እምነት ስለ መመለሳቸው የተገለጸ ነገር ባይኖርም ከጳውሎስ ጋር አብረው ስለሠሩ (ቍ3)፣ ክርስትናን ቀደም ሲል መቀበላቸው አያጠራጥርም። ምናልባትም በዓለ አምሳን አክብረው ወደ ሮም በተመለሱት ሰዎች ወይም በኋላ ጊዜ በሌሎች ክርስቲያኖች አማካይነት የክርስትናን እምነት ሳይቀበሉ አልቀሩም። *አይሁድ ሁሉ ከሮም እንዲወጡ፤* ታሪክ ጸሓፊው ሱጦንዮስ አይሁድ “በክርስቶስ” ምክንያት ደጋግመው ሁከት ስላስነሡ ከሮም እንደ

ከኢጣሊያ የመጣ ነበር። ጳውሎስም ሊያያ
ቸው ወደ እነርሱ ሄደ፤ 3እርሱም እንደ እነ
ርሱ ድንኳን ሰፊ ስለ ነበረ፣ ከእነርሱ ጋር
ተቀምጦ በተመሳሳይ ሥራ ላይ ተሰማራ።
4በየሰንበቱም ከአይሁድና ከግሪክ ሰዎች
ጋር በምኵራብ ውስጥ እየተነጋገረ ሊያሳምና
ቸው ይጥር ነበር።

5ሲላስና ጢሞቴዎስ ከመቄዶንያ በወረዱ
ጊዜ፣ ጳውሎስ በስብከት እየተጋ፣ ኢየሱስ
እርሱ ክርስቶስ* እንደ ሆነ ለአይሁድ ይመ
ሰክር ነበር። 6ነገር ግን በተቃወሙትና በሰ
ደቡት ጊዜ ልብሱን አራግፎ፣ "ደማችሁ በራ
ሳችሁ ላይ ይሁን! እኔ ንጹሕ ነኝ፤ ከእን
ግዲህ ወደ አሕዛብ እሄዳለሁ" አላቸው።

7ከዚያም ወጥቶ ቲቶስ ኢዮስጦስ ወደ
ተባለ፣ እግዚአብሔርን ወደሚያመልክ ሰው ቤት
ሄደ፤ የዚህም ሰው ቤት በምኵራቡ አጠገብ
ነበር። 8የምኵራብ አለቃ የነበረው ቀርስጶስ
ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር በጌታ አመነ፤ ጳው
ሎስ ሲናገር የሰሙ ብዙ የቆሮንቶስ ሰዎ
ችም አምነው ተጠመቁ።

9ጌታም ሌሊት በራእይ ጳውሎስን እንዲህ
አለው፤ "አትፍራ፤ ተናገር፣ ዝምም አትበል፤
10እኔ ከአንተ ጋር ነኝና ማንም በአንተ ላይ
ተነሥቶ ሊጐዳህ አይችልም፤ በዚች ከተማ
ብዙ ሰዎች አሉ ኝና"። 11ስለዚህ ጳውሎስ
የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማራቸው አንድ ዓመት
ተኩል አብሮአቸው ተቀመጠ።

12ጋልዮስ የአካይያ ገዥ በነበረበት ጊዜ
አይሁድ ተባብረው በጳውሎስ ላይ ተነሡ፤
ፍርድ ወንበር ፊት አቅርበውትም፣ 13"ይህ
ሰው ሕጉ በማይፈቅደው መንገድ፣ ሰዎች እግዚ
አብሔርን እንዲያመልኩ እያሳሳታቸው ነው"
አሉ።

14ጳውሎስ ሊናገር ገና አፉን ሲከፍት፣
ጋልዮስ አይሁድን እንዲህ አላቸው፤ "የአይ
ሁድ ሰዎች ሆይ፤ ያቀረባችሁት ጉዳይ
ስለ ዐመፅ ወይም ስለ ከባድ ወንጀል ቢሆን
ኖሮ ላዳምጣችሁ በተገባኝ ነበር፤ 15ነገር ግን
ክርክራችሁ ስለ ቃላትና ስለ ስሞች እንዲ
ሁም ስለ ሕጋችሁ በመሆኑ፣ እናንተው
ጨርሱት፤ እኔ በእንዲህ ዐይነት ነገር ፈራጅ
ለመሆን አልሻም።" 16ስለዚህ ከፍርድ ወን
በር ፊት አስወጣቸው። 17በዚህ ጊዜ ሁሉም
የምኵራቡን አለቃ፣ ሶስቴንስን ይዘው በፍ
ርድ ቤቱ ፊት ደበደቡት፤ ጋልዮስ ግን
ነገሩ ደንታም አልሰጠውም።

### ጵርስቅላ፣ አቂላና አጵሎስ

18ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ብዙ ቀን በቆሮን
ቶስ ተቀመጠ፤ ከዚያም ወንድሞችን ተሰና
ብቶ ከጵርስቅላና ከአቂላ ጋር በመርከብ
ወደ ሶርያ ሄደ። ስእለትም ስለነበረበት ክን
ክራኦስ በተባለ ቦታ ራሱን ተላጨ። 19ኤፌ
ሶን በደረሰ ጊዜም ጵርስቅላንና አቂላን እዚ
ያው ተዋቸው፤ እርሱ ራሱ ግን ወደ ምኵ
ራብ ገብቶ ከአይሁድ ጋር ይነጋገር ነበር።
20ከእነርሱ ጋር እንዲሰነብት በጠየቁትም ጊዜ

18፥3 ሐሥ20፥34፤ 1ቆሮ4፥12፤ 1ተሰ2፥9፤2ተሰ3፥8
18፥4 ሐሥ9፥20፤ 13፥14
18፥5 ሐሥ9፥22፤ 15፥22፤16፥1፡9፤17፥14:15
18፥6 2ሳሙ1፥16፤ ሕዝ3፥17-19፤33፥4፤ ማቴ10፥14፤ሐሥ 13፥45:46፤20፥26
18፥7 ሐሥ16፥14
18፥8 ማር5፥22፤ ሐሥ11፥14፤ 1ቆሮ 1፥14
18፥9 ማቴ14፥27፤ሐሥ 9፥10
18፥10 ማቴ28፥20
18፥11 ዕብ4፥12
18፥12 ቍ27፤ ሐሥ 13፥7:8:12፤ 19፥38፤ሮሜ 15፥26፤1ቆሮ 16፥15፤2ቆሮ9፥2፤1 ተሰ1፥7:8
18፥15 ሐሥ 23፥29፤ 25፥11:19
18፥17 ቍ8፤ 1ቆሮ1፥1
18፥18 ቍ2:27፤ ዘኍ6፥2:5:18፤ሉቃ 2፥21፤ሐሥ1፥16፤ 21፥24፤ ሮሜ16፥1
18፥19 ቍ21:24፤ ሐሥ 19፥1:17:26፤ 1ቆሮ15፥32፤16፥8፤ ኤፌ1፥1፤1ጢሞ1፥3፤ ራእ 1፥11፤ 2፥1

*5 ወይም መሲሕ፤ እንዲሁም ቍ 25

ተባረሩ ጽፎአል፤ ጸሓፊው፣ "ክርስቶስ" ያለው ጌታችንን ለማመ ልከት ከሆነ፣ ሁከቱ የተመራው በክርስቶስ ሳይሆን፣ በእርሱ ምክ ንያት መሆኑ ግልጽ ነው። *ቀላው ዴዎስ፤* ከ41-54 ዓ.ም የሮም ንጉሠ ነገሥት ነበር።

18፥3 *ድንኳን ሰፊ፤* ጳውሎስ ይህን ሙያ በልጅነቱ ሳይ ማር አልቀረም፤ በአይሁድ ልማድ፣ አንድ ሰው ባለ ጸጋም ይሁን ድሀ፣ ወንድ ልጁን ተግባረ ዕድ ማስተማር ነበረበት።

18፥4 *በምኵራብ፤* የ13፥14 ማብ ይመ።

18፥5 *ሲላስና ጢሞቴዎስ ከመቄዶንያ በወረዱ ጊዜ፤* ጳው ሎስ ሁለቱም እርሱ ወዳለበት ወደ አቴና እንዲመጡ ነግሮአ ቸው ነበር (17፥15)፤ እነርሱም አልቀሩም ሄዱ (1ተሰ3፥1)፤ ነገር ግን የአብያተ ክርስቲያናትን ሁኔታ ያዩ ዘንድ ወዲያውኑ ወደ መቄዶንያ ተልከው ሳይመለሱ አልቀሩም፤ የተመለሱትም ሲላስ ወደ ፊልጵስዩስ፣ ጢሞቴዎስ ወደ ተሰሎንቄ ሳይሆን አይቀርም።

18፥7 *ቲቶስ ኢዮስጦስ፤* ቲቶስ የተለመደ ሮማዊ ስም ነው። 'ኢዮስጦስ' የሚለው ስም እዚህ ላይ የተጨመረው፣ በ2ቆሮ 2፥13፤ 7፥13-14፤ 8፥16፡23 ላይ ስሙ ከተወሣው "ከቲቶ" ለመለ የት ነው። *እግዚአብሔርን ወደሚያመልክ፤* እንደ ቲቶ ሁሉ ያል ተገረዘ አሕዛብ ቢሆንም፣ በምኵራብ እየተገኘ ያመልክ ነበር።

18፥8 *ቀርስጶስ፤* ይህን ሰው ያጠመቀው ጳውሎስ ነው (1ቆሮ 1፥14)። *የምኵራብ አለቃ፤* የ13፥15 ማብ ይመ። *አም ነው፣ ተጠመቁ፤* ወንጌልን ከልብ ስለ ተቀበሉ ነው፤ ግሱ በግሪክ ቋንቋ የሚያመለክተው ነገሩ በየቀኑ የሚቀጥል መሆኑን ነው።

18፥9 *በራእይ፤* ጳውሎስ ባመነ ጊዜ ጌታን ያየው ከሙታን በተነሣው አካሉ ነው (9፥4-6፤1ቆሮ 15፥8)፤ እንዲሁም በኢየሩ ሳሌም ቤተ መቅደስ ያየው በተመስጦ ሳለ ሲሆን (22፥17-18)፤ አሁን ደግሞ ያየው በራዕይ ነው (23፥11 ይመ)።

18፥11 *አንድ ዓመት ተኩል፤* እንዲሁም በዚህ ጊዜ አጎራ ባች ወደ ሆኑት ወደ አካይያ አውራጃዎች ሄዶ ወንጌልን አስተ ምሮ ሊሆን ይችላል (2ቆሮ 1፥1)።

18፥12 *ጋልዮስ፤* የኔሮ አስተማሪ የነበረው የፈላስፋው፣ የሴኔካ ወንድም ነው። ጋልዮስ ያደላል ተብሎ የማይጠረጠርና በእርጋታውም የተደነቀ ሰው ነበር፤ በደልፊ ከተማ የተገኘ አንድ የድንጋይ ቅርጽ እንደሚያስረዳው፣ ጋልዮስ ከ51-52 ዓ.ም ባለው ጊዜ የአካይያ ሹም ነበር። እንግዲህ ከዚህ ግንዛቤ ተነሥተን ጳውሎስ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ለሁለተኛ ጊዜ የጐበኛት መቼ እንደሆነ፣ የተሰሎንቄንም መልእክቶች መቼ እንደ ጻፈ መረዳት ይቻላል።

18፥13 *ሕጉ በማይፈቅደው መንገድ፤* አይሁድ፣ ጳውሎስን የሚከስሱት እንደ እነርሱ ሃይማኖት በሮም ሕግ ዕውቅና ያላገኘ ውን እምነት ያስተምራል በማለት ነበር። የመናገር ዕድል ቢያ ጋጥመው ኖሮ ግን፣ የሰበከው ወንጌል የአባቶቹ እምነት መሆኑን ማስረዳት በቻለና (24፥14-15፤ 26፥6-7) በሮም ሕግ ፊት ዕውቅና ባገኘ ነበር።

18፥17 *ሁሉም…ሶስቴንስን ይዘው፤* የግሪክ ሰዎች በአ ይሁድ ላይ ያላቸውን ቍጣ ለማብረድ ሲሉ ይደበድቡት ወይም አይሁድ የምኵራባቸው አለቃ ጉዳያቸውን በአግባቡ ለማ ቅረብ ባለመቻሉ ይደብድቡት በግልጽ አይታወቅም፤ ይሁን እንጂ የመ ጀመሪያው ሐሳብ ትክክል ይመስላል። በመጀመሪያው የቆሮ ንቶስ መልእክት (1ቆሮ 1፥1) ሶስቴንስ የተባለ ሰው ከጳውሎስ ጋር እንደ ነበረ ተመልክቶአል። ምናልባት ጳውሎስ ከሰበከው ወን ጌል የተነሣ፣ ወደ ክርስትና እምነት የተመለሰ ሁለተኛው የቆ ሮንቶስ ምኵራብ አለቃ ነው (ቍ8 ይመ)።

18፥18 *ከጰርስቅላና ከአቂላ፤* እዚህ ላይ እንደሚታየው የስ ማቸው ቅደም ተከተል (ከቍ2 ጋር ያነጻጽሩ)፣ የጵርስቅላን ከፍ ተኛ የሥራ ኀላፊነት ወይም የላቀ ማኅበራዊ ዕውቅናዋን ሳያ መለክት አይቀርም (ሮሜ 16፥3፤ 2ጢሞ 4፥19 ይመ)። *ስእ ለትም ስለነበረበት፤* ጊዜያዊ የናዝራዊነት ስእለት ሊሆን ይችላል (ዘኍ 6፥1-21 ይመ)። ከአደጋ መትረፍም በምስጋና የሚገለጸው፣ የተለያዩ ስእለቶችን በየወቅቱ በማቅረብ ነበር። ጠጕር መላጨትም የስእለቱ ጊዜ መፈጸሙን ያመለክታል።

18፥19 *ኤፌሶን፤* የእስያ አውራጃ ዋና ከተማና የትንሿ እስያ የንግድ ማእከል ነበረች፤ የአርጤምስ (ወይም የዲያና) ቤተ መቅደስ ዋና ባላደራ ነበረች። *ጵርስቅላንና አቂላን እዚያው ተዋ ቸው፤* ጳውሎስ በሚመለስበት ጊዜ፣ ሥራው መቼና እንዴት መጀመር እንዳለበት ምክር በመስጠት አስፈላጊውን ርዳታ የሚ ያደርጉለት እነርሱ ናቸው።

ፈቃደኛ አልሆነም፤ 21ነገር ግን ሲለያቸው፣
"የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ተመልሼ እመ
ጣለሁ" አላቸው፤ ከኤፌሶንም ተነሥቶ በመ
ርከብ ተጓዘ። 22ቂሳርያም በደረሰ ጊዜ፣ ወጥቶ
ለቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቀረበ፤ ከዚያም
ወደ አንጾኪያ ወረደ።
23በአንጾኪያም ጥቂት ጊዜ ከቈየ በኋላ፣
ከዚያ ተነሥቶ በገላትያና በፍርግያ አገሮች
ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ደቀ መዛሙርትን ሁሉ
አበረታታ።
24በዚህ ጊዜ የእስክንድርያ ተወላጅ የሆነ
አጵሎስ የሚባል አንድ አይሁዳዊ ወደ
ኤፌሶን መጣ፤ እርሱም የተማረና ቅዱሳት
መጻሕፍትን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነበር።
25ይህ ሰው፣ የጌታን መንገድ የተማረ፣ ስለ
ኢየሱስም በትክክል የሚናገርና በመንፈስ
እየተቃጠለ° የሚያስተምር ነበር፤ ይሁን
እንጂ እርሱ የሚያውቀው የዮሐንስን ጥም
ቀት ብቻ ነበር። 26እርሱም በምኵራብ በድ
ፍረት ይናገር ጀመር፤ ጵርስቅላና አቂላም
በሰሙት ጊዜ፣ ወደ ቤታቸው ወስደው የእግ
ዚአብሔርን መንገድ ይበልጥ አስተካክለው
አስረዱት።
27አጵሎስ ወደ አካይያ ለመሄድ በፈለገ
ጊዜ፣ ወንድሞች አበረታቱት፤ በዚያ የነበሩት
ደቀ መዛሙርትም እንዲቀበሉት ደብዳቤ
ጻፉለት። እዚያም በደረሰ ጊዜ ከጸጋው የተ
ነሣ አምነው ለነበሩት ትልቅ ረዳት ሆና
ቸው፤ 28ከቅዱሳት መጻሕፍት እያመሳከረ፣ ኢየ
ሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ከአይሁድ
ጋር በጽኑ በመከራከር በሕዝብ ፊት ይረ
ታቸው ነበርና።

### ጳውሎስ በኤፌሶን

19 አጵሎስ በቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ፣

°25 ወይም በትልቅ ግለት

18፥21 ሮሜ1፥10፤ 15፥32፤1ቆሮ4፥19፤ ያዕ4፥15
18፥22 ሐሥ8፥40፤ 11፥19
18፥23 ሐሥ2፥10፤ 14፥22፤15፥32፡41፤ 16፥6
18፥24 ቍ19፤ ሐሥ 19፥1፤ 1ቆሮ1፥12፤3፥5፡6፡22 ፤4፥6፤16፥12፤ቲቶ3፥13
18፥25 ማር1፥4፤ ሮሜ12፥11
18፥26 ቍ2
18፥27 ቍ12፡ 18፤ሐሥ1፥16
18፥28 ቍ5፤ ሐሥ 8፥35፤ 9፥22፤17፥2
19፥1 ሐሥ18፥1፡ 19፡24

18፥22 *ለቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቀረበ፤* በቂሳርያ ለሚገኙ ምእመናን ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን "ወጥቶ" የሚለው ቃል 2500 ጫማ ያህል ከባሕር ወለል በላይ ከፍታ ላላት፣ ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሆኑን ያመለክታል።


18፥23 *በገላትያና በፍርግያ አገሮች፤* በጥናት ጽሑፉ መጨረሻ አካባቢ ካርታ ቍጥር ገጽ ይመ። የጕዞው አቅጣጫ ከሁለተኛው የወንጌል ተልእኮ ጕዞ ጋር አንድ ሲሆን፣ ልዩነቱ መነሻውና መድረሻው ተቃራኒ መሆኑ ብቻ ነው (16፥6)። የሐረጉ አገባብ በፍርግያ ውስጥ ደቡብ ገላትያን ሊያመለክት ይችላል (የ16፥6 ማብ ይመ)።

18፥24 *የእስክንድርያ፤* በምድረ ግብፅ ትገኛለች። በሮማውያን ግዛት ሁለተኛዋ ዋና ከተማ ስትሆን፣ በውስጧ ብዙ አይሁድ ይኖሩ ነበር።

18፥25 *የዮሐንስን ጥምቀት፤* የሚያጠምቀው በኢየሱስ ስም አልነበረም (19፥2-4 ይመ)። አጵሎስ ስለ ኢየሱስ የሚያውቀው በመጠኑ ነበር፤ ነገር ግን እርሱም እንደ መጥምቁ ዮሐንስ፣ የመሲሕን መምጣት ገና ይጠባበቅ ነበር። የአጵሎስ ጥምቀቱ የተመሠረተው በተፈጸመው የጌታ ሥራ ላይ ሳይሆን፣ በንስሓ ላይ ብቻ ነበር።

18፥27 *አካይያ፤* የሮማውያን አውራጃ ስትሆን፣ ዋና ከተማዋም ቆሮንቶስ ነበረች።

19፥1 *አጵሎስ በቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ፤* ጳውሎስ




**የጳውሎስ ሦስተኛው የወንጌል ጕዞ**
ሐሥ 18:23-21:17
53-57 ዓ.ም

ጳውሎስ በላይኛው አገር ዐልፎ ወደ ኤፌሶን
መጣ፤ በዚያም አንዳንድ ደቀ መዛሙር
ትን አግኝቶ፣ 2“ባመናችሁ[u] ጊዜ መንፈስ ቅዱ
ስን ተቀበላችሁን?” አላቸው።

እነርሱም፣ “አልተቀበልንም፤ እንዲያውም
መንፈስ ቅዱስ መኖሩን እንኳ አልሰማንም”
አሉት።

3ጳውሎስም፣ “ታዲያ፣ በምን ተጠመቃ
ችሁ?” አላቸው።

እነርሱም፣ “የዮሐንስን ጥምቀት” አሉት ።

4ጳውሎስም፣ “የዮሐንስ ጥምቀትማ የን
ስሓ ጥምቀት ነበር፤ ዮሐንስም ራሱ ሰዎች
ከእርሱ በኋላ በሚመጣው በኢየሱስ እንዲ
ያምኑ ተናግሮአል” አላቸው። 5እነርሱም ይህን
በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ።
6ጳውሎስም እጁን በላያቸው በጫነ ጊዜ፣ መን
ፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ በሌሎች ቋንቋዎች[T]
ተናገሩ፤ ትንቢትም ተናገሩ። 7ሰዎቹም በአጠ
ቃላይ ዐሥራ ሁለት ያህል ነበሩ።

8ጳውሎስም ወደ ምኵራብ እየገባ፣ ስለ
እግዚአብሔር መንግሥት እየተነጋገረና እያሳ
መናቸው ሦስት ወር ሙሉ ምንም ሳይፈራ
ፈት ለፊት ይናገር ነበር። 9አንዳንዶቹ ግን
ግትር በመሆን፣ ለማመን ፈቃደኞች አልነ
በሩም፤ የጌታንም መንገድ በገሃድ ያጥላሉ
ነበር። ስለዚህ ጳውሎስ ትቶአቸው ሄደ፤
ደቀ መዛሙርትንም ለብቻቸው ወስዶ በጢ
ራኖስ የትምህርት አዳራሽ ውስጥ በየዕለቱ
ያነጋግራቸው ነበር። 10ይህን ማድረጉንም
ሁለት ዓመት ስለ ቀጠለ፣ በእስያ አውራጃ
ይኖሩ የነበሩት የአይሁድና የግሪክ ሰዎች
ሁሉ የጌታን ቃል ለመስማት ቻሉ።

11እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ እጅግ
የሚያስደንቅ ታምራትን ያደርግ ነበር፤ 12መሐ
ረብ ወይም ሰውነቱን የነካ ጨርቅ እንኳ
ወደ ሕመምተኞች ሲወስዱ በሽታቸው ይለቃ
ቸው ነበር፤ ርኵሳን መናፍስትም ይወጡ ነበር።

13እየዞሩ አጋንንትን ያስወጡ ከነበሩት
አይሁድ አንዳንዶቹ፣ “ጳውሎስ በሚሰብከው
በኢየሱስ ስም እንድትወጡ አዛችኋለሁ!” እያሉ
የጌታን የኢየሱስን ስም ርኵሳን መናፍስት
በያዟቸው ሰዎች ላይ ለመጥራት ሞከሩ፤
14የአይሁዳዊው የካህናቱ አለቃ የአስቄዋ
ሰባት ወንዶች ልጆችም ይህንኑ ያደርጉ
ነበር። 15ርኩስ መንፈሱም፣ “ኢየሱስን ዐው
ቀዋለሁ፤ ጳውሎስንም ዐውቀዋለሁ፤ እናንተ ግን
እነማን ናችሁ?” አላቸው። 16ከዚያም ርኩስ
መንፈስ ያደረበት ሰው ዘሎ ያዛቸው፤ በረታ
ባቸውም፤ እጅግ ስላየለባቸውም ቤቱን
ጥለው ዕራቁታቸውን ሸሹ።

17ይህም በኤፌሶን በሚኖሩት፣ በአይሁ
ድና በግሪክ ሰዎች ሁሉ ዘንድ በታወቀ ጊዜ፣
ሁሉም ፍርሀት ያዛቸው፤ በዚህም የጌታ
የኢየሱስ ስም ተከበረ። 18ካመኑትም ሰዎች
ብዙዎቹ እየቀረቡ ክፉ ሥራቸውን በግልጥ
ተናዘዙ፤ 19ሲጠነቁሉ ከነበሩትም መካከል

19፥2 ዮሐ20፥22
19፥4 ማር1፥4፤ ዮሐ1፥7
19፥5 ሐሥ2፥38
19፥6 ማር16፥17፤ ሐሥ6፥6፤10፥44
19፥8 ማቴ3፥2፤ ሐሥ9፥20፤28፥23
19፥9 ቍ23፡30፤ ሐሥ 9፥2-11፥26፤ 14፥4
19፥10 ቍ22፡26፡ 27፤ሐሥ2፥9፤13፥48፤ 20፥31
19፥11 ሐሥ8፥13
19፥12 ሐሥ5፥15
19፥13 ማቴ12፥27፤ማር9፥38
19፥17 ሐሥ5፥5፡ 11፤18፥19

[u]2 ወይም ካመናችሁ በኋላ

[T]6 ወይም ልሳን

በኤፌሶን ባልነበረበት ጊዜ አጵሎስ በዚያ ነበር (18፥24)፤ ወደ ቆሮንቶስ የሄደውም ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ከመመለሱ በፊት ሲሆን፣ ኋላ ግን አጵሎስ ወደ ኤፌሶን የተመለሰው፣ ጳውሎስ እዚያው በማ ገልገል ላይ ስለ ነበር (1ቆሮ 16፥12 ይመ)። *በላይኛው አገር፤* በላይኮስና በሜንደር ሸለቆዎች ያለውን የታችኛውን ቀጥታ መሥ መር ይዞ ሳይሆን፣ በሰሜን በኩል ወደ ኤፌሶን የሚወስደውን ላይኛውን የፍርግያን መንገድ ይዞ ማለት ነው። ጳውሎስ ወደ ሰሜን ገላትያ ሄደ ማለቱ የማይመስል ነገር ነው እንጂ፣ መሄዱ እውነት ከሆነ ከጕዞዎቹ በአንዱ መሆን አለበት (16፥6፤ 18፥23 ይመ)። *ኤፌሶን፤* የ18፥19 ማብ ይመ። *አንዳንድ ደቀ መዛሙር ትን፤* እነዚህ ዐሥራ ሁለቱ (ቍ7) የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሆ ኑት በቀጥታም ባይሆን፣ በተዘዋዋሪ መንገድ በመጥምቁ ዮሐንስ ወይም በደቀ መዛሙርቱ አማካይነት ሳይሆን አይቀርም፤ ወይም አጵሎስ ገና ስለ ክርስትና ብዙ ሳይገባው የወንጌልን ትምህርት ከእርሱ ሳያገኙ አልቀሩም (18፥26 ይመ)። እነርሱም እንደ አጵሎስ ስለ ወንጌል ያላቸው ግንዛቤ መጠነኛ ነበር (የ18፥25 ማብ ይመ)።

19፥2 *መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?* ጳውሎስ፣ ስለ መን ፈስ ቅዱስ ምንም እንዳልተናገራቸው ተገነዘበ (ቍ3-6)።

19፥4 *የዮሐንስ ጥምቀትማ፤* የማቴ 3፥11፡15 ማብ ይመ። *የንስሓ ጥምቀት፤* የመጥምቁ ዮሐንስ ትምህርት ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ይህን ይመስላል፤ የዮሐንስ ጥምቀት ጊዜያዊና ልብን ለወንጌል የሚያዘጋጅ ነው፤ ይኸውም ኀጢአተኝነትን አጕ ልቶ ሲያሳይ፣ የሰውን ልብ ለወንጌል የሚያመቻች ነበር። የዮሐ ንስ ጥምቀት በሞቱ የኀጢአትን ስርየት እውን ወደሚያ ደርገው ወደ ጌታ ኢየሱስ አሻግሮ ያመለክታል (የማር 1፥4 ማብ ይመ)።

19፥6 *እጁን በላያቸው በጫነ ጊዜ፤* የ6፥6 ማብ ይመ። *መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ በሌሎች ቋንቋዎች ተናገሩ፤ ትንቢ ትም ተናገሩ፤* ደቀ መዛሙርት በጴንጤቆስጤ ቀን (2፥4፡11)፣ ይህም አሕዛብ በቂሳርያ እንደ ተለማመዱት (10፥46) ዐይነት ማለት ነው።

19፥8 *ሦስት ወር፤* በተሰሎንቄ ሦስት ሰንበት ከቈየበት ጋር (17፥2) ሲነጻጸር ይህኛው ረዘም ያለ ጊዜ ነው፤ ይሁን እንጂ አቀራረቡ አንድ ዐይነት ነው፤ ይኸውም በመጀመሪያ ለአይሁድ ቀጥሎም ለግሪኮች ነው (የ13፥14 ማብ ይመ)።

19፥9 *የጌታንም መንገድ፤* የ9፥2 ማብ ይመ። *በጢራኖስ የትምህርት አዳራሽ፤* ጢራኖስ የተባለው ፈላስፋ ዘወትር የሚያ ስተምርበት ሊሆን ይችላል፤ ትምህርት የሚሰጠውም ጧት ጧት ሳይሆን አይቀርም። ጳውሎስ ከጧቱ አምስት ሰዓት እስከ ዐሥር ሰዓት ባለው ጊዜ ያስተምር እንደ ነበር በግሪኮች ቋንቋ ተጽፎ የተገኘ አንድ የእጅ ጽሑፍ ያስረዳል። ሰዓቱ ፀሓይ የሚጠነክርበት ጊዜ ቢሆ ንም፣ ሰዎች ከመደበኛ ሥራቸው የሚያርፉበት ሰዓት ከመሆኑም በላይ፣ አዳራሹ ነጻ የሚሆንበት ወቅት ስለ ሆነ ነው።

19፥10 *ሁለት ዓመት፤* ሉቃስ እንደዘገበው ከሆነ የሁለት ዓመት ከሦስት ወር (ቍ8 ይመ)፣ ይህ በአንድ በተወሰነ ስፍራ ለወንጌል ሥራ የተዳረገ የረጅሙ ጊዜ ቈይታ ነው። በአይሁድ የቀን አቈ ጣጠር ልማድ የዓመቱም ክፍል እንደ አንድ ሙሉ ዓመት ይቈጠ ራል፤ በዚህም መሠረት ሁለቱ ዓመትና ሦስቱ ወር እንደ ሦስት ዓ መት ሊቈጠር ችሎአል (20፥31)። *በእስያ አውራጃ ይኖሩ የነ በሩት... ሁሉ፤* ከጳውሎስ የወንጌል አገልግሎት ስልቶች አንዱ እዚህ ላይ ይታያል። ጳውሎስ አብያተ ክርስቲያናትን የመሠረ ተባቸው ብዙዎቹ ከተሞች አማካይ ቦታዎች ላይ ነበሩ፤ ወንጌል በእነዚህ ቦታዎች በተሰበከ ጊዜ በየአካባቢዎቻቸው በቀላሉ ሊሠራጭ ችሎአል። ሌሎች በምሳሌነት የሚጠቀሱ ከተሞች በጲስድያ የም ትገኘው አንጾኪያ (13፥14)፣ ተሰሎንቄ (17፥1)፣ አቴና (17፥15)፣ እንዲሁም ቆሮንቶስ (18፥1) ናቸው።

19፥12 *ጨርቅ፤* ጳውሎስ ለድንኳን ሥራው ከተጠቀመባቸው ነገሮች የተወሰደ (የተረፈ) ሳይሆን አይቀርም፤ ይኸውም አንዱ ራሱ ላይ የሚጠመጠመው ጨርቅ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ወገቡ ላይ እንደ ድግ የሚታጠቀው ይሆናል (ከ5፥15 ጋር ያነጻጽሩ)።

19፥14 *የካህናቱ አለቃ የአይሁዳዊው የአስቄዋ፤* ከኢየሩሳ ሌም ሊቃነ ካህናት ቤተ ሰብ ጋር የሥጋ ዝምድና ሊኖረው ይችላል። የሚመስለው ግን፣ ድግምቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ ራሱን በዚህ ስም ሳይጠራ አልቀረም፤ ጳውሎስ ርኵሳን መናፍስትን ሲያስወጣ ባዩ ጊዜ እነርሱም እንደዚሁ ለማድረግ ሞከሩ።

19፥19 *መጽሐፎቻቸውን፤* እነዚህን የመሳሰሉ የመተት ድግምት አላቸው የተባሉና ምስጢራዊ ነክ መጻሕፍት በቍፋሮ ከተቀበሩበት ተገኝተዋል። ኤፌሶን የጥንቈላ ሥራ ማእከል ነበረች። *አምሳ ሺህ ብር፤* መጻሕፍቱ ይህን ያህል ከፍተኛ ዋጋ ያወጡት በጥ ራታቸው ብዛት ሳይሆን፣ በውስጣቸው የሚገኙት የጥንቈላ የመ ተት ድግምቶች ኀይል አላቸው ተብሎ ስለሚታመን ነው።

ብዙዎች መጽሐፋቸውን ሰብስበው በማምጣት
በሕዝብ ፊት አቃጠሉ፤ ዋጋቸውም ሲሰላ አምሳ
ሺህ ብር ያህል ሆኖ ተገኘ። 20በዚህ ሁኔታ
የጌታ ቃል በኀይል እያደገና እያሸነፈ ሄደ።
21ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ፣ ጳውሎስ በመ
ቄዶንያና በአካይያ በኩል ዐልፎ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ለመሄድ በመንፈሱ ወስኖ፣ "እዚያ
ከደረስሁ በኋላ ሮምን ደግሞ ማየት አለ
ብኝ" አለ። 22ከረዳቶቹም ሁለቱን፣ ጢሞቴ
ዎስንና ኤርስጦንን፣ ወደ መቄዶንያ ልኮ
እርሱ ራሱ ግን በእስያ አውራጃ ጥቂት
ቀን ተቀመጠ።

## በኤፌሶን የተነሣው ሁከት

23በዚህ ጊዜ፣ ስለ ጌታ መንገድ ታላቅ
ሁከት ተፈጠረ። 24ድሜጥሮስ የተባለ አንድ
የብር አንጥረኛ የአርጤምስን ቤተ መቅደስ
ምስሎች ከብር ቀጥቅጦ እየሠራ ለሠራተኞቹ
የሚያስገኘው ገቢ ቀላል አልነበረም። 25እር
ሱም እነዚህን ሠራተኞችና በተመሳሳይ ሙያ
የሚተዳደሩትን ሌሎቹን ሰዎች በአንድነት
ሰብስቦ እንዲህ አላቸው፤ "ሰዎች ሆይ፤ ይህ
ሥራ ጥሩ ገቢ እንደሚያስገኝልን ታውቃላችሁ።
26ይህ ጳውሎስ የተባለ ሰው በኤፌሶን ብቻ
ሳይሆን፣ በመላው የእስያ አውራጃ የሚገ
ኘውን በርካታ ሕዝብ እያሳመነ እንዳሳታ
ቸው ይኸው የምታዩትና የምትሰሙት ነገር
ነው፤ በሰው እጅ የተሠሩ አማልክት በፍ
ጹም አማልክት እንዳልሆኑ ይናገራልና።
27የዚህ የሥራችን መልካም ስም ከመጕደ
ፉም በላይ፣ መላው እስያና ዓለም የሚያ
መልካት የታላቋ አርጤምስ ቤተ መቅደስም
ዋጋ ቢስ ይሆናል፤ ደግሞም ገናናው ክብሯ
ይዋረዳል።"
28ሰዎቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ክፉኛ ተቈጥ
ተው፣ "የኤፌሶኗ አርጤምስ ታላቅ ናት!"
እያሉ ይጮኹ ጀመር። 29ወዲያውም በከተ
ማው ሁሉ ሁከት ተነሣ፤ ሕዝቡም አንድ
ላይ በማበር የመቄዶንያ ተወላጅ የሆኑት
ንና ከጳውሎስ ጋር ይጓዙ የነበሩትን ጓደ
ኞቹን፣ ጋይዮስንና አርስጥሮኮስን ይዘው
ወደ ጨዋታ ማሳያው ስፍራ እየሮጡ ገቡ።
30ጳውሎስም ወጥቶ ሕዝቡ ፊት ለመቅረብ
ፈልጎ ነበር፤ ደቀ መዛሙርት ግን ከለከ
ሉት። 31ከአውራጃው ባለ ሥልጣኖች አንዳ
ንድ ወዳጆቹ እንኳ፣ ጳውሎስ ወደ ጨዋታ
ማሳያው ስፍራ ደፍሮ እንዳይገባ ሰው ልከው
ለመኑት።
32ጉባኤውም ተበጣብጦ፣ አንዱ አንድ
ነገር ሲናገር ሌላውም ሌላ እየተናገረ ይጯ
ጯኽ ነበር፤ አብዛኛውም ሰው ለምን እዚያ
እንደ ተሰበሰበ እንኳ አያውቅም ነበር።
33አይሁድም እስክንድሮስን ከሕዝቡ መካከል
ገፍተው ወደ ፊት ባወጡት ጊዜ፤ አንዳን
ዶቹ እንዲናገርላቸው ጮኹ፤ እርሱም ሊከራ
ከርላቸው ፈልጎ ዝም እንዲሉ በምልክት ጠቀ
ሳቸው። 34ነገር ግን እርሱ አይሁዳዊ መሆኑን
ባወቁ ጊዜ ሁሉም በአንድ ድምፅ፣ "የኤፌሶኗ
አርጤምስ ታላቅ ናት" እያሉ ሁለት ሰዓት
ያህል ጮኹ።
35የከተማዪቱም ዋና ጸሐፊ ሕዝቡን
ጸጥ አሰኝቶ እንዲህ አለ፤ "የኤፌሶን ሰዎች
ሆይ፤ የታላቋ የአርጤምስ ቤተ መቅደስና
ከሰማይ የወረደው ምስሏ ጠባቂ የኤፌሶን ከተማ
ሕዝብ መሆኑን የማያውቅ ማን አለ? 36ስለዚህ፣
ይህ ሐቅ የማይካድ እንደ መሆኑ መጠን፣
ልትረጋጉና አንዳች ነገር በጥድፊያ ከመፈ
ጸም ልትቈጠቡ ይገባችኋል። 37እነዚህን
ሰዎች ቤተ መቅደስን ሳይዘርፉ ወይም
አምላካችንን በሆነችው ላይ የስድብ ቃል ሳይ
ሰነዝሩ ይዛችሁ እዚህ ድረስ እንዲያው አምጥ
ታችኋቸዋል። 38እንግዲህ፣ ድሜጥሮስና ከእ
ርሱ ጋር ያሉት አንጥረኞች በማንም ላይ
አቤቱታ ካላቸው፣ ፍርድ ቤቱ ክፍት ነው፤
ዳኞችም አሉ፤ ክስ ማቅረብ ይችላሉ። 39ከዚህ
ሌላ ልታቀርቡ የፈለጋችሁት ነገር ካለ፣ በሕ
ጋዊ ጉባኤ ይታያል። 40አለበለዚያ ዛሬ ስለ

19፥20 ሐሥ6፥7፤ 12፥24፤13፥48
19፥21 ሐሥ16፥9፤ 18፥12፤20፥16፡22፤ 21፥4፡12፡15፤ ሮሜ15፥24፡25፡28
19፥22 ቀሉ10፡ 26፡27፤ሐሥ2፥9፤ 13፥5፤16፥1፤ሮሜ 16፥23፤2ጢሞ4፥20
19፥23 ሐሥ9፥2
19፥25 ሐሥ16፥ 16፡19፡20
19፥26 ዘዳ4፥28፤ መዝ115፥4፤ኢሳ44፥ 10-20፤ኤር10፥3-5፤ ሐሥ2፥9፤17፥29፤ 18፥19፤1ቆሮ8፥4፤ ራእ9፥20
19፥28 ሐሥ18፥19
19፥29 ሐሥ16፥9፤ 20፥4፤27፥2፤ሮሜ 16፥23፤1ቆሮ1፥14፤ ቈላ4፥10፤ፊሞ24
19፥30 ሐሥ11፥26
19፥32 ሐሥ21፥34
19፥33 ሐሥ12፥17
19፥34 ቀሉ28
19፥35 ሐሥ18፥19
19፥37 ሮሜ2፥22
19፥38 ቀሉ24፤ሐሥ 13፥7፡8፡12፤18፥12

19፥22 *ኤርስጦን፤* በቆሮንቶስ የታወቀ ሰው ሲሆን፣ በአንድ ወቅት የከተማዪቱ ሕዝባዊ ጕዳዮች ኀላፊ ነበር (የሮሜ 16፥23 ማብ ይመ)። በኋላ ጊዜም በቆሮንቶስ እንዲቀመጥ ተደርጎአል (2ጢሞ 4፥20)። በአሁኑ ጊዜ ግን ከጢሞቴዎስ ጋር በመቄዶንያ አድርጎ ወደ ቆሮንቶስ ተመልሶአል።

19፥24 *ድሜጥሮስ የተባለ አንድ የብር አንጥረኛ፤* እያንዳንዱ ሙያ የራሱ የሆነ ማኅበር ነበረው፤ ድሜጥሮስም የብር ምስልና ቅርጻ ቅርጽ ሠራተኞች ማኅበር መሪ ሳይሆን አይቀርም። *የአርጤምስን፤* በሮማውያን ዘንድ ዲያና ተብላ ለምትታወቅ ሴት አምላክ ግሪኮች የሰጧት ስም ነው። ነገር ግን በኤፌሶን የነበረችው አርጤምስ፣ በግሪኮችና በሮማውያን ዘንድ ከታወቀችው አርጤምስ የተለየች ናት። በትንሹ እስያ ልጅ የምትሰጥ አምላክ ተብላ የምትመለክና በቤተ ጣዖቱ ውስጥ ለዝሙት ሥራ በተመደቡት በብዙ ሴቶች የምትገለገለውን የሳቤላን ብዙ ባሕርይ ወርሳለች። አርጤምስ ከሰማይ የወረደች ባለ ብዙ ጡት አምላክ ነች ለሚለው እምነት መሠረቱ ከሰማይ የወደቀ የተወርዋሪ ኮከብ ስባሪ ሊሆን ይችላል (ቍ35)። ከንጉሠ ነገሥቱ ከድምጥያኖስ ዘመን (81-96 ዓ.ም) አንሥቶ የመጀመሪያ ምስሏ ቅጅ የሆነ አንድ ሌላ ምስል በኤፌሶን ተገኝቶአል።

19፥25 *ጥሩ ገቢ፤* በዓለም ሰማቸው ከታወቀው "ከሰባቱ ድንቆች" አንዱ የአርጤምስ ቤተ መቅደስ በመሆኑ፣ ይህን ድንቅ ነገር ለማየት ሰዎች ከዓለም ዙሪያ ሁሉ ሳይቀር ይመጡ ነበር። የቤተ መቅደሷና የራሷ የአርጤምስ ምስሎች ሽያጭ ለአንጥረኞቹ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ነበር።

19፥29 አርስጥሮኮስን፤ በኋላ ጊዜ ከጳውሎስ ጋር ከቆሮንቶስ ወደ ኢየሩሳሌም አብሮ ተጕዞአል (20፥3-4)፤ ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም ወደ ሮም በሄደ ጊዜም አብሮት ነበር (27፥1-2፤ ቈላ 4፥10)።

19፥31 *የአውራጃው ባለ ሥልጣኖች፤* ንጉሠ ነገሥቱ የሚመለክበትን ዘዴ ለመፈለግ በሕዝብ የተመረጡ ታላላቅ የሸንጎ አባላት ነበሩ። ጳውሎስ ከእነዚህ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ውስጥ ወዳጆች ነበሩት።

19፥33 *እስክንድሮስን፤* አይሁድ ይህን ሰው ወደ ፊት ገፋ ያደረጉት እምነታቸው ከክርስቲያኖች የተለየ መሆኑን እንዲገልጽላቸው፣ ወይም ክርስቲያኖች በግሪኮች ላይ አድርሰዋል የሚሉትን ተጨማሪ በደል እንዲናገርላቸው ሊሆን ይችላል፤ ወይም ለሁለቱም ዐላማ ሊሆን ይችላል። ሕዝቡ ግን አይሁድም እንደ ክርስቲያኖቹ ሁሉ አርጤምስን እንደማያመልኩ ተገንዝበዋል።

19፥35 *የከተማዪቱ ዋና ጸሐፊ፤* የከተማዋ ሸንጎ ያሳለፈውን ውሳኔ ሁሉ ሕዝቡ እንዲያውቅ የሚያደርግ የአገሩ ተወላጅ ዋና የሆነ ሹም ነበር። በኤፌሶንና በሮም መካከል ላለ ውም ግንኙነት አማካይ በመሆን፣ የሸንጎው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ነበር።

19፥38 *ፍርድ ቤቱ... ዳኞችም፤* ከአንድ በላይ የሆኑ ፍርድ ቤቶችን ወይም ዳኞችን ለማመልከት ሳይሆን፣ አጠቃላይ ስያሜውን ለማሳየት ሊሆን ይችላል። ኤፌሶን የትንሹ እስያ ዋና ከተማ እንደ መሆኗ መጠን የአስተዳደሩ ማእከል ነበረች።

19፥39 *በሕጋዊ ጉባኤ፤* መደበኛ የሕዝብ ጉባኤ በወር

ሆነው ነገር፣ በሁከት እንዳንከ
ሰስ ያሠጋናል፤ አጥጋቢ ምክንያት ስለሌ
ለንም፣ ስለ ሁከቱ ብንጠየቅበት መልስ
መስጠት አንችልም።” 41ይህን ከተናገረ በኋ
ላም ጉባኤው እንዲበተን አደረገ።

## ወደ መቄዶንያና ወደ ግሪክ ጕዞ

**20** ሁከቱም እንደ በረደ፣ ጳውሎስ ደቀ
መዛሙርትን አስጠርቶ መከራቸው፤
ተሰናበቶአቸውም ወደ መቄዶንያ ለመሄድ
ተነሣ። 2ባለፈባቸውም ስፍራዎች ሕዝቡን
በብዙ ቃል እየመከረ ግሪክ አገር ደረሰ፤
3በዚያም ሦስት ወር ተቀመጠ። ወደ ሶርያ
በመርከብ ለመሄድ ሲዘጋጅም አይሁድ አሢ
ረውበት ስለ ነበር፣ በመቄዶንያ በኩል
አድርጎ ለመመለስ ወሰነ። 4የጳይሮስ ልጅ
የቤርያው ሱሲጳጥሮስ፣ የተሰሎንቄዎቹ አር
ስጥ ሮኮስና ሲኮንዱስ፣ የደርቤኑ ጋይዮስ፣
ከእስያ አውራጃ የመጡት ቲኪቆስና ጥሮፊ
ሞስ፣ እንዲሁም ጢሞቴዎስ አብረውት
ሄዱ። 5እነዚህም ሰዎች ወደ ፊት ቀድመ
ውን በጢሮአዳ ጠበቁን። 6እኛ ግን፣ የቂጣ
በዓል ካለፈ በኋላ፣ ከፊልጵስዩስ በመርከብ
ተነሣን፤ ከአምስት ቀንም በኋላ ከሌሎቹ
ጋር በጢሮአዳ ተገናኘን፤ በዚያም ሰባት ቀን
ተቀመጥን።

## አውጤኪስ በጢሮአዳ ከሞት ተነሣ

7በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመ
ቍረስ ተሰብስበን ሳለን፣ ጳውሎስ በማግ
ስቱ ለመሄድ ስላሰበ፣ ከእነርሱ ጋር ይነ
ጋገር ነበር፤ ንግግሩንም እስከ እኩለ ሌሊት
ድረስ አራዘመ። 8በተሰበሰብንበትም ሰገነት
ላይ ብዙ መብራት ነበር። 9አውጤኪስ የተ
ባለ አንድ ጕበዝም በመስኮት ላይ ተቀምጦ
ነበር፤ ጳውሎስ ንግግሩን ባስረዘመ ጊዜ፣
እንቅልፍ እንቅልፍ አለውና ጭልጥ ብሎ
ተኛ፤ ከሦስተኛውም ፎቅ ቍልቍል ወደቀ፤
ሞቶም አነሡት። 10ጳውሎስም ወርዶ በላዩ
ተጋድሞ ዐቀፈውና፣ “ሕይወቱ በውስጡ ስላ
ለች ሁከት አትፍጠሩ” አላቸው። 11ተመ
ልሶም እንደ ገና ወደ ፎቁ ወጣ፤ እንጀራውንም
ቈርሶ በላ፤ እስኪነጋም ድረስ ብዙ ከተናገረ
በኋላ ተነሥቶ ሄደ። 12ሰዎችም ያን ጕበዝ
ሕያው ሆኖ ወሰዱት፤ በዚህም እጅግ ተጽናኑ።

## ጳውሎስ የኤፌሶንን ሽማግሌዎች ተሰናበተ

13እኛ ግን ጳውሎስን ለመቀበል ቀድመን
ወደ መርከቡ ሄድን፤ ከዚያም በመርከብ
ወደ አሶን ተጓዝን፤ ይህን ያደረግነውም

20፥1 ሐሥ11፥26፤ 16፥9
20፥3 ቍ19፤ ሉቃ 2፥2፤ ሐሥ9፥23፡24፤ 14፥5፤16፥9፤23፥12፡15፡30፤25፥3፤2ቆሮ 11፥26፤1ተሰ2፥16
20፥4 ሐሥ2፥9፤ 16፥1፤17፥1፤19፥29፤ 21፥29፤ኤፌ6፥21፤ ቈላ4፥7፤2ጢሞ 4፥20፤ቲቶ3፥12
20፥5 ሐሥ16፥8፡10
20፥6 ሐሥ16፥8፡12
20፥7 ግቴ14፥19፤ 1ቆሮ16፥2፤ራእ1፥10
20፥8 ሐሥ1፥13፤ 9፥37
20፥10 1ነገ17፥21፤ 2ነገ4፥34፤ ግቴ9፥23፡24
20፥11 ቍ7፤ ግቴ 14፥19

ሦስት ጊዜ ይጠራ ነበር።

20፥1 *ተሰናብቶአቸውም...ለመሄድ ተነሣ፤* ጳውሎስ በሚከተሉት ምክንያቶች ከኤፌሶን ለመውጣት ፈልጎአል፦ (1) ከኤፌሶን ለቆ ለመሄድ፤ (2) ወደ መቄዶንያ ሲሄድ እግረ መንገዱን በጢሮአዳ ወንጌልን ለመስበክ፤ (3) ቲቶ ስለ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የዘገበውን ይዞ ሲመጣ በጢሮአዳ ከእርሱ ጋር ለመገናኘት (2ቆሮ 2፥12-13 ይመ)፤ (4) በይሁዳ ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን መባ መሰብሰቡን ለመቀጠል (1ቆሮ 16፥1-4፤ 2ቆሮ 8፥1-9፡15፤ ሮሜ 15፥25-28 ይመ)።

20፥2 *ባለፈባቸውም ስፍራዎች፤* በነዚህ ስፍራዎች ብዙ ጊዜ ሳይሳልፍ አልቀረም፤ በዚህ ጊዜ ወደ እልዋሪቆን ሄዶ ይሆናል (ሮሜ 15፥19 ይመ)።

20፥3 *ሦስት ወር፤* የአካይያ ዋና ከተማ በሆነችው በቆሮንቶስ የቈየበትን ጊዜ ሊያመለክት ይችላል፤ ጊዜውም መርከቦች እንደ ልብ የማይመላለሱበት የክረምት ወቅት መሆን አለበት። ጳውሎስ የሮሜን መልእክት የጻፈው በዚህ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም። *አሢረውበት፤* አይሁድ የጳውሎስን ሕይወት ለማጥፋት ቈርጠው ተነሥተው ነበር፤ ጳውሎስ በይሁዳ ለሚገኙት ክርስቲያኖች የሰበሰበውን መባ ይዞ ስለ ነበር አይሁድ የመዝረፍ ሐሳብ ሳያድርባቸው አልቀረም። ወደ ሶርያ ለመሄድ በመርከብ ተሳፍሮ በሚነሣበት ጊዜ፣ የክንክራኦስ ወደብ ጳውሎስን ለመሰለል ለጠላቶቹ አመች ነበር።

20፥4፤ እነዚህ ሰዎች ጳውሎስንና ከምእመናን ለይሁዳ ችግረኞች የተሰበሰበውን ገንዘብ አጅበው እንዲያደርሱ የተወከሉ ሳይሆኑ አይቀሩም (የ2ቆሮ 8፥23 ማብ ይመ)። ሰዎቹም ሦስቱ ከመቄዶንያ፣ ሁለቱ ከገላትያ አውራጃዎች እንዲሁም ሌሎች ሁለቱ ከእስያ አውራጃ የወጡ ነበሩ። ሉቃስም የተቀላቀላቸው በፊልጵስዩስ ሳይሆን አይቀርም (ቍ6 ላይ “በመርከብ ተነሣን” የሚለውንና የ16፥10 ማብ ይመ)። ሱሲጳጥሮስ በሮሜ 16፥21 ከተጠቀሰው ጋር አንድ ሳይሆን አይቀርም። *አርስጥሮኮስና፤* የ19፥29 ማብ ይመ። *ሲኮንዱስ፤* ስሙ እዚህ ላይ እንጂ በሌላ ቦታ አልተጠቀሰም፤ ጤርጥዮስ (ሮሜ 16፥22 ይመ)። ማለት “ሦስተኛ”፣ ኤርስጦስ (ሮሜ 16፥23 ይመ) ማለት “አራተኛ” ማለት እንደ ሆነ ሁሉ የዚህም ስም ትርጕም “ሁለተኛ” ማለት ነው። *የደርቤኑ ጋይዮስ ፤* ይህኛው ጋይዮስ የሚጠራው ከአርጥሮኮስ ጋር ነው (19፥29 ይመ)፤ ይሁን እንጂ የስሞቹ በጥንድ በጥንድ መቀመጥ የሚያሳየው ይህኛው ጋይዮስ ስሙ የተያያዘው ከሮሜዋ ገላትያ ጋር ሲሆን ከመቄዶንያው ጋይዮስ ጋር ግን የተለየ ነው። *ጢሞቴዎስ፤* ውክልናው ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ብቻ አይመስልም፤ የመጣው ከልስጥራን ሲሆን፣ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትንም በኀላፊነት ያገለግል ነበር (1ቆሮ 16፥10-11፤ ፊል2፥19-23)። *ቲኪቆስና፤* በአገልግሎት ከጳውሎስ የማይለይ ረዳቱ ነበር፤ በተለይም በእስያ አውራጃ በነበሩት አብያተ ክርስቲያናት (ኤፌ 6፥21-22፤ ቈላ 4፥7-9፤ 2ጢሞ 4፥12፤ ቲቶ 3፥12)። ጥሮፊሞስ፤ በ21፥29 ስሙ በድጋሚ ተወሥቶአል (2ጢሞ 4፥20 ይመ)። የኤፌሶን ሰው በመሆኑ ከአሕዛብ ወገን እንደ ሆነ ይገመታል።

20፥5 *በጢሮአዳ፤* ጳውሎስና ቀድመውት ከናጱሊ በባሕር የተጓዙት ሰዎች የተገናኙበት ስፍራ ናት፤ ናጱሌ ለፊልጵስዩስ ከተማ የባሕር ወደብ ነበረች (16፥11)። ጳውሎስና የቅርብ ባለደረቦቹ በባሕር ከመጓዛቸው በፊት በፊልጵስዩስ አንድ ሳምንት ቈይተዋል።

20፥6 *ከፊልጵስዩስ፤* የባሕር ወደቧ ከሆነችው ከናጱሌ 16 ኪ.ሜ. ያህል ርቆ ማለት ነው። *የቂጣ በዓል፤* ከፋሲካ በዓል ዕለት ጀምሮ ለአንድ ሳምንት ይከበራል። ጳውሎስ ይህን ሳምንት የቈየው በፊልጵስዩስ ነበር። ቀደም ሲል ኢየሩሳሌም ቶሎ ለመድረስ ተስፋ አድርጎ ነበር (19፥21)፤ አሁን ግን እዚያ ለመገኘት ተስፋ ያደረገው በበዓለ አምሳ ቀን ነው (20፥16 ይመ)። *ከአምስት ቀንም በኋላ፤* ከናጱሌ ወደ ጢሮስ የሚደረገው አምስት ቀን ያህል ይፈጃል፤ በሌላ አቅጣጫ ከተሄደ ግን ሁለት ቀን ያህል ብቻ ነው የሚፈጀው (16፥11)። *ሰባት ቀን፤* ጳውሎስ ለበዓለ ኀምሳ ኢየሩሳሌም ለመድረስ ቢቸኵልም፣ ሰባት ቀን በጢሮአዳ መቈየት ነበረበት፤ ይኸውም መርከቡ የሚነሣበት ጊዜ በመዘግየቱ ሊሆን ይችላል፤ ይበልጥ የሚመስለው ግን፣ በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከክርስቲያኖች ጋር ተገናኝቶ የጌታን ራት ለመካፈል ስለ ፈለገ ነበር።

20፥7 *በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን፤* እሑድ ማለት ነው። በአይሁድ የቀን አቈጣጠር ቀኑ አንድ ብሎ የሚጀምረው ምሽት ላይ በዐሥራ ሁለት ሰዓት ስለሆነ፣ ቀኑ ቅዳሜ ነው የሚሉ አንዳንድ ወገኖች አሉ፤ ይሁን እንጂ የግሪክን ሥልጣኔ ባጣጣመችው በጢሮአዳ ከተማ የተከናወነውን ነገር ሲገልጽ፣ የአይሁድን የቀን አቈጣጠር የሚጠቀምበት ምክንያት አይኖርም። *እንጀራ ለመቍረስ፤* እዚህ ላይ የጌታን ራት ማለቱ ነው፤ ሥርዐት ባለው መንገድ የመገናኘታቸው ምክንያት ይኸው ነውና። የጌታን ራት መቀበል እንደሚገባ ታዞአል (ሉቃ 22፥19) ይህም በየጊዜው የሚፈጸም ነበር (2፥42 ይመ)።

20፥9 *አውጤኪስ፤* ነጻ በወጡ ወገኖች ዘንድ የተለመደ ስም ነበር (የ 6፥9 ማብ ይመ)።

20፥10 *ሕይወቱ ስላለች፤* ጴጥሮስ ጣቢታን ከሞት እንዳስነሣት ሁሉ (9፥40)፣ ጳውሎስም አውጤኪስን ከሞት አስነሥቶታል።

20፥13 *አሶን፤* ጢሮአዳ ካለችበት ልሳነ ምድር ባሻገር፣ በየብስ 32 ኪ.ሜ. ያህል ርቃ የምትገኝ፣ የባሕር ወደብ ነበረች። የባሕርን ጠረፍ ተከትሎ ለሚጓዝ ግን 64 ኪ.ሜ ያህል ያስኬዳል፤

ጳውሎስ በየብስ በእግሩ ሊሄድ ስላሰበ
ነበር:: 14በአሶን ከተገናኘንም በኋላ፣ ተቀ
ብለነው አብረን በመርከብ ወደ ሚጢሊኒ
ሄድን:: 15በማግስቱም በመርከብ ተጒዘን
ከኪዩ ደሴት ትይዩ ደረስን:: በሚቀጥለውም
ቀን ወደ ሳሞን ተሻገርን፤ በማግስቱም
ሚሊጢን ደረስን:: 16ጳውሎስም በእስያ
አውራጃ ብዙ መቈየት ስላልፈለገ፣ ወደ
ኤፌሶን ሳይገባ ዐልፎ ለመሄድ ወሰነ፤ ቢቻል
በዓለ ኀምሳን በኢየሩሳሌም ለመዋል ቸኵሎ
ነበርና::
17ከሚሊጢንም ወደ ኤፌሶን ሰው ልኮ
የቤተ ክርስቲያኒቱን ሽማግሌዎች አስጠራ፤
18በመጡም ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ "ወደ
እስያ አውራጃ ከገባሁባት ከመጀመሪያዋ ዕለት
አንሥቶ ዘወትር ከእናንተ ጋር እንዴት
እንደ ኖርሁ ታውቃላችሁ:: 19ምንም እንኳ
ከአይሁድ ሤራ የተነሣ መከራ ቢያደርሱ
ብኝም፣ ጌታን በታላቅ ትሕትናና በእንባ ከማ
ገልገል አልተቈጠብሁም 20በአደባባይም ሆነ
ከቤት ቤት በመዘዋወር፣ እናንተን ከማስተ
ማርና ይጠቅማችኋል ብዬ ያሰብሁትን ከመስ
በክ ወደ ኋላ አላልሁም:: 21በንስሓ ወደ
እግዚአብሔር እንዲመለሱና በጌታችን በኢየ
ሱስ እንዲያምኑ፣ ለአይሁድም ለግሪክ
ሰዎችም አጥብቄ መስክሬላቸዋለሁ::
22"አሁንም እዚያ ስደርስ የሚደርስብ
ኝን ባላውቅም፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ ኢየሩ
ሳሌም እንድሄድ ግድ እያለኝ ነው:: 23ነገር
ግን በምሄድባቸው ከተሞች ሁሉ እስራትና
መከራ እንደሚጠብቀኝ መንፈስ ቅዱስ ይመሰ
ክርልኛል:: 24ይሁን እንጂ ከጌታ ከኢየሱስ
የተቀበልሁትን ሩጫዬንና የእግዚአብሔርን የጸጋ
ወንጌል የመመስከር አገልግሎቴን ብፈጽም፣
ለእኔ ሕይወቴ ከምንም እንደማይቈጠር
እንደ ከንቱ ነገር ናት::
25"አሁንም ቢሆን፣ በመካከላችሁ ተዘዋ
ውሬ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሰበክሁላ
ችሁ፣ እናንተ ሁላችሁ ከእንግዲህ ወዲያ
ፊቴን እንደማታዩ ዐውቃለሁ:: 26ስለዚህ
ከሰው ሁሉ ደም ንጹሕ መሆኔን በዚች ቀን
እመሰክርላችኋለሁ፤ 27የእግዚአብሔርን ፈቃድ
ሁሉ ለእናንተ ከመግለጽ የተቈጠብሁበት ጊዜ
የለምና:: 28ለራሳችሁና መንፈስ ቅዱስ ጠባቂ[ሀ]
አድርጎ በላዩ ለሾማችሁ መንጋ ሁሉ ተጠን
ቀቁ፤ በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን^
ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ:: 29እኔ ከሄድሁ
በኋላ፣ ነጣቂ ተኵላዎች መጥተው በመካከ
ላችሁ ሰርገው እንደሚገቡና ለመንጋውም
እንደማይራሩ ዐውቃለሁ:: 30ከእናንተው
መካከል እንኳ የራሳቸውን ደቀ መዛሙርት
ለማፍራት እውነትን የሚያጣምሙ ይነሣሉ::
31ስለዚህ ተጠንቀቁ፤ ሦስት ዓመት ሙሉ
ሌሊትና ቀን ምንም ያህል ሳላቋርጥ በእንባ
እያንዳንዳችሁን እንደ መከርኋችሁ አስታውሱ::
32"አሁንም ለእግዚአብሔር፣ እንዲሁም ሊያን
ጻችሁና በቅዱሳኑ ሁሉ መካከል ርስት ሊያ
ወርሳችሁ ለሚችለው ለጸጋው ቃል ዐደራ
እሰጣችኋለሁ:: 33የማንንም ብር ወይም ወርቅ
ወይም ልብስ አልተመኘሁም፤ 34እነዚህ እጆቼ
ለእኔና ከኔ ጋር ላሉት በሚያስፈልገን ነገር
እንዳገለገሉን እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ::
35በጒልበታችን ደክመን ችግረኞችን መር
ዳት እንዳለብን ባደረግሁት ሁሉ አሳይቻች
ኋለሁ፤ 'ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው'
ያለውን የጌታ የኢየሱስን ቃል እናስታውስ::"

20፥15 ቍ17፤ 2ጢሞ 4፥20
20፥16 ሐሥ2፥1፡9፤ 18፥19፤19፥21
20፥17 ቍ15፤ ሐሥ 11፥30
20፥18 ሐሥ2፥9፤ 18፥19-21፤19፥1-41
20፥19 ቍ3፤ መዝ 6፥6
20፥20 ቍ27፤ መዝ 40፥10፤ ኤር26፥2፤42፥4
20፥21 ሐሥ2፥38፤ 18፥5፤24፥24፤26፥18 ፤ኤፌ1፥15፤ ቈላ2፥5፤ፊሞ5
20፥22 ቍ16
20፥23 ሐሥ8፥29፤ 9፥16፤21፥4
20፥24 ሐሥ11፥23፤ 21፥13፤2ቆሮ4፥1፤ ገላ1፥1፤2ጢሞ4፥7፤ ቲቶ1፥3
20፥25 ቍ38፤ ማቴ 4፥23
20፥26 ሕዝ3፥17-19፤ሐሥ18፥6
20፥27 ቍ20
20፥28 ቍ29፤ዮሐ 21፥16፤ሮሜ3፥25፤ 1ቆሮ6፥20፤10፥32፤ 1ጢሞ3፥1
20፥29 ቍ28፤ ማቴ7፥15፤ሕዝ34፥5
20፥30 ሐሥ11፥26
20፥31 ቍ19፤ሐሥ 19፥10
20፥32 ማቴ25፥34፤ ሐሥ14፥23፤26፥18፤ ኤፌ1፥14፤ቈላ1፥12፤ 3፥24፤ዕብ9፥15፤ 1ጴጥ1፥4
20፥33 1ሳሙ12፥ 3፤1ቆሮ9፥12፤2ቆሮ2፥ 17፤7፥2፤11፥9፤12፥1 4-17፤1ተሰ2፥5
20፥34 ሐሥ18፥3

ሀ28 በትውፊት *ጳጳሳት* ሲባል የመጣው ነው
^28 ብዙ የጥንት ቅጆች *የጌታን*

ስለዚህ ጳውሎስ በልሳነ ምድሩ ዙሪያ ከምትጓዘው መርከብ ብዙ ወደ ኋላ እንዳልቀረ ያመለክታል::

20፥14 *ሚጢሊኒ፤* የመጀመሪያው ቀን የባሕር ላይ ጒዞ ካበቃ በኋላ፣ ከሌስቦስ ደሴት በስተ ደቡብ ምሥራቅ በምትገኘው በዚች ወደብ ዐረፉ::

20፥15 *ከኪዩ፤* በሁለተኛው ሌሊት ከትንሿ እስያ በስተ ምዕራብ ከሚገኘው ከዚሁ ከትልቁ ደሴት ጠረፍ ፈቀቅ ብለው ሄዱ:: *ሳሞን፤* ወደ ኤፌሶን የሚወስደውን የባሕር ወሽመጥ አቋርጠው በሦስተኛው ቀን ወደዚሁ ደሴት ደረሱ፤ ይህም በኤጂያን ባሕር ከሚገኙትና ዐበይት የንግድ እንቅስቃሴ ከሚታይባቸው ደሴቶች አንዱ ነበር:: *ሚሊጢን፤* ከኤፌሶን በስተ ደቡብ 48 ኪ.ሜ ርቃ የምትገኝ ወደብ ስትሆን፣ ጳውሎስ የተሳፈረበት ጀልባ በመጨረሻ የምታርፍበት ቦታ ነበር:: ወደ ኤፌሶን ጒራ ማለት ከፈለገም መርከብ መለወጥ ሊኖርበት ነው፤ ይህ ደግሞ ጊዜ ይፈጃል (ቍ 16 ይመ):: ወደ ኤፌሶን ከገባ ደግሞ፣ አያሌ ቤተ ሰቦችን መጠየቅ ይኖርበታል፤ ይህም ብዙውን ጊዜ ይሻማበታል:: እንዳለፈው ዓመት ሁከት ቢነሣ ደግሞ (19፥23-41)፣ የበለጠ ጊዜ ይጠፋል፤ ስለዚህ በወጣ ያውጣው የሚባል ጒዳይ አልነበረም::

20፥16 *በዓለ ኀምሳ፤* ከፋሲካ በዓል ጀምሮ ሲቈጠር አምሳኛው ቀን ማለት ነው:: አምስትና ሰባት ቀን ሲደመር (ቍ 6)፤ እንዲሁም አራት ቀን ሲታከልበት (ቍ 13፥15) ዐሥራ ስድስት ቀን ዐልፎአል፤ ስለዚህ ቀሪው ሁለት ሦስተኛው ጊዜ ብቻ ነበር::

20፥17 *የቤተ ክርስቲያኒቱን ሽማግሌዎች፤* የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አገልግሎት ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ፣ በማንኛውም የጳውሎስ አገልግሎት ግልጽ ሆኖ ይታያል:: ለራቡ እንዲውል ከአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን የተላከውንም ርዳታ ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ኀላፊዎች አስረክቦአል ሐዋ11፥30:: ጳውሎስ በመጀምሪያው ሐዋርያዊ ጒዞው ሽማግሌዎችን ሾሞአል (ሐዋ 14፥23):: በዚህ ወሳኝ በሆነው የስንብት ወቅት (ቍ 28) ደግሞ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ከእነርሱ ጋር እንዲገናኙ አስጠራቸው (ቍ 17 ይመ):: ከዓመታት በኋላም፣ ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ለመሆን የሚያበቁት መመዘኛዎች ምን ምን እንደ ሆኑ ጭምር ጽፎአል (1ጢሞ3፤ቲቶ 1) ::

20፥19 *በእንባ፤* ቍ 31 ይመ:: በኤፌሶን የጳውሎስ አገልግሎት የተከናወነው በጋለ ስሜትና በትጋት ነበር::

20፥22 *መንፈስ ቅዱስ...ግድ እያለኝ ነው፤* የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ተከትሎ እንጂ፣ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ጥሶ ወደ ኢየሩሳሌም አልሄደም፤ ይልቁንስ ሰዎቹ እንዳይሄድ የለመኑት (21፥4:12)፣ መንፈስ ቅዱስ ስለከለከለው ሳይሆን፣ በጳውሎስ ላይ የሚደርሰውን እስራት ስለ ገለጠ ነበር (22፥11-12)::

20፥28 *ጠባቂ...በላዩ... ጠብቁ፤* የቤተ ክርስቲያን "ሽማግሌዎች" (ቍ 17)፣ "ጠባቂዎች" ተብለው ይጠራሉ፤ መንጋውንም እንዲያስማሩ ታዘዋል፤ እነዚህ ሰዎች "ሽማግሌዎች" "ጠባቂዎች" ወይም "መጋቢዎች" ተብለው ሊጠሩ እንደሚችሉ ተጽፎአል:: *በገዛ ደሙ፤* "በገዛ ልጁ ደም" ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፤ "በገዛ" የሚለው ቃል ተወዳጅነትን ለመግለጽ የገባ ነው፤ ይህም ልጁን ያመለክታል::

20፥31 *ሦስት ዓመት፤* የ19፥10 ማብ ይመ::

20፥32 *በቅዱሳኑ፤* በምድር ላይ የምእመናን መቀደስ ፍጹም ባይሆንም፣ ወደ ፊት የሚጠብቃቸውን የተሟላ ቅድስና የሚያመለክት ነው (26፥18፤ እንዲሁም የ1ቆሮ 1፥2 ማብ ይመ)::

20፥34 *ለእኔና...በሚያስፈልገን ነገር እንዳገለገሉኝ* ጳውሎስ በተሰሎንቄና (1ተሰ2፥9) በቆሮንቶስ (ሐሥ 18፥3) ሳለ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ለማግኘት በገዛ እጁ ይሠራ ነበር::

20፥35 *ያለውን የጌታ የኢየሱስን ቃል እናስታውስ፤*

36ይህን ካለ በኋላ፣ ተንበርክኮ ከሁሉም
ጋር ጸለየ። 37ሁሉም እጅግ አለቀሱ፤ ጳውሎ
ስንም ዐንገቱን ዐቅፈው ሳሙት፤ 38ከሁሉም
በላይ ልባቸውን የነካው፣ ከእንግዲህ ወዲህ
ፊቱን እንደማያዩ የተናገራቸው ቃል
ነበር። ከዚያም እስከ መርከቡ ድረስ ሸኙት።

## ወደ ኢየሩሳሌም ጒዞ

21 ከእነርሱ ከተለየን በኋላ ቀጥታ በመር
ከብ ወደ ቆስ ተጓዝን፤ በማግስቱም
ወደ ሩድ፣ ከዚያም ወደ ጳጥራ አመራን።
2በዚያም ወደ ፊንቄ የሚሄድ መርከብ ስላ
ገኘን፣ ተሳፍረን ጒዞአችንን ቀጠልን። 3ቆጵ
ሮስ በታየችን ጊዜ፣ ወደ ግራ ትተናት ዐለ
ፍንና ወደ ሶርያ አመራን፤ መርከባችን ጭነ
ቱን በጢሮስ ማራገፍ ስለ ነበረበት፣ እኛም
እዚያው ወረድን። 4ደቀ መዛሙርትንም
በዚያ አግኝተን፣ ሰባት ቀን ከእነርሱ ጋር
ተቀመጥን። እነርሱም በመንፈስ ሆነው
ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ ነገሩት።
5የቈይታ ጊዜያችን ባለቀ ጊዜ፣ ትተና
ቸው ጒዞአችንን ቀጠልን፤ ደቀ መዛሙርቱም
ሁሉ ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር እስከ
ከተማው ውጭ ድረስ ሸኙን፤ በባሕሩም
ዳር ተንበ ርክከን ጸለይን፤ 6ከተሰነባበትንም
በኋላ እኛ ወደ መርከቡ ገባን፤ እነርሱም
ወደ ቤታቸው ተመለሱ።
7ከጢሮስ ተነሥተን ጒዞአችንን በመ
ቀጠል ጴጤሌማይስ ደረስን፤ ከመርከብ
ወርደንም ለወንድሞች ሰላምታ ካቀረብን
በኋላ፣ አንድ ቀን ከእነርሱ ጋር ቈየን። 8በማግ
ስቱ ከዚያ ተነሥተን ቂሳርያ ደረስን፤ ከሰ
ባቱ ወንጌላውያን አንዱ በሆነው በፊልጶስ
ቤትም ዐረፍን። 9እርሱም ትንቢት የሚና
ገሩ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች ነበሩት።
10በዚያም ብዙ ቀን ከተቀመጥን በኋላ
አጋቦስ የተባለ ነቢይ ከይሁዳ ወረደ፤ 11ወደ
እኛም መጣና የጳውሎስን መታጠቂያ ወሰደ፤
የራሱንም እጅና እግር በማሰር፣ "መንፈስ
ቅዱስ፣ 'በኢየሩሳሌም ያሉ አይሁድ የዚህን
መታጠቂያ ባለቤት እንዲህ አድርገው በማሰር
ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል' ይላል" አለ።
12ይህን ስንሰማ እኛና በዚያም የሚኖሩት፣
ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ ለመ
ነው። 13ጳውሎስ ግን፣ "ለምን እንዲህ እያ
ለቀሳችሁ ልቤን ታባቡታላችሁ? እኔ መታሰር
ቀርቶ ስለ ጌታ ኢየሱስ ስም በኢየሩሳሌም
ለመሞት እንኳን ዝግጁ ነኝ' አላቸው። 14ምክ
ራችንን አልቀበል ስላለን፣ "እንግዲህ የጌታ
ፈቃድ ይሁን" ብለን ተውነው።
15ከዚህ በኋላ ተዘጋጅተን ወደ ኢየሩሳ
ሌም ወጣን። 16በቂሳርያ ከነበሩት ደቀ መዛ
ሙርትም አንዳንዶቹ ወደ ምናሶን ቤት
ይዘውን መጡ፤ እኛም በዚያው ተቀመጥን።
ምናሶን የቆጵሮስ ሰው ሲሆን፣ ከመጀመሪያ
ዎቹ ደቀ መዛሙርት አንዱ ነበር።

## ጳውሎስ ኢየሩሳሌም ደረሰ

17ኢየሩሳሌም በደረስን ጊዜ፣ ወንድሞች
በደስታ ተቀበሉን። 18በማግስቱም ጳውሎ
ስና ሌሎቻችንም ያዕቆብን ለማየት ሄድን፤
ሽማግሌዎችም ሁሉ በዚያ ነበሩ። 19ጳውሎ
ስም ሰላምታ ካቀረበላቸው በኋላ፣ እግዚአብሔር
በእርሱ አገልግሎት አማካይነት በአሕዛብ መካ
ከል ያደረገውን ሁሉ በዝርዝር አስረዳቸው።
20እነርሱም ይህን ሲሰሙ፣ እግዚአብሔርን
አመሰገኑ፤ ጳውሎስንም እንዲህ አሉት፤ "ወን

20፥36 ሉቃ22፥41፤ሐሥ9፥40፤21፥5
20፥37 ሉቃ15፥20
20፥38 ቍ25፤ ሐሥ 21፥5
21፥1 ሐሥ16፥10
21፥2 ሐሥ11፥19
21፥3 ሉቃ2፥2
21፥4 ቍ11፤ ሐሥ 11፥26፤20፥23
21፥5 ሉቃ22፥41፤ ሐሥ9፥40፤20፥36
21፥7 ሐሥ1፥16፤ 12፥20
21፥8 ሐሥ6፥5፤ 8፥5-40፤ኤፌ4፥11፤ 2ጢሞ4፥5
21፥9 ዘፀ15፥20፤ መሳ4፥4፤ነህ6፥14፤ ሉቃ2፥36፤ሐሥ 2፥17፤1ቆሮ11፥5
21፥10 ሐሥ11፥28
21፥11 ቍ33፤1ነገ 22፥11፤ኢሳ20፥2-4፤ ኤር13፥1-11፤ማቴ 20፥19፤ሐሥ8፥29
21፥13 የሐ15፥21፤ ሐሥ9፥16፤20፥24
21፥14 ሩት1፥18፤ ማቴ26፥39
21፥15 ሐሥ19፥21
21፥16 ቍ3:4፤ሐሥ 8፥40
21፥17 ሐሥ9፥ 30፤15፥4
21፥18 ሐሥ11፥ 30፤15፥13
21፥19 ሐሥ1፥7፤ 14፥27፤15፥4:12
21፥20 ሐሥ15፥1፡ 5፤22፥3፤ሮሜ10፥2፤ ገላ1፥14፤ፊል3፥6

በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ጌታ ኢየሱስ የተናገረው ቃል ሲጠቀስ፣ በዚህ መልክ ይቀርብ ነበር። በአራቱ ወንጌሉች ውስጥ ከማይገኙት የኢየሱስ ንግግሮች አንዱ ይህ ምሳሌ ነው።

21፥1 *ቀጥታ በመርከብ ወደ ቆስ ተጓዝን፤* ነፋሱ ምቹ ስለነበር ወደዚች ደሴት ደርሰው አዳር በዚያ ሆነ። *ሩድ፤* ከተማዪቱ የምትጠራው በደሴቲቱ ስም ነው፤ የደሴቲቱም ዋና ከተማ ስትሆንም በዓለም ከሚደነቁ ሰባቱ ድንቆች አንዱ በወደቧ ላይ የቆመው እጅግ ግዙፍ የሰው ምስል ነበር፤ ይሁን እንጂ ምስሉ ጳውሎስ በዚያ ከመድረሱ ከሁለት መቶ ዓመት በፊት ተንኰታኵቶ ወድቆአል። እነ ጳውሎስ ሩድ ለመድረስ አንድ ቀን ሙሉ ተጒዘዋል። *ጳጥራ፤* በሉቅያ ወረዳ በስተ ደቡብ ጠረፍ ላይ የምትገኝ ነበረች። ጳውሎስ የትንሿን እስያ ጠረፍ ሳይለቅ ጥግ ጥጉን ይዞ ከሚሄደው ጀልባ ወርዶ በቀጥታ ወደ ጢሮስና ወደ ፊንቄ የሚጓዘውን መርከብ ያዘ።

21፥3 *ቆጵሮስ፤* 13፥4 ይመ። *በጢሮስ፤* ጳውሎስ ከዚህ በፊት ይህችን የፊንቄ ምድር ከዚህ ቀደም ቢያንስ አንድ ጊዜ ሳይረግጣት አልቀረም (15፥3)፤ ከማር 7፥24 ጋር ያነጻጽሩ)።

21፥4 *ሰባት ቀን፤* በፊልጵስዩስ የፋሲካን በዓል ካከበሩ በኋላ፣ ሃያ ዘጠኝ ቀን ሆኗቸዋል፤ እነዚህ ሰባት ቀናት ሲታከሉበት፣ ለበዓለ አምሳ የሚቀረው ሁለት ሳምንት ብቻ ነው። *ጳውሎስ...እንዳይሄድ ነገሩት፤* ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ስለሚጠብቀው መከራ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ አስጠንቅቆት ነበር፤ ወንድሞችም ማስጠንቀቂያውንና ጳውሎስ የሚደርስበትንም መከራ አስቀድመው ስለተረዱ፣ ወደዚያ እንዳይሄድ አጥብቀው ለመኑት፤ ጳውሎስ ግን "መንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል." ባለው መሠረት (20፥22) መሄድ እንዳለበት ተሰማው።

21፥7 *ጴጤሌማይስ፤* ከቀርሜሎስ ተራራ በስተ ሰሜን የምትገኝና በአሁኑ ጊዜ አኮ የምትባለው ከተማ ናት። በስተ ሰሜን፣ ከጢሮስ እስከ ጴጤሌማይስ የአንድ ቀን መንገድ ነው፤ በስተ ደቡብ በኩል ያለው ቂሳርያ ደግሞ 56 ኪ.ሜ ያህል ይርቃል።

21፥8 *ቂሳርያ፤* አሕዛብ የሚኖሩባት በሮማውያን ግዛት የይሁዳ አውራጃ ዋና ከተማ ነበረች (የ10፥1 ማብ ይመ)። *ከ ... ወንጌላውያን... በፊልጶስ፤* ፊልጶስ ወደ ሃያ አምስት ዓመት ገደማ የወንጌላዊነት አገልግሎቱን ያከናወነው በቂሣርያ ከተማ ሳይሆን አይቀርም (የ8፥40 ማብ ይመ)። "ወንጌላዊ" የሚለውን ቃል የምናገኘው በዚህና በኤፌ 4፥11፤ በ2ጢሞ 4፥5 ላይ ብቻ ነው።

21፥9 *ደናግል፤* ጌታን ለማገልገል በልዩ መንገድ የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ። *ትንቢት የሚናገሩ፤* 1ቆሮ 11፥5፤ 12፥8-10 ይመ፤ ከሉቃ 2፥36 ጋር ያነጻጽሩ። በብሉይ ኪዳን ትንቢት ስለ ተናገሩ ሴቶች ዘፀ 15፥20 ፤ መሳ 4፥4፤ 2ነገ 22፥14፤ ነህ6፥14 ይመ።

21፥10 *አጋቦስ የተባለ ነቢይ፤* ፊልጶስ ወንጌላዊ እንደ ነበር ሁሉ (ቍ8) አጋቦስም ነቢይ እንደ ነበር ግልጽ ነው። ከአሥራ አምስት ዓመት በፊት በአንጾኪያ ሳለ፣ በኢየሩሳሌም ስለሚደርስ ሰው ራብ ትንቢት የተናገረውም ይኸው ነቢይ ነበር (11፥27-29)።

21፥12 *እኛና በዚያ የሚኖሩት፤* በዚህ ጊዜ ሉቃስም ከጳውሎስ ባልደረቦች ጋር ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ ጳውሎስን ለምኖታል።

21፥14 *የጌታ ፈቃድ ይሁን፤* ይህ እንግዲህ እነርሱም በመጨረሻ ጊዜ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዱ የጌታ ፈቃድ መሆኑን በመጨረሻ ላይ ተረድተውታል ማለት ነው።

21፥16 *ምናሶን፤* ጳውሎስንና አብረውት የተጓዙትን ዘጠኝ ሰዎች ስላስተናገደ፣ ሀብታም ሳይሆን አይቀርም።

21፥17 *ኢየሩሳሌም በደረስን ጊዜ፤* በዓለ ጰንጠቆስጤ አንድ ወይም ሁለት ቀን ብቻ ሲቀረው ማለት ነው። *ወንድሞች በደስታ ተቀበሉን፤* የተሰበሰበውንና የተላከላቸውን ርዳታ አክብረው ከምስጋና ጋር መቀበላቸውንም ሊያመለክት ይችላል።

21፥18 *ያዕቆብን፤* የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪና የ'ያዕቆብን መልእክት' የጻፈው የጌታ ወንድም ነው (ገላ 1፥19፤ 2፥9 ይመ)። ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት አንዱ ባይሆንም፣ ሐዋርያ ተብሎአል።

ድም ሆይ፤ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ አይ
ሁድ እንዳመኑ ተመልከት፤ ሁሉም ደግሞ
ለሙሴ ሕግ የሚቀኑ ናቸው። 21በአሕዛብ
መካከል የሚኖሩ አይሁድ ሁሉ ሙሴን እን
ዲተዉና ልጆቻቸውን እንዳይገርዙ፣ በቈየው
ልማዳችን መሠረት እንዳይኖሩ እንደምታስ
ተምር ስለ አንተ ተነግሮአቸዋል። 22መም
ጣትህን መስማታቸው የማይቀር ነውና፣
እንግዲህ ምን እናድርግ? 23ስለዚህ የምንልህን
አድርግ። ስእለት ያለባቸው አራት ሰዎች
በእኛ ዘንድ አሉ፤ 24እነዚህን ሰዎች ይዘህ
ከእነርሱ ጋር የመንጻቱን ሥርዐት ፈጽም፤
ራሳቸውንም እንዲላጩ የሚጠየቀውን
ገንዘብ ክፈልላቸው፤ በዚህም ስለ አንተ
የተነገራቸው ሰዎች ሁሉ፣ የሰሙት እውነት
እንዳልሆነና አንተ ራስህ ሕጉን ጠብቀህ
የምትኖር መሆንህን ያውቃሉ። 25ከአሕዛብ
ወገን ያመኑትን በተመለከተ ግን ለጣዖት የተ
ሠዋ ምግብ፣ ደምና ታንቆ የሞተ ከብት
እንዳይበሉ፣ ደግሞም ከዝሙት ርኩሰት ራሳ
ቸውን እንዲጠብቁ ወስነን ጽፈንላቸዋል።"

26ጳውሎስም በማግስቱ ሰዎቹን ይዞ ሄደ፤
አብሮአቸውም የመንጻቱን ሥርዐት ፈጸመ።
ከዚያም የመንጻቱ ሥርዐት መቼ እንደሚያበ
ቃና የእያንዳንዳቸውም መሥዋዕት መቼ እንደ
ሚቀርብ ለማስታወቅ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ።

### ጳውሎስ ተያዘ

27ሰባቱ ቀንም ሊፈጸም ሲቃረብ፣ ከእስያ
አውራጃ የመጡት አይሁድ ጳውሎስን በቤተ
መቅደስ ባዩት ጊዜ፣ ሕዝቡን ሁሉ አነሣ
ሥተው ያዙት፤ 28እንዲህም እያሉ ጮኹ፤
"የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤ ርዱን! ሕዝባች
ንንና ሕጋችንን እንዲሁም ይህን ስፍራ በማ
ጥላላት በደረሰበት ስፍራ የሚገኙትን ሰዎች
ሁሉ የሚያስተምረው ሰው ይህ ነው፤ ከዚ
ህም በላይ ግሪኮችን ወደ ቤተ መቅደስ እያ
ስገባ ይህን የተቀደሰ ስፍራ የሚያረክሰው
እርሱ ነው።" 29ይህንም ያሉት ቀደም ሲል፣
የኤፌሶኑን ሰው ጥሮፊሞስን ከጳውሎስ ጋር
በከተማው ውስጥ ስላዩት፣ ጳውሎስ እር
ሱንም ወደ ቤተ መቅደስ ይዞ የገባ ስለ
መሰላቸው ነበር።

30ከተማው በሙሉ ታወከ፤ ሕዝቡም ከየአ
ቅጣጫው እየተሯሯጡ መጡ፤ ጳውሎስንም
ይዘው እየጐተቱ ከቤተ መቅደሱ ግቢ
አወጡት፤ በሮቹም ወዲያውኑ ተዘጉ። 31ሊገ
ድሉት ሲፈልጉም የኢየሩሳሌም ከተማ ፍጹም
ታወከች፤ ወሬውም ለሮማ ጦር አዛዥ ደረ
ሰው። 32እርሱም ወዲያው አንዳንድ የጦር
መኰንኖችንና ወታደሮችን ይዞ እየሮጠ
ወደ እነርሱ ወረደ፤ እነርሱም መኰንኖቹ
ንና ወታደሮቹን ባዩ ጊዜ ጳውሎስን መደ
ብደብ ተዉ።

33የጦር አዛዡም ቀርቦ ያዘው፤ በሁለት
ሰንሰለትም እንዲታሰር ትእዛዝ ሰጠ፤ ከዚያም
ማን መሆኑንና ምን እንዳደረገ ጠየቀ።
34ሕዝቡም ከፊሉ አንድ ነገር ሲናገር፣ ከፊሉ
ደግሞ ሌላ ይናገር ነበር፤ ከጫጫታው የተ
ነሣም አዛዡ ምንም ነገር ሊሰማ አልቻለም፤
ስለዚህ ጳውሎስ ወደ ጦር ሰፈር እንዲወ
ሰድ አዘዘ። 35ከሕዝቡ ሁካታ የተነሣ፣ ጳውሎስ
ወደ መውጫው ደረጃ ሲደርስ ወታደሮቹ
ይሸከሙት ዘንድ ግድ ሆነባቸው። 36ከኋላ የተ
ከተለውም ሕዝብ፣ "አስወግደው!" እያለ
ይጮኽ ነበር።

### ጳውሎስ ለሕዝቡ ተናገረ

37ወታደሮቹ ወደ ጦር ሰፈር ይዘውት ሊሄዱ
ሲሉ፣ ጳውሎስ ጦር አዛዡን፣ "አንድ ነገር
እንድነግርህ ፍቀድልኝ?" አለው።

አዛዡም እንዲህ አለው፤ "የግሪክ ቋንቋ
ታውቃለህ? 38አንተ ከዚህ ቀደም ዐመፅ

21፥21 ቍ28፤ሐሥ 6፥14፤15፥19-21፤ 1ቆሮ7፥18፡19
21፥23 ዘኍ6፥2፡ 5፤ሐሥ18፥18
21፥24 ቍ26፤ ሐሥ 18፥18፤24፥18
21፥25 ሐሥ15፥ 20፡29
21፥26 ዘኍ6፥13- 20፤ሐሥ24፥18
21፥27 ኤር26፥ 8፤ ሐሥ24፥18፤26፥ 21፤1ተሰ2፥16
21፥28 ማቴ24፥ 15፤ሐሥ6፥13፤ 24፥5፡6
21፥29 ሐሥ18፥ 19፤20፥4፤2ጢሞ 4፥20
21፥30 ሐሥ16፥ 19፤26፥21
21፥32 ሐሥ23፥27
21፥33 ቍ11፤ ሐሥ 12፥6፤20፥23፤ 22፥29፤ ኤፌ6፥20፤2ጢሞ2፥9
21፥34 ቍ37፤ ሐሥ 19፥32፤ 22፥24፤23፥10፡ 16፡32
21፥35 ቍ40
21፥36 ሉቃ23፥ 18፤ዮሐ19፥15፤ ሐሥ 22፥22
21፥37 ቍ34

21፥23 *ስእለት ያለባቸው፤* ጊዜያዊ የሆነ የ'ናዝራዊ ስእለት' ሳይላጩ አልቀሩም። የስእለታቸው ወቅት ከመፈጸሙ በፊት ረክሰው ነበር፤ ምናልባትም ሬሳ ነክተው ሊሆን ይችላል (ከዘኍ 6፥2-12 ያነጻጽሩ)።

21፥24 *የመንጻቱን ሥርዐት፤* አንዳንድ ጊዜ፣ ሥርዐቱ መሥዋዕት ማቅረብንም ይጠይቃል፤ ይህ ሥርዐት የሚጠበቀው በአንዳንድ የአይሁድ ክርስቲያኖች ሲሆን፣ ይኸውም በራስ ፍላጎት ነበር፤ ይሁን እንጂ አይሁድም ሆኑ ከአሕዛብ ወገን የሆኑት ክርስቲያኖች ይህን ሥርዐት እንዲጠብቁ ግዴታ አልነበረባቸውም። *ገንዘቡን ክፈልላቸው፤* ጳውሎስ እነዚህን ሰዎች ሲረዳቸው የሚከተሉትን ነገሮች ይጨምራል፤ (1) ለመሥዋዕት የሚቀርቡትን እንስሳት ይኸውም የስምንት ርግቦችና የአራት በግ ጠቦቶች (ዘኍ 6፥ 9-12) ዋጋ ግማሹን ወይም ሙሉውን በመክፈል፤ (2) ካህኑ መሥዋዕታቸውን ለማቅረብ ይዘጋጅ ዘንድ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዶ የመንጻት ሥርዐታቸውን መቼ እንደሚፈጸም ማስታወስ ነው (ቍ 26)። *ሕጉን ጠብቀህ የምትኖር፤* ቀደም ሲል ጳውሎስ ራሱ ስእለት አቅርቦአል (18፥18)፤ ለአይሁድ እንደ አይሁድ ሆኖአል (1ቆሮ 9፥20-21 ይመ)፤ ጢሞቴዎስም ተገርዞ ነበር (16፥3)። ነገር ግን ጳውሎስ የኦሪትን ሕግ ቢጠብቅም የክርስትና መርሕ እንዳይዛባ ወይም መንገዱን እንዳይስት እጅግ ይጠነቀቅ ነበር (ለምሳሌ ቲቶ እንዲገረዝ አላደረገውም፤ ገላ 2፥3)።

21፥27 *ሰባቱ ቀንም፤* ከዘኍ 6፥9 ጋር ያነጻጽሩ። ለመንጻት ሥርዐት የተወሰነው ጊዜ ይህ ሲሆን፣ ራሳቸውን በመሥዋዕቱ አቅራቢያ አጠገብ መላጨት እንዲሁም ለእያንዳንዱ የኀጢአት ማስተስረያ መሥዋዕትና የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ ከዚያም የመንጻት ሥርዐቱ መፈጸሙን ለካህናቱ መንገር ነበረባቸው። *ከእስያ አውራጃ የመጡት አይሁድ፤* በእስያ የሚኖሩት አይሁድ ከዚህ ቀደም በጳውሎስ ላይ መከራ አድርሰውበት ነበር (20፥19)።

21፥28 *ግሪኮችን ወደ ቤተ መቅደስ እያስገባ፤* በድንጋይ ላይ በተቀረጸው ጽሑፍ መሠረት የተከለከለ ነው (ይህ የድንጋይ ጽሑፍ ዛሬም አለ)። እስራኤላውያን ሥርዐተ አምልኮአቸውን በሚፈጽሙበት ክልል ውስጥ የተገኘ አሕዛብ ይገደል ነበር፤ ነገር ግን ጳውሎስ ከአይሁድ በቀር አሕዛብን ወደዚህ ስፍራ ስለማስገባቱ ማረጋገጫ የለም።

21፥29 *ጥሮፊሞስን፤* ይህን ሰው ጳውሎስ ወደ ተከለከለው ስፍራ የወሰደው አይመስልም፤ ወስዶትማ ቢሆን ኖሮ፣ ከጳውሎስ ይልቅ ጥሮፊሞስን ደብድበው በገደሉት ነበር።

21፥30 *በሮቹም ወዲያውኑ ተዘጉ፤* በተቀደሰው ቅጥር ግቢ ውስጥ የከፋ ብጥብጥ እንዳይነሣ በማለት፣ የቤተ መቅደሱ ኀላፊ በሮቹ እንዲዘጉ አዘዘ።

21፥31 *የጦር አዛዡም፤* የአንድ ሺህ ወታደር አዛዥ ማለት ነው፤ ስሙ ቀላውዴዎስ ሉስዮስ ይባላል (23፥26)፤ ምድቡም በአንጦንያ የጦር ሰፈር ነበር (የቍ 37 ማብ ይመ)።

21፥32 *አንዳንድ የጦር መኰንኖችንና፤* የመቶ አለቆች ማለት ነው። "መኰንኖች" ስለሚል፣ ቢያንስ ቢያንስ ሁለት የመቶ አለቆችና 200 ወታደሮች በግዳጅ ላይ ነበሩ ማለት ነው።

21፥33 *በሁለት ሰንሰለትም፤* ምናልባት የግራና የቀኝ እጆቹ፣ ከአንዳንድ ወታደር ጋር ተቈራኝተው ይሆናል።

21፥37 *ጦር ሰፈር፤* የአንጦንያ ምሽግ ከቤተ መቅደሱ አደባባይ ጋር በሰሜን በኩል በሁለት መወጣጫ ደረጃ የተያያዘ ነበር፤ የምሽጉ ከፍተኛው ግንብ ከቤተ መቅደሱ አደባባይ ላቅ ብሎ ይታያል።

አስነሥተህ፣ አራት ሺህ ነፍሰ ገዳዮችን
ወደ በረሓ ያሸፈትኸው ግብፃዊ አይደለህምን?”
39 ጳውሎስም፣ “እኔስ በኪልቅያ ያለችው
የታዋቂዋ የጠርሴስ ከተማ ነዋሪ የሆንሁ
አይሁዳዊ ነኝ፤ ለሕዝቡ ንግግር እንዳደርግ
ፍቀድልኝ” አለው::
40 ጳውሎስም የጦር አዛዡን ካስፈቀደ በኋላ፣
በደረጃው ላይ ቆሞ ሕዝቡን በእጁ ጠቀሰ፤
ሁሉም ጸጥ ባሉ ጊዜ፣ በዕብራይስጥ[a] ቋንቋ
እንዲህ አለ፤

22 “ወንድሞችና አባቶች ሆይ፤ አሁን
የማቀርብላችሁን የመከላከያ መል
ሴን ስሙኝ::”
2 እነርሱም በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲናገር
በሰሙ ጊዜ ከፊት ይልቅ ጸጥ አሉ::
ጳውሎስም እንዲህ አለ፤ 3 “እኔ በኪልቅያ
በምትገኘው በጠርሴስ የተወለድሁ አይሁዳዊ
ስሆን፣ ያደግሁት ግን በዚህ ከተማ ነው::
የአባቶቻችንን ሕግ በገማልያል እግር ሥር
ተቀምጬ በሚገባ ተምሬአለሁ፤ ዛሬ እና
ንተ እንዲህ የምትቀኑለትን ያህል እኔም ለእ
ግዚአብሔር እቀና ነበር:: 4 ይህን መንገድ
የሚከተሉትንም እስከ ሞት ድረስ እያሳደ
ድሁ፣ ወንዶችንም ሴቶችንም አስሬ ወደ
ወህኒ እጥላቸው ነበር:: 5 ይህን ተግባሬን ሊቀ
ካህናቱም ሆኑ ሸንጎው ሁሉ ሊመሰክሩ
ይችላሉ:: ከእነርሱ ደብዳቤ ተቀብዬ ደማ
ስቆ ወዳሉት ወንድሞቻቸው በመሄድ፣
እነዚህን ሰዎች አሳስሬ ወደ ኢየሩሳሌም
አምጥቼ ለማስቀጣት ወደዚያ እሄድ ነበር::
6 “ስንጓዝም እኩለ ቀን ገደማ ወደ ደማ
ስቆ እንደ ተቃረብሁ፣ ድንገት ታላቅ ብር
ሃን ከሰማይ በዙሪያዬ በራ፤ 7 እኔም ምድር
ላይ ወደቅሁ፤ ከዚያም፣ ‘ሳውል፤ ሳውል፤
ለምን ታሳድደኛለህ?’ የሚለኝን ድምፅ ሰማሁ::
8 “እኔም፣ ‘ጌታ ሆይ፤ አንተ ማን ነህ?’
አልሁት::
“እርሱም፣ ‘አንተ የምታሳድደኝ የናዝሬቱ
ኢየሱስ ነኝ’ አለኝ:: 9 ከእኔ ጋር የነበሩትም
ብርሃኑን አዩ፤ ነገር ግን የሚናገረኝን የእር
ሱን ድምፅ በትክክል አልሰሙም::
10 “እኔም፣ ‘ጌታ ሆይ፤ ምን ላድርግ?’
አልሁት::
“ጌታም፣ ‘ተነሥተህ ወደ ደማስቆ ሂድ፤
በዚያም ልታደርገው የሚገባህን ሁሉ ይነግሩ
ሃል’ አለኝ:: 11 ከብርሃኑም ጸዳል የተነሣ ዐይኔ
ስለታወረ፣ ከእኔ ጋር የነበሩት እጄን ይዘው
እየመሩ ወደ ደማስቆ አደረሱኝ::
12 “ከዚያም ሐናንያ የተባለ ሰው ሊያየኝ
ወደ እኔ መጣ፤ እርሱም ሕግን በጥንቃቄ
የሚጠብቅና እዚያ በሚኖሩት አይሁድ ሁሉ
ዘንድ እጅግ የተከበረ ሰው ነበረ:: 13 በአጠገ
ቤም ቆሞ፣ ‘ወንድም ሳውል ሆይ፤ ዐይኖችህ
ይብሩልህ!’ አለኝ፤ እኔም በዚያችው ቅጽበት
አየሁት::
14 “እርሱም ቀጥሎ እንዲህ አለ፤ ‘የአባቶ
ቻችን አምላክ ፈቃዱን እንድታውቅ፣ ጻድቁን
እንድታይና ቃሉን ከአንደበቱ እንድትሰማ
መርጦሃል፤ 15 ስላየኸውና ስለ ሰማኸው ነገር
በሰው ሁሉ ፊት ምስክር ትሆነዋለህና::
16 ታዲያ፣ አሁን ምን ትጠብቃለህ? ተነሥተህ
ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ፤ ከኀጢአትህም
ታጠብ::’
17 “ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሼ በቤተ
መቅደስ ስጸልይም ተመሰጥሁ፤ 18 ጌታም ሲና
ገረኝ አየሁ፤ እርሱም አሁኑኑ፣ ‘ፈጥነህ ከኢ
የሩሳሌም ውጣ! ስለ እኔ የምትመሰክረውን
አይቀበሉህምና’ አለኝ::

21፡38 ማቴ24፡26፤ ሐሥ5፡36
21፡39 ሐሥ6፡9፤ 9፡11
21፡40 ዮሐ5፡2፤ ሐሥ12፡17
22፡1 ሐሥ7፡2
22፡2 ዮሐ5፡2፤ ሐሥ21፡40
22፡3 1ነገ19፡10፤ ሉቃ10፡39፤ ሐሥ 5፡34፤6፡9፤9፡11፤21፡20፡39፤26፡5
22፡4 ቍ19፡20፤ ሐሥ8፡3፤9፡2
22፡5 ሉቃ22፡66፤ ሐሥ1፡16፤2፡29፤ 9፡2፤13፡26፤23፡1፤28፡17፡21፤ሮሜ7፡1፤ 9፡3
22፡6 ሐሥ9፡3
22፡8 ማር1፡24
22፡9 ሐሥ9፡7፤ 26፡13
22፡10 ሐሥ16፡30
22፡11 ሐሥ9፡8
22፡12 ሐሥ9፡17፤ 10፡22
22፡14 ሐሥ3፡13፤ 7፡52፤1ቆሮ15፡8
22፡15 ቍ14፤ሐሥ 23፡11፤26፡16
22፡16 ዘሌ8፡6፤ መዝ51፡2፤ሕዝ36፡25፤ዮሐ3፡5፤ሐሥ2፡38፤ሮሜ10፡13፤ 1ቆሮ 6፡11፤ኤፌ5፡26፤ ቲቶ3፡5፤ዕብ10፡22፤ 1ጴጥ3፡21
22፡17 ሐሥ9፡26፤ 10፡10

[a] 40 ወይም አራማይክ፤ እንዲሁም ቍ 22፡2

21፡38 ዐመፅ አስነሥተህ...ግብጻዊ፤ የአይሁድን ታሪክ የጻፈው ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን አንድ ሐሰተኛ ግብጻዊ ነቢይ ቀደም ሲል አራት ሺህ ሰው ይዞ ወደ ደብረዘይት ተራራ እንደሸፈተ ይናገራል፤ የሮም ወታደሮች ከእነዚህ በመቶ የሚቈጠሩትን ሲገድሉ፣ መሪያቸው ግን አምልጦ ነበር:: ነፍሰ ገዳዮች፤ ጩቤ የታጠቁ ነፍሰ ገዳዮች ማለት ነው::

21፡39 የጠርሴስ፤ የ22፡3 ማብ ይመ::

22፡1 ወንድሞችና፤ የ11፡1 ማብ ይመ::

22፡3 በጠርሴስ የተወለድሁ፤ ጳውሎስ የጠርሴስም (21፡39) የሮምም ዜግነት ነበረው:: ዩሪፒደስ የአቴናን ከተማ ታላቅነት ለመግለጽ “ስመጥር” እንዳላት ሁሉ፣ ጳውሎስም ጠርሴስን በተመሳሳይ መልክ ይገልጻታል (21፡39):: ጠርሴስ ከሲድነስ ወንዝ 16 ኪ.ሜ.፣ “የኪልቅያ መግቢያ” በተባለው ጠባብና ጥልቅ ሸለቆ ከተከፈሉት ተራራዎች 48 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ትገኛለች:: ታላቅ የንግድ መናኸሪያና ከፍተኛ የትምህርት ደብር እንዲሁም ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች የሚያመሩ ብዙ አውራ ጐዳናዎች የሚያልፉባት ከተማ ነበረች:: ያደግሁት... በዚህ ከተማ ነው፤ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው በልጅነቱ ሳይሆን አይቀርም፤ አንዳንድ ትርጒሞች ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው ካደገ በኋላ መሆኑን ያመለክታሉ:: በገማልያል፤ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት ከነበሩት ሁሉ እጅግ የተከበረ መምህር ነበር፤ የሂሌል የልጅ ልጅ ሳይሆን አይቀርም (5፡34-40 ይመ)::

22፡4 ይህን መንገድ የሚከተሉትንም ... እያሳደድሁ፤ 9፡1-4 ይመ::

22፡5 ሊቀ ካህናቱም፤ በዚህ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ ነበረ (23፡2 ይመ)፤ ከሃያ ዓመት በላይ ሊቀ ካህናት የነበረው ቀያፋ ቀደም ሲል ሞቶአል፤ ነገር ግን የሊቀ ካህናቱም መዝገብ፣ የጳውሎስ ምስክርነት ትክክል መሆኑን ያመለክታል::

22፡6 እኩለ ቀን ገደማ፤ ቀደም ባለው ትረካ ላይ ያልተገለጸ ተጨማሪ ነገር ነው (9፡1-22)::

22፡8 ጌታ ሆይ፤ አንተ ማነህ? የ9፡5 ማብ ይመ:: የምታሳድደኝ፤ የ9፡4 ማብ ይመ::

22፡9 ... ድምፅ... አልሰሙም፤ መስማቱን ድምፅ ሰምተዋል (9፡7)፣ ነገር ግን ምን እንደ ተባለ አላስተዋሉም ለማለት ነው::

22፡12 ሐናንያ...ሕግን በጥንቃቄ የሚጠብቅና፤ ላደመጡት ሰዎች ተገቢ የሆነ ማስገንዘቢያ ነው (የሉቃ 1፡6 ማብ ይመ)::

22፡14 ጻድቁን እንድታይና፤ ከ3፡14 ጋር ያነጻጽሩ:: ለጳውሎስ ትልቁ ቁም ነገር ከሞት የተነሣውን ኢየሱስን ማየቱ ነበር (26፡16፤ 1ቆሮ 9፡1፤ 15፡8 ይመ):: ወንጌልን አምኖ እንዲቀበል ያደረገውና ለትምህርተ መለኮት ትምህርቱም መሠረት የሆነው ይኸው ነው::

22፡16 ከኀጢአትህም ታጠብ፤ ጥምቀት፣ በውስጥ ለሚከናወነው የጸጋ ሥራ ውጫዊ ምልክት ነው:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ በድርጊት የሚፈጸም እውነታና ድርጊቱ የሚያመለክተው ውጫዊ ምልክት በጥብቅ የተሳሰሩ ናቸው (2፡38፤ ቲቶ 3፡5፤ 1ጴጥ 3፡21 ይመ):: ይሁን እንጂ ውጫዊው የምልክቱ ሥርዐት፣ ውስጣዊ የሆነውን የጸጋ ሥራ አያስገኝም (ከሮሜ 2፡28-29፤ ከኤፌ 3፡4-9 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የሮሜ 6፡3-4 ማብ ይመ::

22፡17 ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሼ፤ በ9፡26 እንዲሁም በገላ 1፡17-18 ላይ የተገለጸውን ጒብኝት ያመለክታል:: በቤተ መቅደስ...ተመሰጥሁ፤ ስለ ጴጥሮስ መመሰጥ የሚናገረውን ክፍል ይመ (10፡10፤ 11፡5 ይመ፤ ከ2ቆሮ 12፡3 ጋር ያነጻጽሩ)::

19“እኔም እንዲህ አልሁት፤ ‘ጌታ ሆይ፤
በአንተ የሚያምኑትን ሰዎች ለማሰርና ለመ
ደብደብ፣ በየምኵራቡ ስዞር እንደ ነበር
እነዚህ ሰዎች ያውቃሉ፤ 20ደግሞም የአንተን
ሰማዕት⁼ የእስጢፋኖስን ደም በሚያፈሱበት
ጊዜ፣ በድርጊታቸው ተስማምቼ በቦታው
ቆሜ የገዳዮቹን ልብስ እጠብቅ ነበር።’
“ጌታም፣ ‘ሂድ፤ በሩቅ ወዳሉት አሕዛብ
እልክሃለሁና’ አለኝ።”

### ጳውሎስ የሮም ዜጋ መሆኑ ታወቀ

22ሕዝቡም ይህን ቃል እስኪናገር ድረስ
ሰሙት፤ ከዚህ በኋላ ግን ድምፃቸውን ከፍ
በማድረግ፣ “ይህስ ከምድር ገጽ ይወገድ! በሕ
ይወት መኖር አይገባውም!” ብለው ጮኹ በት።
23እነርሱም እየጮኹና ልብሳቸውን እየ
ወረወሩ፣ ትቢያም ወደ ላይ እየበተኑ ሳሉ፣
24የጦር አዛዡ ጳውሎስን ወደ ጦር ሰፈር እንዲ
ያስገቡትና ሕዝቡ ለምን እንዲህ እንደሚ
ጮኹበት እየተገረፈ እንዲመረመር ትእ
ዛዝ ሰጠ። 25ጳውሎስም በጠፍር ወጥረው ሊገ
ርፉት ሲሉ፣ አጠገቡ የቆመውን የመቶ
አለቃ፣ “አንድን የሮም ዜጋ ያለ ፍርድ
ለመግረፍ ሕግ ይፈቅድላችኋልን?” አለው።
26የመቶ አለቃውም ይህን ሲሰማ፣ ወደ ጦር
አዛዡ ቀርቦ፣ “ምን እያደረግህ እንደ ሆነ ዐው
ቀሃል? ሰውየው እኮ ሮማዊ ነው” አለው።
27አዛዡም ወደ ጳውሎስ ቀርቦ፣ “አንተ
ሰው እስቲ ንገረኝ፤ ሮማዊ ነህን?” አለው።
እርሱም፣ “አዎን፤ ነኝ” አለው።
28አዛዡም መልሶ፣ “እኔ ይህን ዜግነት
ያገኘሁት ብዙ ገንዘብ አውጥቼ ነው” አለ።
ጳውሎስም፣ “እኔ ግን ከተወለድሁ ጀምሮ
ሮማዊ ነኝ” አለው።
29ስለዚህ ሊመረምሩት ያሰቡት ሰዎች
ወዲያው ከእርሱ ሸሹ፤ የጦር አዛዡም የሮም
ዜጋ መሆኑን ባወቀ ጊዜ፣ በሰንሰለት
አስሮት ስለ ነበር ፈራ።

### ጳውሎስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቀረበ

30በማግስቱም የጦር አዛዡ፣ አይሁድ
ጳውሎስን የከሰሱበት ትክክለኛው ምክንያት
ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ስለ ፈለገ ፈታው፤
ከዚያም የካህናት አለቆችና የአይሁድ ሸንጎ
አባላት በሙሉ እንዲሰበሰቡ አዘዘ፤ ጳውሎስ
ንም ከደረጃው አውርዶ በፊታቸው አቆመው።

23 ጳውሎስም ወደ ሸንጎው ትኵር ብሎ
በመመልከት፣ “ወንድሞች ሆይ፤ እኔ
እስከዚች ቀን ድረስ በእግዚአብሔር ፊት በን
ጹሕ ሕሊና ተመላልሻለሁ” አለ። 2በዚህ ጊዜ
ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ በጳውሎስ አጠገብ
የቆሙትን ሰዎች አፉን እንዲመቱት አዘዘ።
3ጳውሎስም፣ “አንተ በኖራ የተለሰንህ ግድ
ግዳ! እግዚአብሔር ደግሞ አንተን ይመታሃል፤
በሕጉ መሠረት ልትፈርድብኝ ተቀምጠህ
ሳለህ፣ ያለ ሕግ ስላስመታኸኝ አንተ ራስህ
ሕጉን ጥሰሃል” አለው።
4ጳውሎስ አጠገብ ቆመው የነበሩትም፣
“የእግዚአብሔርን ሊቀ ካህናት ደፍረህ ትሰድ
ባለህን?” አሉት።
5ጳውሎስም፣ “ወንድሞች ሆይ፤ ሊቀ ካህ
ናት መሆኑን ባለማወቄ ነው፤ ‘በሕዝብህ አለቃ
ላይ ክፉ አትናገር’ ተብሎ ተጽፎአልና” አላ
ቸው።

22፥19 ቍ4፤ማቴ 10፥17፤ሐሥ8፥3
22፥20 ሐሥ7፥57-60፤8፥1
22፥21 ሐሥ9፥15፤13፥46
22፥22 ሐሥ21፥36፤25፥24
22፥23 2ሳሙ16፥13፤ሐሥ7፥58
22፥24 ቍ29፤ ሐሥ 21፥34
22፥25 ሐሥ16፥37
22፥29 ቍ24፡25፤ሐሥ16፥38፤21፥33
22፥30 ማቴ5፥22፤ ሐሥ21፥33፤23፥28
23፥1 ሐሥ22፥5፡30፤24፥16፤1ቆሮ4፥4፤2ቆሮ1፥12፤1ጢሞ1፥5፡19፤3፥9፤2ጢሞ1፥3፤ዕብ9፥14፤10፥22፤13፥18፤1ጴጥ3፥16፡21
23፥2 ዮሐ18፥22፤ ሐሥ24፥1
23፥3 ዘሌ19፥15፤ ዘዳ25፥1:2፤ማቴ23፥27፤ዮሐ7፥51
23፥5 ዘፀ22፥28

⁼20 ወይም *ምስክር*

22፥20 *ተስማምቼ፤* ነገሩ ለአንዳንዶቹ እንደዚያ ቢመስላ ቸውም፣ ጳውሎስ የሸንጎው አባል ነበር ማለት አይደለም (የ26፥10 ማብ ይመ)። መደረቢያቸውን እግሩ አጠገብ እንዲያስ ቀምጡ መፍቀዱ፣ መስማማቱን ያመለክታል።

22፥24 *የጦር አዛዡ፤* የ21፥31 ማብ ይመ። *ጦር ሰፈር፤* የ21፥37 ማብ ይመ። *እየተገረፈ፤* በፊልጵስዮስ በበትር እንደመቱት ሳይሆን (16፥22-24) ከፉኛ በሚያሠቃይ ጅራፍ ነበር። ይህም አንድ ባሪያ ወይም የውጭ ሰው የደበቀውን ምስጢር እንዲያወጣ የሚያስለፈልፉበት ሕጋዊ መሣሪያ ነበር፤ የሮም ዜግነት ያለውን ሰው ግን እንዲህ አድርጎ ማሠቃየት ከቶም የሚታሰብ አልነ በረም። መግረፊያው የጠፍር ዐለንጋ ሲሆን፣ በየጫፉ ላይ የአ ጥንት ስብርባሪዎች ወይም የብረት ቍርጥራጮች ይሸረቡበት ነበር።

22፥25 *ወጥረው፤* ወንጀለኛ ከግንድ ጋር ተጠፍሮ ይገረፍ ነበር። *የመቶ አለቃ፤* የ10፥1 ማብ ይመ። *የሮም ዜጋ፤* በሮም ሕግ መሠረት፣ የሮም ዜጋ የሆነ ሁሉ፣ ሰብእናን ከሚያዋርድ ቅጣት ማለት በዱላ ከመደብደብ፣ በጅራፍ ከመገረፍና እንዲሁም በመስቀል ላይ ከመሰቀል ነጻ ነበር።

22፥28 *ብዙ አውጥቼ ከፍዬ፤* የሮም ዜጋ ለመሆን የሚያ በቁ ሦስት መንገዶች ነበሩ፤ እነርሱም (1) የሮምን መንግሥት በሚገባ ማገልገል፤ (2) ከፍ ያለ ገንዘብ አውጥቶ መግዛት፤ (3) የሮም ዜግነት ካለው ቤተ ሰብ መወለድ ናቸው። የጳውሎስ አባት ወይም ቀደም ያሉ ዘመዶቹ የሮምን ዜግነት እንዴት እንዳገኙ አይታወቅም። በ171 ዓ.ቅ.ክ. ላይ አያሌ አይሁድ የጠ ርሴስ ዜጎች ሆነው ነበር፤ ከእነዚህም የተወሰነ ቍጥር ያላቸው የዜግነቱን መብት ያገኙት የተወሰኑት በፖምፔ ዘመን (106-48 ዓ.ቅ.ክ.) ሳይሆን አይቀርም፤ ከ16፥37 ያነጻጽሩ።

22፥30 *ፈታው፤* ሸንጎው እንዲታሰር ባይፈልግ ኖሮ ጳውሎስ ከእንግዲህ ፈጽሞ እስራት አያገኘውም ነበር። *የካህናት አለቆችና፤* ከካህናት አለቆች ዘር የሆኑና በአብዛኛው ሰዱቃውያን ናቸው፤ ይሁን እንጂ በዚህ ጊዜ ሸንጎው አያሌ ፈሪሳውያንንም ዐቅፎ ነበር። እነዚህ ሰዎች የአይሁድ ኅብረተሰብ ገዥ ወገን ነበሩ። የአይሁድ ካላጸደቀው በቀር ከፍተኛ ቅጣት የማይ ፈጸም ቢሆ ንም፣ የአይሁድ ሸንጎ በሮም እንደራሴ ዘንድ የተከበረ ነበር።

23፥1 *ሸንጎውን፤* የ5፥21 ማብ ይመ። *ወንድሞች፤* ከአይሁድ ወገን የሆኑትን ለማለት ነው (የ11፥1 ማብ ይመ)። *በንጹሕ ሕሊና፤* ይህን ጳውሎስ ስለ ራሱ አዘውትሮ ይናገረዋል።

23፥2 *ሐናንያ፤* የነቢዳኦስ ልጅ ሲሆን፣ ከ47-59 ዓ.ም. ሊቀ ካህናት ነበረ። ከ6-15 ዓ.ም. ሊቀ ካህናት ከነበረው ከሐና ጋር አንድ አለመሆኑን ማስተዋል አለብን (የሉቃ 3፥2 ማብ ይመ)። ሐ ናንያ በጭካኔና በዐመፅ ሥራው የታወቀ ሰው ነበር። በሮም መንግሥት ላይ ዐመፅ በተነሣ ጊዜ፣ በገዛ ወገኖቹ እጅ ተገድሏል።

23፥3 *በኖራ የተለሰንህ ግድግዳ፤* ላዩ ያማረ ሆኖ በውስጡ የፈረሰ ገላና የገጠጠ አጥንት የሞላበት ይዞ እንደሚገኝ መቃብር፣ ማለት ነው (ማቴ 23፥27 ይመ)፤ ወይም ለምንም የ ማይበገር ጠንካራ መስሎ ነፋስ ሲመጣ እንደሚፈረካከስ ግንብ ማለት ነው (ሕዝ 13፥10-12 ይመ)። የግብዝን ሰው ማንነት ለመግለጽ የሚገባ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው።

23፥5 *ሊቀ ካህናት ባለማወቄ ነው፤* የዚህ ዐረፍተ ነገር ትርጕም በተለያየ መንገድ ተገልጿል፤ (1) ጳውሎስ ዐይኑ ደካማ ስለ ነበር (ገላ 4፥15፤ 6፥11 ይመ) በሥልጣን ወንበር ላይ የተቀመጠ ውን ሰው ለመለየት ስላልቻለ ነው፤ (2) በሥልጣን ወንበር ላይ የተቀመጠው ሊቀ ካህናቱ መሆኑን መለየት ያልቻለው፣ አንዳንድ ጊዜ ሌሎችም በወንበሩ ስለሚቀመጡበት ነው፤ (3) እውነተኛ ሊቀ ካህናት እንደዚህ ያለ ትእዛዝ ስለማይሰጥ የምጸት አነጋገር ነው (4) በአጠቃላይ ከአድራጎቱ የተነሣ ሐናንያን ሊቀ ካህናት ነው ብሎ መቀበል ስላልፈለገ ነው።

23፥6 *ሰዱቃውያን፤* የ4፥1፤ የማቴ 3፥7፤ የማር 12፥18፤ የሉቃ

6ጳውሎስም ሕዝቡ፣ ከፊሎቹ ሰዱቃውያን፣ ከፊሎቹ ፈሪሳውያን መሆናቸውን ስላ
ወቀ፣ "ወንድሞቼ ሆይ፤ እኔ ከፈሪሳዊ የተ
ወለድሁ ፈሪሳዊ ነኝ፤ ለፍርድ የቀረብሁ
ትም የሙታንን ትንሣኤ ተስፋ በማድረጌ
ነው" ሲል በሸንጎው ፊት ጮኸ:: 7ይህንንም
በተናገረ ጊዜ፣ በፈሪሳውያንና በሰዱቃው
ያን መካከል ጠብ ተነሣ፤ ሸንጎውም ለሁለት
ተከፈለ:: 8ሰዱቃውያን የሙታን ትንሣኤ
የለም፤ መላእክትም መናፍስትም የሉም
የሚሉ ሲሆኑ፣ ፈሪሳውያን ግን በእነዚህ
ሁሉ መኖር የሚያምኑ ነበሩ::

9ታላቅ ሁከትም ሆነ፤ ከፈሪሳውያን ወገን
የሆኑ አንዳንድ የኦሪት ሕግ መምህራን
ተነሥተው፣ "በዚህ ሰው ላይ ምንም ጥፋት አላ
ገኘንበትም፤ መንፈስ ወይም መልአክ ተናግ
ሮትስ እንደ ሆነ ምን ይታወቃል?" በማለት
አጥብቀው ተከራከሩ:: 10ጠቡ ከማየሉ የተጠ
ነሣም አዛዡ ጳውሎስን እንዳይገነጣጥሉት
ፈራ፤ ስለዚህ ወታደሮቹ ወርደው ከመካከ
ላቸው ነጥቀው ወደ ጦሩ ሰፈር እንዲያስ
ገቡት አዘዘ::

11በሚቀጥለውም ሌሊት ጌታ በአጠገቡ
ቆሞ፣ "ጳውሎስ ሆይ፤ አይዞህ! በኢየሩሳሌም
እንደ መሰከርህልኝ፣ በሮምም ደግሞ ልት
መሰክርልኝ ይገባሃል" አለው::

### ጳውሎስን ለመግደል የተደረገ ሤራ

12በነጋም ጊዜ፣ አይሁድ ተሰብስበው በማ
ሤር ጳውሎስን እስኪገድሉ ድረስ እህል
ውሃ ላለመቅመስ ተማማሉ:: በዚህ ሤራ
13የተማማሉትም ከአርባ በላይ ነበሩ:: 14እነር
ሱም ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ሽማግሌ
ዎች ሄደው እንዲህ አሉ፤ "ጳውሎስን ሳንገ
ድል እህል ላለመቅመስ ጽኑ መሐላ አድርገ
ናል:: 15እንግዲህ እናንተ ከሸንጎው ጋር
ሆናችሁ፣ ስለ ጉዳዩ ትክክለኛ የሆነ ተጨ
ማሪ መረጃ ከእርሱ እንደምትፈልጉ አስ
መስላችሁ ጳውሎስን ወደ እናንተ እንዲሰ
ደው የጦር አዛዡን ለምኑት፤ እኛም ገና
ወደዚህ ሳይደርስ ልንገድለው ዝግጁ ነን::"

16ነገር ግን የጳውሎስ የእኅት ልጅ ስለ
ሤራው በመስማቱ፣ ወደ ጦሩ ሰፈር ገብቶ
ሁኔታውን ለጳውሎስ ነገረው::

17ጳውሎስም ከመቶ አለቆቹ አንዱን
ጠርቶ፣ "ይህ ልጅ ለጦር አዛዡ የሚነግ
ረው ነገር ስላለ ወደ እርሱ ውሰደው" አለው::
18እርሱም ወደ ጦር አዛዡ ወሰደው::

የመቶ አለቃውም፣ "እስረኛው ጳውሎስ ጠር
ቶኝ፣ ይህ ጕልማሳ የሚነግርህ ነገር ስላ
ለው ወደ አንተ እንዳቀርበው ለመነኝ"
አለው::

19አዛዡም የጕልማሳውን እጅ ይዞ ለብ
ቻው ገለል በማድረግ፣ "ልትነግረኝ የምት
ፈልገው ምንድን ነው?" አለው::

20ልጁም እንዲህ አለው፤ "አይሁድ ስለ
እርሱ ትክክለኛ የሆነ ተጨማሪ መረጃ ለማ
ግኘት የፈለጉ በመምሰል፣ ጳውሎስን ነገ
ሸንጎው ፊት እንድታቀርብላቸው ሊለምኑህ
ተስማምተዋል:: 21ስለዚህ እሺ አትበላቸው፤
ምክንያቱም ከመካከላቸው ከአርባ በላይ
የሚሆኑት ሊገድሉት አድፍጠው እየጠበቁት
ነው፤ ደግሞም እስኪገድሉት ድረስ እህል ውሃ
ላለመቅመስ ተማምለዋል፤ አሁንም ተዘጋጅ
ተው የአንተን መልስ እየተጠባበቁ ነው::"

22የጦር አዛዡም፣ "ይህን ለእኔ የገለጥ
ህልኝን ነገር ለማንም እንዳትናገር" ብሎ ጕል
ማሳውን አስጠንቅቆ አሰናበተው::

### ጳውሎስ ወደ ቂሳርያ ተላከ

23ከዚያም ከመቶ አለቆቹ* ሁለቱን ጠርቶ
እንዲህ አላቸው፤ "ከምሽቱ ሦስት ሰዓት፣
ወደ ቂሳርያ የሚሄዱ ሁለት መቶ ወታደ
ሮች፣ ሰባ ፈረሰኞችና ሁለት መቶ ባለ ጦር
ጭፍራ አዘጋጁ፤ 24ደግሞም ጳውሎስ ተቀ
ምጦበት ወደ አገረ ገዡ ወደ ፊልክስ በደ
ኅና የሚደርስበት ከብት ይዘጋጅ::"

25ደብዳቤም ጻፈ፤ እንዲህ የሚል:-

26ከቀላውዴዎስ ሉስዩስ፤

ለክቡር አገረ ገዥ ለፊልክስ፤

ሰላም ለአንተ ይሁን::

አይሁድ፣ ይህን ሰው ይዘው ሊገድሉት
ነበር፤ ነገር ግን የሮም ዜጋ መሆኑን ስላወ
ቅሁ፣ ከወታደሮቼ ጋር ደርሼ አተረፍሁት::
28ለምን ሊከሱት እንደ ፈለጉ ለማወቅም፣
ወደ ሸንጎአቸው አቀረብሁት:: 29የተከሰሰ
ውም ሕጋቸውን በተመለከተ እንጂ ለሞት
ወይም ለእስራት የሚያበቃ እንዳልሆነ ተረ

*23 በግሪኩ የዚህ ቃል ትርጕም አይታወቅም::

23፥6 ቍ7:8፤ ሐሥ 4፥1፤22፥5፤ 24፥15: 21፤26፥5:8፤ፊል3፥5
23፥8 ማቴ22፥23፤ 1ቆሮ15፥12
23፥9 ቍ29፤ኤር 26፥16፤ማር2፥16፤ ሉቃ23፥4፤ሐሥ22፥7: 17:18፤25፥25፤26፥ 31፤28፥18
23፥10 ሐሥ21፥34
23፥11 ማቴ14፥27፤ ሐሥ19፥21፤28፥23
23፥12 ቍ14:21: 30፤ሐሥ20፥3፤25፥3
23፥14 ቍ12
23፥15 ቍ1ሐሥ 22፥30
23፥16 ቍ10፤ ሐሥ 21፥34
23፥18 ኤፌ3፥1
23፥20 ቍ1:14:15
23፥21 ቍ12:13:14
23፥23 ቍ33፤ሐሥ 8፥40
23፥24 ቍ26: 33፤ሐሥ24፥1-3:10፤ 25፥14
23፥26 ሉቃ1፥3፤ ሐሥ15፥23፤24፥3፤ 26፥25
23፥27 ሐሥ21፥ 32:33፤22፥25-29
23፥28 ሐሥ22፥30
23፥29 ቍ9፤ ሐሥ 18፥15፤25፥19

20፥27 ማብ ይመ:: ትንሣኤ ሙታን፣ መላእክትና መናፍ ስት መኖራ ቸውን አይቀበሉም:: *ፈሪሳውያን፣* የማቴ 3፥7፤ የማቴ 2፥16፤ የሉቃ 5፥17 ማብ ይመ::

23፥10 *አዛዡ፤* የ21፥31 ማብ ይመ:: የጦር ሰፈር፤ የ21፥37 ማብ ይመ::

23፥11 *ጌታ በአጠገቡ ቆሞ፤* በጭንቅ ሰዓቱና ርዳታ በሚ ፈልግበት ጊዜ፣ ጳውሎስ ይህንኑ ያገኘው ነበር (18፥9፤ 22፥18፤ 27፥23 ይመ)::

23፥12 *ተማማሉ፤* እነዚህ በኋላ ጊዜ በሮም መንግሥት ላይ ዐምፀው የተነሡ "ቀናተኞች" በሚል መጠሪያ የሚታወቁ ተቀናቃኞች ወይም "ሽብርተኞች" ሊሆኑ ይችላሉ (የ21፥38 ማብ ይመ)::

23፥17 *ከመቶ አለቆቹ፤* የ10፥1 ማብ ይመ:: *ለጦር አዛዡ፤* የ21፥31 ማብ ይመ::

23፥22 *ለማንም እንዳትናገር፤* የዚህ ልጅ ሕይወት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ በማለትና የጦር አዛዡም ጨለማን ተገን አድ ርጎ ጳውሎስን ለማሸሽ በማሰቡ ነው (ቍ 23 ይመ)::

23፥23 *ወታደሮች... ፈረሰኞች... ባለ ጦር ጭፍራ፤* ከባድ መሣሪያ የታጠቁ እግረኞች፣ ፈረሰኞችና ቀላል መሣሪያ የያዙ ወታደሮች ናቸው:: አዛዡ የሮም ዜጋ የሆነውን የጳውሎስን ደኅንነት እንዲጠብቁ የመደባቸው አራት መቶ ሰባ ሰዎች ናቸው (ከ22፥25-29 ጋር ያነጻጽሩ)::

23፥27 *የሮም ዜጋ መሆኑን ስላወቅሁ፤* አዛዡ በሮም ገዥዎች ዘንድ ተወዳጅነትን ለማትረፍ ሲል ይህን ተናገረ እንጂ ነገሩ እውነትን ያዘለ ንግግር አልነበረም፤ ምክንያቱም ጳውሎስን አስገርፎ ለማውጣጣት ቈርጦ እስከተነሣበት ሰዓት ድረስ ጳው ሎስ የሮም ዜጋ መሆኑን አላወቀም ነበርና::

23፥30 *ከሳሾቹም ከእርሱ ጋር ያላቸውን ክርክር ለአንተ*

ድቻለሁ:: 30አይሁድ ግን በዚህ ሰው ላይ
ማሤራቸውን በተረዳሁ ጊዜ፣ ወዲያው
ወደ አንተ ላክሁት፤ ከሳሾቹም ከእርሱ ጋር
ያላቸውን ክርክር ለአንተ እንዲያቀርቡ አዘ
ዝኋቸው::

31ስለዚህ ወታደሮቹ በታዘዙት መሠ
ረት፣ ጳውሎስን ይዘው በሌሊት እስከ አን
ቲጳጥሪስ ድረስ ወሰዱት:: 32በማግስቱ፣
ፈረሰኞቹ ብቻ እንዲያደርሱት አድርገው፣
ሌሎቹ ወደ ጦር ሰፈር ተመለሱ:: 33ፈረሰ
ኞቹም ቂሳርያ በደረሱ ጊዜ፣ ደብዳቤውን
ለአገረ ገዡው ሰጡት፤ ጳውሎስንም አስረ
ከቡት:: 34አገረ ገዡም ደብዳቤውን ካነበበ
በኋላ፣ ጳውሎስን ከየትኛው አውራጃ እንደ
መጣ ጠየቀው፤ የኪልቅያ ሰው መሆኑን
ባወቀ ጊዜ፣ 35"የአንተን ጉዳይ ከሳሾችህ
ሲቀርቡ አያለሁ" አለው:: ከዚያም ጳውሎስ
በሄሮድስ ግቢ ውስጥ እንዲጠበቅ አዘዘ::

### ጳውሎስ በፊልክስ ፊት ቀረበ

**24** ከአምስት ቀን በኋላ፣ ሊቀ ካህናቱ
ሐናንያ ከአንዳንድ ሽማግሌዎ
ችና ጠርጡለስ ከሚባል ጠበቃ ጋር ወደ
ቂሳርያ ወረደ፤ በጳውሎስም ላይ ያላቸውን
ክስ ለአገረ ገዡ አቀረቡ:: 2ጳውሎስ ተጠ
ርቶ በቀረበ ጊዜ፣ ጠርጠሉስ እንዲህ ሲል
ክሱን አቀረበ፤ "ክቡር ፊልክስ ሆይ፤ በአንተ
ዘመን ሰላም ለብዙ ጊዜ ሰፍኖልናል፤ አርቆ
አስተዋይነትህም ለዚህ ሕዝብ መሻሻልን
አስገኝቶለታል፤ 3በየቦታውና በየጊዜው ይህን
ውለታ በታላቅ ምስጋና እንቀበላለን:: 4ነገር
ግን ይበልጥ እንዳላደክምህ፣ በአጭሩ እንድ
ትሰማን መልካም ፈቃድህን እለምንሃለሁ::

5"ይህ ሰው፣ በዓለም[a] ባሉት አይሁድ ሁሉ
መካከል በሽታ ሆኖ ሁከት የሚያስነሣ፣
ደግሞም የናዝራውያን ወገን ቀንደኛ መሪ
ሆኖ አግኝተነዋል:: 6ከዚህም በላይ ቤተ
መቅደሱን ለማርከስ ሲሞክር አግኝተን ያዝ
ነው:: በሕጋችንም መሠረት ልንፈርድበት
አስበን ነበር፤ 7ነገር ግን የጦር አዛዡ ሉስ
ዮስ መጥቶ በታላቅ ኀይል ከእጃችን ነጥቆ
ወሰደው፤ ከሳሾቹም ወደ አንተ እንዲመጡ
አዘዘ:: 8እንግዲህ አንተ ራስህ መርምረኸው
እርሱን የከሰስንበትን ነገር ሁሉ እውነት
መሆኑን ልታረጋግጥ ትችላለህ::"[ሬ]

9አይሁድም ነገሩን እንደተባለው መሆ
ኑን በመደገፍ በክሱ ተባበሩ::

10አገረ ገዡም እንዲናገር በእጁ ምልክት
በሰጠው ጊዜ፣ ጳውሎስ እንዲህ ሲል መለሰ፤
"ከብዙ ዘመን ጀምሮ የዚህ ሕዝብ ፈራጅ
መሆንህን ዐውቃለሁ፤ ስለዚህ የመከላከያ
መልሴን የማቀርበው በደስታ ነው:: 11ልሰ
ግድ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣሁት ከዐሥራ
ሁለት ቀን በፊት መሆኑን አንተው ራስህ
በቀላሉ ማረጋገጥ ትችላለህ:: 12ከሳሾቼም
በቤተ መቅደስ ከማንም ጋር ስከራከር
ወይም በምኵራብ ወይም በከተማ ውስጥ
በየትኛውም ስፍራ ሕዝብን ሳነሣሣ አላገኙ
ኝም:: 13አሁንም ለተከሰስሁበት ነገር ማስ
ረጃ ሊያቀርቡልህ አይችሉም:: 14ይሁን እንጂ
እነርሱ ኑፋቄ በሚሉት፣ በጌታ መንገድ የአባ
ቶቻችንን አምላክ አመልካለሁ:: 15እኔም እንደ

23፥30 ቍ20፡ 21:35፤ሐሥ20፥3፤ 24፥19፤25፥16
23፥32 ቍ23፤ ሐሥ 21፥34
23፥33 ቍ23:24፡ 26፤ሐሥ8፥40
23፥34 ሐሥ6፥9፤ 21፥39
23፥35 ቍ30፤ ሐሥ 24፥19:27፤25፥16
24፥1 ሐሥ23፥2፡ 24:30:35
24፥3 ሉቃ1፥3፤ ሐሥ23፥28፤26፥25
24፥5 ቍ14፤ ማር1፥24፤ ሐሥ 16፥20፤ 17፥6፤ 21፥28፤26፥5፤28፥22
24፥6 ሐሥ21፥28
24፥9 1ተሰ2፥16
24፥10 ሐሥ23፥24
24፥11 ቍ1፤ሐሥ 21፥27
24፥12 ቍ18፤ሐሥ 25፥8፤28፥17
24፥13 ሐሥ25፥7
24፥14 ቍ5፤ሐሥ 3፥13፤9፥2፤26፥6:22፤ 28፥23
24፥15 ማቴ25፥ 46፤ሐሥ23፥6፤28፥20

[ሬ] 6-8 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ቍ7 እና የቍ6 ክፊል የላቸውም::

*እንዲያቀርቡ፤* ደብዳቤው እንደ ደረሰ ትእዛዝ የሚተላለፍ መሆኑን ገምቶ ነበር::

23፥31 *አንቲጳጥሪስ፤* ታላቁ ሄሮድስ እንደ ገና ሠርቶ በአባቱ ስም የሰየመው፣ ከኢየሩሳሌም 48 ኪ.ሜ የራቀ ሲሆን፣ በሰማርያና በይሁዳ መካከል ያለውን ጸጥታ ለመቈጣጠር ወታደሮች የተመደቡበት ቦታ ነው::

23፥33 *ቂሳርያ፤* በሰማርያና በይሁዳ አውራጃዎች ላይ የሚሾመው የሮም መንግሥት እንደራሴ የሚቀመጥባት ከተማ ነበረች:: ከአንቲጳጥሪስ 45 ኪ.ሜ. ያህል ትርቃለች::

23፥34 *አገረ ገዡም፤* እንጦንዮስ ፊልክስ ነው:: በ52 ዓ.ም ገደማ ቄሳር ቀላውዴዎስ የይሁዳ ገዥ አድርጎ ሾመው፤ በዚህ ጊዜም የፊልክስ ወንድም ነበረ:: ወንድማማቾቹ ቀደም ሲል ባሮች፣ በኋላም አርነት ወጥተው ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ለመሆን በቅተዋል:: ታሪክ ጸሓፊው ታሲተስ ስለ ፊልክስ "ከባርነት ጠባዩ ሳይላቀቅ የፈላጭ ቈራጭነትን ሥልጣን የተቀዳጀ ሰው ነው" ይለዋል:: በተከታታይ ሦስት ንግሥቶች ያገባ ሲሆን፣ ከእነዚህም አንዷ ድሩሲላ ነበረች (የ24፥24 ማብ ይመ):: *የኪልቅያ ሰው፤* ጳውሎስ የመጣው ቅርብ ከሆነ አውራጃ ቢሆን ኖሮ፣ በዚያው ሄዶ እንዲዳኝ ፊልክስ አሳልፎ በሰጠው ነበር::

23፥35 *በሄሮድስ ግቢ፤* ታላቁ ሄሮድስ ለንጉሣዊ ቤተ ሰቡ መኖሪያ እንዲሆን ያሠራው ነበር፤ ኋላ ግን የመንግሥት ሥራ ማከናወኛ ግቢ፣ ወይም የንጉሡ ነገሥቱ እንደራሴ ማረፊያ ሆነ:: እንዲህ ያለው ግቢ በሮም (ፊል 1፥13)፣ በኤፌሶን፣ በኢየሩሳሌም (ዮሐ18፥28)፣ በቂሳርያ እንዲሁም በሌሎች የሮማውያን ግዛቶች ውስጥ ይገኝ ነበር::

24፥1 *ከአምስት ቀን በኋላ፤* ከኢየሩሳሌም ከወጣ በኋላ ማለት ነው:: ይህም መልእክተኛው ከቂሳርያ ተነሥቶ ኢየሩሳሌም ለመድረስ፣ የሸንጎ አባላቱ ተወካዮቻቸውን ለመምረጥ፣ የተሾሙትም ወደ ቂሳርያ ለመመለስ በቂ ጊዜ ነበር:: *ሐናንያ፤* የ23፥2 ማብ ይመ:: ሊቀ ካህናቱ ራሱ የክሱን ሁኔታ ለመከታተል ራሱ 96 ኪ.ሜ. ተጓዘ:: *ሽማግሌዎችና፤* የአይሁድ ሸንጎ ሰባ አንድ ሽማግሌዎች ያቀፈ ነበር፤ የሽማግሌዎቹም ኀላፊነት የሃይማኖትና የፖለቲካ ሸንጎዎችን ጉዳይ የሚመለከት ነበር፤ የዘፀ 3፥16፤ የ2 ሳሙ 3፥17፤ የኢል1፥2 የማቴ 15፥2 ማብ ይመ:: *ጠበቃ፤* የግሪኩ ቃል ቀጥታ ትርጉም፣ "የንግግር ችሎታ ያለው" ሰው ማለት ነው:: የፍርድ ቤት ክርክር ሲኖር፣ በንግግር ችሎታ የሠለጠነ ሰው ዐቃቤ ሕግ ሆኖ ያገለግላል:: *ጠርጠሉስ፤* ዜግነቱ ሮማዊ ቢመስልም፣ የሮምን ፍርድ ቤት ሥርዐት የሚያውቅ በግሪክ ቋንቋና ባህል የሠለጠነ አይሁዳዊ ሳይሆን አይቀርም::

24፥2-3 *ሰላም... ሰፍኖልናል... በታላቅ ምስጋና፤* በዳኛ ፊት በሚቀርብበት ጊዜ ወደ ርእሰ ጉዳዩ ከመግባቱ በፊት፣ የዳኛን ልብ ለመማረክ ከባለ ጉዳዩ የሚጠበቅ የማሞካሻ አባባል ነው:: ፊልክስ ስድስት ዓመት ሙሉ ሥልጣን ላይ በቈየበት ወቅት፣ የቀማኞችን መንጋ ደብዛ አጥፍቷል፤ የተደራጁ ነፍሰ ገዳዮችን ተቋቁሞአል፤ በአንድ ግብፃዊ የተመራውንም እንቅስቃሴ ደምስሶአል (የ21፥38 ማብ ይመ):: በጥቅሉ ሲታይ ግን አስተዳደሩ የሚመሰገን አልነበረም፤ ይህ በመሆኑም፣ የሮም መንግሥት ከሁለት ዓመት በኋላ ወደ ቀድሞ ቦታው እንዲመለስ ጠርቶታል:: ያደረገው ለውጥና መሻሻልም በታሪክ የሚታወቅ አይደለም::

24፥5 *ሁከት የሚያስነሣ...የናዝራውያን ወገን ቀንደኛ መሪ፤* ሕዝብን ማነሣሣት ቄሳርን እንደ መካድ ይቈጠራል፤ ከሮም መንግሥት ፈቃድ ሳይቀበሉ የአንድ የሃይማኖት ክፍል መሪም መሆን፣ ሕግን መዳፈር ነበር:: *የናዝራውያን ወገን፤* የክርስትናን እምነት ለማለት ነው::

24፥6 *ቤተ መቅደሱን ለማርከስ ሲሞክር፤* ቀድሞ፣ "ይህን የተቀደሰ ስፍራ የሚያረክሰውም እርሱ ነው" (21፥28 ማብ ይመ) ካሉት ይልቅ በዚህ ጊዜ ክሱ ለስለስ ብሎ ቀርቦአል::

*24፥10፤* ጳውሎስ አለሳልሶ ያቀረበው የንግግሩ መግቢያ፣ እንደ ጠርጠሉስ ንግግር ማሞካሻ አልነበረውም (ቍ 2-4)::

24፥11 *ከዐሥራ ሁለት ቀን በፊት፤* ጳውሎስ ለቀረበበት ክስ መልስ ሲሰጥ፣ ችግር ፈጣሪ አለመሆኑን፣ እጁን በዐመፅ ውስጥም አለማስገባቱን አስረግጦ ተናገረ፤ ነገሩ በእርግጥም ሲታይ፣ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው በቅርቡ ነው፤ የቈየውም በቂሳርያ አምስት ቀን በኢየሩሳሌም ደግሞ ወደ ሰባት ቀን ገደማ ነው::

24፥14 *...በጌታ መንገድ... አምላክ አመልካለሁ፤* ጳውሎስ በራሱ በኩል የጌታን መንገድ እንደሚከተል ያረጋግጣል፤ ይህም

ነዚህ ሰዎች ሁሉ፣ ጻድቃንና ኀጥአን ከሙ
ታን እንደሚነሡ በእግዚአብሔር ተስፋ አለኝ።
[16]ስለዚህ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ንጹሕ
ኅሊና እንዲኖረኝ ሁልጊዜ እጥራለሁ።
[17]"ከብዙ ዓመት በኋላም፣ ለድኻው ወገኔ
ምጽዋትና መባ ይዤ ወደ ኢየሩሳሌም
መጣሁ። [18]እነርሱም በቤተ መቅደስ የመጠ
ንጻት ሥርዐት ፈጽሜ ይህንኑ ሳደርግ አገ
ኙኝ፤ የሕዝብ ሁካታ ወይም ረብሻ አልነበ
ረም። [19]ነገር ግን ክስ ካላቸው አንተ ፊት
ቀርበው ሊከሱኝ የሚገባቸው ከእስያ አውራጃ
የመጡ አንዳንድ አይሁድ አሉ፤ [20]ወይም
በዚህ ያሉት በሸንጎው ፊት ቀርቤ በነበ
ረበት ጊዜ ያገኙብኝ ወንጀል ካለ ይናገሩ፤
[21]በመካከላቸው በቆምሁበት ጊዜ ስለሙታን
ትንሣኤ ከተናገርሁት አንድ ነገር በስተቀር
ዛሬ ተከስሼ የቀረብሁበት ሌላ ነገር የለም።
[22]ፊልክስ ግን የጌታን መንገድ በሚ
ገባ ዐውቆ ስለ ነበር፣ "የጦር አዛዡ ሉስዮስ ሲ
መጣ ለጉዳያችሁ ውሳኔ እሰጣለሁ" ብሎ ነገሩን
በቀጠሮ አሳደረው። [23]ከዚያም ለጳውሎስ መጠ
ነኛ ነጻነት እየሰጠ እንዲጠብቀው፣ ወዳጆቹም
ገብተው እንዲጠይቁት ፈቃድ እንዲሰጣቸውና
የመቶ አለቃውን አዘዘው።
[24]ከጥቂት ቀን በኋላ፣ ፊልክስ ከአይሁዳ
ዊት ሚስቱ ከድሩሲላ ጋር መጣ፤ ጳውሎስንም
አስጠርቶ በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ማመን ሲና
ገር አዳመጠው። [25]ጳውሎስ ስለ ጽድቅና ራስን
ስለ መግዛት ስለሚመጣውም ፍርድ በሚናገ
ርበት ጊዜ ግን ፊልክስ ፈርቶ፣ "ለጊዜው ይህ
ይበቃል፤ ወደ ፊት ሲመቸኝ አስጠራሃለሁ፤
አሁን ልትሄድ ትችላለህ" አለው። [26]ደግ
ሞም ከጳውሎስ ጉቦ ለመቀበል ተስፋ ያደ
ርግ ስለ ነበር፣ በየጊዜው እያስጠራ ያነጋግ
ረው ነበር።
[27]ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላም፣ ፊል
ክስ በጶርቅዮስ ፊስጦስ ተተካ፤ ፊልክስም
አይሁድን ለማስደሰት ሲል፣ ጳውሎስን እንደ
ታሰረ ተወው።

### ጳውሎስ በፊስጦስ ፊት ቀረበ

25 ፊስጦስም ወደ አውራጃው ከገባ ከሦ
ስት ቀን በኋላ፣ ከቂሳርያ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ወጣ። [2]የካህናት አለቆችና የአይሁድ
መሪዎች ፊቱ ቀርበው ጳውሎስን ከሰሱት።
[3]ጳውሎስን መንገድ ላይ አድፍጠው ሊገድ
ሉት ስለ ፈለጉ፣ ፊስጦስ ለእነርሱ እንዲያ
ዳላላቸውና ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያስመጣው
አጥብቀው ለመኑት። [4]ፊስጦስም እንዲህ ሲል
መለሰላቸው፤ "ጳውሎስ ታስሮ በቂሳርያ እስር
ቤት ይገኛል፤ እኔም በቅርቡ ወደዚያው
እሄዳለሁ፤ [5]ስለዚህ ከባለሥልጣኖቻችሁ መካ
ከል አንዳንዶች ከእኔ ጋር ይምጡና ሰውየው
ጥፋት ካለበት ክሱን በዚያው ያቅርቡ።"
[6]ከእነርሱም ጋር ስምንት ወይም ዐሥር
ቀን ያህል ከሰነበተ በኋላ፣ ወደ ቂሳርያ ወረደ፤
በማግስቱም ፍርድ ወንበር ላይ ተቀምጦ
ጳውሎስን እንዲያመጡት አዘዘ። [7]ጳውሎስ

24፥16 ሐሥ23፥1
24፥17 ሐሥ11፥29፡30፤ሮሜ15፥25-28፡31፤1ቆሮ16፥1-4፡15፤2ቆሮ8፥1-4፤ገላ2፥10
24፥18 ቊ12፤ሐሥ21፥26
24፥19 ሐሥ2፥9፤23፥30
24፥21 ሐሥ23፥6
24፥22 ሐሥ9፥2
24፥23 ሐሥ23፥16፡35፤27፥3፤28፥16
24፥24 ሐሥ20፥21
24፥25 ኤር36፥16፤ሐሥ10፥42፤ገላ5፥23፤1ተሰ5፥6፤1ጴጥ4፥7፡5፥8፤2ጴጥ1፥6
24፥27 ሐሥ12፥3፤23፥35፤25፥1፡4፡9፡14
25፥1 ሐሥ8፥40፤24፥27
25፥2 ቊ15፤ሐሥ 24፥1
25፥3 ሐሥ20፥3
25፥4 ሐሥ8፥40፤24፥23

ሆኖ እንኳ ሕግና ነቢያት ትክክል መሆናቸውን ያምናል፤ እርሱም እንደ ሌሎቹ አይሁድ ትንሣኤ ሙታንንና የመጨረሻውን ፍርድ ተስፋ ያደርጋል (ቍ 15)።

24፥16 *ንጹሕ ኅሊና*፤ የ 23፥1 ማብ ይመ።

24፥17 *ለድኻው ወገኔ ምጽዋትና... ይዤ፤* በጳውሎስ ዘንድ ትልቅ ስፍራ የተሰጠው ምጽዋት መሰብሰብ፣ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በግልጽ የተጠቀሰው እዚህ ላይ ብቻ ነው (የ20፥4 ማብ ይመ)። *መባ ይዤ፤* ጳውሎስ ስእለት ለሚያደርሱ ሰዎች ያደረገላቸውን ዕገዛ ሊያመለክት ይችላል (21፥24 ይመ)፤ ወይም ለራሱ መባ ለማቅረብ አስቦ ሊሆን ይችላል።

24፥19 ከእስያ አውራጃ የመጡ ... አይሁድ፤ 21፥27-29 ይመ። እነዚህ ከእስያ አውራጃ የመጡት አይሁድ ከኢየሩሳሌም ተከትለው አለመምጣታቸው በክሳቸው ሊገፉበት አለመፈለጋቸውን ያሳያል።

24፥21 *ስለ ሙታን ትንሣኤ፤* ጳውሎስ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያንን ሲያከራክሩበት ከነበሩት ነገሮች አንዱ እዚህ ላይ ብቅ ሲያደርገው ይታያል።

24፥22 *የጌታን መንገድ በሚገባ ዐውቆ፤* ፊልክስ ይሁዳንና ሰማርያን ስድስት ዓመት ሙሉ በገዛበት ጊዜ፣ ክርስቲያኖች የሚ ገኙበትን ቦታና እንቅስቃሴያቸውን ሳያውቅ ኖረ ማለት አይ ቻልም።

24፥23 *መጠነኛ ነጻነት እየሰጠ፤* ጳውሎስ በሮም ሆኖ ክሱን በሚጠባበቅበት ወቅት እንደ ሆነው ሁሉ (28፥30-31)፣ በዚህ ጊዜም የቁም እስረኛ ሳይሆን አልቀረም፤ ምንም ዐይነት ወንጀል ያልተገኘበት የሮም ዜጋ ነበርና።

24፥24 *ድሩሲላ፤* የቀዳማዊ አግሪጳ ልጅ የፊልክስ ሦስተኛ ሚስቱ ነበረች። በዐስራ አምስት ዓመትዋ የኢሜሳውን ንጉሥ አዚዙስን አገባች፤ ከአንድ ዓመት በኋላ ግን ኮብልላ ፊልክስን አገባች። በአያቱ ስም የተጠራው አግሪጳ የተባለው ልጇ በ79 ዓ.ም የቪሱቪስ ኩረብታ በእሳተ ገሞራ በፈነዳበት ጊዜ በዚሁ አደጋ ሞተ።

24፥25 *ፊልክስ ፈርቶ*፤ ፊልክስ ስለ ጽድቅና ራስን ስለ መግዛት እንዲሁም ስለ ፍርድ በመስማቱ የቀድሞ ሕይወቱን ዘወር ብሎ ሲመለከት ሥጋት አደረበት። የቅንነትና ስለ ሌላ ሰው የማሰብ ባሕርይም ብልጭ አለበት። *ሲመቸኝ፤* ከፉ ምኞት፣ ትዕቢት፣ ስስትና ራስ ወዳድነት ወደ አዲስ የሕይወት ምዕራፍ እንዳይገባ በመደጋገም ሲፈታተኑት ይታያል።

24፥26 *ጉቦ ለመቀበል*፤ ፊልክስ፣ ጳውሎስ የሚያ ዝበት ብዙ ገንዘብ አለ ብሎ አስቦአል፤ ጳውሎስ በቅድስት ምድር ለነበሩት አይሁድ ክርስቲያኖች መባ ሰብስቦ መምጣቱንም ሰምቶ ነበር (ቍ 17)፤ ስለዚህ ጳውሎስ ከእስር ለመፈታት ከፈለገ፣ ፊልክስ ጉቦ ሊሰጠኝ ይገባል ሲል እጅ እጁን ያይ ነበር፤ ጳውሎስ ግን ቢ ኖረውም እንኳ ጉቦ እንደማይሰጠው የታወቀ ነው።

24፥27 *ፊልክስ በጶርቅዮስ ፊስጦስ ተተካ፤* ፊልክስ በግዛቱ ስለተነሣው ዐመፅና ዐልፎ ዐልፎም ስለታየው አለመረጋጋት፣ ለምሳሌ በአይሁድና በሶርያውያን መካከል ስለ ነበረው ግጭት እንዲያስረዳ በ59 ወይም በ60 ዓ.ም. ወደ ሮም ተጠርቶ ነበር። ፊስጦስ ወደ ፓሌስቲና (ቅድስት ምድር) ከመምጣቱ በፊት፣ በየትኛውም ታሪክ ስሙ ተወሥቶ አያውቅም ነበር፤ ነገር ግን ከሁለት ዓመት በኋላ በሥራ ላይ እንዳለ መሞቱ ተመዝግቦ ይገኛል፤ ፊስጦስ በጥበብና በሐቀኝነት ረገድ ከእርሱ በፊት ከነበረው ከፊልክስ እንዲሁም ከእርሱ በኋላ ከተነሣው ከአልቢኑን እንደሚልቅ ስለ እርሱ የተጻፈው ታሪክ ያመለክታል። *አይሁድን ለማስደሰት ሲል፤* ፊልክስ በአይሁድ ዘንድ የባሰ ሁከት እንዲ ነሣሣ አልፈለገም፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በሮሙ የፍርድ ወንበር ተቀምጦ በሚያስችልበት ወቅት እንደሚያገኛቸው ያውቅ ነበ ርና። ጳውሎስን ከፈታውም ሁከቱ መነሣቱ ስለማይቀር ለፍርድ መቅረቡ የግድ ነው።

25፥1 *ከቂሳሪያ ወደ ኢየሩሳሌም፤* ዘጠና ስድስት ኪ.ሜ. ርቀት ያለው የሁለት ቀን መንገድ ነበር። ፊስጦስ የአይሁድ አስተዳደርና የአምልኮ ማእከል ወደ ሆነችው ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ቸኩሎአል።

25፥2 *የካህናት አለቆችና የአይሁድ መሪዎች*፤ የአይሁድ ሸንጎ አባላት ማለት ነው (የማር 14፥55 ማብ ይመ)።

25፥3 አድፍጠው፤ ቀደም ሲል የጳውሎስን ሕይወት ለማ ጥፋት ተማምለው የነበሩት እነዚያው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ (የ23፥12 ማብ ይመ)።

25፥6 *ፍርድ ወንበር ተቀምጦ፤* ደንቡን ተከትሎ ውሳ ኔው ሕጋዊ መልክ እንዲኖረው ለማድረግ ነው።

25፥7 በ*ማስረጃ ያልተደገፉ*፤ የጳውሎስ ከሳሾች እንደ መጀመሪያው ክስ ሁሉ፣ አሁንም አንዳች ምስክር ወይም ማስ

በቀረበ ጊዜ፣ ከኢየሩሳሌም የመጡት አይሁድ
ከበቡት፤ በማስረጃ ያልተደገፉ ብዙ ከባድ
ክሶችም አቀረቡበት።
8ጳውሎስም፣ "እኔ በአይሁድም ሕግ ሆነ
በቤተ መቅደሱ ወይም በቄሳር ላይ የፈጸምሁት
በደል የለም" ሲል የመከላከያ መልሱን ሰጠ።
9ፊስጦስም ለአይሁድ በጎ ለመዋል ፈልጎ፣
ጳውሎስን "ስለዚህ ጉዳይ ወደ ኢየሩሳሌም
ወጥተህ በእኔ ፊት ለመፋረድ ፈቃደኛ ነህን?"
አለው።
10ጳውሎስም እንዲህ አለ፤ "አሁንም ቢሆን
ፍትሕ ማግኘት በምችልበት፣ በቄሳር ፍርድ
ወንበር ፊት ቆሜአለሁ፤ አንተ ራስህ በሚ
ገባ እንደምታውቀው በአይሁድ ላይ ምንም
በደል አልፈጸምሁም፤ 11ይሁን እንጂ ለሞት
የሚያበቃ በደል ከተገኘብኝ፣ አልሙት
አልልም፤ እነዚህ አይሁድ የሚያቀርቡብኝ
ክስ እውነት ካልሆነ ግን፣ እኔን ለእነርሱ
አሳልፎ ሊሰጥ የሚችል የለም፤ ወደ ቄሳር
ይግባኝ ብያለሁ።"
12ፊስጦስ ከመማክርቱ ጋር ከተመካከረ በኋላ፣
"ወደ ቄሳር ይግባኝ ስላልህ፣ ወደ ቄሳር ትሄ
ዳለህ" አለው።

## ፊስጦስ ከንጉሥ አግሪጳ ምክር ጠየቀ

13ከጥቂት ቀንም በኋላ፣ ንጉሥ አግሪጳና
በርኒቄ ፊስጦስን እጅ ሊነሡ ወደ ቂሳርያ
ወረዱ፤ 14በዚያም ብዙ ቀን ተቀመጡ፤ ፊስ
ጦስም የጳውሎስን ጉዳይ አንሥቶ ለንጉሡ
እንዲህ አለው፤ "ፊልክስ በእስር ቤት የተ
ወው አንድ ሰው እዚህ አለ፤ 15ወደ ኢየሩሳ
ሌም በሄድሁ ጊዜ፣ የካህናት አለቆችና የአ
ይሁድ ሽማግሌዎች እንድፈርድበት ከሰ
ውት ነበር።
16"እኔም፣ ተከሳሽ በከሳሾቹ ፊት ቆሞ
ለተከሰሰበት ነገር መልስ ለመስጠት ዕድል
ሳያገኝ፣ አሳልፎ መስጠት የሮማውያን ልማድ
እንዳልሆነ ነገርኋቸው። 17ስለዚህ ከሳሾቹ
ከእኔ ጋር ወደዚህ በመጡ ጊዜ፣ ጉዳዩን
ሳላጓትት በማግስቱ ችሎት ተቀምጬ ያን
ሰው እንዲያቀርቡት አዘዝሁ። 18ከሳሾቹም
ተነሥተው በመቆም ሲናገሩ፣ እኔ ያሰብሁ
ትን ያህል ከባድ ክስ አላቀረቡበትም፤ 19ይል
ቁን ስለ ገዛ ሃይማኖታቸውና ሞቶ ስለ ነበ
ረው፣ ጳውሎስ ግን ሕያው ነው ስለሚ
ለው ሰው፣ ስለ ኢየሱስ ይከራከሩት ነበር።
20እኔም ይህን ነገር እንዴት እንደ ምፈ
ታው ግራ ስለገባኝ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ
ስለዚሁ ጉዳይ እንዲፋረድ ፈቃደኝነቱን ጠየ
ቅሁት። 21ነገር ግን ጳውሎስ ጉዳዩ በንጉሠ
ነገሥቱ እንዲታይለት ይግባኝ ባለ ጊዜ፣
እኔም ወደ ቄሳር እስከምልከው ድረስ እስር
ቤት እንዲቈይ አዘዝሁ።"
22አግሪጳም ፊስጦስን፣ "እኔም እኮ ይህ ሰው
ሲናገር መስማት እፈልግ ነበር" አለው።
እርሱም፣ "እንግዲያውስ ነገ ትሰማዋለህ"
አለው።

## ጳውሎስ በንጉሥ አግሪጳ ፊት

23በማግስቱም አግሪጳና በርኒቄ በታላቅ
ክብር መጥተው፣ ከከፍተኛ መኰንኖችና
ከከተማዪቱ ታላላቅ ሰዎች ጋር ወደ መሰ
ብሰቢያው አዳራሽ ገቡ፤ በፊስጦስም ትእ
ዛዝ ጳውሎስ እንዲቀርብ ተደረገ። 24በዚህ

25፥6 ቍ10:17
25፥7 ማር15፥3፤ ሉቃ23፥2:10፤ ሐሥ 24፥5:6:13
25፥8 ሐሥ6፥13፤ 24፥12፤28፥17
25፥9 ቍ20፤ ሐሥ 12፥3፤24፥27
25፥10 ቍ8
25፥11 ቍ21: 25፤ሐሥ26፥32፤ 28፥19
25፥13 ሐሥ8፥40
25፥14 ሐሥ24፥27
25፥15 ቍ2፤ ሐሥ 24፥1
25፥16 ቍ4:5፤ ሐሥ23፥30
25፥17 ቍ6:10
25፥19 ሐሥ17፥22፤18፥15፤23፥29
25፥20 ቍ9
25፥21 ቍ11:12
25፥22 ሐሥ9፥15
25፥23 ቍ13፤ ሐሥ 26፥30

*ረጃ ማቅረብ አልቻሉም።*

25፥8 *በ...ሕግ...የፈጸምሁት በደል የለም፤* ጳውሎስ የኦሪትን ሕግ ያከብር ነበር (ሮሜ 7፥12፤8፥3-4፤ 1ቆሮ 9፥20 ይመ)። *በቤተ መቅደሱ ... ላይ፤* የ21፥28-29 ማብ ይመ። ጳውሎስ ወደ ተከለከለው ስፍራ ጥሮፊሞስን በማስገባት ልማዳቸውን አላቃለለም (21፥29)፤ ቤተ መቅደሱ እንዳልነበር እንደሚሆንም ጌታ ኢየሱስ ትንቢት ተናግሮበታል፤ ይህ አስከፊ ሁኔታ የደረሰውም ከእነርሱ ኀጢአት የተነሣ ነበር (ሉቃ 21፥5-6)። *በቂሳርያ ላይ፤* ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች ዐወጀ እንጂ፣ የሮም መንግሥት ተቀናቃኝ አልነበረም (ከ 17፥6-7 ጋር ያነጻጽሩ)። ጳውሎስ የመንግሥት ሕግና ሥርዓት እንዲከበር (ሮም 13፥1-7)፣ ለገዦችም እንዲጸለይ (1ጢሞ 2፥2) በጥብቅ አበክሮ አሳስቦአል።

25፥9 *ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተህ...ፈቃደኛ ነህን?* ጳውሎስ ፈቃደኛ እንደማይሆን የታወቀ ነበር። ክሱ የሚቀርበው በእርሱ ፊት እንደሚሆን ፊስጦስ ተናግሮአል፤ ስለዚህ ጳውሎስ አሁን የቆመበትም የሮም መንግሥት ችሎት መሆኑን በአጽንዖት ገልጾአል (ቍ 10)። ከዚህ የተነሣም በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቀርቦ ከሚንገላታ፣ ክሱ እዚያው እንዲሆንለት ፈለገ። የሮም ዜጋ እንደ መሆኑ መጠን፣ በአውራጃ ደረጃ መዳኘት የለብኝም ማለት ይችላል፤ ከዚህ ይልቅ ወደ ከፍተኛው የሮም ፍርድ ችሎት ለመቅረብ ፈለገ።

25፥11 *ወደ ቄሳር ይግባኝ ብያለሁ፤* በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ኔሮ ነበር። የሮም ዜጋ የሆነ ሁሉ ወደ ሮም ሄዶ በቄሳር ወይም በተወካዩ ፊት ጉዳዩን የማሰማት መብት ነበረው፤ ይህም የመጨረሻው ይግባኝ ሰሚ አካል ነበር፤ በዚህ ችሎት ላይ መርታት ማለት፣ ጳውሎስ ከቀረበበት ክስ ነጻ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ክርስትናም ከአይሁድ ሃይማኖት ተለይቶ በመንግሥት ዘንድ ዕውቅናን እንዳገኘ የሚያስቈጥር ነው።

25፥12 *ከመማክርቱ፤* ሕግ ዐዋቂ የሆኑ የሮም ገዥ አማካሪዎች ናቸው።

25፥13 *ንጉሥ አግሪጳና፤* ዳግማዊ ሄሮድስ አግሪጳ ማለት ነው። አባቱ በ44 ዓ.ም ሲሞት ገና የ17 ዓመት ወጣት ነበር (12፥23)። በአባቱ ወንበር እንዳይተካ ልጅ በመሆኑ በታውን የሮም ገዦች እንዲይዙ አድርጎአል። ከስምንት ዓመት በኋላ ግን ቀስ በቀስ ሥልጣኑን እያሰፋ ሄደ፤ በመጨረሻም ከገሊላ ባሕር ሰሜንና በሰሜን ምሥራቅ ያለውን ማለት ብዙዎቹን የገሊላ ከተሞችና ከዮርዳኖስ ማዶ በጴርያ ያሉትን አንዳንድ ከተሞች ገዛ። አይሁድ ዐምፀው ኢየሩሳሌም በወደቀችበት ወቅት የሮም መንግሥት ደጋፊ ነበር። አግሪጳ የሄሮድስ ሥርወ መንግሥት የመጨረሻው ንጉሥ ሲሆን፣ በ 100 ዓ.ም ሞተ። *በርኒቄ፤* የቀዳማዊ አግሪጳ ትልቋ ሴት ልጅ ስትሆን፣ አባቷ ሲሞት የ16 ዓመት ወጣት ነበረች። ገና የ13 ዓመት ልጅ ሳለች አጎቷን የቻሲሱን ሄሮድስ አግብታ ሁለት ወንድ ልጆች ወልዳለች። ባሏ ሄሮድስ ሲሞትም ከወንድሟ ከዳግማዊ አግሪጳ ጋር ተቀመጠች። ከወንድሟ ጋር ማግጣለች የሚለውን ሐሜት ለመሸፈንም የኪልቅያውን ንጉሥ ፖሊሞንን አገባች፤ ነገር ግን እርሱንም ወዲያው ትታ ወደ አግሪጳ ቤት ተመለሰች። የንጉሠ ነገሥቱ የቬስፓስያን ልጅ፣ የቲቶ ቁባትም ሆና ነበር፤ ቈይቶ ግን እርሱም አልፈለጋትም፤ ተዋት። *እጅ ሊነሡ* የቀድሞዎቹ ገዦች ተሽረው አዲስ ገዦች ሲሾሙ፣ ደስታቸውን ለአዲሶቹ ገዦች መግለጽ የተለመደ ነበር፤ በዚህ ሁኔታ ከበሬታን መቀባበሉም ለግራ ለቀኙ የሚበጅ ነው ተብሎም ይታመናል፤ ሄሮድስ አንቲጳስ ከጲላጦስ ጋር ያደረገውን ከዚህ ሁኔታ ጋር ያነጻጽሩ፤ ሉቃ 23፥6-12።

25፥19 *ሃይማኖታቸውና፤* የ17፥22 ማብ ይመ።

25፥22 *እኔም እኮ መስማት እፈልግ ነበር፤* አግሪጳ ቀድሞውኑ ጳውሎስ የሚለውን ለመስማት ጓጉቶ ነበር፤ ሄሮድስ አንቲጳስ ኢየሱስን ለማየት ከመፈለጉ ጋር ያነጻጽሩ፤ ሉቃ 9፥9፤ 23፥8።

25፥23 *መሰብሰቢያው አዳራሽ፤* ነገሩ በችሎት የሚታይ ጉዳይ ስላልሆነ፣ ቦታው ፍርድ ቤት አልነበረም። ንጉሡና እኅቱ የሮም መንግሥት እንደራሴ እንዲሁም የታወቁ የአይሁድና የሮም መንግሥት ታዋቂ ባለሥልጣኖች በሰው ፊት አምረው ደምቀው

ጊዜ ፌስጦስ እንዲህ አለ፤ ንጉሥ “አግሪጳ ሆይ፤ እንዲሁም እዚህ አብራችሁን ያላችሁ ሁሉ፤ ይህን ሰው ታዩታላችሁ? በኢየሩሳሌምና እዚህ በቂሳርያም የሚኖሩ አይሁድ ሁሉ፣ ይህ ሰው ከእንግዲህ በሕይወት መኖር አይገባውም በማለት እየጮኹ ለመኑኝ:: [25]እኔም ለሞት የሚያበቃ አንዳች ነገር አለማድረጉን ተረዳሁ፤ ሆኖም ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ይግባኝ በማለቱ ወደ ሮም ልልከው ወሰንሁ:: [26]ነገር ግን ስለ እርሱ ወደ ጌታዬ የምጽፈው የተረጋገጠ ነገር አላገኘሁም፤ ስለዚህም ከተመረመረ በኋላ የምጽፈውን ነገር ለማግኘት ሁላችሁም ፊት በተለይ ደግሞ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፤ በአንተ ፊት አቀረብሁት፤ [27]ይኸውም አንድ እስረኛ ወደ በላይ ሲላክ የተከሰሰበትን ምክንያት አለ መግለጽ ትክክል ስላልመሰለኝ ነው::”

**26** አግሪጳም ጳውሎስን፣ “ስለ ራስህ እንድትናገር ተፈቅዶልሃል” አለው:: በዚህ ጊዜ ጳውሎስ እጁን ዘርግቶ እንዲህ ሲል መከላከያውን አቀረበ፤ [2]“ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፤ አይሁድ በእኔ ላይ ላቀረቡት ክስ ሁሉ ዛሬ በፊትህ የመከላከያ መልስ ለማቅረብ በመቻሌ ራሴን እንደ ዕድለኛ እቈጥረዋለሁ፤ [3]ይኸውም አንተ በተለይ የአይሁድን ልማድና ክርክር ሁሉ በሚገባ ስለምታውቅ ነው፤ ስለዚህ በትዕግሥት እንድታደምጠኝ እለምንሃለሁ::

[4]“ገና ከልጅነቴ ጀምሮ፣ በአገሬም ሆነ በኢየሩሳሌም እንዴት እንደኖርሁ አይሁድ ሁሉ ያውቃሉ፤ [5]ደግሞም ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ስለሚያውቁኝ ከሃይማኖታችን እጅግ ጥብቅ በሆነው ወገን ውስጥ ሆኜ እንደ አንድ ፈሪሳዊ መኖሬን ሊመሰክሩ ፈቃደኞች ከሆኑ ቃላቸውን ሊሰጡ ይችላሉ:: [6]አሁንም ተከስሼ እዚህ የቀረብሁበት ምክንያት እግዚአብሔር ለአባቶቻችን ቃል የገባውን ነገር ተስፋ በማድረጌ ነው:: [7]ዐሥራ ሁለቱ ነገዶቻችን ቀንና ሌሊት እግዚአብሔርን ከልብ እያገለገሉ፣ ሲፈጸም ለማየት የሚተጉለትም ተስፋ ይኸው ነው:: ንጉሥ ሆይ፤ አይሁድም የሚከሱኝ ስለዚሁ ተስፋ ነው:: [8]ለመሆኑ፣ እግዚአብሔር ሙታንን ማስነሣት እንደማይችል አድርጋችሁ የምትቈጥሩት ለምንድን ነው?

[9]“እኔም ራሴ የናዝሬቱን የኢየሱስን ስም በምችለው መንገድ ሁሉ መቃወም እንዳለብኝ ወስኜ ነበር:: [10]በኢየሩሳሌምም ያደረግሁት ይህንኑ ነበር፤ ከካህናት አለቆች ሥልጣን ተቀብዬ ብዙ ቅዱሳንን አሳስሬአለሁ፤ በመገደላቸውም ተስማምቻለሁ፤ [11]ላስቀጣቸውም ብዙ ጊዜ ከምኵራብ ምኵራብ እየተዘዋወርሁ፣ የስድብ ቃል እንዲናገሩ አስገድጃቸው ነበር፤ በቍጣም ተሞልቼ በውጭ አገር እስከሚገኙ ከተሞች ድረስ ተከታትዬ አሳደድኋቸው::

[12]“በዚህ መሠረት አንድ ቀን ከካህናት አለቆች ሥልጣንና ትእዛዝ ተቀብዬ ወደ ደማስቆ በምንዝበት ጊዜ፣ [13]ንጉሥ ሆይ፤ እኩለ ቀን ላይ በመንገድ ሳለሁ፣ ብሩህነቱ ከፀሓይ የሚበልጥ ብርሃን በእኔና በባልንጀሮቼ ዙሪያ ከሰማይ ሲያበራ አየሁ፤ [14]ሁላችንም በምድር ላይ ወደቅን፤ እኔም በዕብራይስጥ^ ቋንቋ፣ ‘ሳውል፤ ሳውል፤ ለምን ታሳድደኛለህ? መውጊያውን መጋፋት ጕዳቱ በአንተ ይብሳል” የሚለኝን ድምፅ ሰማሁ::

[15]“እኔም፣ ‘ጌታ ሆይ፤ አንተ ማን ነህ?’ ” አልሁ::

“ጌታም እንዲህ አለኝ፤ ‘እኔ፣ አንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ:: [16]አሁንም፣ ተነሣና በእግርህ ቁም፤ ስለ እኔ ስላየኸውና ወደ ፊትም ስለማሳይህ ነገር አገልጋይና ምስክር እንድትሆን ልሾምህ ተገልጬልሃለሁ::

^14 ወይም አራማይክ #23 ወይም መሲሕ

25፥24 ቈላ2፥3፥7፤ ሐሥ22፥22
25፥25 ቈላ11፤ ሐሥ23፥9
26፥1 ሐሥ9፥15፤ 12፥17፤25፥22
26፥2 መዝ119፥46፤ሐሥ24፥1፡5፤ 25፥2፡7፡11
26፥3 ቈላ7፤ ሐሥ 6፥14፤25፥19
26፥4 ገላ1፥13፡14፤ፊል3፥5
26፥5 ሐሥ22፥3፤ 23፥6፤24፥5፤ፊል3፥5
26፥6 ሐሥ13፥32፤ 23፥6፤24፥15፤28፥20፤ሮሜ15፥8
26፥7 ቈላ2፤ 1ተሰ3፥10፤ 1ጢሞ5፥5፤ያዕ 1፥1
26፥8 ሐሥ23፥6
26፥9 ዮሐ15፥21፤ 16፥2፤1ጢሞ1፥13
26፥10 ሐሥ8፥3፤ 9፥2፡13፡14፡21፤22፥20
26፥11 ማቴ10፥17
26፥14 ዮሐ5፥2፤ ሐሥ9፥7
26፥16 ሕዝ2፥1፤ ዳን10፥11፤ ሐሥ22፥ 14፡15

እንዲታዩ የተገኙበት ታላቅ አዳራሽ ነበር:: *ከከፍተኛ መኮንኖችና*፤ በቂሳርያ አምስት እዞች ስለ ነበሩ፣ የእዝ መሪዎቹ ሁሉ በስብሰ ባው ላይ ተገኝተው ነበር (የ 21፥31 ማብ ይመ)::

25፥26 *የተረጋገጠ ነገር አላገኘሁም*፤ ይግባኝ ከተባለ፣ ፌስጦስ ተጨባጭነት ያለው ዘገባ ለቄሳር መላክ አለበት:: ፌስጦስም አግሪጳ በዚህ ጒዳይ በሐሳብ እንዲረዳው ፈልጎ ነበር:: ይህ መደበኛ የክስ ችሎት ሳይሆን፣ የአግሪጳን ፍላጎት ለማርካትና ፌስጦስንም በሐሳብ ለመርዳት የተደረገ ግምገማ ነበር:: *ይልቁንም፣ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፤ በአንተ ፊት*፤ ፌስጦስ፣ በፈሪሳውያንና በሰዱቃውያን መካከል ስላለው ልዩነት፣ የመሲሑን መምጣት ስለ መጠባበቅ፣ በአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮችና በክርስቲያኖች መካከል ስላለው ልዩነት እንዲሁም የአይሁድ ልማድ ከእነዚህ አከራካሪ ጒዳዮች ጋር ስላለው ግንኙነት ለማወቅ ጒጒት ዐድሮበታል::

26፥1 *እንድትናገር ተፈቅዶልሃል*፤ አግሪጳ፣ ጳውሎስ እንዲናገር የፈቀደለት አግሪጳ ክሱን እንዲሰማ ፌስጦስ ኀላፊነት ስለሰጠው ነው

26፥3 *የአይሁድን ልማድና ክርክር ሁሉ በሚገባ ስለምታውቅ*፤ አግሪጳ ንጉሥ እንደ መሆኑ መጠን የቤተ መቅደሱን ንብረትና በሊቀ ካህናቱ በኩል የሚደረገውን ወጪ ይቈጣጠር ነበር፤ ሊቀ ካህናቱንም የመሾም ሥልጣን ነበረው:: የአይሁድን ሃይማኖት ጒዳይ በተመለከተም የሮም ባለ ሥልጣናት የሚያማክሩት እርሱን ነበር፤ ፌስጦስም የጳውሎስን ጒዳይ ለመመር መር አግሪጳን ያማከረበት አንዱ ምክንያት ይኸው ነው::

26፥5 *እንደ አንድ ፈሪሳዊ መኖሬን*፤ ከገላ 1፥14 ጋር ያነጻጽሩ::

26፥6 *እግዚአብሔር ቃል የገባውን ነገር ተስፋ በማድረጌ ነው*፤ ይህ ተስፋ የእግዚአብሔርን መንግሥት፣ የመሲሑን መምጣትና የሙታንን ትንሣኤ የሚጨምር ነው (ቍ 8 ይመ)::

*26፥8*፤ ጳውሎስ እስካሁን የሚናገረው ለአግሪጳ ነበር፤ እዚህ ላይ ግን በትንሣኤ ሙታን ለማያምኑት ለፌስጦስና ለጦር አዛዦቹ (የ21፥31 ማብ ይመ) እንዲሁም ለሌሎቹ ጭምር ሳይሆን አይቀርም:: አግሪጳ ሊቃነ ካህናት አድርጎ ከሾማቸው ከሰዱቃውያን ጋር የወገነ ስለ ነበር፣ የክርስቶስን ከሙታን መነሣት በአጠቃላይም ትንሣኤ ሙታንን የማይቀበል ሰው ሳይሆን አይቀርም::

26፥10 *በመገደላቸውም ተስማምቻለሁ*፤ ጳውሎስ የአይሁድ ሸንጎ አባል ነበር ማለት ሳይሆን (የ22፥20 ማብ ይመ)፤ በጒዳዩ መስማማቱን በግልጽ እንዲያሳይ ክርስቲያኖችን አሳዶ የማሰር ኀላፊነት ተሰጥቶት ነበር ለማለት ነው (ቍ 12)::

26፥11 *በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል እንዲናገሩ አስገድጃቸው ነበር*፤ ኢየሱስን እንዲረግሙ፣ እንዲሰድቡ ወይም በይፋ “ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው” ብለው እንዲናገሩና በዚሁ ምክንያት እንዲወገሩ ሳያስገድዳቸው አልቀረም:: (ማቴ 26፥63-66 ይመ)::

26፥12 *ወደ ደማስቆ በምጓዝበት ጊዜ*፤ ጳውሎስ ወደ ጌታ ስለተመለሰበት ሁኔታ እንደገና ይተርካል (9፥1-19፤ 22፥4-21 እና ማብ ይመ)::

26፥14 *ድምፅ ሰማሁ*፤ የ9፥7፤ የ22፥9 ማብ ይመ:: የመውጊያውን ብረት መቃወሙ፤ እንዲያው በከንቱ መፍጨርጨርን ለመግለጽ የሚነገር የግሪኮች ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፤ ይኸውም፣

17ከገዛ ሕዝብህና ወደ እነርሱ ከምልክህ
ከአሕዛብ አድንሃለሁ፤ 18አንተም ዐይናቸ
ውን ትከፍታለህ፤ ከጨለማ ወደ ብርሃን፣
ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር
ትመልሳቸዋለህ፤ እነርሱም የኀጢአትን ይቅ
ርታ ይቀበላሉ፤ በእኔም በማመን በተቀደ
ሱት መካከል ርስት ያገኛሉ።'
19"እንግዲህ፣ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፤ ከሰማይ
ለታየኝ ራእይ አልታዘዝ አላልሁም፤ 20ነገር
ግን በመጀመሪያ በደማስቆ ለሚኖሩ፣ ቀጥ
ሎም በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላሉት ሁሉ፣ ከዚ
ያም ለአሕዛብ፣ ንስሓ እንዲገቡና ወደ እግ
ዚአብሔር እንዲመለሱ፣ የንስሓም ፍሬ እንዲ
ያሳዩ ገልጬ ተናገርሁ። 21አይሁድም በመ
ቅደስ ይዘው ሊገድሉኝ የሞከሩት በዚሁ ምክ
ንያት ነው። 22የእግዚአብሔር ርዳታ እስከ ዛሬ
ስላልተለየኝ፣ እነሆ፤ እዚህ ቆሜ ለትንሹም
ለትልቁም እመሰክራለሁ፤ ነቢያትና ሙሴ
ይሆናል ይፈጸማል ካሉት በስተቀር አንዳች
ነገር አልተናገርሁም፤ 23ይኸውም ክርስቶስ[a]
መከራን እንደሚቀበልና ከሙታን ቀዳሚ ሆኖ
በመነሣት ለሕዝቡና ለአሕዛብ ብርሃንን
እንደሚሰብክ ነው።"
24ፊስጦስም የጳውሎስን ንግግር እዚህ ላይ
በማቋረጥ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ "ጳውሎስ
ሆይ፤ አእምሮህን ስተሃል፤ የትምህርትህም
ብዛት አሳብዶሃል" አለው።
25ጳውሎስ ግን እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ክቡር
ፊስጦስ ሆይ፤ የምናገረው እውነተኛና ትክ
ክለኛ ነገር እንጂ እብድስ አይደለሁም። 26ይህን
የምናገረውን ነገር ንጉሡ ያውቀዋልና፤ በፊቱ
በልበ ሙሉነት እናገራለሁ፤ ደግሞም በድ
ብቅ የተደረገ ነገር ባለመኖሩ፣ ከዚህ ነገር

26፥17 ኤር1፥8፡ 19፤ሐሥ9፥15፤ 13፥46
26፥18 መዝ18፥ 28፤ኢሳ35፥5፤42፥7፡ 16፤ሉቃ24፥47፤ሐሥ 2፥38፤20፥21፤ ኤፌ5፥ 8፤ቈላ1፥13፤1ጴጥ2፥9
26፥19 ኢሳ50፥5
26፥20 ኤር18፥ 11፤35፥15፤ማቴ 3፥8፤ሉቃ3፥8፤ ሐሥ 3፥19፤ 9፥15፡19-25፡ 26-29፤13፥46፤ 22፥17-20
26፥21 ሐሥ21፥ 27፡30፡31
26፥22 ሉቃ24፥27፡ 44፤ሐሥ10፥43፤24፥14
26፥23 ማቴ16፥ 21፤ሉቃ2፥32፤1ቆሮ 15፥20፡23፤ቈላ1፥18፤ ራእ1፥5
26፥24 ዮሐ7፥15፤ 10፥20፤1ቆሮ4፥10
26፥25 ሐሥ23፥26
26፥26 ቍ3
26፥28 ሐሥ11፥26
26፥29 ሐሥ21፥33
26፥30 ሐሥ25፥23
26፥31 ሐሥ23፥9
26፥32 ሐሥ25፥ 11፤28፥18
27፥1 ሐሥ10፥1፤ 16፥10፤18፥2፤25፥12፡25
27፥2 ሐሥ2፥9፤ 16፥9፤17፥1፤19፥29
27፥3 ቍ43፤ ማቴ11፥21፤ ሐሥ 24፥23፤28፥16
27፥4 ቍ7

አንድም እንደማይሰወርበት እርግጠኛ ነኝ።
27ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፤ ነቢያትን ታምን የለም
ወይ? አዎን፤ እንደምታምን ዐውቃለሁ።"
28አግሪጳም ጳውሎስን፣ "እንዲህ በቀላሉ
ክርስቲያን የምታደርገኝ ይመስልሃልን?"
አለው።
29ጳውሎስም፣ "በቀላሉም ሆነ በብዙ፣ አንተ
ብቻ ሳትሆን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ፣ ከዚህ ከታ
ሰርሁበት ሰንሰለት በስተቀር፣ እንደ እኔ ይሆኑ
ዘንድ እግዚአብሔርን እለምናለሁ" አለ።
30ከዚህ በኋላ ንጉሡም፣ አገረ ገዡም፣
በርኒቄም፣ ከእነርሱ ጋር የተቀመጡትም
ተነሡ፤ 31ወጥተውም ሲሄዱ፣ "ይህ ሰው እን
ኳን ለሞት ለእስራት የሚያበቃው ነገር
አላደረገም" ተባባሉ።
32አግሪጳም ፊስጦስን፣ "ይህ ሰው ወደ ቄሳር
ይግባኝ ባይል ኖሮ መልቀቅ ይቻል ነበር"
አለው።

## ጳውሎስ በመርከብ ወደ ሮም ተወሰደ

27 ወደ ኢጣሊያ እንድንሄድ በተወሰነ
ጊዜ፣ ጳውሎስንና ሌሎቹን እስረ
ኞች የንጉሠ ነገሥቱ ክፍለ ጦር አባል
ለሆነው፣ ዩልዮስ ለተባለ የመቶ አለቃ አስ
ረከቧቸው። 2ከአድራሚጢስ ተነሥቶ በእስያ
አውራጃ ባሕር ዳርቻ ላይ ወዳሉት ወደቦች
በሚሄደው መርከብ ተሳፍረን የባሕር ጕዞ
ጀመርን፤ በተሰሎንቄ ይኖር የነበረው የመ
ቄዶንያ ሰው፣ አርስጥሮኮስም ከእኛ ጋር ነበረ።
3በሚቀጥለው ቀን ሲዶና ደረስን፤ ዩልዮ
ስም ለጳውሎስ ደግነት በማሳየት ወደ ወዳ
ጆቹ ሄዶ ርዳታ እንዲቀበል ፈቀደለት።
4ከዚያም ተነሥተን በባሕር ተጓዝን፤ ነፋስ

---

'በቅሎ ገመዷን ብትበጥስ ለራሷ አሳጠረች' እንደሚባለው ማለት ነው።

26፥17 *ወደ እነርሱ፤* ወደ አይሁድ ብቻ ሳይሆን፣ ወደ አሕዛብም ጭምር ነው (22፥21፤ገላ 1፥15-16 ይመ)፤ ተልእኮውም ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው (ገላ 1፥1)።

26፥18 *ከጨለማ ወደ ብርሃን፤* በተለይ የጳውሎስን ሕይወት የሚገልጽ አነጋገር ነው (ሮሜ13፥12፤ 2ቆሮ 4፥6፤ ኤፌ 5፥8-14፤ ቈላ 1፥13፤ 1ተሰ 5፥5 ይመ)። *በተቀደሱት፤* የ20፥32፤ የ1ቆሮ 1፥2 ማብ ይመ።

26፥22 *ነቢያትና ሙሴ፤* የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ማለት ነው (ሉቃ 24፥27፡44)።

26፥23 *ከሙታን ቀዳሚ ሆኖ በመነሣት፤* ክርስቶስ ከሙታን ለሚነሡት በኵር ነው፤ ከእንግዲህም ሞትን አያይም (1ቆሮ 15፥20፤ ቈላ 1፥18 ይመ)። *ለአሕዛብ፤* ከኢሳ 49፥ 6 ጋር ያነጻጽሩ።

26፥24 *አእምሮህን ስተሃል፤* ዮሐ 10፥20፤ 1ቆሮ 14፥23 ይመ። ፊስጦስም፣ ጳውሎስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከመማሩና ከማንበቡ ብዛት የተነሣ ስለ ትንቢትና ስለ ትንሣኤ ከተዛባ ግንዛቤ ላይ የደረሰ መሰለው።

26፥26 *በድብቅ የተደረገ ነገር ባለመኖሩ፤* ይህ ጳውሎስ የሚሰብከው ወንጌል በታሪክ ውስጥ በታወቀ ቦታና ጊዜ በተፈጸመ እውነተኛ ድርጊት ላይ የተመሠረተ ነው። ንጉሡም ቢሆን፣ ጳውሎስ ስለሚናገረው እውነት ራሱ ሊመሰክርና ሊያረጋግጥ የሚገባው ነገር ነው።

26፥27 *ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፤ ነቢያትን ታምን የለም ወይ?* "አዎን" የሚል መልስ ቢሰጥ፣ ትንቢቶቹ በክርስቶስ የተፈጸሙ መሆናቸውን እንዲቀበል ጳውሎስ የሚገፋፋው ሆነ፤ የለም፣ "አላምንም" ቢል ደግሞ፣ የነቢያት ቃል ከእግዚአብሔር አፍ የወጣ መሆኑን ከሚያምኑት አይሁድ ዘንድ ችግር ሊገጥመው ሆነ፤ ስለዚህ ንጉሡ የሚመልሰውን አጥቶ በመኻል ቤት ዋለለ።

26፥28 *እንዲህ በቀላሉ ክርስቲያን የምታደርገኝ ይመስልሃልን?* በጥያቄ መልክ የሰጠው መልስ፣ በቀጥታ መልስ ለመስጠት አለመፈለጉንና ጳውሎስ ቀጥሎ ይጠይቃል ብሎ ላሰበው ጥያቄ አስቀድሞ መልስ መስጠቱ ነበር። ዞሮ ዞሮ ግን የአግሪጳ ሐሳብ ጳውሎስ በዚያች አጭር ንግግሩ ሊያግባባው እንደማይችል ለመግለጽ ነው።

26፥29 *ከዚህ ከታሰርኩበት ሰንሰለት፤* ጳውሎስ አሁንም እጁን በሰንሰለት እንደታሰረ ነበር።

27፥1 *እንድንሄድ፤* "እኛ" የሚለው ትረካ (የ16፥10 ማብ ይመ) እዚህ ላይ እንደ ገና ይጀምራል፤ "እኛ" በማለት የሚጀምረው ትረካ ከዚህ ቀደም ሲል ቀርቦ የምናገኘው በ21፥18 ላይ ነው። ጳውሎስ በቂሳርያ ታስሮ በነበረበት ጊዜ፣ ሉቃስ ሁለቱንም ዓመት በዚያው አቅራቢያ ሳይቈይ አልቀረም፤ አሁን ደግሞ ለጕዞ ከተነሡት ጋር አብሮ ለመሄድ ሲዘጋጅ እናገኘዋለን። *ዩልዮስ ለተባለ የመቶ አለቃ፤* ወይም እስከዚህ የሚታወቅ ሰው አይደለም። የቤተ መንግሥት መልእክተኛ ሆኖ ከሥራዎቹ አንዱ እስረኞችን ወደ ፍርድ አደባባይ ማድረስ ሳይሆን አይቀርም። *የንጉሠ ነገሥቱ ክፍለ ጦር፤* የሮም ጦር ሰራዊት በቍጥር ተለይቶ የሚመደብ ነበር፤ እያንዳንዱም ክፍለ ጦር መለያ ስም ነበረው (የ10፥1 ማብ ይመ)።

27፥2 *ከአድራሚጢስ፤* በእስያ አውራጃ ምዕራብ ጠረፍ ላይ ከጢሮአዳ በደቡብ ምሥራቅ በኩል ከአሶን በስተ ምሥራቅ የምትገኝ ወደብ ነበረች። ባሕር ዳርቻ ላይ ወዳሉት ወደቦች፤ ከእነዚህ ወደ አንዱ በደረሱ ጊዜ፣ ዩልዮስ ወደ ሮም በሚሄደው መርከብ ለመሳፈር ሳያቅድ አይቀርም (ቍ6)። *አርስጥሮኮስም፤* 19፥29፤ 20፥4 እንዲሁም ፊል 24 እና ቈላ 4፥10 ይመ፤ ከጳውሎስ ጋር ሮም እንደ ነበር እነዚህ ጥቅሶች ያመለክታሉ።

27፥3 *ሲዶና፤* ከቂሳርያ በስተ ሰሜን 112 ኪ.ሜ. ርቃ የምትገኝ ከተማ ነበረች።

27፥4 *የቆጵሮስን ደሴት ተገን አድርገን፤* የደሴቲቱን ተገን ለማግኘት ስለፈለጉ ከደሴቷ በስተ ምሥራቅ በኩል አድር

ከፊት ለፊት ስለገጠመን፣ የቆጵሮስን ደሴት
ተገን አድርገን ፀለፍን። 5በኪልቅያና በጵን
ፍልያ ዳርቻ ያለውን ባሕር ከተሻገርን በኋላ
በሉቅያ አገር ሙራ የተባለ ቦታ ደረስን።
6ከዚያም የመቶ አለቃው ወደ ኢጣሊያ
የሚሄድ የእስክንድርያ መርከብ አግኝቶ
አሳፈረን። 7ብዙ ቀን በዝግታ እየተጓዝን
ቀኒዶስ አካባቢ በጭንቅ ደረስን፤ ነፋሱም
ወደ ፊት እንዳንሄድ በከለከለን ጊዜ፣ በሰል
ሙና አጠገብ አድርገን በቀርጤስ ተተግነን
ሄድን፤ 8ጥግ ጥጉንም ይዘን፣ በላሲያ ከተማ
አጠገብ ወዳለው፣ 'መልካም ወደብ' ወደ
ተባለ ስፍራ በጭንቅ ደረስን።
9ብዙ ጊዜ ባክኖ፤ የጾሙ ጊዜ ስላለፈ*
በመርከብ መጓዙ አደገኛ ሆኖ ነበርና ጳው
ሎስ፣ 10"እናንት ሰዎች፤ ጉዞው አደገኛ እን
ደሚሆን፣ በመርከቡና በጭነቱ እንዲሁም
በእኛ በራሳችን ላይ እንኳ ትልቅ ጉዳት
እንደሚደርስ ይታየኛል" ብሎ አስጠነቀ
ቃቸው። 11የመቶ አለቃው ግን ከጳውሎስ
ምክር ይልቅ የመርከቡ መሪና የመርከቡ
ባለቤት ያሉትን ይሰማ ነበር። 12ክረምቱንም
በዚያ ለማሳለፍ ወደቡ አመቺ ስላ ልነበረ፣
አብዛኞዎቹ ፍንቄ ወደተባለው ወደብ
ደርሰው በዚያ ለመክረም ተስፋ በማ ድረግ
ጉዞአችንን እንድንቀጥል ውሳኔ አስ
ተላለፉ፤ ወደቡም በቀርጤስ ደቡብ ምዕራ
ብና ሰሜን ምዕራብ ትይዩ የሚገኝ ነበር።

### የባሕሩ ማዕበል

13መጠነኛ የደቡብ ነፋስ በነፈሰ ጊዜም
እንዳሰቡት የሆነላቸው መስሎአቸው መልሕ
ቁን ነቅለው፣ የቀርጤስን ዳርቻ በመያዝ

27፥5 ሐሥ2፥10፤ 6፥9
27፥6 ቁ1፤ሐሥ 18፥2፤25፥12፡25፤28፥11
27፥7 ቁ4:12፡ 13:21፤ቲቶ1፥5
27፥9 ዘሌ16፥29-31፤23፥27-29፤ ዘኍ29፥7
27፥10 ቁ21
27፥12 ቁ7

*9 የሰርየትን ዕለት ያሳያል።

ገው ወደ ሰሜን ከዚያም በሰሜን በኩል አድርገው ወደ ምዕራብ ተጓዙ። *ነፋስ ከፊት ለፊት ስለ ገጠመን፤* አካባቢው በበጋ ወራት ከበስተ ምዕራብ የሚመጣ ኀይለኛ ነፋስ ነበር።

27፥5 *በኪልቅያና በጵንፍልያ* በትንሿ እስያ ደቡብ የባሕር ዳርቻ ላይ ወሰንተኛ አውራጃዎች ነበሩ። ከሲዶና ተነሥቶ በዚህ ጠረፍ ወደ ሙራ ለመድረስ ከፀሥር እስከ ዐሥራ አምስት ቀን ይፈጅ ነበር። *በሉቅያ አገር ሙራ፤* የሙራ ከተማ ማደግ፣ ከባሕር ጉዞው እየተለመደ መምጣት ጋር የተያያዘ ነበር። ብዙ መርከቦች በጠረፉ ላይ ያሉትን ከተሞች ጥግ ከዳር እስከ ዳር በማዳረስ ፈንታ፣ በግብጽ ከምትገኘው ከእስክንድርያ ተነስተው በትንሿ እስያ ወደ ምትገኘው ወደ ሙራና ወደ መሳሰሉት ወደቦች በቀጥታ ይጓዙ ነበር። ይህ የጉዞ አቅጣጫ ዙሪያ ጥምጥም ቢሆንም እንኳ፣ ከበስተ ምዕራብ ከሚመጣው ኀይለኛ ነፋስ የተነሣ ከግብጽ ወደ ሮም ለመጓዝ ችግር ነበረበት። ስለዚህ ሙራ የእህል ማከማቻ ከተማ ሆነች።

27፥6 *የእስክንድርያ መርከብ፤* ከግብፅ ወደ ሮም እህል የምትጭን (ቍ 38) መርከብ ነበረች። ጳውሎስና ሌሎቹ በመጡበት መርከብ ወደ መቄዶንያ ጠረፍ በመቀጠል፣ የየብሱን መንገድ በመያዝ በ"ኢግናሽያን ጎዳና" አድርገው ግሪክን በማቋረጥ ሮም መግባት ይችሉ ነበር፤ ይህም በብሩንዲዝየም ወደብ በኩል ኢጣልያ ደረሱ ማለት ነው። ነገር ግን ዩልዮስ በቀጥታ ወደ ሮም የሚሄድ መርከብ ስላጋጠመው ይህን መረጠ። አንዳንዶች እንደ ሚሉት፣ ከመቄዶንያ የመጣው አርስጥሮኮስ ከመጡበት መርከብ ሳይወርድ፣ ጳውሎስ በእስር ወደ ሮም እንደሚመጣ ለመንገር ወደ አገሩ ሄደ፤ በኋላም እንደተባለው ከሆነም፣ ከጳውሎስ ጋር ተገናኝቶአል (የቍ 2 ማብ ይመ)።


27፥7 *ቀኒዶስ፤* ከሙራ በትንሿ እስያ ደቡብ ምሥራቅ ጠርዝ ላይ እስከምትገኘው፣ እስከ ቀኒዶስ፣ 272 ኪ.ሜ ያህል ርቀት አለ፤ ይህ ደግሞ ከዐሥር እስከ ዐሥራ አምስት ቀን የሚፈጅ ሌላ ተጨማሪ ጉዞ ሳይሆን አይቀርም። *በቀርጤስ፤* 256 ኪ.ሜ ርዝመት ያላት ደሴት ናት። መርከቢቱ የተንጣለለውን ባሕር አቋርጣ ወደ ግሪክ በመጓዝ ፈንታ፣ ወደ ደቡብ ማቅናት ግድ ሆነባት፤ ይኸውም የቀርጤስን ደሴት ተገን በመፈለግ ነበር። *በሰልሙና፤* በሰሜን ምሥራቅ ቀርጤስ ጫፍ ላይ የምትገኝ ልሳነ ምድር ናት።

27፥8 *በላሲያ ...'መልካም ወደብ'፤* ላሲያ፣ 'መልካም ወደብ' ከተባለችው ቦታ 8 ኪ.ሜ ያህል ርቃ የምትገኝ ከተማ ነበረች፤ 'መልካም ወደብ' የተባለችውም በቀርጤስ ደሴት ደቡብ ዳርቻ፣ ላይ ከአንዱ የደሴቲቱ ጫፍ እስከ ሌላው ባለው ርቀት መሐል ቦታ ላይ የምትገኝ ወደብ ነበረች።

27፥9 *የጾሙ ጊዜ፤* የአይሁድ የማስተስረያ ቀን የሚውለው በመስከረም ወር መጨረሻ ገደማ ላይ ነው። በአይሁድ ስሌት መሠረት የባሕር ላይ ጉዞ የሚፈቀደው ከበዓለ አምሳ በዓል (ግንቦት ወይም ሰኔ) ጀምሮ እስከ ዳስ በዓል (ጥቅምት መጀመሪያ) ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፤ የዳስ በዓል የሚውለውም ከጾሙ ዕለት በአምስተኛው ቀን ነው። ሮማውያን ከመስከረም 4 ወይም 5 በኋላ የባሕር ላይ ጉዞ አሥጊ ነው ሲሉ፣ ከኅዳር 11 በኋላ መጓዝ ግን በዝእጅ ታንቆ እንደ መሞት ይቈጠራል ይላሉ።

27፥12 *ፍንቄ፤* ከማዕበል የሚከልል ወደብ ያላት ትልቅ ከተማ ስትሆን፣ ክረምቱን በዚያ ለማሳለፍ ምቹ ነበረች።

27፥14 *'ሰሜናዊ ምሥራቅ'፤* መርከቢቱ አቅጣጫዋን እን ድትቀይር ያደረገ ሞገደኛ ዐውሎ ነፋስ ሲሆን፣ በዚያ ጊዜ 'አው



ተጓዙ:: 14ብዙም ሳይቈይ ግን፣ 'ሰሜናዊ
ምሥራቅ' የሚሉት ኀይለኛ ዐውሎ ነፋስ
ከደሴቲቱ ተነሥቶ ቍልቍል መጣባቸው::
15መርከቢቱም በማዕበሉ ስለ ተያዘች፣ ወደ
ነፋሱ ልትገፋ አልቻለችም፤ ስለዚህ መን
ገድ ለቀን በነፋሱ ተነዳን:: 16ቄዳ የተባለ
ችውን ትንሽ ደሴት ተገን አድርገን በማ
ለፍ፣ የመርከቧን ሕይወት አድን ጀልባ
በብዙ ድካም ለማትረፍ ቻልን፤ 17ጀልባዋ
ንም ወደ ላይ ጐትተው ካወጧት በኋላ
መርከቧ እንዳትፈራርስ ዙሪያዋን በገመድ ጠም
ጥመው አሰሯት፤ ስርቲስ ከተባለው አሸዋማ
ደለል ጋር ሄደው እንዳይላተሙ ስለ ፈሩም፣
የመርከቧን ሸራ አውርደው እንዲሁ በዘፈ
ቀደ እንድትነዳ አደረጉ:: 18ማዕበሉም ክፉኛ
ስላንገላታን፣ በማግስቱ ጭነቱን እያነሡ
ወደ ባሕር ይጥሉ ጀመር፤ 19በሦስተኛውም
ቀን፣ የመርከቧን ሸራ ማውጫና ማውረጃ
መሣሪያ በገዛ እጃቸው ነቃቅለው ወደ ባሕር
ጣሉት:: 20ብዙ ቀን፣ ፀሓይንም ከዋክብት
ንም ማየት ስላልተቻለና ነፋስ ስለ በረታ
ብን፣ ለመትረፍ የነበረን ተስፋ ሁሉ ተሟጠጠ::
21ሰዎቹ እህል ሳይቀምሱ ብዙ ቀን ከቈዩ
በኋላ፣ ጳውሎስ በመካከላቸው ቆሞ እንዲህ
አለ፤ "እናንት ሰዎች ሆይ፤ የነገርኋችሁን
ሰምታችሁኝ ቢሆን ኖሮ፣ ከቀርጤስ ባልተነ
ሣችሁና ይህ ጕዳትና ጥፋት ባልደረሰባችሁ
ነበር:: 22አሁንም ቢሆን አይዟችሁ! መርከቧ
እንጂ ከእናንተ አንዲት ነፍስ እንኳ አትጠ
ፋምና:: 23በትላንትናዋ ሌሊት፣ የእርሱ
የሆንሁትና የማመልከው እግዚአብሔር የላከው
መልአክ በአጠገቤ ቆሞ፣ 24'ጳውሎስ ሆይ፤
አትፍራ፤ በቄሳር ፊት መቆም ይገባሃል፤
ከአንተ ጋር የሚጓዙትንም ሰዎች ሕይወት
እግዚአብሔር አትርፎልሃል' አለኝ:: 25ስለዚህ፣
እናንት ሰዎች ሆይ፤ አይዞአችሁ! እርሱ እንደ
ነገረኝ እንደዚያው እንደሚሆን በእግዚአብሔር
አምናለሁና:: 26ይሁን እንጂ፣ ወደ አንዲት
ደሴት በነፋስ ተወስደን እዚያ መጣላችን
አይቀርም::"

## በመርከቡ አደጋ መድረሱ

27በዐሥራ አራተኛው ሌሊት በአድርያ[በ]
ባሕር ላይ ከወዲያ ወዲህ ስንገላታ፣ እኩለ
ሌሊት ገደማ መርከበኞቹ ወደ መሬት
የተቃረቡ መሰላቸው፤ 28የጥልቀት መለኪ
ያውን ገመድ ወደ ታች ጥለው ሲመለከቱት
የውሃው ጥልቀት አርባ ሜትር ያህል ሆኖ
አገኙት፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ደግመው
ሲጥሉ ጥልቀቱ፣ ሠላሳ ሜትር ያህል ሆነ::
29ከቋጥኞቹም ጋር እንዳንላተም በመፍራት፣
አራት መልሕቆች ከመርከቡ በስተኋላ ጣሉ፤
ምነው በነጋ እያሉም ይለምኑ ነበር:: 30መርከ
በኞቹም ከመርከቡ በስተ ፊት መልሕቅ
የሚጥሉ መስለው፣ ትንሿን ጀልባ በማው
ረድ ከመርከቧ ሊያመልጡ ሞከሩ:: 31ጳው
ሎስም የመቶ አለቃውንና ወታደሮቹን፣
"እነዚህ ሰዎች መርከቡ ላይ ካልቈዩ እናንተም
ልትተርፉ አትችሉም" አላቸው:: 32በዚህ ጊዜ
ወታደሮቹ ገመዶቹን ቈርጠው ትንሿ ጀልባ
ባሕሩ ላይ ተንሳፋ እንድትቀር ለቀቋት::
33ልክ ሊነጋጋ ሲል፣ ጳውሎስ ሁሉም
ምግብ እንዲበሉ እንዲህ ሲል ለመናቸው፤
"ዐሥራ አራት ቀን ሙሉ ልባችሁ ተንጠል
ጥሎ ምንም ሳትቀምሱ ጦማችሁን ሰነበታ
ችሁ፤ 34ስለዚህ ስለሚያበረታችሁ አሁን እህል
እንድትቀምሱ እለምናችኋለሁ፤ ከእናንተ
መካከል ከራሱ ጠጕር አንዲት እንኳ የሚነ
ካበት ማንም የለምና::" 35ይህን ካለ በኋላም፣
እንጀራ ይዞ በሁሉም ፊት እግዚአብሔርን አመ
ሰገነ፤ ቈርሶም ይበላ ጀመር:: 36ሁሉም ተበ

[27በ] በጥንት ጊዜ ይህ ስም ሰፊውን የኢጣሊያ ደቡባዊ ክፍል ያመለክታል::

27፥14 ማር4፥37
27፥16 ቍ30
27፥17 ቍ26:39
27፥18 ቍ19:38፤ ዮና1፥5
27፥21 ቍ7:10
27፥22 ቍ25:36
27፥23 ሐሥ5፥19፤ 18፥9፤23፥11፤ሮሜ 1፥9፤2ጢሞ4፥17
27፥24 ቍ44፤ ሐሥ 23፥11
27፥25 ቍ22:36፤ ሮሜ4፥20:21
27፥26 ቍ17:39፤ ሐሥ28፥1
27፥30 ቍ16
27፥31 ቍ24
27፥34 ማቴ10፥30
27፥35 ማቴ14፥19
27፥36 ቍ22:25

ራቂስ' በመባል ይታወቅ ነበር::

27፥16 *ቄዳ፤* ከቀርጤስ 38 ኪ.ሜ ያህል ርቃ የምትገኝ ደሴት ነች፤ በዚህ ጊዜ ማዕበሉን ለመከላከል ጥሩ ተገን ሆና ነበር:: *የመርከቧን ሕይወት አድን ጀልባ ... ለመቈጣጠር፤* ከመርከቧ ኋላ የታሰረችው ትንሽ ጀልባ፣ ባሕሩን ለመቅዘፍና ፍጥነት ለመጨመር አላመች አለች:: ከማዕበሉና ከነፋሱ ጽናት የተነሣም ከመርከቡ ጋር ተላትማ ጕዳት ሳይደርስባት አልቀረም፤ በዚህም ምክንያት በመርከቡ ላይ እንድትጫን ግዴታ ሆነ (ቍ 17)::

27፥17 *በገመድ ጠምጥመው...፤* መርከቧ በማዕበሉ እንዳትፈራርስ መስቀለኛ ሳትታሰር አልቀረችም:: *ስርቲስ፤* በሰሜን አፍሪካ፣ በቱኒስያና በትሪፖሊ ትይዩ ረዘም ያለ፣ ደለልና የሚያሰምጥ የአሸዋ ቀልል ያለበት ባዶ ምድር በባሕሩ ውስጥ ነበረ:: ያለበት ቦታ እጅግ ሩቅ ቢሆንም፣ ይህ ሞገድ የሚንጣት መርከብ ረጅም ርቀት ድረስ ትነዳለች ብለው ፈርተው ነበር:: *ሸራ፤* ሸራውን ማውረዳቸው ከስርቲስ የአሸዋ ቀልል ጋር እንዳትላተም ፈርተው ያደረጉት ይመስላል::

27፥18 *ጭነቱን እያነሡ ወደ ባሕር ይጥሉ ጀመር፤* የመርከቧን ክብደት ለማቃለል ነበር፤ ይሁን እንጂ ቍጥራቸው መጠነኛ የሆነ የእህል ጆንያዎች አስቀርተው ነበር (ቍ 38 ይመ)::

27፥19 *የመርከቧን ሸራ ማውጫና ማውረጃ መሣሪያ፤* ይህም ሸራው የሚሰቀልበትን ምሰሶ፣ ጣውላዎችንና የሸራውን መወጠሪያዎች ይጨምራል፤ አንዳንድ ጊዜ እነዚሁ ዕቃዎች መርከቡን ለመግታት ከበስተ ኋላው ይጎተቱ ነበር::

27፥21 *የነገርኋችሁን ሰምታችሁኝ ቢሆን ኖሮ፤* ቀደም ሲል ምክሩን አልተቀበሉትም ነበር፤ ይሁን እንጂ ጳውሎስ ለሁሉም የሚሆን የምሥራች ይዞላቸው ቀርቦአል (ቍ 22-26)::

27፥27 *በዐሥራ አራተኛው ሌሊት፤* 'መልካም ወደብ' ከተባለችው ቦታ ከተነሡ ጀምሮ ማለትነው:: *በአድርያ ባሕር፤* በኢጣሊያ፣ በመላጥያ፣ በቀርጤስና በግሪክ መካከል የሚገኝ ባሕር ነው:: ጥንት፣ የአድርያ ባሕር ስፋት ከዚህም ይበልጥ ነበር::...*መሰላቸው፤* የባሕሩ ሞገድ ከየብሱ ጠረፍ ጋር ሲጋጭ የሚሰጠውን ድምፅ በመስማት ሊሆን ይችላል::

27፥28 *መለኪያውን ገመድ ወደ ታች ጥለው ሲመለከቱት፤* ከጫፉ ላይ ክብደት ያለው ነገር የታሰረበትን ገመድ ወደ ባሕር በመጣል፣ የባሕሩን ጥልቀት ለኩ::

27፥30 *ሊያመልጡ ሞከሩ፤* መርከቧ ማረፊያ ካላገኘች፣ መርከበኞቹ ሕይወታቸውን ለማትረፍ የተሻለው አማራጭ ተስፋ፣ አያሌ ተጓዥ ከተጫናነቀበት ከዋናው መርከብ ይልቅ በሕይወት አድን ጀልባ ማምለጡ እንደሆነ ተገነዘቡ::

27፥31 *እነዚህ ሰዎች መርከቡ ላይ ካልቈዩ፤* መርከበኞቹ ራሳቸውን ለማዳን ሲሉ መርከቧን ጥለው ቢያመልጡ ኖሮ፣ ሌሎቹ ተጓገዦች በሚቀጥለው ቀን መርከቧን ቀዝፈው ዳር ለማድረስ ባልቻሉ ነበር::

27፥33 *ምንም ሳትቀምሱ፤* ማዕበሉ ከተነሣ ጀምሮ፣ ለተጓዦቹ ምግብ አልታደለም፤ እህል ውሃም የቀመሰ አልነበረም::

27፥35 *እንጀራ ይዞ ... አመሰገነ፤* ጳውሎስ በአርአያነቱ ሁለት ነገሮችን አሳይቶአል፤ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረበ፤ ብርታት እንዲሰጠው ምግብ በላ:: ከምግብ በፊት ምስጋና ማቅረብም በእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ የተለመደ ሥርዐት ነበር (ሉቃ 9፥16፤ 24፥30፤ 1ጢሞ 4፥4-5 ይመ)::

27፥37 *በመርከቡም ላይ በአጠቃላይ ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ሰዎች ነበርን፤* ምግቡ በትክክል እንዲዳረስ ለመዘጋጀት

ራቱና እንጀራውን ራሳቸው ወስደው በሉ::
[37]በመርከቡም ላይ በአጠቃላይ ሁለት መቶ
ሰባ ስድስት ሰዎች ነበርን:: [38]በልተውም
ከጠገቡ በኋላ ስንዴውን ወደ ባሕር በመ
ጣል የመርከቡን ክብደት አቃለሉ::
[39]በነጋም ጊዜ፣ ወደ የብስ መቅረባቸውን
አላወቁም ነበር፤ ነገር ግን ዳር ዳሩ አሸዋማ
የሆነ የባሕር ሰርጥ አይተው፣ ቢቻላቸው
መርከቡን ገፍተው ወደዚያ ለማድረስ ወሰኑ::
[40]ከዚያም መልሕቆቹን ቈርጠው ባሕር ውስጥ
ጥለው ሄዱ፤ የመቅዘፊያውንም ገመድ በዚያው
ጊዜ ፈቱ፤ የፊተኛውንም ሸራ ለነፋስ ክፍ አድ
ርገው ወደ ባሕሩ ዳርቻ አቀኑ:: [41]ነገር ግን
መርከቡ ከአሸዋ ቍልል ጋር ተላትሞ፤ መሬት
ነካ፤ የፊተኛው ክፍሉም አሸዋው ውስጥ
ተቀርቅሮ አልነቃነቅ አለ፤ የኋለኛው ክፍ
ሉም በማዕበሉ ክፉኛ ስለ ተመታ ይሰ
ባበር ጀመር::
[42]ወታደሮቹም ከእስረኞች ማንም ዋኝቶ
ለማምለጥ ቢሞክር ለመግደል ተስማሙ::
[43]የመቶ አለቃው ግን ጳውሎስ እንዲተርፍ
ስለ ፈለገ፣ ያሰቡትን እንዳይፈጽሙ ከለከላ
ቸው፤ መዋኘት የሚችሉ ከመርከብ እየዘለሉ
አስቀድመው ከባሕሩ ወደ ምድር እንዲ
ወጡ፣ [44]የተቀሩት ደግሞ በሳንቃዎች ወይም
በመርከቡ ስብርባሪ እየተንጠላጠሉ እንዲ
ወጡ አዘዘ:: በዚህ መንገድ ሁሉም በደኅና
ወደ ምድር ደረሱ::

### ጳውሎስ በመላጥያ ደሴት

**28** በደኅና ወደ ምድር ከደረስን በኋላ፣
ደሴቲቱ መላጥያ ተብላ እንደምትጠራ
ተረዳን:: [2]የደሴቲቱ ነዋሪዎችም የሚያስ
ገርም ደግነት አሳዩን፤ ዝናብና ብርድ ነበርና
እሳት አንድደው ሁላችንን ተቀበሉን:: [3]ጳው
ሎስም ጭራሮ ሰብስቦ ወደ እሳቱ ሲጨ
ምር፣ ከሙቀቱ የተነሣ እፉኝት ወጥታ እጁ
ላይ ተጣበቀች:: [4]የደሴቲቱ ነዋሪዎች እባብ
በእጁ ላይ ተንጠልጥላ ባዩ ጊዜ፣ "ይህ ሰው
በእርግጥ ነፍስ ገዳይ ነው፤ ከባሕር ቢያ
መልጥ እንኳ የፍርድ አምላክ በሕይወት
እንዲኖር አልፈቀደለትም" ተባባሉ:: [5]ጳው
ሎስ ግን እባቢቱን ወደ እሳቱ አራገፋት፤
አንዳችም ጕዳት አልደረሰበትም:: [6]ሰዎቹ
ከአሁን አሁን ሰውነቱ ያብጣል ወይም ድን
ገት ሞቶ ይወድቃል ብለው ይጠባበቁ ነበር፤
ነገር ግን ብዙ ጊዜ ጠብቀው ምንም የተለየ
ነገር እንዳልደረሰበት ባዩ ጊዜ፣ ሐሳባቸውን
ለውጠው፣ "ይህስ አምላክ ነው" አሉ::
[7]በዚያም ስፍራ አጠገብ የደሴቲቱ አለቃ
የፑፕልዮስ ርስት የሆነ መሬት ነበረ፤ እር
ሱም በቤቱ ተቀብሎን ሦስት ቀን በቸር
ነት አስተናገደን:: [8]የፑፕልዮስም አባት
በትኵሳትና በተቅማጥ ሕመም ተይዞ ተኝቶ
ነበር፤ ጳውሎስም ሊጠይቀው ገብቶ ከጸለየ
ለት በኋላ፣ እጁን ጭኖ ፈወሰው:: [9]ይህም
በሆነ ጊዜ፣ በደሴቲቱ የነበሩ ሌሎች ሕመ
ምተኞችም እየመጡ ተፈወሱ:: [10]እኛንም
በብዙ መንገድ አከበሩን፤ በመርከብም ለመ
ሄድ በተዘጋጀን ጊዜ፣ የሚያስፈልገንን
ሁሉ ጫኑልን::

### ጳውሎስ ሮም ደረሰ

[11]ከሦስት ወር በኋላም፣ በደሴቲቱ ክረም
ቱን ቆሞ በሰነበተ በአንድ መርከብ ተነሥ
ተን ጕዞ ጀመርን:: ይህም መርከብ የእስክ
ንድርያ ሲሆን፣ በላዩ ላይ የመንታ አማል
ክቱ የዲዮስቆሮስ ዐርማ ነበረበት:: [12]ወደ
ሰራኩስ ከተማ ገብተን ሦስት ቀን በዚያ
ተቀመጥን:: [13]ከዚያም በመርከብ ተጕዘን
ሬጊዩም ደረስን፤ በማግስቱም የደቡብ ነፋስ
ስለ ተነሣ ፑቲዮሉስ የደረስነው በሚቀጥ

27፥38 ቍ18፤ ዮና1፥5
27፥39 ሐሥ28፥1
27፥40 ቍ29
27፥41 2ቆሮ11፥25
27፥43 ቍ3
27፥44 ቍ22:31
28፥1 ሐሥ16፥10፤ 27፥26:39
28፥4 ማር16፥18፤ ሉቃ13፥2:4
28፥5 ሉቃ10፥19
28፥6 ሐሥ14፥11
28፥8 ሐሥ6፥6፤ 9፥40፤ያዕ5፥14:15
28፥10 መዝ15፥4
28፥11 ሐሥ27፥6

ወይም ወደ ፊት ከጠረፍ ሲደረስ ለሚያጋጥም ሁኔታ ለመሰናዳት፣ የተሳፋሪውን ቍጥር በትክክል ማወቅ አስፈላጊ ነበር:: በዘመኑ ሁኔታ ሲታይ ይህ የተሳፋሪ ቍጥር ከፍተኛ ነው የሚባል አይደ ለም፤ ባለ ታሪኩ ዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን 600 ተሳፋሪዎች ስለ ነበሩ በት አንድ መርከብ ጠቅሶ ጽፎአል::

27፥38 *የመርከቡን ክብደት አቃለሉ፤* ወደ ፊት ለምግብ ይሆናል ብለው ያስቀሩትን ስንዴ (ቍ18)፣ ወደ ባሕር ጣሉ፤ ጭነቱ በተቃለለ ቍጥርም፣ መርከቧ ወደ ባሕሩ ዳርቻ ያለ ብዙ ችግር ለመጓዝ ትችል ነበር::

27፥40 *የመቅዘፊያውንም ገመድ... ፈቱ፤* ይህን ያደረጉት መርከቡን ወደ አሸዋማው ዳርቻ መምራት እንዲቻላቸው የመ ርከቡን የኋለኛ ክፍል መቅዘፊያዎች ዝቅ አድርገው ወደየቦታ ቸው ለመመለስ ነበር:: የጥንት መርከበኞች መርከቡን አቅጣጫ የሚያስይዙት ከመርከቡ በኋለኛው ክፍል ግራና ቀኝ ባሉት ሁለት መሪ መቅዘፊያዎች ነበር::

27፥42 *ወታደሮቹም ከእስረኞች... ለመግደል ተስማሙ፤* አንድ እስረኛ ቢያመልጥ ጠባቂው ወታደር በገመዱ ይገባ ነበር፤ ስለዚህ ወታደሮቹ እስረኛ አምልጦ በገመዱ እንዲገቡ አልፈለጉም::

27፥43፤ የግድያውን ዕቅድ በማስቀረቱና እስረኞቹን በማ ሙ፤ መቶ አለቃው እንደ ገና የሚደነቅ ሰው ሆኖ ተገኝቶአል (ቍ3)::

28፥1 *መላጥያ፤* ሲሲሊ ከተባለችው ታላቅ ደሴት በስተ ደቡብ 93 ኪ.ሜ ያህል ርቃ የምትገኝ ስትሆን፣ በአስተዳደርም ከዚችው ደሴት ጋር ተቀላቅላ ነበር::

28፥2 *የደሴቲቱ ነዋሪዎችም፤* በግሪኩ የቃሉ ትርጕም "በርበሮች" ማለት ነው፤ የግሪክ ተወላጅ ላልሆነ፣ የግሪክን ሥል ጣኔ በረከት ላልቀመሰ ሁሉ ግሪኮች የሰጡት ስም ነው:: የዚች ደሴት ነዋሪዎች ግን ከእነዚህ እጅግ የተለዩና የላቁ፣ የዘር ሐረ ጋቸው ስፋት እስከ ፊንቂያዊያን የሚደርስ፣ የፊንቂያዊያን ሐገረ ሰብ ቋንቋ የሚናገሩ፣ ሆኖም የሮማውያንን የአነጋገር ዘዬ እንዳለ የተካኑበት ነበሩ:: *ዝናብና ብርድ፤* ወቅቱ የጥቅምት ወር መጨ ረሻ ወይም የኅዳር ወር መጀመሪያ ሳይሆን አይቀርም::

28፥3 *እፉኝት፤* መርዛማ የእባብ ዘር መሆኗ በደሴቲቱ ነዋሪዎች ይታወቃል::

28፥6 *ያብጣል፤* በተለመደው የሕክምና ቋንቋ በሰውነት ላይ ፍም መስሎ በመቅላት የሚያቃጥል ማለት ነው:: ሉቃስ የሕክምና ባለ ሙያ እንደ መሆኑ መጠን ይህን ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀመው እርሱ ብቻ ነው:: *ይህስ አምላክ ነው አሉ፤* የልስጥራን ሰዎች ጳውሎስንና በርናባስን ለማምለክ እንደቃጣ ቸው ዓይነት ማለት ነው (14፥11-18)::

28፥7 *የፑፕልዮስ፤* ሮማዊ ስም ሲሆን፣ ይህ የግል መጠ ሪያ ስሙ እንጂ የቤተ ሰብ መጠሪያ ስም አይደለም:: ራሳቸው የደሴቲቱ ነዋሪዎች ያወጡለት ስም መሆን አለበት:: *አለቃ፤* በመላጥያ ደሴት ዋናው ባለ ሥልጣን ነበር፤ ከ 13፥7፤ ከ16፥20፤ ከ17፥6፤ ከ19፥31 ጋር ያነጻጽሩ::

28፥11 *ከሦስት ወር በኋላም፤* መርከቦች ጕዞ የሚጀምሩ በት ጊዜ፣ የየካቲት መጨረሻ ወይም የመጋቢት ወር መጀመሪያ ነበር፤ ስለዚህ እስከዚያው በዚሁ ስፍራ መቈየታቸው ግዴታ ሆነ:: ዲዮስቆሮስ፤ ሁለቱ "የዜውስ ወንዶች ልጆች" (ካስቶርና ፓሉክስ) ሲሆኑ፣ የመርከበኞች ጠባቂ አማልክት በመባል ይታወቁም ነበር::

28፥12 *ሰራኩስ፤* በሲሲሊ ደቡብ ምሥራቅ ጠረፍ ላይ የም ትገኝ ትልቅ ከተማ ነበረች::

28፥13 *ሬጊዩም፤* ኢጣሊያንና ሲሲሊን ከሚለየው እጅግ ጠባብ ከሆነው የባሕር መተላለፊያ አጠገብ፣ በኢጣሊያ ደቡብ ምዕራብ ጠረፍ ጫፍ ላይ ከመሲና ማዶ የምትገኝ ከተማ ነበረች፤ መሲና የሲሲሊ ከተማ

ለው ቀን ነበር:: 14በዚያም ወንድሞችን አገ
ኘን፤ እነርሱም ሰባት ቀን አብረናቸው እን
ድንቀመጥ ለመኑን፤ ከዚያም በኋላ ወደ
ሮም ሄድን:: 15በዚያ የነበሩ ወንድሞችም
መምጣታችንን ስለ ሰሙ፣ እስከ አፍዩስ
ፋሩስ፣ እንዲሁም 'ሦስት ማደሪያ' እስከሚ
ባለው ቦታ ድረስ ሊቀበሉን ወጡ፤ ጳውሎ
ስም ባያቸው ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገነ፤
ተጽናናም:: 16ሮም በደረስን ጊዜም፣ ጳው
ሎስ ይጠብቀው ከነበረው ወታደር ጋር፣
ለብቻው በዚያ እንዲቈይ ተፈቀደለት::

## ጳውሎስ በጥበቃ ሥር ሆኖ ሰበከ

17ከሦስት ቀንም በኋላ፣ ጳውሎስ የአይሁ
ድን መሪዎች በአንድነት ጠራ፤ በተሰበሰቡም
ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ "ወንድሞች ሆይ፤
እኔ፣ ሕዝባችንን ወይም የአባቶቻችንን ሥርዐት
የሚቃረን ምንም ሳላደርግ፣ በኢየሩሳሌም
አስረው ለሮማውያን አሳልፈው ሰጥተው
ኛል:: 18እነርሱም መርምረው ለሞት የሚያ
በቃ በደል ስላላገኙብኝ፣ ሊፈቱኝ ፈልገው
ነበር፤ 19አይሁድ በተቃወሙ ጊዜ ግን፣ ለቄሳር
ይግባኝ ማለት ግድ ሆነብኝ እንጂ ሕዝቤን
የምከስበት ምክንያት ኖሮኝ አይደ ለም::
20እናንተንም ለማየትና ለማነጋገር የጠራ
ኋችሁ በዚሁ ምክንያት ነው፤ በዚህ ሰንሰለት
የታሰርሁትም ለእስራኤል በተሰጠው ተስፋ
ምክንያት ነው::"

21እነርሱም እንዲህ አሉት፤ "ስለ አንተ
ከይሁዳ ምድር የተጻፈ አንድም ደብዳቤ
አልደረሰንም፤ ከዚያ የመጡ ወንድሞችም
ስለ አንተ ያቀረቡት ወይም የተናገሩት አን
ዳች መጥፎ ነገር የለም:: 22ይሁን እንጂ፣
ሰዎች ስለዚህ የእምነት ክፍል በየቦታው
ክፉ እንደሚያወሩበት እናውቃለን፤ የአንተ
አስተያየት ደግሞ ምን እንደ ሆነ መስማት

28፥14 ሐሥ1፥16
28፥15 ሐሥ1፥16
28፥16 ሐሥ24፥23፤27፥3
28፥17 ሐሥ6፥14፤22፥5፤25፥2:8
28፥18 ሐሥ22፥24፤23፥9፤26፥31: 32
28፥19 ሐሥ25፥11
28፥20 ሐሥ21፥33፤26፥6:7
28፥21 ሐሥ22፥5
28፥22 ሐሥ24፥5
28፥23 ማቴ3፥2፤8፥35፤17፥3፤19፥8
28፥24 ሐሥ14፥4፤17፥4:5
28፥25 ዕብ3፥7
28፥27 መዝ119፥70፤ኢሳ6፥9:10፤ማቴ13፥15
28፥28 ሉቃ2፥30፤ሐሥ13፥46

እንፈልጋለን::"

23ቀን ከቀጠሩለትም በኋላ፣ ብዙ ሆነው
ወደ ማረፊያ ስፍራው መጡ፤ እርሱም
ከጧት ጀምሮ እስከ ማታ ስለ እግዚአብሔር
መንግሥት እየመሰከረ ያብራራላቸው ነበር፤
ከሙሴ ሕግና ከነቢያትም በመጥቀስ ስለ
ኢየሱስ ሊያሳምናቸው ሞከረ:: 24አንዳንዶቹ
እርሱ የሚለውን አምነው ተቀበሉ፤ ሌሎቹ
ግን አላመኑበትም፤ 25እርስ በርሳቸውም
አልተስማሙም፤ ጳውሎስም እንዲህ የሚል
የመጨረሻ ቃል ከተናገራቸው በኋላ ሄዱ፤
"መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በኢሳይያስ አማካ
ይነት ለአባቶቻችሁ በትክክል እንዲህ ብሎ
ተናግሮአል፤

26" 'ወደዚህ ሕዝብ ሂድ፤ እንዲህም
  በላቸው፤
 "መስማትን ትሰማላችሁ፤ ነገር ግን
  አታስተውሉም፤
 ማየትን ታያላችሁ፤ ነገር ግን
  አትመለከቱም::"
27የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአልና፤
 ጆሮአቸውም ተደፍኖአል፤
 ዐይናቸውንም ጨፍነዋል::
አለዚያማ፣ በዐይናቸው አይተው፣
 በጆሮአቸው ሰምተው፣
በልባቸው አስተውለው፣
 ይመለሱና እፈውሳቸዋለሁ::'

28"ስለዚህ የእግዚአብሔር ማዳን ለአሕ
ዛብ እንደ ተላከ እንድታውቁ እፈልጋለሁ፤
እነርሱም ይሰሙታል::" 29ይህንንም ከተና
ገረ በኋላ፣ አይሁድ እርስ በርሳቸው እጅግ
እየተከራከሩ ሄዱ::†

30ጳውሎስም ራሱ በተከራየው ቤት ሁለት
ዓመት ሙሉ ተቀመጠ፤ ወደ እርሱ የሚመ

†29 አንዳንድ የጥንት ትርጕሞች ይህ ቍጥር የላቸውም

ናት። ጥጦስ (ቲቶ) የይሁዳን ምድር ድል አድርጎ ወደ ሮም ሲመለስ በሬጊዩም ዐርፎ ነበር:: *ፑቲዮሉስ፤* ከሬጊዩም 320 ኪ.ሜ ያህል ርቃ የምትገኝ በዘመናችን ፓዙአሊ ተብላ የምትጠራ ወደብ ናት፤ ከናጵሌ (ከኔፕልስ) የባሕር ወሽመጥ በስተ ሰሜን ትገኛለች፤ ከሮም ከተማ 120 ኪ.ሜ ብትርቅም እንኳን፣ የሮማ መንግሥት ዋና ወደብ ነበረች፤ አይሁድም ክርስቲያኖችም ይኖሩባት ነበር::

28፥14 *ሰባት ቀን ... እንድንቀመጥ፤* ጳውሎስ በፊት በጢሮአዳ (20፥6) በኋላም በጢሮስ (21፥4) እንዳደረገው ሁሉ፣ የጌታን እራት አብሮ ለመካፈል፣ ለማስተማርና ለመሰበክ አንድ ወይም ሁለት እሑድ አብሮአቸው ሳይቈይ አልቀረም:: እዚያ የቈዩበት ምክ ንያት አንድም የመቶ አለቃው የሚያከናውነው ሥራ ኖሮት ይሆናል፣ አለዚያም ደግሞ ጳውሎስ ያቀረበውን ጥያቄ በደ ግነት ተቀብሎ ፈቅዶለት ሊሆን ይችላል (27፥42-43፤ 27፥3 ይመ)::

28፥15 *አፍዩስ ፋሩስ፤* ከሮም 69 ኪ.ሜ ያህል ርቃ የም ትገኝ በክፋቷ የታወቀች ትንሽ ከተማ ነበረች:: በሮም የሚገኙ አንዳንድ ክርስቲያኖች ጳውሎስን ለመቀበል ይህን ያህል ርቀት ያለው መንገድ ተጓዝዋል፤ ይህም ሆኖ የሚገርመው ጳው ሎስ በዚህ መንገድ ይምጣ አይምጣ እርግጠኞች አለመሆናቸው ነበር:: *ሦስት ማደሪያ፤* ከሮም 53 ኪ.ሜ ያህል ርቃ የምትገኝ ከተማ ነበረች፤ በሮም የሚገኙ ሌሎች ክርስቲያኖች ጳውሎስን የተ ቀበሉትም እዚች ከተማ ድረስ መጥተው ነበር:: 'ማደሪያ' የሚ ለው ቃል ማንኛውንም ዐይነት የንግድ ቤት ያመለክት ነበር::

28፥16 *ለብቻው...እንዲቈይ፤* "ራሱ በተከራየው ቤት" (ቍ30) ማለት ነው:: ከባድ ወንጀል ባለመፈጸሙ፣ አሥጊ የፖለቲካ ተቀ ናቃኝም ባለመሆኑ በፈለገው ቦታ እንዲኖር ተፈቀደለት፤ ይሁን እንጂ ጠባቂ ተመድቦለታል፤ ምናልባትም ከጳውሎስ ጋር ታስሮአል (ኤፌ 6፥20፤ ፊል 1፥13-14:17፤ ቈላ 4፥3: 18፤ ፊሞ ቍ10:13)::

28፥17 *የአይሁድን መሪዎች፤* የቀላውዴዎስ ትእዛዝ (18፥2 ይመ)፣ ለተወሰነ ጊዜ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ስለ ተደረገ፣ አይሁድ ከመሪዎቻቸው ጋር ከተሰደዱበት አገር ወደ ሮም ተመልሰው ነበር:: *ወንድሞች፤* በዘር አንድ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፤ በቍ15 ላይ በክርስቶስ ወንድሞች ስለሆኑት ከሚያመለክተው ጋር ያነጻጽሩ::

28፥20 *ለእስራኤል ... ተስፋ፤* የ26፥6 ማብ ይመ::

28፥22 *የአንተ አስተያየት ደግሞ...መስማት እንፈል ጋለን፤* ስለ ኢየሱስ መሲሕነት ተነሥቶ የነበረውን ክርክር በሮም የነበሩት አይሁድ ቀደም ሲል ሰምተዋል፤ ጳውሎስም ስለዚሁ ጕዳይ የሚለውን ለመስማት ፈልገዋል፤ ጳውሎስም በበኩሉ በኢ የሩሳሌም ካሉት የአይሁድ መሪዎች አፍራሽ ዜና መጥቶ ነገር ከመበላሸቱ በፊት ስለ መሲሑ ያለውን ሐሳብ ለእነሱ ግልጽ ለማ ድረግ ጓጉቶ ነበር::

28፥23 *ከሙሴ ሕግና ከነቢያትም፤* የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ማለት ነው (ሉቃ24፥27:44 ይመ)::

28፥28 *የእግዚአብሔር ማዳን ለአሕዛብ እንደ ተላከ፤* የሐ ዋርያት ሥራ መጽሐፍ ዋናው መልእክት ይኸው ነው:: ወንጌል ለሁሉም ነው፤ ጳውሎስም ይህንኑ ወንጌል ለአሕዛብም ሆነ ለአ ይሁድ ያደርስ ዘንድ የተመረጠ ዕቃ ነው::

28፥30 *ሁለት ዓመት ሙሉ፤* ጳውሎስ፣ ከሳሾቹ ወደ ሮም መጥተው በክሳቸው እስኪገፉበት ድረስ ጌታን በትጋት ከማገ ልገል አላቋረጠም ነበር (ቍ31):: ጳውሎስ ከዚህ እስራቱ መፈታ ቱን የሚጠቍሙ አንዳንድ ምልክቶች አሉ (1) የሐዋርያት ሥራ

ጡትንም ሁሉ በደስታ ይቀበል ነበር፤ 31ማንም
ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን መንግሥት እየ
ሰበከ፣ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም ግል
ጽነት ያስተምር ነበር።

28፥31 ቍ23፤ ማቴ4፥23፤ሐሥ4፥29

መጽሐፍ ትረካ እዚህ ላይ ድንገት ማቆሙ፤ (2) ጳውሎስ ለአብያተ ክርስቲያናት በጻፈው ደብዳቤ በቅርቡ ሊጎበኛቸው ማሰቡን ገልጾ ጽፎላቸዋል፤ ስለዚህ ከእስር ቤት እንደሚወጣ ይጠባበቅ ነበር ማለት ነው (ፊል 2፥24፤ ፊሞ 22)፤ (3) በጳውሎስ መልእክታት ምጋቤ የተመለከቱትዝርዝር ጉዳዮች በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ከቀረበው ታሪክ ጋር አይገጣጠሙም፤ ከመጽሐፉ መደምደምያ ቀጥሎ ያለው ታሪክ ሲጤን፣ ዝርዝር ጉዳዮቹ ጳውሎስ ወደ ትንሹ እስያ፣ ወደ ቀርጤስና ወደ ግሪክ ተመልሶ እንደ ነበር ያመለክታል፤ (4) የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጳውሎስ ወደ እስፓኝ ሄዶ እንደ ነበርም ያመለክታል፤ አልሄደም ቢባል እንኳ፣ ሄዶ እንደ ነበር የሚገልጸው ታሪክ መከሠቱ ራሱ ወደ ተጠቀሱት አገሮች ተጉዞ እንደ ነበር ያሳያል። የጳውሎስን አራተኛ የወንጌል ጉዞ የሚያመለክተውን ካርታ በገጽ 1841 ላይ ይመ።